# ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! 2ኛ መፅሐፍ

## My Bride I am on My way get ready - Book 2 - Amharic



# መግቢያ

ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ በሚል ርዕስ በሶስት መፅሐፍ የቀረቡ እነዚህ መልዕክቶች ከኢየሱስ የተላኩ የፍቅር ደብዳቤዎች በሚል ርዕስ በሲስተር ክሌር ዴቡስ ከቀረቡ መልዕክቶች ተመርጠው የተተረጎሙ ናቸው፡፡ ይህንንም ርዕስ የመረጥንበት ምክንያት በእርግጥም ሙሽራው ሊመጣ በደጅ ስለሆነና ሙሽሪት ይህንን በመገንዘብ መዘጋጀት እንዳለባት አፅንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ሲስተር ክሌር ዴቡስ የ74 ዓመት አሜሪካዊት ነቢይት ስትሆን ከጌታ መልዕክቶችን እየተቀበለች እ.አ.አ. ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ አይነት መንገድ ለአለም እያስተላለፈች ትገኛለች፡፡ በሦስቱም መፅሐፍ ተርጉመን ያቀረብንላችሁ መልዕክቶች ከአንዳንዶች በስተቀር ከሲስተር ክሌር የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህም የእርሷ ያልሆኑ መልዕክቶች በ1ኛው መፅሐፍ የካሮል ጄንጊዝ አንድ መልእክት፣ በሁለተኛው መፅሐፍ የኸርት ድዌለርሷ የናና አንድ መልእክት እንዲሁም በሦስተኛው መፅሐፍ ውስጥ በሲስተር ክሌር መፅሐፍ ውስጥ ቀርቦ የነበረ የማይክ ፐራልታ አንድ መልዕክት ናቸው፡፡ የሲስተር ክሌር መልእክቶች እጅግ ብዙ በመሆናቸው ለእናንተ ለአንባቢዮቻችን የበለጠ ይጠቅማል ብለን የመረጥነውን ብቻ ተርጉመን በመፅሐፍ መልክ በማጠናቀር አቅርበናል፡፡

ዘ ኤንድ ዴይስ ሚኒስትሪስ/ The End Days ministries / ዋና ዓላማው በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና ህዝባችን ሊሰማቸው የሚገቡ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች በመተርጎም ለህዝባችን ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ እነዚህንና ሌሎች መልዕክቶችን በንባብ መልክ በድምፅ ተቀርፆ በዩ ቱዩብ ቻናላችን ላይ ታገኙታላችሁ፡፡

በሲስተር ክሌር የሚተላለፉ መልዕክቶች አጠቃላይ ይዘታቸውን ስንመለከት ሙሽራው በቅርብ ሊመጣ እንደሆነ፣ ሙሽሪት ከጌታዋ ጋር ለመሄድ /ለንጥቀት/ መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዲሁም የማይነጠቁ ሰዎች በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ታላቁ መከራ ተብሎ የተጠቀሰውን ዘመናት በምድር እንደሚያልፉና በዚህም የመከራ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክቱ ወሳኝ መልዕክቶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ጠቅላላውን መልዕክት በሚከተሉት ቻናሎችና ዌብሳቶች ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡

(1) በአማረኛ የተተረጎሙ መልዕክቶችን ለማግኘት/ translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) በአማረኛ ዘ ኤንድ ዴይስ የተተረጎሙ ትንቢታዊ መልዕክቶችንና መፅሐፎችን ለማግኘት - heartdwellers.org – Book በሚለው ውስጥ ገብታችሁ እነዚህን ርዕሶች ታገኛላችሁ፦

- The Rapture was real Book Amharic pdf - ንጥቀቱ እውን ነበር በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- Tethered Book Amharic pdf - ቴተርድ በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- My Bride get ready Book one – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ አንድ
- My Bride get ready Book two – Amharic pdf / ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሁለት
- My Bride get ready Book three – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሦስት
- Events after the rapture Amharic pdf/ በቅርብ ስለሚሆኑ ክስተቶችና ስለ ታላቁ የመከራ ዘመን

(3) በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ መልዕክቶቹን ለማግኘት/ Messages in Engilish

- heartdwellers.org
- Youtube – 1ibesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## ጌታ ዘመናችሁን ይባርክ

# Introduction

The title of this book, in Amharic "ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! " translated to Engilish "My bride get ready I am on my way ", was given to show that the Groom is truly on His way and to alert the bride.  All the messages in the three books (book 1, book 2 and book 3) except same messages were taken and translated from Sister Clare, The other Messages are Calor jenngs message in the first book, Nana's Messagen in the second book and Mike Peralta message (taken from Love letter book- new) in the third book. Sister Clare is a 74 years old American prophetess who hears and transmites messages from God to the world through different Medias since 2014. Her messages are so many and we have tried to translate very few of them.

We are doing this since one of our ministries goals is to acceses prophetice messages spoken in Engilish and which are relevant to our people. For this purpose we have translated and recorded same messages and uploaded them on you tube.

When we look to the content of Sister Clars' messages, they talk about the coming of Jesus sooner than expected, intiate brides to be ready for the rapture and explaine how to be ready. In addition, they reveal what is to come after the rapture, what will the left behind face in the period called great tribulation, which is written in the Bible, and the messages also give same hints how to persevere in the tribulation. Therfore if you want to get the whole messages in English and the translated messages in Amharic you can find them as follows:-

(1) Translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) Translated messages compiled in book pdf - go to - heartdwellers.org to Book folder then search for these titles;-

- ❖ The Rapture was real Book Amharic pdf
- ❖ Tethered Book Amharic pdf
- ❖ My Bride get ready Book one – Amharic pdf
- ❖ My Bride get ready Book two – Amharic pdf
- ❖ My Bride get ready Book three – Amharic pdf
- ❖ Events after the rapture Amharic pdf

(3) The whole Messages in Engilish

- ❖ heartdwellers.org
- ❖ Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## God bless you

| ተራ ቁ. | የመልዕክቱ ዝርዝር ርዕሶች | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | ለእግዚአብሔር እሳት ላይ የመጣድ ፍላጎት / Longing to Be On Fire For God | 5 |
| 2 | በአለም ላይ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ስርጭት / Why Has Coronavirus Been Allowed by God? | |
| 3 | ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ከጌታ ኢየሱስ የተሰጡ መመሪያዎች/ Why coronavirus been allowed | |
| 4 | ኮሮና ቫይረስ - የጌታ የማንቂያ ደውል/ The coronavirus plague | |
| 5 | ኢየሱስ 'እጅግ የምጠላው' ብሎ የገለፀው ነገር / Let the little ones shine | |
| 6 | ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ከጌታ ኢየሱስ የተሰጡ መመሪያዎች / coronavirus spiritual protection | |
| 7 | ነቀፋ በሌለው ህይወት መመላለስ/ Waking a blamless life | |
| 8 | ህዝቤ ሆይ ቀን ሳለ ድምፄን ሰምተህ እንድታመልጥ እየተጣራሁ ነው/ Herken unto Me while there is still time | |
| 9 | ጥበቃዬ በታዛገች ላይ ነው /My protection is with the obedient | |
| 10 | ይህ የጉብኝት ወቅታችሁ ነው/ This is the time of your visitation | |
| 11 | የዘመኑ ሳርዴስ እንሆንን?/ Are we the Church of seredes | |
| 12 | ሙሽራዬ ታስፈልጊኛለሽ/ My Bride I need you | |
| 13 | ሥቃይ - እጅግ ከባዱ ሥራ/ The hard work suffering | |
| 14 | የህይወት ፈተናዎች/ The trial of life | |
| 15 | ወደ ልቤ ለመግባት ቁልፉን እወቁ / Innoocence, the key to my heart | |
| 16 | ሁላችሁም ልዩ ስለሆናችሁ  እኔ ባቀድኩላችሁ ለመጓዝ ተበረታቱ/ courage you are all uiniqe | |
| 17 | ቤተ ክርስቲያኔ ተቋማዊ ሳትሆን ቤተሰባዊ  ነች/ Faith family not institution | |
| 18 | ከሰማያት እሳት ስለሚወድቅ ተዘጋጁ እንጂ አትፍሩ/ Fire will fall from heaven | |
| 19 | በዋይት ኃውስ አደጋ እያገንበበ ነው/ Dolar Trump in a casecatte | |
| 20 | የኮረና ቫይረስ ክትባቱ ውሎ ሲያድር ስለሚገድላችሁ አትውሰዱ በእኔ ብቻ ታመኑ/ Trust in Me alone | |
| 21 | የፍርስራሾች ደመና/ Debris from the sky | |
| 22 | ለጠላቶቻችሁ መፀለይ . . ./ Under attack | |
| 23 | ከምድር በታች እየተደረጉ ያሉ ጦርነቶች/ Underground war in progress | |
| 24 | በልቤ ላይ ዕረፉ/ Rest on My Heart | |
| 25 | አባቶች ተነሱ!/ Fathers arise | |
| 26 | የእግዚአብሔር ጥሪ ደርሷችኋል?/ Is God calling you? | |
| 27 | ለፀሎቶቻችን መልስ ለማግኘት እንዴት መፀለይ አለብን? / Your parayer and answeres | |
| 28 | የጌታን ፈቃድ በትክክል መለየት ለምን ያስቸግራል? / Why discernment fails? | |
| 29 | ሙሽራዬ እንድትሰማኝ እፈልጋለሁ /  I want My Bride to hear Me | |
| 30 | ምህረት የማያደርግ አገልጋይ / The unforgiving servant | |
| 31 | ለድካማችሁ የኔ ስጦታ / Communuion My fulleness for your weakness | |
| 32 | በየቀኑ ክርስቶስን እየመሰሉ መሄድ / Transforming into Christ, daily | |
| 33 | ከኢየሱስ ጋር የጠለቀና አስደሳች ግንኙነት እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ? / Deeper and sweeter with Jesus | |
| 34 | ቅባቱ ያለው በተሿሚዎች ላይ ነው / The anointing is in the appointing | |
| 35 | የንሰሐ ጥሪ ለእግዚአብሔር ህዝብና የጂ5 ቴክኖሎጂ አደገኛነት / War with China | |
| 36 | ወደ ልቤ እንድትቀርቡ ያዘጋጀሁትን እቅድ ማበላሸት/ How you frustrate My plan | |
| 37 | ጥፋት እየመጣ ስለሆነ ጩኹ / Cry out devastation is coming | |
| | ኮሮና ቫይረስ - የጌታ የማንቂያ ደውል  ክፍል 1 / Rapture alert part 1 | |

38 ኮሮና ቫይረስ - የጌታ የማንቂያ ደውል ክፍል 2 / Rapture alert part 2
39 ጊዜው እየደረሰ ስለሆነ የመጨረሻውን ዝግጅት አድርጉ / Keep your oil
40 የወቅቱ የንጥቀት መልዕክት / Rapture update
41 ወደ ሰማያዊ ቤታችን መዘርጋት / The home streach
42 እንጉዳይ ቅርፅ ዳመና በኒዮርክ ከተማ ላይ / Musheroom cloud on New York City

## ለእግዚአብሔር እሳት ላይ የመጣድ ምኞት - ፌብሩዋሪ 14 ቀን 2020 ዓ.ም

## Longing to be on fire for God - Feb 14, 2020

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥንካሬ እና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን ፡፡ አሜን

የተወደዳችሁ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በለመድኩት መንገድ ለመጾም እና እራሴን ለማቀብ ችግር ነበረብኝ፡፡ ደግሞም ጨረቃ ሙሉ ስትሆን የበለጠ ፍላጎት እና እንቅልፍ እንደሚያስቸግረኝ አስተዋልኩ ፡፡ ግን ያ ሰበብ አይሆንም ፡፡ እኔ ሰንፌና በእውነትም ደክሜ እንደነበርኩ ማመን አለብኝ፡፡ ሰውነቴ ከጥቅም ውጪ ሆኖ ግን መቀጠል እንዳለብኝ እየፈለግሁ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባዶነት እየተሰማኝ ጌታን እንደገና እንዴት መጸለይ እንደምችል እጠይቀው ነበር፡፡

የተወደዳችሁ ይቅር በሉኝ፡፡ ምክንያቱም መልዕክቶችን ወደ እናንተ ለማድረስም ቸልተኛ እንደሆንኩ ይሰማኛል ፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለእኔ ምስጢር ናቸው ። ምክንያቱም በሙሉ ልብ ንቁና ታማኝ መሆን ስለምፈልግ ነው ፡፡ ከዚህ የተነሳ ለበርካታ ቀናት ከዳተኛነቴን በማሰብ፣ ተስፋ ቢስ በመሆንና በእርግጠኝነትም ለእናንተ ምሳሌ ልሆን ባለመቻሌ ሳለቅስ ነበር፡፡

የጌታን ሥጋና ደም ከተቀበልኩ በኋላ ጌታ ወደ እኔ መጣና በአንገቴ ዙሪያ ሜዳልያ አጠለቀልኝ፡፡ እኔም 'ምን?' 'እኔ ሶስተኛ ሆኜ አሸነፍኩ' በማለት አሰብኩ። ሜዳሊያውም ቀይ፣ ነጭ እና ሰማያዊ ሪባን ያለበት ነበር፡፡ ከፊት ለፊቱ ግን አላየሁትም ነበር ።

ጌታም "ክሌር ታሸንፊያለሽ፡፡ በሚያበሩ ቀለሞች ታልፊያለሽ።" አለኝ፡፡

ሜዳሊያው የመዳብ መስሎኝ ነበር። ይህ ማለት ደግሞ ሶስተኛ ደረጃ ማለት ነው። ነገር ግን እኔ ለወርቅ የምመጥን መሆን እፈልግ ነበር። እራሴን ሰበሰብኩና ጌታን እንዲህ አልኩት፡፡ 'ጌታ አንተ የምትፈልገውን ብቻ እፈልጋለሁ። ከዚያ ሌላ ምንም አልፈልግም።'

ኢየሱስም እንዲህ አለኝ "ክሌር ለህዝቤ ንገሪልኝ። እንዲህ ብለሽ ንገሪያቸው፡፡ እናንተ ለመቀጠል የምትፈልጉና ለመቀጠልም የምትሞክሩ፣ አንዳንዴም ደግሞ በግማሽ ልባችሁ እንደሆናችሁ የሚሰማችሁ፣ ደክሟችሁ እንጂ መንፈሳችሁ ያለበት ሁኔታ አይደለም። ልክ እንደ ኦሊምፒክ እሳት የእናንተ መንፈስ በፊቴ እየተቀጣጠለ ነው፡፡

"ከተዋጋችኋቸው ብዙ ጦርነቶች የተነሳ ምን ያህል እንደደከማችሁ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እንድታውቁት የምፈልገው ነገር ምንም እንኳን ለብ ያላችሁ ወይም እንደ ወደቃችሁ መስሎ ቢሰማችሁም እውነታው ግን ካካፈላችሁት የፀፀት እንባና የበለጠ ታማኝ ለመሆን በመፈለጋችሁ፣ በስሜትና በአይምሮም እሳት ላይ ለመጣድ በመፈለጋችሁ ፣ እኔ የሰጠኋችሁን ግብ ለማሳካት ከመትጋታችሁ የተነሳ ነው፡፡ እንደ ወደቃችሁ መስሎ ቢሰማችሁም ያቀዘቀዛችሁ ድካማችሁ ነው። ቢሆንም ግን እናንተ ከተጠየፋችኋት ከዛች ጭል ጭል ከምትለው እሳት ሥር የማይጠፋ እሳት አለ።

"ይህንን የፈቀድኩት ለእራሳችሁ ጥቅም ነው፡፡ ይህም ትሑት እንድትሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በመንቃት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት በእውነት እየታገሉ ላሉ ሰዎች ከሚታየው ከእናንተ እሳት ላይ እንዲካፈሉ ለማድረግ ነው። አሁንም

ከዋናው ፍሬ በታች የቀለጠ የአለት እሳት (moleten lava *fire*) ይታየኛል። እናም ይህንን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ እናንተ ያበቃላችሁ፣ ለብ ያላችሁ፣ የወደቃችሁ አይደላችሁም፡፡"

"እናንተ ለእኔ ጥልቅ ፍቅር ያላችሁና ለእኔ ስትሉ እሳት ላይ የተጣዳችሁ ሙሽራዎቼ ናችሁ፡፡"

"ስሜቶቻችሁ አብቅቶላችኋል የሚሏችሁን አምናችሁ እንዳትታለሉ፡፡  ይልቁንም አሁን ስናወራ እንኳን ለውስጥ እሳታችሁ የምመግበውን በመያዝ፣ ከዚህ የጥፋትና የውድቀት ሥፍራ ተነስታችሁ አዲስ ቅባቶችን ፣ ወንጌሉን ለመስበክ አዲስ እድሎችን በመያዝ ነፍሶችን አድኑ ።"

"ውጊያው እጅግ ረዥምና ከባድ ነበር፡፡  ምንም እንኳን ይህ እንዲያደክማችሁ ብፈቅድም፣ አሁን ግን ልባችሁን ወደ ሰማያት ለማንሳት የምትችሉበት አዲስ ፀጋ እየላኩላችሁ ነው፡፡ ይህም ፀጋ እኔ በጠራኋችሁ የቅባትና የኃይል ሙላት ልክ  ጥሪውን ተገንዝባችሁ የጓጓችሁለትን ፍሬ እንድታገኙ ነው።

"አብዛኛዎቻችሁ ኢጋንንት በቋሚነት የሚያፈሱትን ክስ ወደ ውስጣችሁ በደንብ አስገብታችኋል፡፡ እናም በዚህ ክሳቸው መርዝን አሳድጋችኋል። እናም ሕይወት ለእናንተ እንዳበቃለትና በሌሎች ወጣቶች መተካት እንዳለባችሁ ራሳችሁን አሳምናችኋል፡፡ በእርግጥም የኋለኛው እውነት ሲሆን ከጊዜ በኋላ ወጣቶች ሲቀቡ ይተኳችኋል፡፡ ነገር ግን ያለ እናንተ መመሪያ ይወድቃሉ ፡፡

"እናንተ ከጠላት ጋር እጅ-ለእጅ ተያይዛችሁ በጦር ሜዳው ላይ ነበራችሁ፡፡ ስለ ጠላት ስልቶች ብዙ ተምራችኋል።  አሁን የሚነሱትን መጠበቅ፣ የጠላትን ውሸቶችና ማታለያዎች ማሸነፍ እንዲችሉ ማስጠንቀቅ አለባችሁ፡፡ እናንተም ከነናቸው በመቆም መልካሙን ተጋድሎ መጋደል አለባችሁ፡፡

"በእኔ ጸጋ ብዙ ብርታት እና እሳት ወደ እናንተ ይመጣል፡፡ በጦርነቱ ላይ ራሳችሁን ግንባር ቀደም አድርጉና አስታጥቃችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ቅባቱ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።"

"እናንተ የተጠራችሁት በሙዚቃ፣ በጽሑፍና በቲያትር ደቀመዛሙርትን በላቀ ምሳሌነት እንድትዘጋጁ ነው፡፡ አለበለዚያ እየተራመዱ እያሉ ይወድቃሉ። አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች ተፈላጊ ከመሆናቸውና ከድፍረታቸው የተነሳ ከመጠን በላይ በራሳቸው እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል፡፡ እናም እናንተ እንድታስጠነቅቋቸው በቦታው አስቀምጬያችኋለሁ፡፡ እነርሱ የመታዘዝን ዋጋ መማር አለባቸው። ከዚህ ውጪ ሊሳካላቸው አይችልም፡፡ በዋነኝነት ግን በልባቸው ውስጥ ለሚሰሙት ለእኔ ድምፅ ታዛዥ መሆን አለባቸው። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ እነርሱን ለመምራት የተቀቡትን በማወቅ ከራሳቸው ፍላጎት በላይ ማክበር አለባቸው።

"ይህ ትውልድ ኩራት አፍርቶ የመጣ ትውልድ ስለሆነ በትህትና እና ለመማር ዝግጁ በሆነ መንፈስ መቀየር ያስፈልገዋል። በእነዚህ ቁልፍ ነጥቦች ነው ከእነሱ ጋር በአፅንኦት እንድትመለከቱት የምፈልገው፡፡  እነሱ ዝቅ ማለትንና በመንፈስ ድሃ መሆንን መማር አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን በጦር ሜዳ በቀላሉ ተሸናፊዎች ይሆናሉ። እነዚህን ነገሮች በዚህ ቻናል ላይ በደንብ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህም አሁን እነዚህን ትምህርቶች እንደ አዲስ መና እየመጣ ላለው ትውልድ እንድታቀርቧቸው እፈልጋለሁ። በትህትና ስር ካልሰደዱ በስተቀር የሚሰጣቸው ቅባቶችና ስጦታዎች  ለውድቀታቸው ይሆናል።"

“ክሌር ወደ እኔ የጮህሽውን ጩኸት አይቻለሁ ደግሞም አድምጫለሁ ፡፡ የኔ ውድ ራስሽን በእኔ ልብ ላይ አሳርፊ። በአንቺ በጣም ደስተኛ ነኝ።”

ክሌር፦ ጌታ ሆይ ይህንን እየተቃወምኩኝ ነው ፡፡ እንዴት ሊሆን ይችላል?

እርሱም እንዲህ በማለት መለሰልኝ . . . “ክሌር ምን እየተዋጋሽ እንደሆነ አታይም ፡፡ ጠዋት ስትነሺ በምን ዓይነት ከባቢ አየር እንደምትሆኚ አላየሽም። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የክፉ ጸሎቶችንና ጥቃቶችን አላየሽም። ስለ አንቺ መጥፎ የሚናገሩትን አልሰማሽም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ተሰምተውሻል። ወደ ፒያኖሽ እና ወደ መዝሙርሽ ከመሄድሽ በፊት እንኳን የክስ ማዕበሎች ተሰምተውሻል እናም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ተቀብረሽ ነበር።”

“እነዚህ ማዕበሎች ጉልበቶችሽን በማብረክረክ ግራ ማጋባት ባሕር ውስጥ የሚጥሉሽ ናቸው። እዚያ ፣ ወደ እኔ በፍርሃት ትዋኛለሽ ፣ ግን ሁል ጊዜ እየቀጣሁሽ እንደሆነ እየተሰማሽ ነው ፡፡ በዚያ ሆነሽም በጭንቀት እየዋኘሽ ወደእኔ ትመጫለሽ፡፡ ነገር ግን እየቀጣሁሽ ስለሚመስልሽ ሁልጊዜ በደከመ ስሜት ነው የምትመጪው፡፡

"ነገር ግን እየቀጣሁሽ አይደለም። ይልቁንም እነዚህን ነገሮች የፈቀድኩት ችግሮችን ለማቃለል ጠንካራ እንድትሆኚ ፣ ከሚመጣብሽ ማዕበል ጠንክረሽ በተቃራኒው መዋኘት እንድትችይ፣ እንዲሁም እኔ መጥቼ እንደማድንሽ በእምነት እንድትጠነክሪ ነው፡፡

“እነዚህ የማጠንከሪያ ዘዴዎች በአካሌ ውስጥ በጥልቀትና በስፋት ተሰራጭተዋል። በዚህ መንገድ የምትጠቂው አንቺ ብቻ አይደለሽም፡፡ በዚህ መንገድ እየተጎዱ ካሉት በሺዎች ከሚቆጠሩ ተዋጊዎች ውስጥ አንቺ አንዷ ነሽ፡፡ ይህ ደግሞ አዲስ ቅባት ለመሸከም ዝግጁ ያደርግሻል፡፡

“አያችሁ ጠላት አሁንም ለእኔ እየሰራ መሆኑ አልገባውም፡፡ በነፍሳት ላይ የሚያደርገውን ጥረቱን ሁሉ ወደ ፍሬ እለውጠዋለሁ። የሰማዕታት ደም የቤተክርስቲያኑ ዘር እንደሆነ ሁሉ የእናንተም ስቃይና ስደት የእምነትን ጠንካራ ጡንቻ በውስጣችሁ ገንብቷል፡፡ ይህም በታላቅ ጸጋ እንድትሰሩ ያደርጋችኋል። ቤተክርስቲያኔ ሆይ ፣ ታላቅ ጸጋ ወደ እናንተ እየመጣ ነው ፡፡”

“በፀደይ ወቅት ላይ በህይወታችሁ አዲስ ጸጋ በውስጣችሁ እንደሚነሳ ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡ እጅግ በጣም የምትፈልጓቸውን ጸጋዎች በመጠየቅ ወደ እኔ በልበ ሙሉነት ቅረቡ፡፡ ስጋና ደሜን ስትቀበሉ በቀደመው ህይወታችሁ እንቅፋት በመሆን ወደታች የጣሏችሁን ነገሮች ለማሸነፍ እንድተችሉ እኔ ራሴን እያካፈልኳችሁ እንደሆነ እወቁ።

“የእኔ ሙሽሮች ይህ አዲስ የድል ወቅት ነው! ተቀበሉት! ከሞኝነታችሁ የተነሳ እንዳይሰረቅባችሁ በትሕትና መሸፈኛ ሽፍናችሁ ጠብቁት። የወንድማማች ፍቅር ሲያስገድድ ወይም በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በልባችሁ ውስጥ ደብቁት።

“ከዚህ በፊት ያስቸገሯችሁን ለማከናወን በቅርቡ እንደምትነሱ በማወቅ እባካችሁ አሁን እነዚህን ቃላት በእምነት ተቀበሉ፡፡

“በሰው አይን ውስጥ በማይገባ መልኩ፣ ነገር ግን አጋንንቶችን በሚያስፈራ ሁኔታ በኃያልነቴ ከእናንተ ጋር ነኝ። የትህትና ልብስ ሊሰበር እንደማይችል የብረት ካዝና ነው። እጆቻችሁን በልቤ ላይ አድርጉና ፍቅሬ የቀረውን ሁሉ ይሰራል።”

## በአለም ላይ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ስርጭት - ፌብርዋሪ 19 ቀን 2020 ዓ.ም

## Why Has Coronavirus Been Allowed by God? – February 19, 2020

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . . የሉአላዊው አምላክ እምነትና በረከት በእናንተ ላይ በመውረድ ለዘላለም ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ እንዲሁም በእግዚአብሔር የጦር መሳሪያ የታጠቃችሁና መዝሙር 91 በየቀኑ ለማወጅ የጠነከራችሁ ሁኑ፡፡

በአለም ዙሪያ የተከሰተውን ወቅታዊ የኮሮና ቫይረስ የስርጭት ማስጠንቀቂያዎችን ከማይክ ከሰማሁ በኋላ ኢየሱስን ጌታ ሆይ ይህ ነገር እጅግ የሚያስፈራ ነው አልኩት፡፡ ማይክ ለአምስት ተከታታይ አመታት ከአለም ዙሪያ እየሰበሰበ የሚያስተላልፈው ነገር መቶ በመቶ ትክክል በመሆኑ አስተማማኝ ምንጭ መሆኑን አስመዝግቧል፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት መለሰልኝ . . . " ክሌር ምናልባት አሁን ለምን እጅግ እያለቀስኩ እንደነበረ አሁንም እያለቀስኩ እንደሆነ ሊገባሽ ይችላል፡፡ ይህም ነፍሳትን ማጣት መቅሰፍት በመሆኑ ነው፡፡ አሁን እየተከሰተ ያለው ወረርሽኝ እያስከተለ ያለው አደጋ አንቺ ሳትፈጠሪ በፊት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከተከሰተውና ብዙዎችን ከቀጠፈው ከኢንፍሎንዛ ወረርሺኝ (ጌታ የሚናገረው በእስፔን በ1918 ዓ.ም የተከሰተውን ይመስለኛል) ወይም ከሳንባ ነቀርሳ ወይም ከጥቁር ወረርሽኝ ጋር ሊወዳደር የሚችል አይደለም፡፡ እነዚህ ነገሮች እናንተ ልትረዱት ከምትችሉት እውነታ በላይ ናቸው፡፡

"ይህ ክስተት በዜና ከተዘገበው በላይ የበለጠ አሳሳቢ ነው፡፡ በኢኮኖሚውም ላይ ገና ቀውስ ይፈጥራል፡፡ ሰዎች ግን ጉዳዩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነና ምልክቱ የታየባቸውን ሰዎች ለብቻ ለማድረግ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ምን እንደሆነ ግንዛቤው የላቸውም፡፡ ቻይናዎች በበሽታው በተያዙት ላይ ጨቃኞች ሆነዋል፡፡

"ህዝቤ ለእኔ መኖር እንዲጀምር እፈልጋለሁ፡፡ ህይወት ማለት የአኗኗር ዘይቤን ማሻሻል፣ የፈለጉትን ሁሉ ማግኘትና ብዙ ገንዘብ ማካበት እንዳልሆነ እንዲገባቸው እፈልጋለሁ፡፡ ልባቸውን ወደ እኔ መመለስ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ እንዲሆን ለማድረግ ደግሞ መፍቀድ የማልፈልገውን ነገር እንድፈቅድ እያደረገኝ ነው፡፡

"ይህ ወረርሺኝ ገና ጅማሬው ብቻ ነው፡፡ ገንፍሎ ይወጣና አለምን ሁሉ ያስደነግጣል፡፡ በአለም ያላችሁ ሁሉ ልባችሁን ወደ እኔ መልሱ፡፡ ለራሳችሁ ብቻ በጥብቅ በመኖር ከዚህ ወረርሽኝ እናመልጣለን ብላችሁ እንዳታስቡ፡፡ ሁላችሁንም ወደ እኔ እንድትመለሱ እየጠራኋችሁ ነው፡፡ እያያችሁት ያለው ነገር ልዩነት በሌለው በራስ ወዳድነት የምትኖሩት የህይወት ዘይቤ ውጤት ነው፡፡"

ጌታ እኔም የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶኛል፡፡ ከሁለት ሳምንታት በፊት ጌታ ለምንድነው ይህንን ያህል እየተሰቃየ ያለው? ለምንድነው የሚያለቅሰው? እያልኩ ራሴን ስጠይቅ ነበር፡፡ እንዲሁም ህዝቄኤል በዛን ጊዜ እጅግ ታሞ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ በዜና ላይ ተነገረ፡፡

ውድ ቤተሰቦቼ ይህ ጊዜ ለቻይናዎችና ለአለም ሁሉ እጅግ አሳሳቢ ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ቫይረስ የበለጠ ማወቅ ከፈለጋችሁ በሳውንድ ክላውድ ፔጅ ላይ በማይክ የተነገረውን ይኸውም ከቻይና ተጭኖ በመጣ መርከብ ኮንቴነሮች ውስጥ ስለተገኘው

የተገለጸውን መመልከት ትችላላችሁ፡፡ /The sound cloud page, Mike from around the world/፡፡ ለዚህም ነው ይህ መርከብ ወደ አሜሪካ ወደቦች እንዳይገባ የተከለከለው፡፡

ይህም ስለሆነ የዎልማርት መደርደሪያዎች ባዶ እየሆኑ ይመስለኛል፡፡ በነገራችን ላይ ፓስተር ቢጌልስ ከማይክ ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ በዩቱብ ላይ ታገኙታላችሁ፡፡ በዛ ፕሮግራም የመጀመሪያው ክፍል ስለሌላ ጉዳዮች የቀረበ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ግን ከማይክ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ይገኝበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ቫረስ በአገራችን አሜሪካ ውስጥ ቢከሰት ምን ማድረግ እንደሚገባን ዝግጅት ለማድረግ ከጅድ ሄልም /Jade Helm/ጋር አብሮ እየሰራ ነው፡፡ ማይክ ጠንካራ ክርስቲያን በመሆኑ እነዚህን ክስተቶች ከመፅሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ጋር ያገናዝባቸዋል፡፡

የኔ ውዶች ከሁሉም በላይ ደግሞ ለቻይናዎች ፀልዩ፡፡ እነርሱ በመንግስታቸው የተያዙት በጣም በጭቃኔ ነው፡፡ በተጨማሪም መዝሙር 91 በራሳችሁ ላይ ፣ በቤታችሁና በቤተሰባችሁ ላይ በየቀኑ እያወጃችሁ ፀልዩ፡፡ እባካችሁ ቻይናዎች እጅግ እየተሰቃዩ ስለሆነ በእነርሱም ላይም እያወጃችሁ ፀልዩ፡፡

ስለ መዝሙር 91 አንድ እውነተኛ የሆነ ታሪክ ልንገራችሁ፡፡ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት 900 ሰዎችን የያዘ አንድ ክፍለ ጦር ነበር፡፡ የዚህ ክፍለ ጦር አዛዥ ወደ ማንኛውም ጦርነት ከመውጣታቸው በፊት እያንዳንዱ ሰው በየቀኑ መዝሙር 91 ሳይፀልይ ወይም ሳያውጅ እንዳይወጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ቀን 900 ሰዎች ይህንን ያደርጉ ነበር፡፡ ሌሎቹ ክፍለ ጦሮች ግን ይህንን ሳያደርጉ ወደ ጦር ሜዳ ይወጡ ነበር፡፡ እነዚህም በጦርነቱ ይቆስሉና ይሞቱ ነበር፡፡ በጣም የሚገርማችሁ ግን መዝሙር 91 እየፀለዩ ከሚወጡት ከክፍለ ጦሩ ቡድኖች መካከል አንድ እንኳን በጦርነቱ የቆሰለ ወይም የሞተ ሰው አልነበረም፡፡ ከ900 ሰዎች መካከል አንድም እንኳን የቆሰለ ወይም የሞተ አልነበረም፡፡ የተወደዳችሁ ይህ አንድ ነገር ሊያሳያችሁ ይችላል፡፡ ይህም እግዚአብሔር በቃሉ የፀለያችሁትን ፀሎት በማክበር ዙሪያችሁን በመላዕክቶች እንደሚያስጠብቅ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ጌታን ለመስማት በእውነት በመፈለጌ ኢየሱስ አልኩ . . .

ኢየሱስም . . ."እኔ እዚህ ነኝ ቡና መጠጣት አያስፈልግሽም " አለኝ፡፡

አዎ ጌታዬ አንተን ለማግኘትና ይህንን ነገር ሁሉ እንድትገልጥልኝ ብዬ ነው ከአልጋዬ ላይ ፈጥኜ የወረድኩት፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ."እኔ እዚሁ ሆኜ እያንዳንዱን የልብሽን ምት እያደመጥኩ ነኝ፡፡ ህዝቤ ይህንን ፀሎት እንዲፀልይ በመንገርሽ ጥሩ አድርገሻል፡፡ ይህ ፀሎት ከእምንት ጋር ሲሆን እጅግ ኃይል አለው፡፡ የኔ ውዶች ከልባችሁ አውጁት፡፡ በመዝሙሩ ላይ እንደተገለፀው ነገሩን በዓይነ ህሊናችሁ እያሰባችሁ በዝግታና በእውቀት ፀልዩት፡፡ በቃሉ ላይ በገባሁላችሁ መሰረት በእምነት ላይ ተጣብቃችሁ አውጁት፡፡ በልጆቻችሁ ላይ በጥንቃቄ በማወጅ ፀልዩ፡፡ በእውነትም ለአገራችሁ፣ ለህዝባችሁና ለአለም ሁሉ አውጁ፣ ፀልዩ፡፡

"ለዚህ ለተበላሸ አለም ለምንድነው የምፀልየው ብላችሁ ከጠየቃችሁኝ፣ መልሱ በጣም ቀላል ነው፡፡ ይህም ቃሌ አንድ ነገር ሳይሰራ ስለማይመለስ ነው፡፡ በዚህ ፀሎት መልስ የሚያገኙ ቦታዎች ከምትገምቱት በላይ ናቸው፡፡ ጥበቃዬ በስራ ላይ

እንዲውል ኃጢያትን መቃወም አለባችሁ፡፡ ይህንን በማድረጋችሁ በትንሹ የንስሐ እንቅስቃሴ እንዲጀምር እየጠየቃችሁኝ ነው፡፡

"ከዚህ በተሻለ መልኩ ደግሞ መዝሙር 51 በየቀኑ ለአለም ሁሉ ፀልዩ፡፡ ይህንንም በማድረጋችሁ ለፍጥረታት ያለኝን የልቤን ሐሳብ ትለማመዳላችሁ፡፡ በዚህም ብዙ ሚሊዮን ነፍሳት ኃጢያታቸውን እየተናዘዙ ንስሐ እንዲገቡ ትጋብዛላችሁ፡፡

ጌታ የተናገረውን እያሰብኩ እያለ ጌታ በአለም ሁሉ ላይ ብርድ ልብስ፣ በጣም ትልቅ ብርድ ልብስ፣ የንስሐ ብርድ ልብስ፣ የጥበቃ ብርድ ልብስ በአለም በሚኖሩ ነፍሶች ሁሉ ላይ ሲሸፍን ተመለከትኩ፡፡ በዚህ ላይ ለመጨመር የምፈልገው ዘ ዲቫይን ሜርሲ ቻፕሌት /The Divine Mercy Chaplet/ የሚለውን አብራችሁ እንድትፀልዩ ነው፡፡ ይህ ፀሎት ደግሞ በሞት አፋፍ ላይ ለደረሱ ኃጢያተኞች ኃይል ያለው ፀሎት ነው፡፡ ይህ ፀሎት ኃጢያተኞች ሊሞቱ በአልጋ ቁራኛ ላይ በሆኑ ጊዜ የመዳን እጅ እንደሚዘረጋላቸው ፋሁስቲን ለምትባል የእግዚአብሔር ሴት ጌታ ቃል የገባላት ነበር፡፡

እዚህጋ አንድ ልጨምር የምፈልገው ነገር አለ፡፡ በአዲሱ ዘመን እንቅስቀሴ ጠልቄ ገብቼ እያለሁ ነገር ግን በአንፃሩ ደግሞ እውነተኛውን አምላክ እየፈለግሁ እያለ፣ አንድ ቀን እግዚአብሔር መንፈሱን ወደ እኔ ላከ፡፡ ይህም ቀን በፈረንጆች አቆጣጠር ሜይ 5 ሲሆን ለሜክሲኮ የነፃነት ቀን ለእኔ ደግሞ የመዳን ቀኔ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጤ ሲገባ መፅሐፍ ቅዱስን አንብቤ የማላውቅ ሴት ወይም በህይወቴ ሰምቼ የማላውቀውን ቃል መዝሙር 51 በቃሌ እየደጋገምኩ ማለት ጀመርኩ፡፡ ከአመታት በኋላ ይህንን በቃሌ ያልኩትን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎ አገኘሁት፡፡ ይህ በዛን ቀን የተሰጠኝ የመዝሙር ክፍል ለመዳኔ ፀሎት አድርጎ መንፈስ ቅዱስ እንደሰጠኝ ተገንዝቤ በደስታ ተሞላሁ፡፡ የኔ ውዶች የእርሱ ቃል እጅግ ኃይል አለው፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." በመዳንሽ ቀን አንቺ አታውቂኝም ነበር፡፡ እኔ ግን ያንጊዜም አውቅሽ ነበር፡፡ ደግሞም አንድ ቀን የኔ ሙሽራ እንደምትሆኚ አውቅ ነበር፡፡ እናም ለመስራት ትፈልጊ የነበረውን ሥራ ይኸውም ሰዎች እኔን እንዲያውቁኝ የምትፈልጊውን አሁን አብረን እየሰራን እንገኛለን፡፡ እድሜሽን ሙሉ ፎቶግራፈር ሆነሽ ትቀሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ገና ከመፈጠርሽ በፊት በአንቺ ውስጥ የፈጠርኩትን ጣፋጭ ቦታ ሊያረካ አይችልም ነበር፡፡ ያም ቦታ የፍቅርና የጠፉትን ክብካቤ የማድረግ ቦታ ነው፡፡ ክሌር በአንቺ ውስጥ ያለውን እሳት ለማቀጣጠል እንዴት እወዳለሁ !"

ጌታ አመሰግናለሁ፣ ይህ እሳት እጅግ ያስፈልገኛል፡፡

ጌታም . . . " ሁላችሁም ይህ ያስፈልጋችኋል፡፡ እናም ከልባችሁ ስትፈልጉኝ ታገኙኛላችሁ፡፡ እንዲሁም የምትመኙትን ይህንን እሳት ታገኛላችሁ፡፡ ይህ ወቅት እናንተን የማነሳሳበትና ወደ ብዙ ተልዕኮዎች የማስተኩሳችሁ ወቅት ነው፡፡ ስቃይ ሲበዛ ብዙ ንስሐ መግባትና መለወጥ ይኖራል፡፡ ይህም አለምን ዘልቆ ከማጥፋቱ በፊት በአገልጋዮቼ መጀመር አለበት፡፡

"የኔ ውዶች በየቀኑ እውነተኛ ንስሐ ካልገባችሁ በቀር በእኔ መገኘት ውስጥም ቀዝቃዛና ግድየለሽ ሆናችሁ ትቀጥላላችሁ፡፡ ጥልቅ የሆነ ኃጢያታችሁንና የአለምን ኃጢያት ንስሐ መግባታችሁን እጅግ እፈልገዋለሁ፡፡ በዚህ ፀፀት በተሞላበት ልብ ውስጥ ከመንግስተ ሰማያት የተትረፈረፈ ቅባት ይፈሳል፡፡ ከዚህ ቅባት ውጪ ግን እንደ ድንጋይ ሃውልት ቀዝቀዛ፣ ማንን እንደምታገለግሉ ግንዛቤ የሌላችሁ፣ በእውነት ማን መሆናችሁንና ወይም ያለመሆናችሁን እንኳን የማታውቁ ሙታኖች ትሆናላችሁ፡፡

"በየቀኑ በምታደርጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ እጅግ ጠንቃቃ እንድትሆኑ አይደለም የምፈልገው፡፡ እኔ የምፈልገው ባዶ መሆናችሁን፣ ድካማችሁንና ጉድለታችሁን እንድትገነዘቡ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ እኔን የበለጠ በመፈለግ እንድትጮሁ ነው የምፈልገው፡፡

"እኔን ለመስጠት እንዴት እፈልጋለሁ መሰላችሁ! የኔ ውዶች ጩሁ አትፍሩ፡፡ 'ጌታ ሆይ አንተን እፈልጋለሁ! አንተን የበለጠ እፈለጋለሁ ብላችሁ ጩሁ! ጌታ እባክህ አንተን የበለጠ ስጠኝ' በሉ፡፡

"ይህንን አድርጉና እኔን በሙላት ታገኙኛላችሁ፡፡ መንግስተ ሰማያት በብዙ ትገፋለች የሚያገኟትም ብርቶዎች ናቸው የሚለውን አልሰማችሁም?(ማቴዎስ 11፡12)፡፡ ስለዚህም ጩኸታችሁ በመንግስተ ሰማይ ይሰማ እኔም ቅር አልሰኝም፡፡ እንዳውም እጅግ ደስ ብሎኝ እናንተ ይሆናል ብላችሁ ከጠበቃችሁት በላይ እሰጣችኋለሁ፡፡ እኔን የበለጠ እንድሰጣችሁ ጩሁ! በእውነትም ደግሞ ትቀበላላችሁ፡፡"

## ኮሮና ቫይረስ - የጌታ የማንቂያ ደውል - ፌብርዋሪ 25 ቀን 2020 ዓ.ም

## The Coronavirus Plague – February 25, 2020

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . ለተጎዱት እየፀለይን የእኛን ልብ ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበቃና ሰላም ይግዛ፣ አሜን፡፡

ጌታ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለህ ለማሰብ እንኳን አልችልም፡፡ የሰውን ክፋት ለማሰብም ከምችለው በላይ ነው፡፡ በዚህ ምድር ላይ ህይወት እንዴት ተሰባሪ እንደሆነ በእውነት በማየቴ በድንጋጤ ፀጥ ብያለሁ፡፡

በቻይና እየተካሄደ ያለውን ነገር አይታችሁ ወይም አላያችሁ እንደሆነ አላውቅም፡፡ በዩ-ቲዩብ የተለቀቁ አንዳንድ ፎቶዎችን ብትመለከቱ እጅግ ልብን የሚያሳዝን ነው፡፡ በምን ሁኔታ እያለፉ እንደሆነ ለመገንዘብ ከቻይና እየወጡ ያሉትን እነዚህን ቪዲዮዎች ለጥቂት ሰዓታት ተከታትያለሁ፡፡ ቪዲዮዎቹን ካየሁ በኋላ ይህንን መልዕክት መፃፍ ጀመርኩ፡፡

ጌታ እነዚህን በማጣትህ የሚሰማህን ስቃይ ልጋራህ እንደማልችል አውቃለሁ፡፡ የደረሰባቸውን ይህንን ጥቂት ነገር ስሰማ በኃዘን ጉልበቴ ተብረከረከ፡፡ ለምን እንዲህ ሆነ ብዬ አልጠይቅም፡፡ ምክንያቱም በጉዳዩ ጀርባ ሰይጣን ስላለበት ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ጥያቄ መጠየቅ አያስፈልገኝም፡፡ ነገር ግን ጌታ ሆይ ጥበብና ብርታት ስጠኝ፡፡ ለህዝብህ ለማካፈል የሚያስችለኝን ብርታት ስጠኝ፡፡

ጌታ ሆይ እኔ የማካፍለው ምንም የለኝም፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . " ቀናቶቹ አጭር ባይሆኑ ኖሮ አንድም እንኳን አይተርፍም ነበር፡፡ ይህ የሰይጣን ክፉ እንቅስቃሴ የሰው ልጅ አይምሮ ከሚረዳው በላይ ክፋት የተሞላበት ነው፡፡ አንቺ ያየሽው እጅግ ጥቂቱን ክፍል ብቻ ነው፡፡ እኔ ግን የሚሞቱን ጩኸት ሰምቻለሁ ደግሞም አይቻለሁ፡፡ ማለቂያ የሌለውን ኃዘናቸውን ተጋርቻለሁ፡፡ ክሌር ህመማቸውና ስቃያቸው ወደር የሌለው ነው፡፡ እያንዳንዳቸው በፍቅር የምወዳቸው ልጆቼ ናቸው፡፡ ቢሆንም ግን ይህንን ልንገራችሁ በሚመጡት ጊዜያት በህይወት ያሉት በሞቱት ይቀናሉ፡፡

ይህንን ለመግታት የማይቻል ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን የሚቻለው ከተለመደው መንገድ ውጪ ነው፡፡ ይህንን ለመቀበል ደግሞ የተዘጋጁ ወይም የሚፈልጉ ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ይህ በሽታ እንደ እሳት ሰደድ ይዛመታል፡፡ እኔን ካልተቀበሉና በእኔ ጥበቃ ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር ብዙዎች ያላቸው መልስ በሽታውን መቆጣጠር የሚል ብቻ ነው፡፡ ከሌር እኔ እየጮኹኩ ያለሁት ለሚሞቱት ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ከእርዳታ ውጪ አላደረኳቸውም ፡፡ እኔን እንዲቀበሉ እድል ስጥቻቸዋለሁ፡፡

ነገር ግን ብዙዎቹ እኔ አምላካቸሁ እንደሆንኩ በእውነት አያውቁም ወይም አይገባቸውም፡፡ ምክንያቱም አይምሮአቸው በዚህ መንገድ እንዲለወጥ ስለተደረገ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ይህንን ሐሳብ እንዲለወጡ የሚያስደርጋቸው ከተለመደው ውጪ የሆነ ቅባት ብቻ ነው፡፡

"ይህ ወረርሽን ወደ አሜሪካም እየመጣ ነው፡፡ ወደ ምድራችሁ ዳርቻ እየመጣ ነው፡፡ እዚሁ ነው ደርሷል፡፡ ስለዚህም የኔን ጥበቃ ለማይፈልጉ ትልቅ አደጋ ተጋርጦባቸዋል፡፡ ምንም ይስሩ ምንም ወደ እኔ እንዲመጡ እፈልጋለሁ፡፡ በሁኔታዎች የማይገድበውን ፍቅሬንና ምህረቴን እንዲያውቁ እፈልጋለሁ፡፡ ነፃ አውጪነቴን፣ የቃል ኪዳኔን ማዳንና ኃይሌን እንዲለማመዱ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን ብዙዎች አያምኑም፣ አይታመኑም ስለዚህም በእምነት ወደ እኔ አይመለሱም፡፡

"እንዲህም ቢሆን ግን በሚያምኑ ዘመዶቻቸው በኩል እነርሱን ለመድረስ እየሰራሁ ነው፡፡ ማዳኔን አሳያቸዋለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ ወደ ማመን ይመጣሉ፡፡

"በአለም ያላችሁ ሁላችሁም የእኔ ናችሁ፡፡ የእያንዳንዳችሁን ህይወት ከመለኮት ዓላማ ጋር በረቀቀ መንገድ አስሬዋለሁሁ፡፡ ነገር ግን በአለም ያለው ህብረተሰብ እኔ ጠንካራ ነፃ አውጪና ፈዋሽ ምንጭ መሆኔን እንዳትረዱ ከእናንተ ውስጥ አውጥቶኛል፡፡ እነርሱ ከእኔ ይልቅ ወደሚያምኑት ሐኪም ቢሄዱ ይሻላቸዋል፡፡ ነገር ግን ለብዙዎች የሐኪም እርዳታ ፍፁም የማይጠቅም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ይህ የተፈበረከው እንደ ጦር መሳሪያ እንዲያገለግል ሆን ተብሎ ነው፡፡

"የኔ ውዶች ሁላችሁም በእኔ የተፈቀራችሁ ናችሁ፡፡ ደግሞም ረዳታችሁ እኔ ብቻ ነኝ እያንዳንዳችሁን በቅርበት አውቃችኋለሁ፡፡ ህልማችሁ፣ ትግላችሁ፣ ስብራታችሁን እንዲሁም በሥራ ውጤታማ መሆናችሁ ይገባኛል፡፡ ሁሉንም ነገር በትክክል አውቀዋለሁ፡፡ ደግሞም የምመኝላችሁ ህይወት እንጂ ሞትን አይደለም፡፡

"እኔ የምመኘው ወደ መንግስቴ ገብታችሁ፣ በእውቀት፣ በማስተዋልና በፍቅር እንድትከብሩ ነው፡፡ እኔ ለእናንተ የምመኘው ነገር በምድር ያላችሁን የህይወት ዓላማ እንድትፈፅሙና በመንግስተ ሰማይ ደግሞ ከእኔ ጎን እንድትሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ከእኔ አትራቁ፡፡ በልባችሁ ውስጥ በመኖር ከእኔ ጋር ተጣበቁ፡፡

"በምድር ያለው ህይወትና እንዲሁም ዘላለማዊው ህይወት ምን እንደሆነ ሳይገባችሁ መመላለስ ሃዘኑ የሚቻል አይደለም፡፡ በቀንና በሌሊት እኔ ወደ እናንተ የምጮኸው በአዲስ መንገድ ልባችሁን ወደ እኔ እንድትመልሱ ነው፡፡ ይህም መንገድ አዲስና እስካሁን ያልገባችሁ ነው፡፡

"እኔ የግንኙነትና የህብረት አምላክ እንጂ ሃማኖት አይደለሁም፡፡ ደግሞ ላቅፋችሁ፣ ላፅናናችሁና አዲስ ተስፋ ልሰጣችሁ እጓጓለሁ፡፡ ነገር ግን በእኔ ፊት ኃጢያት መሆናቸውን የምታውቋቸውን እነዚያን መንገዶች ትታችሁ ወደ እኔ መመለስ

ይኖርባችኋል፡፡ ከኃጢያት ላነፃችሁ፣ በህይወታችሁ ያለውን ጨለማ ላጥብላችሁና በብርሃኔ ልሞላችሁ በዚህም የሰው ልጆችን በማፍቀር እንድትቀጣጠሉ እፈልጋለሁ፡፡

"ይህ መቅሰፍት ከአባቴ ዘንድ የተፈቀደው ከመርፌዱ በፊት እንድትነቁ ለማድረግ ነው፡፡ አብዛኛው የእኔ ህዝብ የሚኖረው ለሌሎች ሳይሆን ለራሱ ብቻ ነው፡፡ አብዛኛዎቻችሁ ባላችሁ ነገርና ብዙ ለመግዛት ባላችሁ ችሎታ ምክንያት እስረኞች ሆናችኋል፡፡ ይህም ውሸት የተሞላበት የደህንነት ስሜት እንዲሰማችሁ አድርጓል፡፡ ስለዚህም ህይወታችሁ እንዴት በቀላሉ ተሰባሪ እንደሆነና በዚህም ራሳችሁን ደስ ማሰኘታችሁ ውጤቱ ምን እንደሆነ  አልታያችሁም፡፡ እናንተ የምታዩት በባህላችሁ ተቀባይነት ማግኘቱን ብቻ ነው፡፡ ይህም ደህንነት እንዲሰማችሁና 'ውጤታማ' የመሆን ስሜት ፈጥሮላችኋል፡፡

"ነገር ግን ይህ በአንድ ሌሊት ከእናንተ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሁላችሁም ከእንቅልፋችሁ እንድትነቁ እንዴት እሻለሁ! በእያንዳንዱ ቀን ለእናንተ የምሻው ነገር ሌሎችን ለመባረክ አዲስ መንገድ እንድትቀይሱ ነው፡፡ ደግሞም በቂ ጊዜ ወስዳችሁ ነፃ ለመውጣትና ጥበብ ለማግኘት ወደ እኔ እንድትጮኹ ነው፡፡

 "ብዙዎች ከእስራት የሚፈቱት ቀላል በሆነ ፀሎት አይደለም ፡፡ ንስሐ መግባትና ከኃጢያት መንገድ መመለስ እንዲሁም እስካሁን የኖራችሁት ህይወት ለእኔ ሳይሆን ለራሳችሁ ብቻ እንደነበረ ማገናዘብን ይጠይቃል፡፡ ነገር ግን በዚህ ወቅት ለሌሎች ትልቅ ምህረት ያሳያችሁ እናንተ ከእኔ ትልቅ ምህረትን ትቀበላላችሁ፡፡ ይህንን ወረርሽኝ ከእናንተ ድንበር ለመመለስ እጓጓለሁ፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ ንስሐን፣ ራስ ወዳድነት የሌለበት የውስጥ ፍላጎትን  እንዲሁም መልካምና ትክክለኛ የሆነ ህይወትን ማየት እፈልጋለሁ፡፡

"ነገሮችን በእኔ ዕይታ ማየት በእርግጥ ከባድ ነው፡፡ በተትረፈረፈ ህይወትና በኃጢያት መኖር ተመችቷችኋል፡፡ በመንግስተ ሰማይ ፊት የትኛው የጠራ እንደሆነ ማገናዘብና ማየት ተስኗችኋል፡፡ የምታዩት ባህላችሁ የሚያሞካሸውን ብቻ ነው፡፡ ይህ ወሳኝ እርምጃ የተወሰደውም ይህንን አመለካከት እንድትቀይሩ ለማድረግ ነው፡፡

"እንዲህም ሆኖ ግን ከምህረት ውጪ አይደለሁም፡፡ እናም ይህንን ወረርሽኝ ለማጥፋት ከፕሬዚዳንታችሁ ጋር እሰራለሁ፡፡ አንድ የምለምናችሁ ግን በጥልቅ በእውነት ከልባችሁ ፀልዩ፡፡ ለቤተሰቦቻችሁ፣ ለሌሎችና ለአገራችሁ ፀልዩ፡፡ በተጨማሪም እጅግ ስቃይ ላይ ላሉ ለቻይናዎች ፀልዩ፡፡ ለማታውቋቸውና ለእንግዶች በፍቅር ልብ የምትፀልዩት ፀሎት በእኔ የህይወት መፅሐፍ በእናንተ መዝገብ ላይ ይፃፋል፡፡ ደግሞም ሙሽራዬ ለእኔ ያዘጋጀችሁ የተገባ ስጦታ ይሆንላታል፡፡

## ኢየሱስ 'እጅግ የምጠላው' ብሎ የገለፀው ነገር - ፌብርዋሪ 27 ቀን 2020 ዓ.ም

## Let the little ones shine, Feb 27, 2020

ጌታ በልቡ ባለው ትህትናና አገልግሎት ሁላችንንም ይባርከን፡፡ እንዲሁም በዚህ ወቅት ራሳችንን ወደ ውስጥ ለመመልከትና በህይወታችን መለወጥ ያለባቸውን ነገሮች ለማየት የምንችልበት ችሎታ ይስጠን፣ አሜን፡፡

ትላንትና ጌታ በመስቀሉ ያደረገውን መስዋዕትና ትንሳኤን ምክንያት በማድረግ የሚደረገው የአርባ ቀን ፆም የጀመረበት ቀን ነበር፡፡

ይህ ወቅት ኩራታችንን ጥለንና ራሳችንን ማገልገል ትተን እኛነታችንን ባዶ የምናደርግበት ወቅት ነው፡፡ እንዲሁም የነፍሳችንን ህመም ጌታ እንዲገልጥልን የምንፈቅድበት፣ በዚህም የምንነፃበትና ጌታ ከሙታን በተነሳበት ክብር ዳግም የምንወለድበት ነው፡፡ የአለም ሥራ አሰልቺ፣ ባዶ የሚያደርግና ለሥጋችን ሲባልም ብዙ ማመቻመች የምናደርግበት ነው፡፡ ይህ ማመቻመች ደግሞ ለማይገባ ነገር ትኩረት በመስጠት ለብ ያለ ህይወት እንዲኖረን የሚያደርግ ነው፡፡ የተወደዳችሁ ይህንን የምላችሁ በትልቅ የእምነት ፅናት ነው፡፡ በወቅቱ ምንም ለማይመስሉ ማመቻመቾች ፈቃዴን ሰጥቼ ራሴን ለማደናገር አጋልጬ ነበር፡፡ በኋላ ግን ራሴን ስመረምረው እነዚህ ነገሮች ከጌታ ጋር ያለኝን ግንኙነት ለማበላሸት ወሳኝ እንደሆኑ ተረዳሁ፡፡

ስለ እነዚህ ነገሮች ንስሐ እየገባሁ ልቤን እንዲያነፃና ንፁህ እንዲያደርገው ጌታን እየጠየኩት ነው፡፡ ጥሩ መስራት ሲገባኝ ጉድለት የፈፀምኩባቸውን ነገሮች እውቅና በመስጠት ጌታን "ሐሳቤን እንዳልሰበስብ የሚያደርጉ ምድራዊ ነገሮችን፣ አንተን የማያስደስቱ የልብ ዝንባሌዎችንና ከአንተ ጋር በአግባቡ እንዳልሆን ጊዜን ከአንተ የሚሰርቁ ነገሮችን አንሳልኝ" በማለት እየጠየኩት ነው፡፡

በዚህ ማለዳ ጌታ የቤተ ክርስቲያንን ከንቱነት በአይምሮ አመጣ፡፡ ይህም ብዙዎች ታዋቂ፣ የተከበረና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ባለሥልጣን ለመሆን በመፈለግ የሚያደርጉትን ውድድር የሚመለከት ነበር፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሊሰራ ላለው የዝግጅት ወቅት ወደ ስህተትና ወደ ግብዝነት የሚመራ ነው፡፡ እርሱ የሚጠይቀን የራሳችንን ታላቅነት ትተን በእርሱ ዝቅ ማለት እንድንቆይ ነው፡፡

በዚህ ዓይነት መንገድ የእኛን ሳይሆን የእርሱ ብርሃን ይንፀባረቃል፡፡ የእርሱ መንገድ እየገባቸው ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር ያሳያቸውን ለመግለፅ የሚችሉበት ክፍትና ደህንነት ያለበት ጉባኤ ያገኛሉ፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ብዙ ጊዜ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሁታንና ለታናናሾች ግን ሚስጥራትን ይገልፃል፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "ሌሎችን ለመምራት እውቀትና ብቃት እንዳለው እንደ ቤተ ክርስቲያን ምሰሶ ለመታወቅ በመለማመድ ያደከው ህዝቤ ከንቱ የሆነውን መንገድህን አጢነው፡፡

"ቅዱስ በሆነ ትህትና በእኔ ላይ የፀኑትንና በዙሪያህ የሚገኙትን ታናናሾችን በመመልከት ራስህን ትሁት ባደረግህ ነበር፡፡ እነርሱ የተነሳሱት አጋጣሚዎችን በመጠቀም ባላቸው እውቀት አንፀባርቀው በሌሎች ፊት ከብረው ለመታየት ሳይሆን በእኔ ላይ ፀንተው ቅዱስ በሆነ በእግዚአብሔር ፍርሃት፣ታናሽ ሆነው በመደበቅ ለመቀጠል ባላቸው ጥልቅ ፍላጎት ነው፡፡ ይልቅም እነርሱ የሚጓዙት በእኔ ላይ ባላቸው ትልቅ ፍርሃትና ከእነርሱ በላይ የሆኑትን ሁሉ ክብር በመስጠት ነው፡፡

"ከዚህም የተነሳ እነርሱ የሚናገሩት ጥቂት ነው፡፡ በእነዚህ ደግሞ እኔ ደስተኛ ነኝ፡፡

"ልጆቼ የእናንተን አስፈላጊ መሆን ትታችሁ የኔን ድህነትና ትህትና ያዙ፡፡ ትኩረት ለመሳብ አትወዳደሩ ወይም በሥልጣን ንግግር አትናገሩ፡፡እንዲህ ዓይነቱ ነገር ያቅለሸልሸኛል! ይልቅስ ለመደነቅም ይሁን ለመታወቅ ምንም ፍላጎት የሌላቸውን በአጠገባችሁ የሚገኙትንና የማይናገሩትን ታናናሾች ዝም ብላችሁ በአክብሮታዊ ፍርሃት አድንቋቸው፡፡ እነርሱ የተጠመዱበት ዋና ሥራ በታናሽነታቸው በእኔ ላይ ፀንቶ ለመኖር፣ የኔን አዲስ መንገድ ለመማርና ወንድሞቻቸውን ላለማስቀየም ነው፡፡

"እነዚህ ከእኔ ጋር በሚያምር ወርድና ስፋት የሚኖሩ ናቸው፡፡ ይህም ወርድና ስፋት በሰዎች ለመታወቅ ካለው ትግል፣ እርስ በርስ ከመወዳደር፣ ከሰዎች ምስጋናና ክብር ከመቀበል የፀዳና ሰላምና ነፃነት ያለበት ነው፡፡ በዚህም ሥፍራ ዕረፍት እሰጣቸዋለሁ፡፡

ስለዚህ በሰዎች ፊት ለመታየት የሚፈልጉ አትሁኑ፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶች አዋቂ መሆናቸውንና ያላቸውን እውቀት ለማሳየት ሁልጊዜ መንገድን የሚፈልጉ ስለሆነ ሁልጊዜ በልባቸው ሰላም ያጡ ናቸው፡፡

"የምጠይቃችሁ ይህንን ትልቅ ጥረት ትታችሁ ሰላማችሁንና እረፍታችሁን እንድታገኙ ነው፡፡ የኔን አዎንታ ለማግኘት እንጂ በምንም ነገር አትሸበሩ፡፡ ለመከበርና እውቅና ለማግኘት በሚል ሐሳብ አትጠመዱ፡፡ እናም የኔን ዝቅ ማለት እና ልታይ ልታይ አለማለትን ልበሱ፡፡ በዚህም ከፍ ለማለት የሚፈልጉትን ከሚያጠምደው ሞኝ ስጋቶችን ከሚፈጥረው የግብዝነት መረብ ታመልጣላችሁ

"እነዚህን ነገሮች የምነግራችሁ ጣፋጭ ከሆነው ህብረታችን መንገድ ላይ በመቆማቸው ነው፡፡ በእውነትም ደግሞ ሌሎችን ከእኔ ያምታታል፡፡ ይህ ደግሞ ሌሎች እኔን ከማየትና ከማድነቅ ይልቅ እናንተን እንዲያደንቁ ያደርጋል፡፡

"የኔ ውዶች አነስተኛ በመሆናችሁ ደስ እያላችሁ እኔ በሌሎች ላይ እንዳፀባርቅ ፍቀዱልኝ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሞ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፣ ፍሬውም እጅግ ጣፋጭ ይሆናል፡፡"

## ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ከጌታ ኢየሱስ የተሰጡ መመሪያዎች - ማርች 7 ቀን 2020 ዓ.ም
## Coronavirus - Spiritual Protection and Practical Measures – March 7, 2020

የጌታ ሰላም ከእናንተ ጋር በመሆን ወደ ፅድቁ ሁሉ ይምራችሁ፡፡ ልባችሁ በጌታ ለመለወጥ የለሰለሰና የተዘጋጀ ይሁን፣ አሜን፡፡

የተወደዳችሁ ሆይ ህዝቅኤል ጉልህና እውነተኛ የሆነ ህልም አይቶ ነበር፡፡ ይህም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ተረጋግጦለታል፡፡ በዚህ ህልሙ ውስጥ ብዙ ቅዱሳን ሊጎበኙት መጥተው ነበር፡፡ በኋላም እግዚአብሔር አብ መጥቶ ነበር፡፡ ከጉብኝቱም መጨረሻ ላይ ብዙ ሚዛኖች እንዲያይ ተደርጎ 'ሰባት ዓመት' የሚል ድምፅ ሰማ፡፡ ታዲያ እኛ የሰባት አመቱ የመከራ ዘመን ሊጀምር መስሎን ነበር፡፡ ነገር ግን እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ከጌታ ብዙ ጥበብ እንዲሰጠኝ እየፈለግሁ እገኛለሁ፡፡

<u>"ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው እንስሳ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። አየሁም፥ እነሆም፥ ጥቁር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ይዟል። በአራቱም እንስሶች መካከል አንድ ድምፅ አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር፣ ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ ዘይትንና ወይንንም አትጉዳ ሲል ሰማሁ።"</u> ራዕይ 6፡5-6፡፡ በእኛ ዘመን ስናሰላው አንድ ፓውንድ የሚመዝን ስንዴ በአንድ ሳንቲም እጅግ ርካሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዛ ዘመን አንድ ወዝአደር አንድ ፓውንድ ስንዴ ለመግዛት የቀን ደሞዙን ሁሉ ይወስድበታል፡፡

ዛሬም ህዝቄኤል ብዙ ሰዎች በቻይና፣ በአሜሪካና በአለም ሁሉ በኮሮና ቫይረስ ሲሞቱ ስላየ በብርቱ ምልጃ ውስጥ ነበር፡፡ እየፀለይን እያለም በኮሮና ቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች በሚሰቀቃዩበት አንዳንድ የስቃይ ምልክቶች እርሱም እየተሰቃየ ነበር፡፡ እኔም ጌታን ለመንደራችን የሚሆን ምግብ ማስቀመጥ እንዳለብኝ ስጠይቀው ስለፈቀደልኝ ለአንድ ወር የሚሆን ትንሽ ምግብ ለአባላቶቻችን ገዝቼ አስቀመጥኩ፡፡ እናም ከሌሎች ጋር የምንካፈለው ተጨማሪ ምግብ እየፈለግን ነው፡፡

ነገሩን በአጠቃላይ መልኩ ስመለከተው ምናልባት በአገሪቷ ውስጥ የምርትና የትራንስፖርት  እጥረት ቢከሰት የሚያስፈልገንን ምግብና ውኃ እንዲሁም መድኃኒቶች፣ አልኮልና እጅን ማፅጃ ሳኒታይዘር፣ ማስኮች፣ ጋዝና ዘይት፣ የሽንት ቤት ወረቀትና በቤት የምንጠቀምባቸው ሌሎች ቁሳቁሶችን ገዝቶ ማስቀመጥ ጥበብ መስሎ ይታየኛል፡፡ ምክንያቱም ወደ ገበያ ማዕከላት የሚያጓጉዙ መኪናዎችም በተለመደው መጠን ጭነው እንደ ወትሮው በመንቀሳቀስ ሥራቸውን በተለመደ መልኩ ላያከናውኑ ይችላሉ፡፡

ካሮል አንድ ጓደኛዋ አየሁ ያለችውን ህልም እንዲህ ስትል መስክራልኛለች፡፡

"ዕቃ ለመግዛት በገበያ ማዕከል እያለሁ ሰምቼ የማላውቀው ክሎሬላ (Chlorella) የሚባል ነገር ድንገት በመንፈሴ ለኮሮና ቫይረስ ማርከሻ (antidote) መሆኑን አወኩ፡፡

"ስለዚህም ይህንን ነገር ለመግዛት ተሰለፍኩ፡፡ በገበያ ማዕከሉ የነበሩ ሰዎችም እንደ እኔ እውቀቱ ስለተሰጣቸው ሁሉም ለመግዛት ተረባርቦ ስለነበር ቶሎ አለቀ፡፡ ከእንቅልፌ ስነቃም  ክሎሬላ የሚለውን ስም እንዳልረሳው በተደጋጋሚ በጭንቅላቴ እየመጣ ነበር፡፡ ይህ ነገር ለመሆኑ ያለ ነገር ነው? በማለት በድህረ ገፆች ስፈልግ  በጣም የሚያስደንቅ ፅሑፍ አገኘሁ፡፡ ፅሑፉም ክሎሬላ(Chlorella) በሽታን ለመከላከል ለሰውነታችንና ለሳንባችን  የሚጠቅም  ትልቅ ኢጋዥ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

"አንዳንዱ ክሎሬላ(Chlorella) ደግሞ የአይረን ንጥረ ነገር(Iron) ስላለው ልጆች  እንዲወስዱት አይመከርም፡፡ ይህ ደግሞ በጣም የሚገርም ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ልጆች በቫረሱ ብዙም ስለማይጠቁ ነው፡፡

"ለማንኛውም ህልሙ ከጌታ ከሆነ ሊረዳን የፈለገው ጤነኞች ሆነን በህይወት በመኖር  የእርሱን ሥራ ለመስራት እንድንችል ነው፡፡"

ክሎሬላ(Chlorella) ከነጠላ አልጌ ዝርያና ኮሎራይት ከሚባለው ክፍል የሚመደብ አረንጓዴ አልጌ ነው፡፡ የተጠቃሚዎች ሰነድ እንደሚያሳየው በየቀኑ ክሎሬላ(Chlorella) ከ2-5 ግራም ወይም 300 ሚሊግራም የሆነ ከ10-15 ክኒን በመውሰድ የሚታይ ለውጥ በሰውነታችን ላይ እንደሚያመጣ ያመላክታል፡፡ ዶክተሮችና የስርዓተ ምግብ ባለሞያዎች በየቀኑ ከ3-5 ሚሊግራም ክሎሬላ ኪኒን (Chlorella) በመውሰድ በጤና ላይ የሚያመጡ ችግሮችንና በሽታዎችን መከላከል እንደሚቻል ይመክራሉ፡፡ ክሎሬላ(Chlorella) ሰውነታችን እንዲሁም ሳንባችን በሽታን እንዲከላከል የሚረዳ ነው፡፡ ስለዚህ መድኃኒት በድህረ ገፆች ላይ ራሳችሁ መመልከት ትችላላችሁ፡፡

ሌሎች መድኃኒቶችን የምትወስዱ ሰዎች ይህንን ኢጋዥ መድኃኒት ከመውሰዳችሁ በፊት ከዚህ ጋር የማይስማሙ መድኃኒቶች ስላሉ ከመውሰዳችሁ በፊት ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባችኋል፡፡ ከእነዚህ መድኃኒቶች ውስጥ በድህረ ገፁ ላይ እንደ

ምሳሌ የቀረበው ደምን የሚያቀጥን መድኃኒት ይገኝበታል፡፡ ስለዚህም ይህንን መድኃኒት የምትወስዱ ሰዎች ከመውሰዳችሁ በፊት ተጨማሪ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ እኔ በሽታን ለመከላከል እንዲረዳኝ ዚንክና ቫይታሚን ዲ-3 በየቀኑ በተጨማሪ እወስዳለሁ፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ ረድቶኛል፡፡

የተወደዳችሁ ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ጌታ እኛ እንድናደርግ እየነገረን ያለው ነገር መዝሙር 91 በየቀኑ እንድንፀልይ ነው፡፡ እኔ ደግሞ በተጨማሪ የምመክራችሁ ነገር በመጀመሪያ መዝሙር 51 በጣም ዝግ ብላችሁ ከልባችሁ እንድትፀልዩ ነው፡፡ እንዲሁም ጌታ ደስ የማይሰኝበትን ነገር ከገለጠላችሁ እባካች፣ እባካችሁ ያንን ነገር ከህይወታችሁ አስወግዱ፡፡

ለምንም ነገር በር አትክፈቱ፡፡ የጎዳችሁ ሰው ካለ ይቅርታ ጠየቀም አልጠየቀም ይቅር በሉ፡፡ መራራ ዘር በውስጣችሁ ካለ በእርግጠኝነት ይበክላችኋል፡፡ እናም በርን ይከፍታል፡፡

እኛ ለሰዎች ይቅርታ የማናደርግ ከሆነ ጌታ እኛን እንዴት ይቅር ይለናል? ይህ በጣም ቀላል ነው፡፡ ይቅር አይለንም፡፡ ቃል የገባልን ነገር ሌሎችን ይቅር ካልን እርሱም ይቅር እንደሚለን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በር አትክፈቱ፡፡

እንዲሁም በቂ እረፍት አድርጉ፡፡ መሥራት አለብኝ በሚል ፍላጎት ብቻ ትልቅ ሥራ በመጀመር ሰውነታችሁን አታድክሙ፡፡ እንደዚህ ዓይነት መነሳሳት ሰውነታችሁን አቅም ለማሳጣት በእርግጥም ከጠላት የሚላክ ነው፡፡

የተወደዳችሁ በጣም ትልቁ የመከላከል ዘዴ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ መውደድ ነው፡፡ እንዲሁም በትህትና መመላለስና ሌሎች ከእኛ ይበልጣሉ ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ይህንን ቃል እገባላችኋለሁ ሌሎችን ቀርባችሁ ብታዮአቸው እናንተጋ የሌለ ብዙ ፀጋ እነርሱጋ ታገኛላችሁ፡፡ ስለዚህ ይህ ነገሮችን ሁሉ ቀለል ያደርግላችኋል፡፡

ይህ ጊዜ ለለውጥ የምንነሳሳበትና ራሳችንን የምናፀዳበት ወቅት ነው፡፡ ሁላችንም በህይወታችን እንዲሆን ከፈቀድነው የተደጋገመ ኃጢያት እንድንወጣ ጌታ እየገፋፋን ነው፡፡ ስለምንም ጉዳይ ጌታ ህሊናችንን እንዲነካ ካደረገ እባካችሁ ያንን ተቀበሉና ከማድረግ ተቆጠቡ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ደም ለእድገቷ ዘር በመሆኑ በዚህ የወረርሽኝ በሽታ ብዙ ክርስቲያኖች ሌሎች እንዲለወጡ እየጮሁ ነው እየሞቱ ያሉት፡፡ ጌታ ይህንን እየፈቀደ ያለው ማመቻመችን ትተን ጌታን አጥብቀን እንድንይዝ ነው፡፡

በተጨማሪ ስለ ራሴ የማካፍላችሁ ነገር ጌታ አንዳንድ ዝንባሌዎችንና ፍላጎቶችን እንድተው በእኔ ላይ እየሰራ መሆኑን ነው፡፡ በእንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ግድ የለሽ የሆንኩባቸው ነገሮች አሉ፡፡ በእነዚህም ነገሮች ላይ ልቤ ለጥቂት ጊዜያት ያስቸግረኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰነፍ ሆኜ ነበር፡፡ አሁን ግን ፀጋውን በመስጠት ራሴው እንዳፀዳው ለእኔ አሳልፎ ሰጥቶኛል፡፡

ጌታ በዚህ ላይ የምትጨምረው ነገር አለህ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "የሰጠሸው መመሪያ እውቀት የተሞላበትና ዒላማውን  የሚመታ ነው፡፡ አንዳንዶች ቀላሉን መንገድ ለምሳሌ ተጨማሪ መድኃኒቶችን መግዛትን በመምረጥ መልስ ይሰጣሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ለእኔ ክብደት በመስጠት ንስሐ በመግባት ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ የኔ ውዶች ላልዳኑት የቤተሰብ አባላት እንድትቆሙ ካልጠራኋችሁ በቀር ከዚህ ቫይረስ የሚያድናችሁ ጠንካራው ከለላ ንስሐ መግባትና ከልብ በሆነ ፍላጎት እኔን ለማስደሰት የምታደርጉት ምላሽ ነው፡፡

በተጨማሪም ለድሆች መስጠትን፣ የታመሙትን መጠየቅንና እስረኞችን መጎብኘትን  አታቋርጡ፡፡ ቸርነት ከእኔ ጥበቃ ለማግኘት ትልቅ ምሽግ ነው፡፡ ምግብ ለማስቀመጥ ችሎታው ካላችሁ ለሌሎች ብላችሁ ካደረጋችሁት ያስደስተኛል፡፡ ይህንን አስታወሱ እጅግ አስፈላጊ በሆነ ወቅት ወደ እኔ በመምጣት ጠይቁኝ፡፡ ያለውን ዳቦ ማባዛት መቼም አቁሜ አላውቅም፣ ወደፊትም አላቆምም፡፡ ይህንን የማደርገው ግን ራሳቸውን ለሚያገለግሉ ስስታም ነፍሶች አይደለም፡፡ ነገር ግን ወንድሞቻቸውን እንደ ራሳቸው ለሚወዱ ነፍሳት ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፡፡ ቸርነት ማድረግ የኃጢያትንም ብዛት ይሸፍናል፡፡ በመንግስተ ሰማያት ህይወታችሁን መለስ ብላችሁ ስትመለከቱት የዚህን ኃይል እንቅስቃሴ ትመለከታላችሁ፡፡

"አትደናገጡ፡፡ በሰዎችም ላይ ድንጋጤን አትቀስቅሱ፡፡በዚህ ፋንታ ሰዎችን ለፀሎት አነሳሱ፡፡  እናም ለህዝቤ ኃይል ያለው ፀሎት ላይ መሆኑን ንገሩ፡፡ በተቀደሰ ህይወትና ከልብ በሆነ ፀሎት ብቻ ብዙ ማድረግ እችላለሁ፡፡

"ህዝቤ አሁን በማያቋርጥ ኃጢያትና በማይበገር ስህተት ውስጥ ካላችሁ መልካሙን ገድል ተጋደሉ፡፡ ወደ እኔ ኑና ፀሎታችሁን አከብራለሁ፡፡ አስታውሱ እውነተኛ መፀፀትና ለመለወጥ የሚደረግ ጥረትን በማየት ቅድስናን እንደተጎናፀፋችሁ ያህል ፀሎትን አከብራለሁ፡፡

"የኔ ብርቅዬዎች እኔ የምመለከተው ልብን ነው፡፡ ልባችሁን ከፍርድ፣ ከኩራት፣ ከዝሙትና ከስስት ጠብቁ፡፡ ለራሳችሁ ሃቀኛና ጥብቅ ሆናችሁ ከቆያችሁ በእኔ መገኘት ምንም የሚያስፈራችሁ ነገር የለም፡፡ አሸናፊ ለመሆን የምትችሉበትን ርህራሔና ፀጋን ትቀበላላችሁ፡፡

"ከእናንተ የቀረሁበት አንድም ደቂቃ እንደሌለ እወቁ፡፡ የልባችሁን አቤቱታ፣ የምታስቡትን ሐሳብ፣ አስተያየትና ፍርድ የሌለውን ልባችሁን፣ እንዲሁም ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁንና ያለገደብ ለማፍቀር ያላችሁን ፍላጎት አደምጣለሁ፡፡

"እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ በእነዚህ ባህርያት ላይ ተጣበቁ፡፡ እኔ ደግሞ አስጨናቂ ቀን በመጣ ጊዜ እታደጋችኋለሁ፡፡"

## ነቀፋ በሌለው ህይወት መመላለስ - ማርች 12 ቀን 2020 ዓ.ም

## Walking a Blameless Life - March, 12, 2020

ውድ ቤተሰቦች ህዝቅኤልና እኔ ጉድለት በተገኘበን የህይወታችን ክፍል ትላንትና ማታ በጌታ ግሳፄ ተጎብኝተን ነበር፡፡ ግሳፃውም በትልቅ ደግነትና በትልቅ ምህረት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ጌታን በበለጠ እንድንፈራውና እንድናወድሰው ተደርገናል፡፡ ይህ ህመም ያለበት ተሞክሮ ለሁላችንም የተሰጠ በመሆኑ አካፍላችኋለሁ፡፡ ይህ ወቅት የመስተካከልና ወደሚቀጥለው ክብር ለመሸጋገር የምንዘጋጅበት ወቅት መሆኑን መረዳት ያስፈልገናል፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ህዝቦቼ እናንተ እንድትሰቃዩ የልቤ ሐሳብ ወይም  እቅዴ አይደለም፡፡ ለሰይጣን ታልፋችሁ የምትሰጡበትን አጋጣሚ ስለምፀየፈው  በህይወታችሁ ተግባርያዊ እያደረጋችሁ ያላችሁትን አደገኛ ልምምዶች እንድትተዉ ማድረግ አለብኝ፡፡ እነዚህ ልምምዶች ናቸው ለሰይጣን በር ከፍተው ቀስ በቀስ እንዲገባ በማድረግ ወደ ጥልቅ ኃዘን እንዲከቷችሁ የሚያደርጋችሁ፡፡

"ትላንትና ምሽት ከሌርንና ሀዝቄልን በግሳፄና በምህረት ጎብኝቻቸዋለሁ፡፡ ይህ ለሁላችንም የሚያም ነገር ቢሆንም መደረግ የነበረበት ነበር፡፡ እነርሱ ፍፁም አይደሉም፡፡ ቢሆንም ግን ፍፁም ለመሆን ፍላጎት ያላቸውና በእኔ እርዳታ ፍፁም ለመሆን የሚጥሩ ናቸው፡፡ ስለዚህም እጅግ ፈታኝ በሆነ ወቅት በእኔ ላይ የፀኑ ቢሆኑም እንደ ዱቄት እንዲልሙ መደቆስ ነበረብኝ፡፡"

(ከሌር) የሚገርም ነው! ይህ በትንሹ ተደርጎ ሲታይ ነው፡፡ ምን ብዬ ልገልፀው እንደምችል እንኳን አላውቅም፡፡ እጅግ የላመ ዱቄት! እንዳውም ከላመ ዱቄት እጅግ የበለጠ ማለት ነው የምችለው ፡፡ እንደ ጭስ ያህል ድምጥማጡ የጠፋና ብናኝ የሆነ!

ኢየሱስም . . . "ሁላችሁንም በዚህ ዓይነት መንገድ ብጎበኛችሁ እወዳለሁ፡፡ ምክንያቱም የእናንተ ልምምድ ፅድቅ የሌለበት በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ደግሞ ከእኔ የሚለያችሁና የማይንቀሳቀስና ቀዝቃዛ ህይወት እንዲኖራችሁ የሚያደርግ ነው፡፡ ነገር ግን እንድታውቁልኝ የምፈልገው በዚህ ዓይነት መንገድ እናንተን ለመጎብኘት ስገደድ እናንተ ማወቅ ከምትችሉት በላይ ልቤ እየተጎዳ እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም የላመ ዱቄት እስክትሆኑ ድረስ እናንተን ስደቁስ እኔም በእናንተ ውስጥ ሆኜ እየተደቆስኩ እንደሆነ ማወቅ አለባችሁ፡፡ ስለዚህም እናንተ በምትሰቃዩበት ስቃይ እኔ በበለጠ መልኩ እሰቃያለሁ፡፡

"ኃጢያትን በተመለከተ ከሌር ተከታታይ ትምህርቶችን እንድታዘጋጅ ጠይቄያታለሁ፡፡ ይህም በቅድስና ምን ጉድለት እንዳለባችሁና ከእኔ ጋር ምን ደረጃ ላይ እንዳላችሁ የሚያሳያችሁ ይሆናል፡፡ ሁኔታውን በመሸፋፈን በለዘበ መንገድ ልገልፅላችሁ እችላለሁ፡፡ እንደዚህ ባደርግ ደግሞ ፍርዱ ከመምጣቱ በፊት በኃጢያታችሁ ላይ እርምጃን ባለመውሰዴ ያልጠበቃችሁት መሸማቀቅ ይገጥማችኋል፡፡ አዎን ፍርድ በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወደ አሜሪካና ወደ አለም ሁሉ እየመጣ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህን ውድ የሆኑ የህይወት ውኃዎችን ለመሸከም እንድትችሉ ፅድቅ ከሌላቸው ነገሮች መለየትና ንፁህ መሆን አለባችሁ፡፡

"ይህ እናንተን ለማውገዝ የተዘጋጀ ክፍለ ጊዜ አይደለም፡፡ ይልቁንም በዝሙት እጅ ከፍንጅ እንደ ተያዘችው ሴት እንኳን ቢሆን ገስፆ ለመመለስ እንቅስቃሴ የሚደረግበት ወቅት ነው፡፡ ያችን ሴት ከሳሾቿ የፈለጉት ሊገድሏት ነበር፡፡ ነገር ግን በዚች ነፍስ ውስጥ ያለውን መልካምነት ስለማወቅ በመካከል ጣልቃ ገብቼ ኃጢያቷን ይቅር አልኳት፡፡ እርሷን ለመውገር ድንጋይ ያነሱባት እነዚያም ተመሳሳይ ኃጢያት በልባቸውና በህይወታቸው ውስጥ ይገኝ ነበር፡፡

"ትላንት ምሽት ሙሽራዬን ለማንፃት እርምጃ የጀመርኩበት ጊዜ ነበር፡፡ እናም ይህ መልዕክት ለአለም ሁሉ እንዲሰራጭ ፍላጎቴ ነው፡፡ ለአንዳንዶች ይህ ምክንያት የሌለውና ጠንካራ ሆኖ ይታያቸዋል፡፡ እንደዚህ የሚሰማችሁ ሰዎች የህይወታችሁን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በውዳሴ ፍርሃት ለእኔ ለመስጠት ከሚያስችለው ከቅድስናዬ ጋር ገና አልተገናኛችሁም ወይም በክብሬ ገና አላያችሁኝም፡፡

"እነዚህን የህይወት ውኃዎች ለመሸከምና ለአገራት ደህንነት ለማምጣት እንደዚህ ዓይነት ፍርሃት በእናንተ ውስጥ ሊኖር ይገባል፡፡

"የዚህ ዓይነት ኃጢያት ነው የእኔንና የእናንተን ግንኙነት በማቋረጥ በመካከላችን ገብቶ አጥር የሚሰራ፡፡ ይህም ተመልሶ ምስክርነታችሁንና እምነታችሁን ያዳክማል፡፡ለዚህ ነው ሰይጣን የወንድሞች ከሳሽ የተባለው፡፡ የእናንተን ፈቃድ ሰጥታችሁ መቼ እንዳመቻመቻችሁ በደንብ ታውቁታላችሁ፡፡ ስለዚህም ያቺ ዝሙት ስትፈፅም የተያዘችውን ሴት እንዳነፃኋት እንደዛው ላጥባችሁና በጣም አስቸጋሪና ፈታኝ በሆነ ወቅት እንኳን በንፁህ ህሊና ከእኔ ጋር እንድትፀኑ እፈልጋለሁ፡፡

"ውድ ኸርት ድዌለርስ በእርግጥም ትንንሽ ቀበሮዎች ናቸው የወይኑን ቦታ የሚያጠፉት፡፡ ሰይጣን ሰውን ለመግደል እናንተን ማነሳሳት ባይችልም እንኳን በሞት አፋፍ ላይ ያሉትን ድሆች ባለመርዳታችሁ ወይም ችላ እንድትሉ በማድረጋችሁ እንዲሁም መናገር የሌለባችሁን መልካም ያልሆነ ንግግር እንድትናገሩ በማድረግ በአገልግሎታችሁ ላይ ትልቅ ጥፋት ሊያመጣ ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተግባራት የነፍሳትን ህይወት ስለሚሰርቁ ውጤታቸው ከግድያ ጋር ምንም አይተናነስም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ሲፈፀሙ ሰዎች ከአገልግሎቱ ጋር ወይም ከህብረተሰቡ ጋር እንዳይቀጥሉ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም ለቤተሰብ የሚያስፈልገው ገንዘብ እንዲቋረጥ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም በበለጠ ደግሞ የሚከተሏችሁ ሰዎች በእናንተ ላይ ያላቸውን አመኔታ ያጣሉ፡፡ በተጨማሪም በትምህርቶቻችሁና በፀሎቶቻቸው ላይ አመኔታን ያጣሉ፡፡ እነዚህ ትምህርቶቻችሁ ደግሞ በእርግጠኝነት በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተመረኮዙና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡

"ባህርይን መግደል የሰይጣን ሥራ ነው፡፡ የእርሱም ኤጋንንቶች በዚህ ሥራ ላይ የሰለጠኑ ናቸው፡፡ ስለዚህም በትክክለኛው ጊዜ የሚገድል ቃልን በአይምሯችሁ ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ እናንተም ባለማስተዋል ያንን ቃል ትደግሙታላችሁ፡፡ ሰይጣን በቀንና በሌሊት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ወንድሞችን ይከሳል የተባለበት ምክንያት አለው፡፡ እርሱ የወንድሞች ከሳሽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ የሚያደክምበት፣ የሚያጠፋበትና የሚገድልበት መርዛማው መሳሪያው ነው፡፡

"ስለዚህም ስለ ራሳችሁ መጥፎ ስሜት ከተሰማችሁ፣ ደስታ ካጣችሁና ወደ ፊት ለመቀጠል መነሳሳት ከሌላችሁ ከእኔ ጋር በፀሎት መቆየት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በእነዚያ ዝማሬዎች እነበኛችሁና ከእኔ ጋር ተመልሳችሁ እንድትቆሙ አደርጋችኋለሁ፡፡ ምንም ያላደረጋችሁ ብትሆኑም እንኳን ይህ እድሳት ያስፈልጋችኋል፡፡ ምክንያቱም ግማሽ ከፍላችሁ የጠላትን ውሸት በማመን በውስጣችሁ ሥር በመስደድና በመስፋፋት በውስጣችሁ ያለውን መንፈስ ያንቃል፡፡

"እዚህ ያለሁት እናንተን ለመኮነን አይደለም ስላችሁ እባካችሁ እመኑኝ፡፡ እኔ እዚህ ያለሁት ሌሎቹን ሳትጎዱ ማሻሻል ያለባችሁን ላሳያችሁና በአለም ላይ መንቀሳቀስ ሊጀምር ያለውን የህይወት ውኃ ለተጠማውና ሊሞት ለተቃረበው አለም ይዛችሁ እንድትሄዱ ነው፡፡ ይህ ንዝህላልነት ውድ የሆኑትን እነዚህን ቅባቶች መያዝ እንደማይችል የተሰነጠቀ ሸክላ አይነት ነው፡፡

"የኔ ክሌር ትላንትና አንቺንና ህዝቄልን ያደረግሁትን የጉብኝት ጊዜ እንድታካፍያቸው እፈልጋለሁ፡፡"

"የኔ ውድ ቤተሰቦች በህይወቴ እንደዚህ ዓይነት ፍፁም ጥልቅ የሆነ የንስሐ ጊዜ ምናልባት በመጀመሪያ ጌታን ሳገኝ ካልሆነ በቀር ኖሮኝ ያውቃል ብዬ አላምንም፡፡ በፀሎታችን ጊዜ ጠላት እኛን እንዲያገደን ጌታ እንደፈቀደ አውቄያለሁ፡፡ ህዝቄል ሆኖ አይቼው በማላውቀው ስቃይ ውስጥ ነበር፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፅሐፍ ስንከፍት (The Bible promises book) "ጠላቶች" የሚል ገፅ ወጣልን፡፡ ስለዚህም ጠላትን እየተቃወምን ለሰዎቹ ደግሞ መለወጥና መልካም ነገር እንዲሆንላቸው መፀለይ ጀመርን፡፡ አንድ ደረጃ ላይ ስንደርስ ግን ሁለታችንም ራሳችንን ፍፁም መከላከል የማንችል ሆኖ ተሰማን፡፡ እናም ጌታ ምህረት! እያልን መፀለይ ጀመርን፡፡ ለረዥም ጊዜያት መፀለይ የቻልነው "እባክህ ጌታ ምህረት አድርግልን" እያልን ብቻ ነበር፡፡ ከዚያም ህዝቅኤል በቅባቱ ተነቃቃና ቆሞ ቃል በማወጅ በታላቅ ድምፅ ጠላቶቻችንን መቃወም ጀመረ፡፡

ከዚያም በኋላ ስቃዩ ወዲያው ቆመ፡፡ ጌታም ዝሙት ፈፅማለች ስለተባለችው ሴት የተነገረውን ቃል እየዘረዘረ በህዝቅኤል በኩል መናገር ጀመረ . . . "ከሳሾቻችሁ አሁን የታሉ? እኔ አልከሳችሁም፡፡ ኃጢያታችሁ ይቅር ስለተባለላችሁ ሌሎችም ሊከሳችሁ አይችሉም፡፡"

እዚህጋ ጌታ እየተናገረ ያለው በህይወታችን ስለተፈፀመ ዝሙት ሳይሆን እየተናገረ ያለው በአጠቃላይ መልኩ ስለ ኃጢያት ነው፡፡ ይህንን ነገር ጌታ ሲናገር ማለት የቻልኩት 'ጌታ ሆይ በአንተ ኃይል ይህንን ኃጢያት ደግሜ አልፈፅመውም' ብቻ ነበር፡፡

ከዚያም ኢየሱስ በህዝቅኤል በኩል ከእርሱ የተቀበልነውንና ሥራ ላይ ያዋልነውን ፍቅሩን፣ መልካምነቱንና ታማኝነቱን እንዲሁም የተሰጠንን ቅባት በማወጅ ተናገረ፡፡ በተጨማሪም መልካም የሆኑ የተስፋ ቃሎችን፣ ለእኛ ያለውን ታማኝነትና እንደማይተወን ማረጋገጫዎችን በለዘበና በለሰለሰ መንገድ ገለጠልን፡፡

በእኔ በኩል ኃጢያት ናቸው ብዬ በራሴ የተሰሙኝ ነገሮች በእውነቱ ከሆነ ጥቂት ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህም ለመፆም መስነፍ፣ ለጉሮሮዬ እጅግ ጣፋጭ የሆኑ ነገሮችን መምረጥ፣ መተው ያለብኝን አንዳንድ ምግቦችን መተው አለመቻል ናቸው፡፡ ድሮ ወጣት እያለሁ ለመፆም የምችልበት ቅባት ተሰጥቶኝ ነበር፡፡ ታዲያ ያን ጊዜ ለምግብ ምንም ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ ደግሞም ስለ ጣዕም ምንም ግድ አልነበረኝም፡፡ ጌታ ይህንን ቅባት እንደገና መልሶ ለመስጠት እንደሞከረ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ራሴን ከመውደድና ከግል ድካም የተነሳ ብዙ ጫና ለመቋቋም አልቻልኩም፡፡ ስለዚህም በዚህ ነገር በቀላሉ እጠመዳለሁ፡፡

የዋናው ፆም ከመጀመሩ በፊት በጣም ጣፋጭ የሆነ ጥቁር ቸኮሌት ኬክ በጥቁር ቸኮሌት ክሬም ቺዝ ሰርቼ ነበር፡፡ ይህ ኬክ "መድኃኒት" ነው ብዬ ራሴን አሳምኜው ነበር፡፡ ከኬኩም የተረፈ ስለነበር የተወሰነውን ፍሪጅ ውስጥ በማስቀመጤ ያንን ለመብላት ሁልጊዜ እፈተናለሁ፡፡ በእውነት ለመናገር በመጀመሪያውም ይህንን ኬክ በሌላ ጊዜ እንኳን መስራት የለብኝም፡፡ ስለዚህም የወደፊት ግቤ መሆን ያለበት ከሚጣፍጡ ምግቦች መራቅ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ለአገልግሎት ይምንጠቀምባቸውን ካርዶች ለመፃፍ የሚያስፈልጉ ቀለሞችንና የመሳሰሉትን ነገሮችን ያላስፈላጊ መሸመቴ ነው፡፡ ቀለሞቹ ሲያልቁ መሙላት ሲገባኝ ያንን ሳላደርግ ቀርቼ ያለ አስፈላጊ ግብይት ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ትክክል ያልሆነ ድርጊት ነበር፡፡ አሁን እነዚህን ሁሉ ነገሮች በእርሱ የኃይል ቅባት ለመተውና ቀለሞቹንም ከሌሎች ጎረቤቶቼ ጋር ለመጋራት ወስኛለሁ፡፡

ውድ ቤተሰቦች እነዚህ ነገሮች ትንንሽ ነገሮች ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምልክቶች ኢየሱስን ለመውደድ እንዴት ቀዝቃዛ እየሆንን እንደሆነና ለእርሱ ምላሽ መስጠት አለመቻላችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት ራሴን እንደምፀየፍ ጌታ ያውቃል፡፡ ደግሞም እንዲቀይረኝ ለእርሱ ፈቃድ ሰጥቼዋለሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ በዚህ ዓይነት ሁኔታ መቀጠል አልፈልግም፡፡ ይህ አካሄድ አንድ መርከበኛ የመርከቡን መስተዋት ትናንሽ አሳዎች ሸፍነውት በፍጥነትና በንቃት እንዳይሄድ እንደሚያደርገው ዓይነት ነው፡፡ ስለዚህም የመርከቡ ካፒቴን ይህንን ነገር ለመቅረፍ መርከቧን ወደ ደረቅ መሬት በማምጣትና አሣዎቹን በማንሳት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ይህ ወቅት ኢየሱስ ትልቅ ሥራ እንድንሰራ እያዘጋጀን ያለ ወቅት ነው፡፡ ሂደቱ ምንም ተስፋ ቢያስቆርጥም ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን፡፡ በእርሱ ፍቅርና እኛን ለመለወጥ ባለው  ፍላጎት ላይ ብቻ እናተኩር፡፡ ማነው በኢየሱስ ፍቅር ሙሉ ለመሆን በመፈለግ ወደ እርሱ የሚጮህና ራሱን ክዶ የበለጠ እርሱን ለመምሰል የሚፈልግ? ውዶች እኛ ለእናንተ እንደምንፀልይ እባካችሁ ለእኛም ፀልዩልን፡፡

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ነው እንዳካፍላቸው የፈለከው?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "አዎ ይህንን ነው፡፡ ነገር ግን እንድትጨምሪበት ፈልጌ የነበረው በቤተ ክርስቲያንና በተመረጡ ነፍሶች ኃጢያት ተሰርቶ ችላ የሚባለውን ነው፡፡ ውድ ኸርት ድዌለርስ በዚህ ሳምንት ብዙ ላያችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይህንን ነው ኢላማ አድርጌ የተነሳሁት፡፡ በተጨማሪም በማፅናናት እጎበኛችኋለሁ፡፡ በዚህም ወደ ላይ ከፍ ብላችሁ በእኔ ከንድ መታቀፍ እንዴት ጣፋጭ እንደሆነ ትቀምሱታላችሁ፡፡"

(ክሌር) ከዋና ቡድናችን አባል የሆነ አንድ ሰው ያነበበውን ለእኛ ሊያካፍለን መጣ፡፡ ይህ ሰው ያካፈለን ቃል ትላንት ከጌታ የተቀበልኩትን ይህንን መልዕክትና ጌታ ወዴት እየመራን እንደሆነ  የሚያረጋግጥልኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ይህ ሰው መለኮታዊ ምህረት ለነፍሴ በሚል ከቅዱስ ፋውስቲን ከተፃፈ ፅሑፍ የተቀበለውን ላስነብባችሁ፡-

"ኢየሱስ በውስጤ ያለውን እጅግ ጥልቅ የሆነውን ችግር እንዳውቅ ስላደረከኝ ትልቅ ባለውለታዬ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ፡፡ እኔ ምንም የጠለቀ ነገር እንደሌለኝ አውቃለሁ፡፡ የአንተ ቅባት ወደ ላይ ደግፎ ካልያዘኝ በስተቀር ወዲያው ባዶ ወደ መሆን እመለሳለሁ፡፡ ስለዚህም የኔ አምላክ በእኔ ላይ ካለህ ምህረት የተነሳ በእያንዳንዱ የልቤ ምት አመሰግንሃለሁ፡፡"

ይህ ወንድማችን የተቀበለው ሁለተኛው ቃል፡-

"ብዙ ፈተናዎችና ችግሮች እየመጡ ነው፡፡ እውነተኛ በሆነ ቅድስና ኑሩ፡፡ ከነቀፋ ውጪ በሆነ ህይወት ተመላለሱ፡፡"

(ክሌር) በዚህ መልዕክት ላይ 'ነቀፋ በሌለው ህይወት መመላለስ' የሚለው ሐሳብ ሁለት ጊዜ ተገልጿል፡፡ የተወደዳችሁ፣ እኛ ሁላችን ትክክለኛ በሆነ አመለካከት ላይ አልተመሰረትንም፡፡ ለዚህ ነው ጌታ በውስጥ ፍላጎቶቻችንና በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ አዲስ አመለካከት እንዲኖረን እየጠየቀን ያለው፡፡ እኛ ምንም ያደረግን የማይመስለን ነገር በእርሱ ቅዱስ ዕይታ ግን ነፍሳችንን የሚጎዳ ነው፡፡ የእኛን አመለካከት የቀረፀው ብልሹ የሆነው ባህላችን ነው፡፡

ስለዚህ እኔ የማስበው ስለ ቅድስና በምናስብ ጊዜ በአይምሮአችን ሊመጣ የሚገባው የቅድስና መገለጫዎች በቃሉ ስለ ብፅዕና የተጠቀሱትን መሆን አለበት፡፡ (ማቴዎስ 5፡1)

የቡድኑ አባላችን ሦስተኛ የተቀበለው ማረጋገጫ የሚሆን መልዕክት ደግሞ መዝሙር 15 ነው፡፡ እኔ ከዚህ በመነሳት "በድንኳንህ ማን ያድራል" በሚል ርዕስ መዝሙር ፅፌ ቀድቼዋለሁ፡፡

መዝሙር 15
"እግዚአብሔር ሆይ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?
በተቀደሰውም ኮረብታህስ ማን መኖር ይችላል?

አካሄዱ ንፁህ የሆነ፣ፅድቅን የሚያደርግ፥
ከልቡ እውነትን የሚናገር።በምላሱ የማይሸነግል፥
በባልንጀራው ላይ ክፉ የማይሰራ፥ወዳጆቹን የማያማ።
ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፥እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ግን የሚያከብር፥
ዋጋ የሚያስከፍለውም ቢሆን፣ቃለ ማላውን የሚጠብቅ፡፡
ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፥በንፁሐን ላይ ጉቦ የማይቀበል።
እነዚህን የሚያደርግ ከቶ አይናወጥም።"

ከዚህም ባለፈ መልኩ የተስፋ ቃል መፅሐፋችንን ለማንበብ (Bible promise readings) እንዴት መለየት እንደምንችል ጌታ ገልፆልናል፡፡ ይህም የሬማ መፅሐፎቻችንን ከማንበባችን በፊት መፅሐፎቹን በክርስቶስ ደም እንድንሸፍናቸውና መፅሐፎቻችንን ወይም የሬማ ካርዶቻችንን ከመጠቀማችን በፊት መስቀል በመሥራት መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን ገፅ እንድንከፍት ነግሮናል፡፡ በዚህም ስልት ትክክለኛ መለየት ማድረግ የሚያስችለንን እንደሚሰጠን ነግሮናል፡፡

አሁንም እንደገና ለህብረተሰቡ ስለምታደርጉት ደግነት የተሞላበት ዕርዳታ ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ እርዳታችሁ መስራት የጀመርነውን ቤት ለመስራት እንድንችል፣ እንዲሁም በተራራው ሥር ያሉትን ህብረተሰብ ከፀለይን በኋላ እርዳታ እንድናደርግ አስችሎናል፡፡ እነዚህ የመንደራችን አባሎች አብዛኛዎቹ ጡረታ የወጡ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ አንዳንዶቹን እግዚአብሔር በመልካም እጆቹ እየነካቸው እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

ስለመንደራችን ትንሽ ግልፅ ለማድረግ እኛ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት እርዳታ ሰጪ ህብረተሰብ አይደለንም፡፡ በእጃችን የያዝነው የምንሰጠውን ዕርዳታ ሳይሆን መፅሐፍ ቅዱስና ፀሎት ነው፡፡ ስለዚህም ስለ መንደራችን፣ ስለ መንግስታችን፣ ስለ አገራችን፣ ስለ ፖሊሶቻችንና ስለ ወታደሮቻችን ጥበቃ እንዲሁም በአለም ላይ ለውጥ እንዲመጣ በፀሎት የምንተጋ ሰዎች ነን፡፡ በተጨማሪም አገራችን ደህንነቷ ተጠብቆ በቅድስና እንድታድግ የምንፀልይ ነን፡፡

እናንተም ስለ መንደራችን ሰዎች ፀልዩላቸው፡፡ አሁን የሚሰሩት ሥራ ብዙ ታክስ ያለበትና የሚያበሳጭ ሥራ ነው፡፡ የእኛ የፀሎት እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለትዳራቸውና ለልጆቻቸውም ፀልዩ፡፡ የፖሊሱ ሚስት ለስራ በተጠራ ጊዜ በጣም ከባድ ጊዜ እያሳለፈች ነው ስለዚህ ፀልዩላት፡፡

ስለ ለአገራችን ተመራጭ የሆነው ፀሎት መዝሙር 91 እና የመለኮት ምህረት የሚለው ነው፡፡ /the Devine Mercy Prayer/፡፡ የኔ ውድ ቤተሰቦች መልካም ለመስራት አትታክቱ፡፡ እንዲሁም ለእኛም ፀልዩልን፡፡ በተለይም ለህዝቄልና ለእኔ ከእኛ ሐሳብ ይልቅ የጌታን ፈቃድ ለመምረጥ የምንችልበት የሞራልና የሰውነት ጥንካሬ እንዲኖረን ፀልዩልን፡፡

ውድ ቤተሰቦች ጌታ በሰላም ይጠብቃችሁ፣ ተባረኩ፡፡ አሜን፡፡

**ህዝቤ ሆይ ቀን ሳለ ድምፄን - ማርች 30 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Harken unto Me while there is yet time – March 30, 2020**

ውድ ኽርት ድዌለርስ ጌታ በዚህ ወቅት ህይወታችንን እንድናስተካክል ጠንከር ባለ ሁኔታ ጥሪ እያቀረበልን ነው፡፡ በየቀኑ የሚያሯሩጠንን ሥራ በማቆም፣ ወዲህና ወዲያ ከመሯሯጥ ተቆጥበን ከጌታ ጋር ያለንን አቋም እንድንመረምር ለማድረግ ሁላችንንም ተገልለን በቤት እንድንቀመጥ/quarantine/ ለማድረግ የመሪዎቻችንን ልብ አንቀሳቅሷል፡፡ እባካችሁ ይህንን መልዕክት በጥሞና አድምጡ፡፡

"ህዝቤ የሮም ንጉሥ ለህዝብ ቆጠራ ሁሉም ወደ ትውልድ አገሩ እንዲመለስ አዋጅ እንዲያወጣ ያነሳሳው የእኔ መንፈስ ነበር፡፡ አሁንም በዚህ ወቅት እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ  በቀር ሥራዎችና የመዝናናት ተግባሮች ቆመው ሁሉ ሰው በአስገዳጅ ትእዛዝ ተገልሎ በቤቱ  እንዲቀመጥ የተደረገው በመንፈሴ አነሳሽነት ነው፡፡

"እንዲገባችሁ የሚያስፈልገው እስካሁኗ ሰአት ድረስ ለመፀለይና እኔ ላቀረብኩላችሁ የማስጠንቀቂያ ቃል ምላሽ ለመስጠት እጅግ ዳተኛ ሆናችኋል፡፡ ይህ በእናንተ በኩል መልስ ሳይሰጥበት ችላ የተባለ ነገር አሁን ሊገባችሁ ለማይችል ትልቅ አደጋ እያጋለጣችሁ ነው፡፡ ስለዚህም አሁን ባህርያችሁንና ጊዜያችሁን ለመቅረፅ የሚያስችል አስገዳጅ ሁኔታዎችን ፈቅጃለሁ፡፡ በህይወታችሁ የማያስፈልጉ እንቅስቃሴዎችን እንዲቆም በማድረግ እንድትፀልዩና ንስሐ እንድትገቡ የመጨረሻ ዕድል ሰጥቼያችኋለሁ፡፡

"ጨዋታዎች፣ ምግቦችና መዝናናቶች፣ የህብረተሰብ ግንኙነቶችንና ማንኛውም ሰውን የሚያቀራርቡ ግንኙነቶች ሁሉ ታግደዋል፡፡ ይህንን የፈቀድኩበት ምክንያት ከእኔ ጋር በፀሎት እንድታሳልፉ ለማድረግ ነው፡፡  ከምንግዜውም በበለጠ መልኩ ለምድራችሁ እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም የሚመጣው ነገር እጅግ አስፈሪ በመሆኑ ይህ ሊገታ የሚችለው ንስሐ በመግባትና በፀሎታችሁ ነው፡፡

"ከአሁን ወዲያ በሥራ እጅግ ተወጥሬያለሁ በማለት ሰበብ ልትፈጥሩ አትችሉም፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ እንደተለመደው ሐሳባችሁን በሚሰርቋችሁ በአዳዲስ አሻንጉሊቶቻችሁ ምክንያት እኔን ችላ ማለት አትችሉም፡፡ ከአሁን ወዲያ በበራችሁ ላይ ሊመጣ ያለውንና የማይቀረውን የሞት አደጋ ማስወገድ አትችሉም፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ምን ታደርጋላችሁ?

"ታዲያ ይህ በፊታችሁ በእውነት የተደቀነውን አደጋ ችላ ብላችሁ እንዲሁ ትተዉታላችሁ  ወይስ በለቅሶና ንስሐ በመግባት በፀሎት አገራችሁን ብሎም አለምን ታድናላችሁ? ይህንን ቤት የመቆየት ፕሮግራም ንስሐ እንድትገቡ፣ እንድትፀልዩና ህይወታችሁን እንድትመረምሩ ጊዜ ለመስጠት ሆን ብዬ የፈቀድኩት ነው፡፡

"ለመሆኑ እስካሁን የኖራችሁት ለራሳችሁና ለቤተሰባችሁ ብቻ ወይስ እንደ እናንተ እድል ላልገጠማቸው ለድሆችም ጭምር? ህይወታችሁን እየመራችሁ ያላችሁት የኔን ፈቃድ ለማድረግ በመፈለግ ወይስ በጣም ደስ የሚላችሁን መንገድ በመከተል? አብዛኞዎቻችሁ ስለሚቀጥለው ቀን ምንም ማስተማመኛ ስለሌላችሁ ፈርታችኋል፡፡ ይህ ደግሞ ትክክለኛ ፍርሃት ነው፡፡ በዛሬው ቀን ብዙዎች እኔ ስለሰጠኋቸው ስጦታ ምን እንዳደረጉበት ከእኔ ጋር መተሳሰብ ይሆናል፡፡ እናም አብዛኞዎቻችሁ ህይወታችሁን እንዴት በኃጢያትና በከንቱ እንዳሳለፋችሁት በመገንዘብ ምላሻችሁ ትልቅ ፀፀት የተሞላበት ይሆናል፡፡

"ይህንን ጊዜ የሰጠኋችሁ ያሳለፋችሁትን ህይወት ወደኋላ እንድትመረምሩ፣ ምርጫዎቻችሁን እንደገና እንድትፈትሹና የቀራችሁ ጊዜ ትንሽ መሆኑን በማወቅ ባለማወላወል በፊታችሁ የቆመውን ሞት እንድትጋፈጡ ነው፡፡ ህዝቤ ይህንን አስቀድሜ ባላስጠነቅቅህ ሥራዬን በአግባቡ ያልተወጣሁ ይሆንብኛል፡፡

"ህዝቦቼ እናንተ ሊገባችሁ ከሚችለው በላይ አፈቅራችኋለሁ፡፡ ይህ ፍቅር ደግሞ አባቴ በአሜሪካ ላይ ሊመጣ ካለው ፍርድ በፊት ወደ ልባችሁ እንድትመለሱ ለማድረግ ምህረት እንዲሆን አስገድዷል፡፡ በዚህም በቂ ንስሐና ፀሎት ከተደረገ ይህንን ምህረት ለመቀበል ጥሩ ዕድል ይኖራችኋል፡፡ ነገር ግን አሁንም አብዛኛው ሰው ዝም ብሎ በራሱ መንገድ ከቀጠለና ንስሐ ለመግባት ሐሳብ ከሌለው ቅጣቱ በእነርሱ ላይ የከፋ ይሆናል፡፡ የማወራው ቅጣትም ከዚህ አለም በሞት ስለ መለየት ሳይሆን ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ቅጣት ነው እያወራሁ ያለሁት፡፡

"ለመሞት የምትፈሩ ከሆነ መንፈሴ እያስጠነቀቃችሁ ያለው ከሞት በኋላ በህይወት ግምገማ ወቅት በምንም ሁኔታ ከእኔ ጋር እንደማትገናኙ ነው፡፡ ለመሆኑ ብዙ ክርስቲያኖች በገሃነም እንዳሉ ታውቃላችሁ? ይህንን ስትሰሙ አስደነገጣችሁ? እንዲህ ብዬ በቃሌ አላስጠነቀቅሁም?

"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" (ማቴዎስ 7፡21-23)

"ስለዚህ የእውነተኛ ክርስቲያን መስፈርቴ ምንድነው? " ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህንን ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።"(ማቴዎስ 7፡24-27)

"ምንድነው እየተናገርኩት ያለሁት? በዚህ ቻናል አማካኝነት ምን እንደምፈልግ ደጋግሜ ብዙ ጊዜ ተናግሬያለሁ፡፡ ስለ ብፁዎች፣ ትክክል ስላልሆነ አገልጋይ፣ ድሆችን ስለሚመግቡ፣ ልብስ ስለሚያለብሱ፣ መጠለያ ስለሚሰጡ፣ህመምተኞችንና የታሰሩትን ስለሚጎበኙ፣ ቤት ለሌላቸው መጠለያ ስለሚሰጡ፣ በሁሉም ግንኙነቶች ደግ፣ ሐቀኛና ይቅርታ ስለሚያደርጉ ሁሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ በግልፅ ተፅፏል፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህ ከራሳቸው ይልቅ ሌሎችን አብልጠው በመውደድ ስቃያቸውን ለማንሳት የሚያስቡ ናቸው፡፡ እንደነዚህ አይነት ሰዎች በሚሞቱ ጊዜ መልካም ሥራቸው ወደ መንግስተ ሰማያት ስለሚከተላቸው ምንም ሊፈሩ አይገባም፡፡ እኔም እንኳን ደህና መጣችሁ ብዬ ወደ መኖሪያቸው በብዙ ደስታ አስገባቸዋለሁ፡፡

"ነገር ግን ቃሉን በደንብ አውቃችሁ በቃሉ መሰረት ያልኖራችሁ፣ ስጦታን ሰጥቻችሁ ስጦታውን ንግድ በማድረግ ለግል ጥቅም ማጋበሻ ያደረጋችሁ፣ ለድሆች ወንጌልን ለመስበክ የተሰጣችሁን የዝማሬና የስብከት ስጦታ ከዳችሁ የራሳችሁን መኖሪያ ማደለቢያ ያደረጋችሁ፣ ባል የሞተባቸውን፣ ወላጅ አልባ ልጆችን፤ እንዲሁም በሌሎች አገሮች ስደት

የሚደርስባቸውን፣ በመንገድ ላይ ስታልፉ እንኳን ለድሆች የደግነት አይን ያላሳያችሁ እናንተ ይህንን አይነት የራስ ወዳድነት ህይወት ስላሳለፋችሁ በሞታችሁ ጊዜ ለመፍራት ብዙ ምክንያት አላችሁ፡፡

"እነዚህ ኃጢያቶች ተገደው በሴተኛ አዳሪነት ከሚተዳደሩት ወይም ህሊናቸው በደንብ ካለመቀረፁ የተነሳ ዝሙት ከሚፈፅሙት እንዲሁም እናንተ የተትረፈረፈ ነገር እያላችሁ ስለማታካፍሉ ከገበያ ከሚሰርቁት በላይ ለእኔ የሚያስጠሉኝ ኃጢያቶች ናቸው፡፡ የኃጢያተኞችና የቀራጮች ብዙ ኃጢያት ይቅር ሲባል ፈሪሳውያን ግን በደንብ ፍተሻ ይካሄድባቸዋል፡፡ ታዲያ ከእናንተ ማነው ፈሪሳዊ? እነዚህም ከራሳቸው ፅድቅ በመነሳት በደሃውና ምንም በማያውቁት ላይ የሚፈርዱና የሚከሱ፣ ፍትህን የሚከለክሉ፣ እርዳታ ከመስጠት ተቆጥበው ድሆች ከእምነታቸው እንዲመለሱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ባል የሌላቸው በችግር እየተሰቃዩ እነሱ የተደላቀቀ ኑሮ የሚኖሩ እንደዛም ሆኖ ግን ካላቸው ከጥቂቱ ባለመስጠታቸው የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ናቸው፡፡

"ይህንን የምናገረው ራሳችሁን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መርምራችሁ በውስጣችሁ እንዲህ ዓይነት ክፋት ካለ በዚህ ጊዜ ንስሐ ገብታችሁ ለሌሎች መልካም መስራት እንድትጀምሩና ለቤተሰባችሁና ለአገራችሁ ከልባችሁ ስለ ምህረት እንድትፀልዩ ነው፡፡ ንስሐ ለሚገቡ ምህረት ማድረግን መቼም አላቆምም፡፡ በፍፁም አላቆምም፡፡ ስለዚህ የራሳችሁን ህይወት ፈትሹና ፀልዩ፡፡ ከዚያም ቃል ገባሁትን አልፈፅም እንደሆነ ታያላችሁ፡፡

"በዚህ በጨለማችሁ ጊዜ እንኳን መንፈሴ ሊረዳችሁና በልባችሁ የፅድቅን ብርሃን ሊያበራላችሁ በላያችሁ ላይ እያንዣበበ ይገኛል፡፡ የምወዳቸውን እገስፃለሁ ስለዚህ ጊዜው ሳያበቃ እኔን ሰምታችሁ ተመለሱ፡፡

## ጥበቃዬ በታዛዦች ላይ ነው - ኤፕሪል 1 ቀን 2020 ዓ.ም

## My protection is with the obedient, April 1st, 2020

የጌታ ሰላም ከእናንተ ጋር በመሆን ወደ ፅድቅ ሁሉ ይምራችሁ፡፡ ልባችሁም የለዘበና ጌታ እንዲያቃናው የቀለለ ይሁን፡፡ አሜን፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ ህዝቄኤል በጣም ግልፅና እውነተኛ ህልም አይቷል፡፡ በዚህ ህልም ውስጥ ብዙ ቅዱሳኖች ሊጎበኙት መጥተው ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አብ ተገኝቶ ነበር፡፡ በጉብኝቱም መጨረሻ የተለያዩ ሚዛኖችን በመመልከት ሰባት አመት የሚል ድምፅ ሰማ፡፡

እኛም ታላቁ የመከራ ዘመን ሊጀምር መስሎን ነበር፡፡ "በጉ ሦስተኛውን ማህተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው ህያው ፍጡር ና ሲል ሰማሁ፡፡ እኔም ተመለከትኩ፣ እነሆ ጥቁር ፈረስ ቆሞ አየሁ፣ ተቀምጦበት የነበረውም በእጁ ሚዛን ይዞ ነበር፡፡ ከዚያም ከአራቱ ህያዋን ፍጡራን መካከል፣ አንድ እርቦ ስንዴ ለአንድ ቀን ደሞዝ፣ ሦስት እርቦ ገብስም ለአንድ ቀን ደሞዝ ይሁን፣ ዘይቱንና የወይን ጠጁን አትጉዳ የሚል ድምጥፅ ሰማሁ፡፡"(ራዕይ 6፡ 5-6)

ህዝቄኤል በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በቻይና፣ በአሜሪካና በአለም ሁሉ ላይ ብዙ ሰዎች ሲሞቱ ሲያይ እንደገና ጠንካራ ምልጃ ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ጠቅላላ ሁኔታውን ሳየው በዚህ አገር (አሜሪካ) ምናልባት የምርት መቀነስ ቢኖር የተወሰነ

ምግብና ውኃ ማስቀመጥ ጥበብ መስሎ ስለታየኝ ምግብ ገዝቼ ለማስቀመጥ እችል እንደሆነ ጌታን ስጠይቀው ስለፈቀደልኝ ለህብረተሰቡ ለአንድ ወር የሚበቃ ተቀማጭ ምግብ አዘጋጀሁ፡፡ በተጨማሪም መድኃኒቶች፣ አልኮሆል፣ የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር፣ የፊት መሸፈኛ፣ ነዳጅ፣ ዘይት፣ የሽንት ቤት ወረቀቶችና ለቤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ብናስቀምጥ መልካም ነው፡፡ እኛ ሰውነታችን በሽታን ለመከላከል እንዲረዳን ዚንክና ቫይታሚን ዲ እንወስዳለን፡፡ ይህ ደግሞ በእውነት ይረዳል፡፡

እኛ በአለም ሁሉ የተሰራጩ ሚሺነሪዎች አሉን፡፡ እነዚህም ሚሺነሪዎች በባዕድ አገር የሚገኙ በሽታዎችን በተለያየ መንገድ እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ተምረዋል፡፡ በአፍሪካ ያሉ አንዳንድ ሚሺነሪዎችን ስጠይቅ ብዙ በሽታዎችን ለመቋቋም ሃኪሞቻቸው ያዘዙላቸውን ጥቂት መድኃኒቶችን ጠቁመውኛል፡፡ ከእነዚህም ክሎሮኩን ከዚትራማክስ ጋር (አዚትሮማይሲን) በጥምር ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም የሳንባ ጀርሞችን ለመግደል ሳውናዎች፣ በእንፋሎት ጭስ መታጠን እንደሚረዳና ለእነርሱም እንደጠቀማቸው ነግረውኛል፡፡

ከዚህ ሁሉ ግን የሚበልጠው ፀሎት ነው፡፡ እናም ጌታ የሚጠይቀን መዝሙር 91 እንድንፀልይ ሲሆን እኔ ደግሞ በዚህ ላይ የምጨምረው መዝሙር 51 በመጀመሪያ ከልባችን እየተሰማን እንድንፀልይ ነው፡፡ ጌታ በህይወታችሁ ያልተደሰተበትን ነገር ከነገራችሁ እባካች፣ እባካችሁ፣ እባካችሁ ከህይወታችሁ ያንን አስወግዱ፡፡ የጎዷችሁ ሰዎች ካሉ ይቅርታ ቢጠይቋችሁም ባይጠይቋችሁም ይቅር በሉ፡፡ ክፍት በር አተተዉ፡፡ መራራ የሆነ ዘር በእርግጠኝነት ይመርዛችኋል፡፡ እናም በሮችን ይከፍታል፡፡ እኛ ሰዎችን ይቅር ካላልን እግዚአብሔር እኛን እንዴት ይቅር ይለናል? ይህ በጣም ቀላል ነው፡፡ እርሱ ቃል የገባልን እኛ የበደሉንን ይቅር ካልን እርሱ ይቅር እንደሚለን ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን በር ክፍቱን መተው የለብንም፡፡

በተጨማሪም በቂ ዕረፍት አግኙ፡፡ አንድን ፕሮጀክት ለማጠናቀቅ ታላቅ ፍላጎት ያላችሁና ራሳችሁን እጅግ የምታደክሙ አትሁኑ፡፡ ይህ ጠላት ያዘጋጀላችሁ ስለሆነ በእርሱ ሐሳብ ባለመጠመድ ጤንነታችሁን ጠብቁ፡፡

በጌታ ለመጠበቅ (ይጠብቃል) ሌላው ዋናው ነገር ራሳችሁን እንደምትወዱ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን መውደድ እንዲሁም ራሳችሁን ትሁት በማድረግ ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ መቁጠር ነው፡፡ ይህንን ቃል እገባላችኋለሁ፣ ሌሎችን ጠጋ ብላችሁ ብትመለከቷቸው እናንተ የሌላችሁን ብዙ ጥሩ ነገሮች በውስጣቸው ታገኛላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ ለእናንተ ነገሮችን ቀለል ያደርግላችኋል፡፡ ይህ ጊዜ ቆም ብላችሁ ራሳችሁን በመፈተሽ ማስተካከል ያለባችሁን የምታስተካክሉበት ጊዜ ነው፡፡ ሁላችንንም መልሰን መላልሰን በህይወታችን እንዲሆን ከፈቀድነው የኃጢያት ልምምድ እንድንወጣ ጌታ እያስጠነቀቀን ነው፡፡ ማንኛውንም ማድረግ የሌለብንን ነገር እንዳናደርግ ህሊናችን ተሰምቶት ከሆነ እባካችሁ የተሰማንን ነገር እናቁመው፡፡

የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው፡፡ ስለዚህም በኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ብዙዎች እየሞቱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን እየፈቀደ ያለው ከእርሱ ጋር ያለንን ህብረት ትኩረት እንድንሰጠውና ማመቻመችን እንድናቆም ነው፡፡ ስለ ራሴ ልመስክርላችሁና ጌታ አንዳንድ አመለካከቶቼንና ፍላጎቶቼን ለመቀየር በእውነት እየሰራ ነው፡፡ በአንዳንድ ነገሮች ላይ ግድ የለሽ ነኝ፡፡ በዚህም ደግሞ ለጥቂት ጊዜያት በልቤ ተቸግሬ ነበር፡፡ አሁን ግን ፀጋውን በመስጠት እኔው ራሴ እንዳስተካክለው ፈቅዶልኛል፡፡

ጌታ በዚህ ላይ ለመጨመር የምትፈልገው ነገር አለ?

ኢየሱስ እንዲህ በማለጥ ጀመረ. . . መመሪያዎችሽ ብልህና በአስፈላጊው ነገሮች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶች ምላሽ የሚሰጡት ቀላል የሆኑትን በመምረጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በሽታውን ለመከላከል ተጨማሪ የሆኑ መድኃኒቶችን በመግዛት ይሆናል፡፡ ሌሎች ደግሞ ለእኔ ትኩረት በመስጠት ምላሽ የሚሰጡት ንስሐ በመግባት ላይ ነው፡፡ የተወደዳችሁ ላልዳኑ ዘመዶቻችሁ አባላት ጣልቃ በመግባት እንድትቆሙ ካልጠራኋችሁ በስተቀር ለበሽታ የእኔን ጥበቃ የሚያስገኝላችሁ ንስሐ መግባታችሁና እኔን ለማስደሰት የምትወስዱት ጥብቅ እርምጃ ነው፡፡ በተጨማሪም ለድሆች መስጠታችሁን፣ የታመሙትን መጎብኘትና የታሰሩትን መጠየቅ አታቁሙ፡፡ ቸርነት ማድረግ ለጥበቃ መሸሸጊያ ነው፡፡ ለሌሎች ምግብ ለማስቀመጥ የምትችሉ ከሆነ ይህ እኔን ያስደስተኛል፡፡ ደግሞ ይህንን አስታውሱ መቼም ቢሆን እጅግ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ዳቦን ማባዛት አላቆምኩም ደግሞም አላቆምም፡፡ ይህ ግን ለግላቸው  ለሚስገበገቡ ሳይሆን እንደ ራሳቸው አድርገው ወንድሞቻቸውን ለሚወዱ ነፍሶች ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ቸርነት ብዙ ኃጢያቶችን ይሸፍናል፡፡ በመንግስተ ሰማያት ሆናችሁ በምድር ያሳለፋችሁትን ህይወት ስትመረምሩ የቸርነትን ኃይል ትገነዘባላችሁ፡፡

"አትደንግጡ፣ ድንጋጤንም አትቀስቅሱ፣ ይልቁንስ ፀሎትን አነሳሱ፡፡ ኃይል ያለው በፀሎት ላይ እንደሆነ ህዝቤን ንገሩት፡፡ በቅን ልቦናና በተቀደሰ ህይወት በተደረገ ፀሎት ብቻ ብዙ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ፡፡ ህዝቤ በማያቋርጥ ኃጢያትና በማይገበር ስህተት ውስጥ ከሆናችሁ መልካሙን ገድል ተጋደሉ፡፡ ወደ እኔ ኑና ፀሎታችሁን አከብራለሁ፡፡ ይህንን አስታውሱ እውነተኛ መፀፀትንና ለመሻሻልም የምታደርጉትን ጥረት ስመለከት የሚያስፈልገው ቅድስና ላይ እንደደረሳችሁ በመቁጠር ፀሎታችሁን አከብራለሁ፡፡ የኔ ውዶች እኔ የምመለከተው ልባችሁን ነው፡፡ እንዲሁም ከፍርድ፣ ከኩራት፣ ከዝሙትና ከስግብግብነት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡ ለራሳችሁ ሃቀኞችና ጥብቅ የሆናችሁ ከሆነ በእኔ መገኘት መፍራት የለባችሁም፡፡ ማሸነፍ እንድትቀጥሉ ርህራሄና ፀጋ ትቀበላላችሁ፡፡

አንድ ደቂቃ እንኳን ከእናንተ  ተለይቼ እንደማላውቅ ማወቅ አለባችሁ፡፡ የልባችሁንና የሐሳባችሁን ልመና እሰማለሁ፡፡ እንዲሁም ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ያለምንም ቅደመ ሁኔታ ለመውደድ ያላችሁን ፍላጎት አደምጣለሁ፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ እነዚህን ባህርያት አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ እኔም በችግር ጊዜ እጠብቃችኋለሁ፡፡

## ይህ የጉብኝት ጊዜያችሁ ነው - እ.አ.አ ኤፕሪል 2 ቀን 2020 ዓ.ም

## This is the time of your visitation - April 2, 2020

(ክሌር) እምነታችንን በመጨመር እግዚአብሔር ለእኛ በመረጠልን መንገድ ላይ እንድንቆይ ይርዳን፡፡ ጌታ ቃል የገባልንን ነገሮች ያለምንም ጥያቄ እንድንተማመንባቸው ያበርታን፡፡ እንዲሁም ወቅቱ የሚሰጠንን እድሎች በድፍረት  እንድንተገብር ይርዳን። አሜን

ውድ ቤተሰቦች አሁን ላካፍላችሁ የፈለኩት ትልቁ ተስፋችን የእግዚአብሔር ጥበቃ መሆኑንን ነው። በቃሉ እንደተፃፈው የሰው ልጅ ዕርዳታ ከንቱ ነው። "እነዚህ በሰረገላ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤ እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡" (መዝሙር 20፡7)

በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደታየው በአለም ከፍተኛ ችሎታ ያለውና ከህዝቡ ቁጥር እጅግ የሚበልጥ ወታደር ያለው ህዝቡን ድምጥማጡን ሊያጠፋ ይፈልግ ነበር። ቢሆንም ግን ሰዎች በታማኝነት እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸው ህግጋት ሲኖሩ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ሲታደጋቸው ታይቷል። እንዲሁም ችግር በገጠማቸው ጊዜ ከኃይለኛ ተቃውሞ በታምራቱ እንዲወጡ አድርጓቸዋል። የቀይ ባሕር ለሁለት መከፈል ከእነዚህ ታምራቶች አንዱ መንገድ ብቻ ቢሆንም ልናስታውሰው የሚገባ ነው፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የበራቸውን መቃን የበግ ደም ቢቀቡት የሞት መልአክ ቤታቸውን አልፎ እንደሚሄድ፣ እንዲሁም የበጉ ደም ያልተቀቡትን ቤቶች ደግሞ የበኩር ልጆቻቸውና እንስሳቶቻቸው እንደሚሞቱ የነገራቸው ሌላው የተአምራቱ ምሳሌ ነው።

ውድ ቤተሰቦች በእነዚህ ውስጣችንን በማፅጃ ወቅቶች ልባችንን እንድንመረምር፣ ኃጥያቶቻችንንና ማመቻመቾችን ንሰሐ ገብተን ህይወታችንን በአዲስ መንገድ እንድንቀጥል ጌታ እየጠራን ነው። በሌላ አነጋገር ኃጥያትንና ማመቻመችን በመተው ህይወታችንን በማረም መጥፎ የነበርንበትን ነገር ወደ ጥሩ እንድንቀይር ያስፈልገናል። እነዚህን በማድረግ የእርሱን ጥበቃ ብንጠይቅ እኛንና የምንወዳቸውን ከበሽታ እንደሚጠብቀን መተማመን እንችላለን።

ጌታ መዝሙር 51ን በየቀኑ በፀሎትና በማስተዋል ሆኜ እንዳነብ አዞኛል። በተጨማሪም ደግሞ እኔ የኢየሱስን ፀሎት "ጌታ ኢየሱስ ለእኔ ለኃጥያተኛዋ ምህረት አድርግልኝ" የሚለውን እፀልያለሁ፡፡ ይህንን ደግሞ በፀሎት መቁጠሪያ በመጠቀምም መፀለይ እንችላለን፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ይህንን ማለት እፈልጋለሁ፡፡ በመቁጠሪያ ስፀልይ ወደ ጌታ ልብ ውስጥ በጥልቅ እንድገባ ረድቶኛል።

ጌታ ለእኛ ምን ያህል መልካም ፣ የጥልቅ ወዳጃችን እና ይቅር ባይ እንደሆነልን ማወቃችን ደስ ቢያሰኘንም አሁን በዚህ ጊዜ ግን ይህንን ሁሉ ትተን ለእሱ ታማኝ አለመሆናችንን በትኩረት በመመልከት ህይወታችንን እንድንቀይር እየጠየቀን ነው። አስተሳሰባችንን ብቻ ሳይሆን ድርጊቶቻችንንም በመቀየር የበፊት መተላለፎቻችን በማስተካከል እርሱን ደስ እንድናሰኘው ይፈልጋል፡፡

የምንኖረው በራስ ወዳድነት ነው? ያልነፁ ነገሮችን እያየን ነው? ለተቸገሩት ሳናካፍል ቀርተን የብክነት ኑሮ እየኖርን ነው? ለሌሎች ደግና ጥሩ ነን ወይንስ ኃይለኛና ፈራጅ ? ከቀናችን ውስጥ ምርጥ የሆኑትን ሰዓቶች በፀሎትና በአምልኮ ለጌታ እየሰጠነው ነው? ለሌሎች አንዳንዴም ለማናውቃቸው ሰዎች እንድንፀልይ ብሎ የምንሰራውን ስራ እንድንተው ሲጠይቀን በመታዘዝ እንመልሳለን ? እንድንሰራው የሰጠንን ስራ ስንሰራ በሙሉ ልባችን ነው?

ደግሞስ የሌሎችን ቁስል እያከምን ነው? ወይንስ ስህተቶቻቸውን እየፈለግን? ባልተመቸን ሰዓት እናመሰግነዋለን ወይንስ ተቆጥተን በመሰላቸት ምስጋናቢስ እንሆናለን? በተጨማሪም ጌታን ለእያንዳንዱ ፈተና ማመስገን ትተን ሳይድኑ ለሚሞቱት የሚሰማንን ህመም ለእሱ በማቅረብ ፋንታ ባለማመስገናችን ራሳችን ላይ አንፈርዳለን ? ትዕግስት በማጣታችንና ባለመቀበላችን የተነሳ ስንት መራራ ዘሮችን በውስጣችን ዘርተናል? እነዚህን ነገሮች እንዲያነሳልኝ በየጠዋቱ ወደ እርሱ መቅረብ አለብኝ ። ሁኔታዎች ሳይመቹኝ ሲቀሩ ወደ ትዕግስት ማጣት አዘነብልና መራራ ዘርን በውስጤ እዘራለሁ፡፡

የተወደዳችሁ ልቀጥል ብል ብዙ ጉድለቶችን በመዘርዘር መቀጠል እችላለሁ፡፡ ባለፈው አመት በእነዚህ ጉድለቶች ሁሉ ጥፋተኛ ሆኜ ተገኝቻለሁ፡፡ በእርሱ ፊት እንከን የሌለባትና ንፁሕ የሆነ የውስጥ ፍላጎት ያላት ሆኜ ለመገኘት እንዴት እሻለሁ!! ከሚያሳዝነው ከእኔ ማንነት፣ ከራሴ ፍላጎትና ቀድሜ ከተዋጥኩበት ከራሴ ሐሳብ እኔን ለማንፃት ጌታ ብዙ ሥራ

ይጠብቀዋል። ለዚህም ሥራ ከእርሱ ጋር በሙሉ ልቤ ለመተባበር እፈልጋለሁ፡፡ ጌታ ሆይ አንተ ለጠራኸኝ ጥሪ እንዳሰብከው ሙሉ ለሙሉ ያደኩኝ ሴት ባልሆኔና ገና ኮረዳ በመሆኔ አዝናለሁ፡፡ እስካሁንም የማይረቡ ነገሮችን እፈልጋለሁ። በደንብ ልንከባከበው የሚገባኝን ነገር እተዋለሁ ... አሁንም ስለማይመቹ ነገሮች አጉረመርማለሁ፡፡ እናት ኤሊሻ እንደምትለው ባጭሩ "እጅግ ግራ የገባኝ ነኝ።" ነገር ግን እርሱ ከዚህም በላይ በሆኑ ነገሮች ላይ ጌታ ነው፡፡ ስለዚህም ሙሉ ለሙሉ እንዲቀይረኝ ፍቃዴን ሰጥቼዋለሁ፡፡

ስለዚህ በጌታ ጥበቃ ዉስጥ እንድንኖር ከፈለግን ህይወታችንን ለራሳችንና ለቤተሰቦቻችን መኖር ሳይሆን ለእርሱ መኖር አለብን። ወይንም ደካሞች ከሆንንና ግትር የሆኑ ልምዶች ውስጥ ከገባን ቢያንስ ቢያንስ ለመቀየር እውነተኛ ፍላጐት ሊኖረን ይገባል፡፡ ለዚህም ነው ሁላችንም ቀናችንን በመዝሙር 51 ብንጀምር ጥሩ ነው ብዬ የማስበው። የዳንኩ ቀን ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዳልንቀሳቀስ ሲያደርገኝ ከዚህ የመዝሙር ክፍል 'ጌታ ሆይ ስለ መተላለፌ ምህረት አድርግልኝ። እነዚህን መተላለፎቼን በደንብ አውቃቸዋለሁ፡፡ አቤቱ ከኃጥያቴ ፊትህን መልስ፣ ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አትውሰድብኝ፡፡ የማዳንህን ደስታ መልስልኝ' የሚለው ተሰጥቶኝ ነበር፡፡ (እንዴት እንደተለወጥኩ የሚለው ታሪኬ ላይ ይህ ተፅፎ ይገኛል)

የተወደዳችሁ እምነቴ ያለስራ ሙት፣ ሙት፣ ሙት ነው፡፡ በእምነቴ ደክሜያለሁ? አዎ ደክሜያለሁ፡፡ ለምን? ምክንያቱም በመንፈሳዊ ህይወቴ አጭር መንገድን እንደምከተል ራሴን አሳምኜዋለሁና ነው፡፡ ይህንን ለሌላ ስለተናገርኩት ማለት ትችላላችሁ፡፡ ምክንያቱም በእርግጥም ይህ እውነት ስለሆነ ነው፡፡ 'ምንም አይደለም ስለደከመህ አሁን መብላት ትችላለህ፡፡' 'ችግር የለውም ሌላ ጊዜ ስትጠነክር ልታደርገው ትችላለህ፡፡' 'ለኢሜሎች መልስ ሳትሰጥና ለሳምንታት ብትቆይ ምንም ችግር የለውም' የሚሉ ነገሮችን ልትሉ ትችላላችሁ። የተወደዳችሁ እነዚህ ሁሉ ለብ ያለ ነፍስ አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ ይህቺ ነፍስ በመጀመሪያ ከጌታ ጋር የነበራትን የፍቅር እሳት ያጣች ነፍስ ናት። እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ የቸልተኝነት ተግባራት ናቸው፡፡ ይህ ለጌታ አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ግድ ማጣትና የእኔ ፍላጎት ከዚህ ሁሉ ይበልጣል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም "ጌታ ለድሆች እሰጣለሁ፣ በምችል ጊዜ እረዳለሁ በዚህም ምክንያት ደህና ሁኔታ ላይ ነኝ" ማለታችን ነው።

በእግዚአብሔር የተመረጠች ነፍስ እንደዚህ ዓይነት ቸልተኝነት ስታሳይ የእግዚአብሔር ቅዱሳንና መላዕክቶቹ ልባቸውን ይታመማል፡፡ ዉድ ቤተሰቦች የት ቦታ ላይ ከመንገድ እንደወጣችሁ ለመረዳት ያስችላችሁ ዘንድ ሁሉንም ግልጥልጥ አድርጌ አስቀምጬላችኋለሁ፡፡ ጌታ ለሰርዴስ ቤተክርስቲያን "ሥራህን አውቃለሁ በስም ሕያው ነህ ነገር ግን ሞተሃል" የሚለውን ክፍል ሰጥቶኛል፡፡

ይህ ከራሴ ስንፍና እና ቸልተኝነት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን በቤተክርስቲያን ውስጥም በስፋት አይቼዋለሁ። እናም እንደገና በህይወት የመነሳት ፀጋን ለማግኘት ከፈለግን ራሳችንን በማስተካከል ከምንጊዜውም በበለጠ ለእግዚአብሔር መኖር ይኖርብናል፡፡ ከእኔ ጋር በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ናችሁ??? እግዚአብሔርን በበለጠ ትፈልጋላችሁ? በውስጡ ሰምጣችሁ በአገልግሎት እንዲጠቀምባችሁና ከእርሱ ጋር በቅድስና ለመራመድ ትፈልጋላችሁ?

ደግሞስ የእርሱን ጥበቃ ትፈልጋለችሁ? ይህ የሚገኘው ደግሞ ልባችንን በመለወጥ ነው፡፡ የተጠራነው ለራሳችንና ለእግዚአብሔር እውነተኛ እንድንሆን ነው፡፡ ይህንን ካደረግን ከዚህ ገዳይ በሽታ ተጠበቅንም አልተጠበቅንም ቢያንስ ከጌታ ጋር ሃቀኛ ለመሆን የምንችለውን ሁሉ ሞክረናል፡፡ ይህም ጥፋቶቻችንንና ጉድለቶቻችንን ሁሉ ተናዝነን ለመፈወስ ወይንም ከእሱ ጋር ለመወሰድ ተዘጋጅተናል ማለት ነው። ስለዚህ ሁላችሁንም የምማፀናችሁ ንስሐ መግባታችሁን እንዳታዘገዩት

ነው፡፡ አሁን ወደ ጌታ ፊታችሁን አዙራችሁ  ስለራሳችሁ እውነቱን ፈልጉ፡፡ የቱጋ ነው ከጌታ ወደኋላ የቀራችሁት? የቱጋ ነው መቀየር ያለባችሁ?

ይህንን ካደረግና በኋላ በሙሉ መተማመን ፍፁም እንዲያደርገን፣ ልባችንንና ህሊናችንን ባዶ ከሆነ ሥራና ከንቱነት እንዲያጥበን እንጠይቀው። ብንኖርም ወይንም ብንሞትም እንድንጠበቅ የሚያደርገን  ቅን የሆነ የልባችን ሐሳብ ነው። ነገር ግን ቢያንስ ጌታ እንድንሆን ለጠራን ማንነት የምንችለውን እንዳደረግን እናውቃለን፡፡ እናም መቼም ተስፋ አንቆርጥም። ጌታንም እንዲህ ብዬ ጠየኩት "ጌታ ሆይ በዚህ ላይ የምትጨምረው ነገር አለ?"

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ክሌር ልብሽን በደንብ እያዳመጥኩት ነው፡፡ ይህ ልብ ደግሞ ለአንቺ የሆነው የኔ ልብ ነው፡፡ የወይኑን ቦታ ከሚያወድሙት ከእነዚህ ትንንሽ ቀበሮዎች ነፅተሽ ለማየት እንዴት እመኛለሁ፡፡ የኔ ፍቅር በእርግጥ ደካማ ነሽ፡፡ ነገር ግን ላስታውስሽ የምፈልገው እጅግ ደካማ በሆንሽበት ነገር ላይ በእርግጥ እጅግ ጠንካራ ሆነሽ ሌሎች ድክመታቸውን እንዲያሸንፉ ትመሪያቸዋለሽ።

"መሆን ያለብሽን ያህል ሳትሆኚ ስትቀሪ እንዴት እንደምታዝኚ አውቃለሁ፡፡ ደግሞም አይምሮሽ ከአንድ ነገር ወደ ሌላው ነገር በመሮጥ ውሳኔሽን እንደሚያስረሳሽና ደስታና ሙላት በማይሰጥሽ መንገድ ላይ ጉዞ እንደምትቀጥዪ አውቃለሁ፡፡ የኔ ውድ በዚህ ጉዳይ ላይ ልጎዳሽ ሳይሆን እያንዳንዱ የምትወስጂው ውሳኔ ውጤቱን በደንብ እንድታጤኚው እየጠየኩሽ ነው። ቅዱስ ፍራንሲስ “የሞትን እህት ጠይቋት” እንዳለው፡፡ በሌላ አነጋገር በምድር ላይ በኖራችሁበት በመጨረሻዎቹ ሰዓታት በውሳኔዎቻችሁ ታለቅሳላችሁ ወይንስ ትደሰታላችሁ?

"ከህዝቤ መካከል ማንም በሁሉም ነገር ፍፁም የሆነ የለም፡፡ አንዳችሁም ብትሆኑ በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ ራሳችሁን መቆጣጠር አትችሉም። ማናችሁም ብትሆኑ እዚህ ደረጃ ላይ አልደረሳችሁም። እስኪ ማዘር ቴሬሳን በመጨረሻ የእድሜዋ ቀናት ተመልከቷት፡፡ ለብዙ አስርት አመታት ከጣፋጩና ከሚጨበጠው መገኘቴ የሚገኘውን መጽናናት ሳታውቀው ኖራለች፡፡ እንዳውም በህይወቷ ትክክለኛውን ነገር ለመስራቷ ጥያቄ ነበረባት፡፡ እናም ይህች ቅድስት ሴት በመታዘዝዋ ያፈራችውን ፍሬ ተመልከቱ፡፡ ከዚህ የተሻለ እንሆናለን ብላችሁ ትጠብቃላችሁ? ትልቁን ተልዕኮአችሁን ለማሳካት የሚያስፈልገውን ሁሉ ነገር ማድረጋችሁን ማረጋገጫ ታገኛላችሁ? የኔ ውዶች ጭንቅ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ይህ መንገዳችሁን ለመፈተሽና ደግሞም መድረቃችሁ ከግምት መሳሳትና ከጥፋተኝነት ስሜት የመነጨ እንደሆነ ለማየት ምክንያት ይሆናችኋል፡፡

"በዚህ የአርባ ቀን የፆም ወቅት ብዙ የፆም ስጦታና መስዋዕቶች በምትችሉት አቅም እንድታቀርቡልኝ እፈልጋለሁ። ከዚህም የተነሳ የእምነትና የመለወጥን ፀጋ ለህይወታችሁ እለቃለሁ። የምህረት ሥራ ለመፈወሳችሁ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው። ድሆችን መመገብ ፣ የታመሙና የታሰሩትን መጐብኘት እንዲሁም ከህይወታችሁ ርቀው ላሉና ፀሎታችሁ ለሚያስፈልጋቸው መፀለይ ያስፈልጋል።  ደግሞም የጐደኛችሁን አንዴና ሁለቴ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅር በሉ፡፡ ይህንን ብታደርጉ በሰማይ ያለው አባታችሁ ደግሞ በእርግጥም ይቅር ይላችኋል፡፡

"ራሳችሁን ዝቅ በማድረግ ሌሎችን ለማገልገል ፈልጉ እንጂ ሌሎችን አትጠብቁ። በኃጢያት ምክንያት ህሊናችሁ ሲነካ ስህተታችሁን ለመሸፈን አትሞክሩ። ይህ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ ኃጥያታችሁን ማወቅ ትልቅ ፀጋና ለመለወጥ ያላችሁን እምነትና ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ የኔ አለሞች፣ የኔ ህዝቦች እንዴት በመለሳለስ እየጠራኋችሁ እንደሆነና ስትሰቃዩ ማየት እንዴት

እንደምጠላ፡፡ አሁን እንኳን እጃችሁን በመያዝ የፀና እምነትና ለመለወጥ እውነተኛ ፍላጎት እንዲኖራችሁ እያካፈልኳችሁ ነው፡፡ በዚህ ምድር ላይ እንደገና ህይወትን ለመዝራት እመኛለሁ፡፡ በዚህም ለውጥ ተሳታፊ የሚሆኑ ያልተሰባበሩና ቀዳዳ ያልበዛባቸው፣ የምሰጣቸውን ፀጋ ሳያፈሱ የሚያቆዩ ማስቀመጫዎችን እፈልጋለሁ። እነዚህም በማይረባ ነገር የማይወጣጠሩ፣ በኩራት ያልተሞሉና ፈራጅ ያልሆኑ፣ በመራራነት ያልተሞሉና ፀጋቸውን የማያፈሱ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

”እነዚህ ዝንባሌዎች አንዳንድ ጊዜ ህይወታችሁን የሚቆጣጠሩና እንድታከናውኑት የምፈልገውን ፀጋዎች የሚገድሉ ናቸው። ለዚህም ነው በአለም  ላይ እንደዚህ አይነት አሰቃቂ የማንቂያ ደወልን የፈቀድኩት፡፡ ከነቃችሁና ህይወታችሁን ካደሳችሁ ነገሩ እንደሚስተካከል እርግጥ ነው፡፡ ምላሽ ካልሰጣችሁ ግን እየባሰ ይሄዳል። ነገሩ ይህንን ያህል ቀላል ነው። በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ መታዘዛችሁንና ታማኝነታችሁን፤ ትብብራችሁን፣ በወንድማማች ፍቅር መመላለሳችሁንና ራሳችሁን መስዋዕት ማድረጋችሁን እፈልገዋለሁ፡፡ መስቀላችሁን በታማኝነት ተሸክማችሁ፣ ሳትንሸራተቱና ሳትደብቁት ማየት እፈልጋለሁ።

"ብዙዎቻችሁ በዚህች ደቂቃ ውስጥ የምላችሁን በመረዳት ለመለወጥ እየተዘጋጃችሁ ነው። አንዳንዶቻችሁ ለመለወጥ ትፈልጋላችሁ ነገር ግን መጥፎ ተግባሮቻችሁን በፍቅር ትወዷቸዋላችሁ፡፡ ሌሎች ደግሞ 'ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ጥሩ ክርስቲያኖች ንሰሐ መግባት አያስፈልጋቸውም' በሚል አመለካከት ምክንያት ስድብ ደርሶባችኋል፡፡ ነገር ግን ሁላችሁም አንድ የሚያመሳስል ነገር አላችሁ፡፡ ሁላችሁም የእኔ አካል ናችሁ እናም እወዳችኃለሁ፡፡ ስለዚህም ለእያንዳንዳችሁ ከኃጥያትና ከመጥፎ ተግባራችሁ  ተለይታችሁ መውጣት የምትችሉበትን፣ እስካሁን ወደኋላ እንድትቀሩ ያደረጓችሁን ነገሮች አብረን በመሆን የምናሸንፍበትን እያዘጋጀሁ ነው፡፡

“ለዚህም ኃጥያታችሁን እርስ በርስ እንድትናዘዙና ለእናንተ ብቻ ያዘጋጀሁትን መስቀል እንድትሸከሙ እየጠየኳችሁ ነው። ይህንንም ስታደርጉ እኔ አብሬያችሁ እንዳለሁ እና የድሮዎቹን ነገሮች ማለፍ እንደምትችሉ እንድታምኑ እፈልጋለሁ። ይህ አዲስ ወቅት በመሆኑ ለቅድስና አዲስ ቃል መግባትን ይፈልጋል። የተወደዳችሁ እኔ ደግሞ ራሳችሁን ማሸነፍ እንድትችሉ ከጐናችሁ በመሆን  እሸከማችኋለሁ።

"አሁን እጄን ያዙና እስከ ዛሬ አውርታችሁ የማታውቁትን ሁሉ በግልፅ ከእኔ ጋር አውሩ፡፡ ምን ያህል ትግል ላይ እንደሆናችሁ ስለማውቀው በቃ ዝም ብላችሁ ፀጋን ጠይቁኝ፡፡ ይህንን ፀጋ ስሰጣችሁ ደግሞ እንዳታባክኑት፣ ታማኝ ሁኑ፡፡ ታማኝ በመሆን ለሚሰሩ ትልቅ ውበትና ሽልማት ይጠብቃቸዋል፡፡  ምክንያቱም የምታከናውኑት በእኔ ፀጋ እንጂ በራሳችሁ ጥንካሬ ስላልሆነ ብቻችሁን ልታከናውኑት የምትችሉት ስላልሆነ በራሳችሁ አትተማመኑ፤፤ እንዳውም የምትችሉትን ሁሉ አድርጉና መጨረሻው ጥሩ እንዲሆን ሌላውን እኔ እንድሞላው ጠብቁኝ፡፡ እኔ ከናንተ ጋር ነኝ፣ ደግሞም ለእናንተም ነኝ፡፡ እናንተ አለሜ ናችሁ፣ ስለዚህም እንሂድና ጠላትን እናሸንፍ።"

**የዘመኑ ሳርዴስ ቤተ ክርስቲያን እንሆንን? - ኤፕሪል 4 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Are we the church of serdes - April 4th, 2020**

የኔ ውዶች በዚህ ሳምንት ለሁላችንም ፀሎቴ ሙሉ ለሙሉ ወደ ጌታ እንድንመለስ፣ አለምን ከህይወታችን ለማስወገድ እንድንችል፣ በልባችን በሚገኘው የአትክልት ሥፍራ ጌታን እንድናገኘው፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የምናሳልፈውን እያንዳንዱን ሰዓት ዋጋ እንድንሰጠው ነው፡፡

ጌታ የሳርዴስ ቤተክርስቲያን የሚለውን ክፍል እየሰጠኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ምን ማለት እንደሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም። እናም ስለ እኔ ነው ብዬ በማሰብ ፈርቼ ነበር፡፡ በመጨረሻውም ትላንት እውነቱን ገለፀልኝ፡፡ ጌታ ስለ ሰርዴስ ቤተክርስቲያን የተናገረው ለተወሰኑት ኸርት ድዌለርስ ከሆነ እኔንም ያስወቅሰኛል፡፡ ምክንያቱም እኔ የማምነው በጐቹ የሚሄዱት እረኛው በሄደበት መንገድ ነው ብዬ ነው ፡፡ ስለዚህ የኔንም ህሊና በደንብ መፈተሽ ነበረብኝ፡፡ እናም እውነቱን አገኘሁ።

ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የተላከ መልዕክት፦ "በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ፃፍ ። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲይ ይላል። ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን ፥ ሊሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና። እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ ፥ ጠብቀውም ንሰሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም።

"ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡" (ራዕይ 3፡1-6)

(ክሌር)፦ መገንባት የያዝነውን ቤት ጉዳይ ፣ ተራራው ላይ ላሉትና ለራሳችንም የሚያስፈልገንን ነገሮች ለማሟላት ፣ እንዲሁም የፀሎት ጊዜዬን በማመጣጠን በሥራ ተጠምጄ ነበር ። ኢያችሁኝ ተራራ ላይ ላሉት ማሟላት የሚለውን ከፀሎት ጊዜዬ ሳስቀድመው? እውነታው ልክ ፀሎት ስጀምር አንድ የሚያቋርጠኝ ነገር አይጠፋም፡፡ ይህም ሰው እኔን በመፈለጉ ብቻ ሳይሆን በኃሳቤ ጭምር መረበሼ ነበር። ለምሳሌ የኮምፖስት መታጠቢያውን ማዘዝ አለብሽ፣ ወይም የሚገዙ ነገሮች ዝርዝር ላይ እሳት ማቀጣጠያ ጨምሪበት፣ ወይንም ቫይታሚንና ከዕፅዋት የተሰሩ መድኃኒቶች በቂ መኖራቸውን ብታረጋግጪ ጥሩ ነው፣ ዝርዝሩ ውስጥ ፍራፍሬ ብትጨምሪበት ወዘተ ወዘተ.. በሌላ አነጋገር ማለቂያ የሌለው ማለት እንችላለ፡፡

እኔና ህዝቅኤልም አንድ ክፍል ውስጥ መሆናችን ምንም አልረዳም፡፡ ምክንያቱም እኛ አንዱ ሲሞቅ ሌላው የሚቀዘቅዝ፣ ወይም አንዱ ፀጥ ያለ አምልኮ ሲፈልግ፣ ሌላው ጮክ ያለ አምልኮ የሚፈልግ አይነት ጥንዶች ነን፡፡ በምንችለው አቅም ሁሉ አብሮ ለመሄድ ሞክረናል፡፡ ይህ በእርግጥም ፈታኝና አስቸጋሪ የወንድማማች ፍቅርና የትዕግስት ትምህርት ነበር። ትምህርት ያልኩበት ምክንያት ጌታ እኛን የሚያስተምረን በራሱ የትምህርት እቅድ እንጂ ከመፃሕፍት ስላልሆነ ነው፡፡ እናም ይህ ስለ ትዕግስት የተማርነው ከሌላው የተለየ አስተምህሮ ነበር።

እናም ላለመነሳት ጠንካራ መሆን ሲገባኝ ብድግ ብዬ ነገሮቹን መፈፀም እጀምራለሁ፡፡ (የበፊቱ ልምምዴ ግን በዝርዝር በመፃፍ ለበኋላ ማቆየት ነበር)፡፡ ታዲያ እንደ ነፋስ ተነስቼ የምፈፅመው ይህ ተግባር የወይኑን ቦታ ጎድቶታል፡፡ በእነዚህም ዝርዝር ሥራዎች በመጠመዴ ምክንያት እስከመለስ ድረስ ጌታ እንዲጠብቀኝ ግድ ሆኖበት ነበር። በመጨረሻም ጌታዬ ለእኔ ድብቅና የማይታይ  ሆነብኝ። በእርሱ ላይ አልፈርድም ምክንያቱም ትናንሽ ቀበሮዎች ፍሬውን እንዲበሉ የወይኑን ሥፍራ ትቼላቸው ሄጃለሁና ነው፡፡ እርሱ ይህንን የሚያሳዝን የአትክልት ቦታ ለምን ቆሞ ይመለከታል?

ባለፈው ወር በተደጋጋሚ ስለ ሳርዴስን ቤተክርስቲያን የሬማ መልዕክት ስለደረሰኝ ቆም ብዬ እንዳስብና ራሴን እንድመለከት አድርጎኛል። ይህ ብቻም አይደለም፣ ጌታ እጅግ ስለናፈቀኝ ለብዙ ቀናት ሳለቅስና በልቤ ውስጥ የሞኝ ድርጊት እንዳደረግሁ ሲሰማኝ ነበር ። ሆኖም ግን ከምህረቱ የተነሳ ትላንትና ከትልቅ ፈገግታ ጋር ራሱን ግልፅ አደረገልኝ ። እናም ልቤ ቀለጠ።

እናም አሁን የእርሱን መልዕክት ለእናንተ ለኸርት ድዌለርስ ማካፈል እፈልጋለሁ።

(ክሌር):- ጌታ ለምንድነው የሳርዴስ ቤተክርስቲያን የሚለውን መልዕክት ደጋግመህ የሰጠኸኝ? የሳርዴስ ቤተክርስቲያን መልዕክትም እንደሚከተለው ነው፡፡

<u>"በሳርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል። ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ሊሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና።እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም</u>።"ዮሐንስ ራዕይ 3፡1-3

ኢየሱስም "ምክንያቱም ከእናንተ መካከል የምናገረውን ክብደት ሰጥተው ሙሉ በሙሉ በመሳብ የማይኖሩ ስላሉ ነው። ስለ ግድ የለሽነታችሁ ንሰሐ በመግባትና በልባችሁ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ትኩረት በመስጠት እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ። አለምን ከልባችሁ ውስጥ አውጡ! አውጡ! ትኩረታችሁን በእኔ ላይና አብረን ልንኖር ባለው ዘላለማም ላይ አድርጉ። በዚህ በተቀደሰ ሥፍራ ይህም በልባችሁ ውስጥ አለምን አታምጡት። በአለም ያላችሁን ተግባር ወደጎን አድርጋችሁ ያላችሁን ጊዜ ሁሉ ለእኔ ስጡኝ። እቃ መሸመትን፣ መዝናናትን፣ ከንቱ ጨዋታዎችንና ጉጉታችሁን በማስቀረት ለእኔ ሥፍራን አዘጋጁ፡፡

"በዚህ ሳምንት በአለም ላይ ነፍሳችሁን የሚመርዙ ብዙ ነገሮች እየተዘጋጀላችሁ ነው። እነዚህም ነገሮች በአምሮአችሁና በልባችሁ ብዙ ፍርሃትን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ የመሰዊያውን ቦታ በንፁህ ፍቅር፣ እንዲሁም እኔ ያዘጋጀሁላችሁን በጉጉት ብትጠብቁ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር። ይህ ሳምንት በሥርግ ላይ በምናደርገው ማሃላ ላይ በመንፈስ ትኩረት የምትሰጡበት እንዲሆን እፈልጋለሁ።"

"ነገር ግን ሰይጣን እየጠነሰሰ ያለውን የምትመገቡ ከሆነ ይህ ያመልጣችኋል። አዕምሮአችሁ  ምስቅልቅል ስለሚል እኔ ያዘጋጀሁላችሁን ፀጋ ለመቀበል ብቁ አትሆኑም። እኔ እጠብቃችኋለሁ፣ ነገር ግን እናንተ ደግሞ ከዘላለም ህይወታችሁ ጋር የማይገናኙትን ነገሮች መተው  አለባችሁ።"

“የእኔ ፍቅር የኔ ፍላጎት አንቺን ለመቅጣት ሳይሆን ይልቁንም ወደተዘጋጀልሽ መጨረሻ እንድትደርሺ መንገዱን ማስተካከል ነው። ነገር ግን አብዛኛዎቹ በዚህ ሳምንት ሊካሄድ ባለው በአለም ጉዳዮች ለመሳተፍ እቅድ በማውጣት እጅግ ተወጥረዋል፡፡ አንቺም አቅጣጫሽን ለማሳት ከሚያደርጉሽ ነገሮች አሁንም እየተፈተንሽ ነው። እስካሁን ድረስ ኃሳብሽን ለመስረቅ የሚሞክሩ ነገሮች ችላ በማለት ጥሩ አድርገሻል። አሁንም የእኔን ምሪቶች በመከተል መተው የምትችያቸውን ነገሮች ሁሉ ወደ ጎን በመተው ቀጥይ። ይህንን በማድረጋሽ መቼም ቢሆን አይቆጭሽም !!

"ለተቀራችሁት ይህንን እላለሁ ጠንከር በማለት አለምን ከውስጣችሁ አውጡ፡፡ ምክንያቱም የባህር ሞገዶቹ አስፈሪና ጠንካራ በመሆናቸው በእዚያ እንድትቆዩ አልፈልግም። ከእኔ ጋር ቅርብ በመሆን፣ ከእኔ ጋር ቆይታ በማድረግና ራሳችሁን በመለየት በተቻላችሁ መጠን አለምን ከህይወታችሁ አውጡ። እየጠራኋችሁ ያለሁት ለአንድ ሳምንት የሚቆይ ከእኔ ጋር የጥሞና ጊዜ እንድታሳልፉ ነው፡፡ በእነዚህም ጊዜያቶች በመንግስተ ሰማያት ምን ለማድረግ እንደምትፈልጉ ህልምን አልሙ፡፡ እስካሁን አይቻልም ብላችሁ የምታስቡትን ሁሉ ለመጠየቅ ድፈሩ፡፡ እንደማዳምጣችሁና ፍላጎታችሁን ሁሉ እንደማሟላ በመጠበቅ ከእኔ የምትፈልጓቸውን ስጦታዎች ሁሉ ጠይቁ።

"ሙሽሮቼ እባካችሁ በዚህ ሳምንት ሁሉ ነገራችሁን ስጡኝ። ከዜና፣ ከገበያ ሥፍራዎች፣ ከኢንተርኔት በመራቅና የፀሎት ቦታችሁ በመግባት ከምንም በላይ እኔን ለማግኘት ፀልዩ። ይህ ለእናንተ ያለኝ የኔ ፍላጎት ነው፡፡ ይህንን ለእኔ እንደሠርግ ስጦታ አድርጋችሁ ትሰጡኛላችሁ? እኔ ደግሞ ይህንን የጠየቋችሁን ለማሟላት የምትችሉበት ፀጋ እሰጣችኋለሁ። ከወደዳችሁኝ ደግሞ ትታዘዙኛላችሁ፡፡"

ጌታ ህዝቅኤልን እንዲህ አለው. . . "በዚህ ሳምንት በጠበቀ መልኩ ራሳችሁን ፍፁም ስነስርአት እንድታስይዙ እፈልጋለሁ። የኔ ታማኝ ሙሽሮች እባካችሁ ኢንተርኔት ከመጠቀም ተቆጠቡ። ጉጉታችሁን ግደሉ። እናም ራሳችሁን በዘላለም ህይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ለሆነው ለዛ ጊዜ እንድታዘጋጁ እፈልጋለሁ። በእኔና በእኔ ላይ ብቻ አተኩሩ፡፡ እኔ መላው ልቤ ፣ አይምሮዬ፣ መንፈሴና ነፍሴ በአጠቃላይ ለሠርጋችን ዕለት እየተዘጋጀ ነው።

“እባካችሁ ውዶቼ የአለም ነገር ይብቃችሁ። ከገበያ ቦታዎች ራቁ። ይህ ጊዜ ለራሳችሁና ለምትወዷቸው ስጦታ የምትገዙበት ጊዜ አይደለም። ለሠርጋችን ንፁህ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። ቴሌቪዝን ከማየት፣ ሬዲዮ ከማድመጥ፣ጋዜጣዎችንና መጋዚኖችን ከማንበብ ተቆጠቡ። በእድሜ ዘመናችሁ ሁሉ ይህንን በማድረግ አሳልፋችኋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በእናንተ ላይ ያመጡባችሁን ተፅዕኖዎች ለማንፃት በብዙ ህመም ውስጥ አልፌያለሁ።

“የእኔ ምርጦች ስለ ልጆችና ስለ ሥራ ጉዳይ እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳዮች የሚጠበቅባችሁን ኃላፊነቶች በአግባቡ ተወጡ። ሆኖም የምታሟሉት ለሌሎች እጅግ አገብጋቢ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ይሁን፡፡ ለምሳሌ ያህል:- ሆስፒታል መሄድ የሚፈልግን ሰው መውሰድ ፣ የታመሙትን፣ የተቸገሩትንና እድሜያቸው የጠና ሰዎችን መርዳትና የመሳሰሉትን። እናንተም ራሳችሁ የትኞቹ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ የትኞቹ ደግሞ አላሰፈላጊ እንደሆኑ ታውቃላችሁ፡፡ ይህንንም በትክክል እንድትፈፅሙ በማስጠንቀቅና ማድረግ ያለባችሁን እንድታደርጉ እንዳስፈላጊነቱ በመጎትጎት እረዳችኋለሁ።

“በሰውኛ ስናየው አንድ ሰው ለሠርጉ ዝግጅት ሲያደርግ በእያንዳንዱ የዝግጅቱ ዝርዝር ጉዳዮች ይወጠራል። እባካችሁ እንደ ሳርዴስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌባ በሌሊት የምመጣባችሁ አትሁኑ። የቀረውን ነገር ሁሉ አጠናክሩ።

“በእኔና በእኔ ላይ ብቻ ተጣብቃችሁ ኑሩ። ሐሳባችሁና ዓላማችሁ ሁሉ በእኔና ለእኔ ብቻ ይሁን። ቀናችሁን እንዲሁም ቀኑ ይዞት የሚመጣውን ሁሉ ለእኔ ስጡኝና ሁሉንም እባርከዋለሁ። ውድቀትና ትግላችሁን እንኳን ቢሆን ለእኔ ስጡኝና እቀድሰዋለሁ። ይህች ናት ለንጉሷ የበቃች ሙሽራ!!!"

**ሙሽሮቼ አሁን ለእኔ ታስፈልጋላችሁ - ኤፕሪል 7 ቀን 2020 ዓ.ም**

**My bride I need you, April 7th, 2020**

እኔና ህዝቅኤል ልንኖርበት ያለው ቤት ገና መጠናቀቁ ነው፡፡ እናም እኔ ወደዚያ ቤት ለመግባት እጅግ ፈልጌያለሁ፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ተጨብጠን በመቆየታችን አንዳንድ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ህዝቅኤል ሳይረበሽ ዕረፍት መውሰድ አልቻለም ነበር። ምክንያቱም እርሱ የአስተዳደር ዝርዝር ጉዳዮች የሚመቹት ሰው አይደለም፡፡

ስለዚህም ይህ ጉዳይ ምን መሆን እንዳለበት በመፀለይ ላይ እያለሁ፣ ጌታ በዚህ በተቀደሰ ሳምንት እንድንለቅ ባይፈልግስ? የሚል ስሜት በውስጤ ተፈጠረ፡፡ እናም ይህ ስሜትና ሐሳብ ከውስጤ በፍፁም ሊጠፋ አልቻለም፡፡ እናም ይህንን ለመለየት የሚረዱኝን ቡድኖቼን ጠራሁና እግዚአብሔር ሳምንቱን ሙሉ ምንም ነገር ፅዳትም ቢሆን ወይም ዕቃችንንም ማጓጓዝ እንደማይፈልግ ተገነዘብን፡፡ ከዚያም ከጌታ እራት በኋላ ጌታን ለማዳመጥ ተቀመጥኩኝ፡፡ ጌታን በትክክል ለማዳመጥ ሥጋ ወደሙ ከተቀበላችሁ በኋላ ቢሆን በጣም ጥሩ ጊዜ ነው፡፡

ጌታንም እባክህ ልብህ ውስጥ ያለውን ንገረኝ? አልኩት

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ፡- "ሰው አለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ህዝቤ እባካችሁ ከአለም ጋር ያላችሁን ግንኙነት እንድትቀንሱ እየጠየኳችሁ ነው። ይህ ሳምንት እስከሚያልፍ ድረስ ከትልልቅ ሥራዎች ተቆጠቡ። ይህንን ሳምንት ልባችሁን በማዘጋጀት አሳልፉት፡፡ ለህይወታችሁ ምን እየተሰራ እንደሆነ አታውቁምና፡፡ መውደቂያችሁ እንዴት እየቀረበ እንደመጣ አልተገነዘባችሁም።

"ይህ ጊዜ ብዙ ጊዜንና ጉልበትን በሚጨርሱ አዳዲስ ሥራዎች የምትጠመዱበት ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ የምትሰበሰቡበት ጊዜ ነው፡፡ እርፋችሁ በመቀመጥ ፀልዩና ተመልከቱ፡፡ ለአለም ለመፀለይ ሰዓታችሁን ስትሰጡ እኔ አብሬያችሁ እሆናለሁ። ከዚህ ተራራ ላይ ብሩህ የሆነ ብርሃንን መመልከት እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም አይኖቼ አለምን ሁሉ ሲቃኙ የፀደይ ወራትና የአለም ተግባራት ሰዎችን ሁሉ በአንድ ላይ ቆልፎ በማያልቅ እንቅስቃሴ ውስጥ በመከተትና በጥልቅ ጨለማ ውስጥ በመጣል፣ በአካባቢያቸው እየተፈጠሩ ስላሉት ነገሮች ደንዝዘው ስላየሁኝ ነው።

“አለም በአሁኑ ጊዜ አደገኛ ሥፍራ ነው፡፡ ምድርን ስቃኝ አሁን በምድር ላይ ያለው ጨለማ ነው። ስለዚህ ከዚህ ተራራ ብርሃን ሲመጣ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ከዚህ ተራራ ተስፋና ማላጅነትን ማየት እፈልጋለሁ፡፡ እያንዳንዳችሁን ከዚህ በፊት ሆኖ እንደማያውቅ ልባርካችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው ለሚታዘዙት ብቻ ነው፡፡ ይህ ጊዜ የመዝናናት ወይም የሥራ ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ ጊዜ የፀሎት ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህም ፀልዩና የሚሆነውን ተመልከቱ፡፡

"የተወደዳችሁ ሆይ የልባችሁን ሁኔታ በደንብ አጣሩ። በአለም ጥቅማጥቅሞች ከመሳባችሁ የተነሳ አለምን በመተው ለመፀለይ፣ ለማጥናት፣ ለማምለክና ንስሐ ለመግባት አቅቷችሁ ይሆን? ለመፀለይና ልባችሁን እንድታዘጋጁ የሚመክራችሁን ድምፄን በንቃት ለማዳመጥ ከብዷችሁ ይሆን? የመሞቴንና ሞትን ድል አድርጌ መነሳቴን በማስታወስ ለተዘጋጁ ነፍሳት የሚመጣ እጅግ ብዙ ቅባት አለ፡፡ ታዲያ እየሰራችሁ ያለውን በመተው ለዚህ ትዘጋጃላችሁ?"

"ይህ ህዝብ ካልታዘዘኝ ታዲያ ማን ይታዘዘኛል ? አንዳንዶች በመሰጠት እኔን እየፈለጉ እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህንን የምነግራችሁ ላሳፍራችሁ ሳይሆን በዚህ ጊዜ ለእኔ እጅግ አስፈላጊው ነገር ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም ደግሞ አስፈላጊ ያልሆነው ምን እንደሆነ እንድትረዱ ብዬ ነው።"

"ደግሞ አድምጣችሁ ስለምትታዘዙ አመሰግናችኋለሁ፡፡ ባርኮቴ በእናንተ ላይ ወርዶ ይሰፍናል፡፡ ፍሬውም በርካታ ነው። ሙሽሮቼ በዚህ ጊዜ ታስፈልጉኛላችሁ!"

ክሌር፦ የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ ጌታ ይህንን ሳምንት ለእርሱ እንድንሰጠው መፈለጉ ግልፅ ነው፡፡ ሱቆች፣ ሥራ ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት መዘጋታቸው ደግሞ ነገሩን ቀላል ያደረገው ይመስለኛል። ጌታ የሚፈልገው ተንበርክከን በትልቅ መቃተትና ጥልቅ ስሜት ለዚህ አለም እንድንፀልይ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ እኛን ኃጥያተኞች ይቅር በለን። ጌታ ኢየሱስ ለዚህ አለም መማለድ የምንችልበትን ሸክምና ፀጋ ስጠን፡፡

አሜን

## ሥቃይ - እጅግ ከባዱ ሥራ - ኤፕሪል 17 ቀን 2020 ዓ.ም

## The hard work suffering, April 17, 2020

ውድ ቤተሰቦች ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡፡ የልባችሁ ቁስሎች በኢየሱስ ድነው ይፅናኑ፡፡ አሜን፡፡ ጌታ ሁለት ጓደኞቼን በሞት በማጣት የሚያመኝን ቦታ በእርግጥ አገኘሁት ፡፡ በተለይም ከአንዷ እህት ጋር በህብረታችን ጊዜ ብዙ ጣፋጭ ትዝታዎች ነበሩን፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ልክ አንድ ነገር በውስጤ እንደሚቃወመኝ ሰላም አላገኘሁም፡፡

ኢየሱስም "ክሌር ለዚች አስደሳች ነፍስ የታመመውን ልብሽን ላጥብልሽ እዚህ ነኝ፡፡ ብዙ ጥሩ ባህርያት ኖረው አንድ ትንሽ ስህተት ብትኖር ያቺ ብቻዋን ሌላውን ሁሉ ታጐድፋለች፡፡"

ክሌር፦ ጌታ ሆይ እንዴት እፈራለሁ፣ እኔ እኮ ብዙ ስህተቶች አሉኝ።

"እንግዲህ በስተመጨረሻው ይካካሳል፡፡ እንዲገባሽ የሚያስፈልገው እኛ እየሞከርን ያለነው ነገሮችን በመፈወስ እንደነበረው ለማድረግና ቁስሎች አመርቅዘው መከፋፈልን እንዳያመጡ ነበር፡፡ ይህ ለአንዳንዶች ከሌሎቹ ይልቅ የበለጠ ቀላል ነው። የኔ ውድ ራሳሽን አትገስጪ ምክንያቱም ሥጋሽን ለመግደል እስካሁን ገና እየታገልሽ በሚደረገው ሂደት ላይ ነሽ፡፡

“ሁላችሁም የማያቋርጥ ቀስቶች ይወረወሩባችኋል፡፡ እነዚህም የቅናት፣ ያለመተማመን ፣ የፉክክር ፣እኔ እበልጣለሁ የሚል፣ በሌሎች ሰዎች የሚለካ የውድቀት ወይም የስኬት ቀስቶች ናቸው፡፡

"ክሌር አንቺ ስኬትን ከእኔ ዕይታ አንፃር ብቻ በመምረጥሽ ጥሩ አድርገሻል። ምክንያቱም ይህ አስተሳሰብ በሰው አመለካከት ስላልተበላሸ በዚህ መንገድ ልብሽን ለማንፃት እችላለሁ፡፡ ፍፁም ነሽ እያልኩ አይደለም ቢሆንም ግን ከበፊት ጀምረሽ የሰዎች ምስጋና ከንቱ መሆኑን ስለተረዳሽ ነው፡፡ ሌሎች ግን እንደዚህ አልተባረኩም ስለዚህም የተሸከሙትን ብዙ ጭነት ለማራገፍ መስራት አለባቸው፡፡

"በልብሽ ውስጥ የተሰሙሽ እነዚህ ህመሞች ልብሽ ህይወት እንዳለው የሚያሳዩ ጥሩ ምልክቶች ናቸው። ብዙዎች ህይወታቸውን በጣም አስደሳች በሆኑ ተግባራት ስለሞሏቸው ውስጣቸው እየተፈጠረ ያለውን ነገር እንዳያዩ ተሸፍኖባቸዋል፡፡ እነሱን በቀላሉ ዝም አስብሎ በውስጣቸው በየዕለቱ በህይወታቸው፣ በዝንባሌያቸው እና በውሳኔያቸው ጀርባ የሚካሄደውን እውነተኛ ስቃይ እንዲያስተውሉ ማድረግ ያስቸግራል፡፡ አንቺ ግን እንደዚህ አይደለሽም፡፡ ለሌሎች ብለሽ ግን ህመምሽን ትደብቂያለሽ፡፡

(ክሌር) ፡- ጌታ እባክህ እኔን ማናገርህን አሁንም ቀጥል ። ኢየሱስ ምን ያህል እንደናፈከኝ ታውቃለህ? ከአንተ በመለየት በብቸኝነት እንድሞት አትፈቅድም አይደል? የምተማመነው በአንተ ምህረት ነው። ምክንያቱም ጣፋጩ እቅፍህና ከአንተ ጋር ያለኝ አብሮነት የማይገባኝ ነኝ፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ከእነዚህ ውጪ ልኖር አልችልም።

ኢየሱስም "መቼም የማንለያይበት ጊዜ እየመጣ ነው። መለያየትን የሚመስል ነገር እንኳን አይኖርም፡፡ የኔ ፍቅር እሩቅ አይደለሁም፡፡ በውስጥሽ እኖራለሁ ደግሞም በውስጥሽ እንቀሳቀሳለሁ። ስታለቅሺ እኔም አብሬሽ አለቅሳለሁ፡፡ ተበሳጭተሽ ነገሮችን በትክክል ማየት ሲያቅትሽ እኔ እፀልያለሁ። ክሌር ሁሌም ከአንቺ ጋር ነኝ፡፡ አንድ ሚስጥር ለአንቺና ለኸርት ድዌለርስ አካፍላችኋለሁ። ከእናንተ መለየት አልፈልግም፡፡ ወደ እኔ ስትመጡ ተጐድታችሁ እንደምትመጡ ባውቅም እንኳን ሥራ ሲበዛባችሁ  የአለምን ሞኝነቶች እስክትተው ድረስ በጭንቀት እጠብቃችኋለሁ።

"ውዴ አንቺ ውስጥ እኖራለሁ፡፡ በበቂ ሁኔታ ልብሽን ብታረጋጊው እኔ ጎልቼ እወጣለሁ። ከሁሉም ስሜቶችሽ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መጥፋት ለእኔ ያልተለመደ ነገር ነው። ይህ የሚሆነው ኃጥያት ስትሰሪ ነው። ያን ጊዜ ነው የመለያየቱ ስሜት በብዛት የሚሰማሽ። በሌላው ጊዜ ግን ሁሌ አብሬሽ ነኝ። ከእኔ ጋር መያያዝ ላይሆንልሽ ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው ጣፋጭ የሆነውን ክፍሌን በጣም ለሚያስፈልገው ነፍስ ስለምሰጥ ነው። ራስሽን ለሌሎች ሳታጉረመርሚ አሳልፈሽ ስትሰጪ በጣም ደስታ ይሰጠኛል። በፈተናዎች መካከል ሆነሽ ስታመሰግኚኝ ደስ ይለኛል፡፡ በዚያን ጊዜ ነው እናቴን የምትመስይው፡፡

"የኔ ውድ የኸርት ድዌለርስ ቤተሰቦች አንዳንዶቻችሁ የገጠሟችሁ እነዚህ ከባድ ፈተናዎች ማለትም መከዳት፣ መተው፣ ድርቀት፣ እነዚህ ሁሉ ለሚሞቱት ትልቅ መስዋዕቶች ናቸው፡፡ በተለይም የኔ ውዶች በእነዚህ ፈተናዎች መካከል ሆናችሁ ዘ ዲቫይን መርሲ ቻፕሌትን ስትፀልዩ ይህ በጣም ከባዱ ሥራ ነው። ስቃይ በጣም ከባድ ሥራ ነው፡፡ ደግሞም የሚታይ ማፅናኛ ወይም ማረጋገጫ አታገኙሉትም። እንዳውም ሌሎች እኔን ባዩበት አመለካከት እናንተንም ያዩአችኋል፡፡ እንዲህም ይላሉ "በጣም ኃጥያተኛና የሐሰት ነብይ ሳይሆን አይቀርም፡፡

“የስምኦንን መስቀል ለመሸከም መፈለግሽና ለእኔ ብለሽ ኃላፊነት በመውሰድ እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ሥራዎችን መሥራትሽ በአገልግሎት ዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጠው ነው፡፡ እንዳውም ሰዎች የሚመለከቱሽ  የተጎዳሽ፣ ምስኪን ደሃ

በመሆንሽ ለትንንሽ መንፈሳዊ ሥራዎች ብቻ ብቁ እንደሆንሽ አድርገው ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ፀሎት በሰዎች ዕይታ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጠው ቢሆንም በመንግስተ ሰማይ ግን ራስ ወዳድነት የሌለበት መስዋዕት በመሆኑ ሁሉንም የሚያስደስት ጉዳይ ነው፡፡

"እንዲህ ዝቅተኛ ተደርጋችሁ ብትቆጠሩም እያንዳንዱ የተጨበጨበለት መጋቢ ቅባቱንና ኃይሉን የሚያገኘው በእናንተ ፀሎት አማካኝነት ነው። የተደበቁትና ራስ ወዳድ ያልሆኑት በፀሎት ክፍላቸው በመሆን ለኃጥያተኞች በማልቀስ፣ ለእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ቅባት እንዲመጣላቸው ይፀልያሉ። ይህንን ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ነግሬያችኋለሁ፡፡ በሰማያት የእናንተ ሽልማት ከታዋቂዎቹ ይበልጣል፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በክብር ከፍ ብለው መቆም የቻሉት በእናንተ ጀርባ ላይ ስለሆነ ነው።

ክሌር ፡- ጌታ መጠየቅ እችላለሁ?

ኢየሱስ፡- አዎ ትችያለሽ"

ጌታ እስቲ እባክህ ንገረኝ፡፡ ግራ በመጋባት ዝም ብዬ ዙሪያዬን ስዞር፣ ከጥሩ ነገር ሁሉ ተራርቄ ፣ በራሴ ጥፋትና ስህተቶች ውስጥ ስዋኝ፣ ለመፀለይ እየሞከርኩ ነገር ግን ካንገት በላይ ሆኖ ሲሰማኝ ፣ ፀሎቶቼ ጥልቀት የሌላቸውና የማይጠቅሙ ሲመስለኝ . .

(ኢየሱስ) "እሺ"

ብቁ ያልሆንኩና ፍፁም የወደቅሁ፣ ከእኔ ምንም ጥሩ ነገር ሊገኝ አይችልም የሚል ስሜት ሲሰማኝና ራሴን እንደዛ ስመለከት፣ በጐቹን በትክክለኛው መንገድ አልመራኋቸው ይሆናል ብዬ ስርበተበት ፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር መንግስት የእውነት ኪሳራ እንደሆንኩ ራሴን ስቆጥር . . . ጌታ እባክህ ንገረኝ ከነዚህ ስሜቶች የሚመነጭ ጥሩ ነገር ይኖር ይሆን?

(ኢየሱስ) "ክሌር ራስሽን በትክክል እንደሆንሽው ስትመለከችው፣ በጭቃው ረግረጋማ ቦታ እስከነቆሻሻው ተቀምጠሽ ፣ የሞትና የኃጥያትን መጥፎ ጠረን እያሸተትሽ፣ በወቀሳ እንደተዋጥሽ ሲሰማሽ፣ እኔን ለመፈለግ እንኳን ራስሽን ቀና ማድረግ ሲያቅትሽ፣ በዚያን ጊዜ ነው ራስሽን እጅግ ዝቅ አድርገሽ የምታይውና በእኔ ዕይታ ግን አስደሳች የምትሆኚው፡፡ ነገራቸውን የሚያውቁ ነፍሳት ለማየት እራባላሁ ደግሞም እጠማለሁ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ራሳቸውን ለውድቀት በመዳረጋቸው መቋቋም ያቃታቸውና በዙሪያቸው ከከበባቸው ሞት ለማምለጥ ከልባቸው የሚፈልጉ ነፍሳት ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ከጠላት እቅድና ስልት ለማምለጥ የምትችሉት፡፡

(ክሌር)፡- እንዲህ ሲሆን ደግሞ በክስ ውስጥ እወድቃለሁ።

"በራስሽ ውስጥ ሊወቀስ የሚገባ ነገር እንዳለ ማየትሽ ጥሩ ነው። ምክንያቱም የእኔን ምህረት በበለጠ እንድትፈልጊ ያደርግሻል፡፡ ያን ጊዜ ነው ላጥብሽና የአለምን ሁሉ ቆሻሻ ከነፍስሽ ላይ በመጥረግ በቅባቴና በአዲስ ህይወት የምሞላሽ፡፡

"እጅግ ጠቃሚ ጥያቄ ጠይቀሽኝ እውነተኛ መልስ እየሰጠሁሽ ስለሆነ እባክሽ እመኚኝ። በነዚያ ጊዜያቶች የተሰቃየሽው ስቃይ ዝቅ እንድትይ ስላደረገሽ የኔን ቅባት ለማቆር በቂ ነው፡፡ ምክንያቱም የኔ ቅባት የሚጠራቀመው እንደዚህ ዝቅ ባለ ሥፍራ ስለሆነ ነው፡፡ የራስሽን ፍፁም ከንቱነት ስትመለከቺ በአንፃሩ ምርጡን ቅባት ለመቀበል ዝግጁ ትሆኛለሽ። ክሌር ምንም ነገር ሳታስቀሪ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለኔ ተናዘዢ። ሳትናዘዢ የሚቀር ነገር ምንም እንዳይኖር፡፡ ሁሉንም ከተናዘዝሽ በኋላም

ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳጥብሽ ጠይቂኝ፡፡ የኔ አሳዛኝ አትፍሪ፡፡ በፍላጐትሽ ጥልቀት ልክ ነው ለበጐቹ የሚፈሰውን የህይወት ውሃዎች ልሞላሽ በፍጥነት የምመጣው። በዚህ ቦታ ነው ምንጮቹ ወደ ሃይቅ ሃይቆቹ ደግሞ ንፁህ ወደሆኑ ወንዞች የሚቀየሩት።

"ይህንን አላልኩምን ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ" ትንቢተ ኢሳይያስ 66፡2

"በጣም እወድሻለሁ፡፡ መዋረድሽን አትጥዪው፡፡ መተዉሽን አትጥዪው፡፡ መከዳትሽንም አትጥይው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ የበለጠ እኔን እየመሰልሽ ትሄጃለሽ። የጐዱሽን ሰዎች በፍቅርና በርህራሄ ብቻ ሰላም በያቸው፡፡ ምክንያቱም የሚያደርጉትን አያውቁምና ለእነርሱ የምትፀልይው ፀሎት ጉልበት አለው፡፡ ጎንሽን የሚወጋውን ስለት፣ ጀርባሽን የሚቆርጠውን ቢላዋና ልብሽ ውስጥ የሚሰነቀረውን ጉራዴ ሁሉ ሳሚው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ እኔን እንድትመስዪ የሚያደርጉሽ መሳሪያዎች ናቸው። ሳሚያቸው፣ ባርኪያቸውና ይቅር በያቸው። አንቺ የእኔ ሙሽራ አሁን የእኔን ስቃይ የሚመስል የማይጠፋ ምልክት ይዘሻልና፡፡ ያቆሰሉሽን ሁሉ በፍቅርሽ ጣፋጭነት አክብሪያቸው። በሂደት የኔ ቅባት ወደ ሙላት ከፍ እንዲሉ ይደግፋቸውና የአንቺም ልብ በእኔ መልካምነት ደስ ይሰኛል።

"አሁን ሂጂና ይህንን ለእህቶችሽና ለወንድሞችሽ አካፍያቸው። ይህንን ለመስማት የሚያስፈልጋቸው ብዙዎች አሉ ፡፡ በእውነቱ ከሆነ በዚህ ሳምንት በሁኔታዎች እየተሰቃዩ ያሉ ስላሉ በዚህ ከባድ ሥራቸውና መከራቸው የሚመጣውን ጥሩ ነገር ማወቅ አለባቸው፡፡ ታማኞቼ አሁን ለነፍሳቸው መልካም እንዲሆንላቸው ጠላቶቻችሁን ይቅር ማለት የምትችሉበትና በልባችሁ ልትሸከሙ በምትችሉበት ፀጋ ባረኳችሁ። ይህንን ፀጋ ተቀበሉና ጠብቁት ወደ ተግባርም ቀይሩት፡፡ በእውነትም የህይወት ውኃ ነው የሞተ ህሊና ያላቸውን እንደገና ማስነሳት የሚችለው።"

"እባርካችኋለሁ፡፡ ደግሞም ለመንግስቴ ብቁ የሆነ የተመረጠ ነፍስ መሆናችሁን በሚያሳይ ምልክት ግንባራችሁን እስማችኋለሁ።"

## የህይወት ፈተናዎች - ኤፕሪል 17 ቀን 2020 ዓ.ም

## The trial of life, April 17, 2020

(ክሌር) ውድ ቤተሰቦች ሰሞኑን ጥሩ ምሳሌ እንዳልነበርኩ ለእናንተ መናዘዝ እፈልጋለሁ፡፡ በቅርብ ወደ ተጠናቀቀው ተራራማው መሸሸጊያ ቤታችን ልንገባ እየተዘጋጀን ነው፡፡ አንዳንዴ ቤት እንደመለወጥ ፈታኝና ራስን የሚያዞር ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ እቃዎቹን ለመውሰድ እንዲመቹ መነቃቀል ፣ ማሸግ፣ ወደ ሻንጣ ማስገባት እንደገና የታሸገውን መፍታት፣ በሻንጣ የተከተተውን ማውጣት በድጋሚ በየቦታው ማስቀመጥ የሚፈጠረው ድካም ትዕግስት የሌለውን ሰው ለኃጥያት ይጋብዛል፡፡

አዎ እኔ ትዕግስት የሌለኝ ሰው ነኝ፡፡ ሰዎች መስራት ያለባቸውን ትተው ሰማይ ሰማይ ሲመለከቱ ባገኝ ብዙም ጥሩ ሰው አልሆንም። ይህንን በውጪ ላላሳየው እችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ውስጤ በትዕግስት ማጣት ትክን ይላል። ሌላው ለኃጢያት ምክንያት የሚሆንብኝ ነገር ደግሞ ከሌሎች የተሻለ ችሎታና ነገሮችን በብቃት ማድረግ የምችል ይመስል! ሰዎች ነገሮችን ለማድረግ ችሎታ ሲያጡና እንደሚገባው ማድረግ ሲያቅታቸው ነው፡፡

ይህ ነገር ለመላእክቶችና ለሰማይ ቅዱሳን ይህም በዙሪያችን ላሉ ምስክሮች መጥፎ ጠረን ያለው እንከን በመሆኑ ንሰሐ ልገባ ግድ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በልቤ ስለፈረድኩ መራራ ዘርን በውስጤ ተክያለሁ።

በሌሎች ሰዎች ስትበሳጩ ምን እንደሚፈጠር ታውቃላችሁ? ኢጋንንት የመራራ መንፈስን በመምሰል በልባችን ውስጥ መኖር ይጀምራል፡፡ በእርግጠኝነት ደግሞ ብስጭት በተከሰተ ቁጥር ተጨማሪ ዘሮችን እየተከላችሁና ውኃ እያጠጣችሁ ነው። መፍረድ፣ መራራነት፣ ንዴት፣ ቅሬታና የመሳሰሉት ሁሉ በኩራተኛው ልቤ ውስጥ የሚያቆጠቁጡ መርዛማ አረም ናቸው። እነዚህ ልክ እንደሰናፍጭ ፍሬ ናቸው፡፡ በትንሽ መተላለፎች በመጀመር፣ አብቦ ቅርንጫፍ በማውጣት ትልልቅ ዛፎችን ያበቅልና ለአጋንንት ማረፊያ ይሆናል፡፡

አጋንንቶችም የሚያርፉበት ቅርንጫፍ ካገኙ በኋላ መጥፎ ስሜቶቻችሁን በመመገብ መርዛማ ነገሮችን ይለቁባችኋል። ሪክ ጆይነር ስለዚህ ጉዳይ በመጽሐፉ ሲፅፍ "ሰይጣን መጥፎ ኩሱን ክርስቲያኖች ላይ በመጣል ክርስቲያኖችን የወንድማማች ፍቅርን ረስተው በሌሎች ላይ እንዲፈርዱ ያደርጓቸዋል" ብሏል፡፡

ለመናደድ ብዙ ጊዜ ይፈጅብኛል፡፡ ስናደድ ግን መላ ሰውነቴ ይጐዳል ፣ ከሰውነቴ ጉልበቴ ሁሉ ይሟጠጥና አጋንንቶቹ ያጭዱታል። ከዛም እነርሱ በተራቸው ደግሞ ውደቱን በመደጋገም በዙሪያዬ ያባዙታል፡፡ በፊት በፊት መናደዴ ትክክል እንደሆነ ለማረጋገጥ እጥር ነበር፡፡ "ችግራቸው ምንድነው? ለምን በዚያ መልክ አደረጉት" ወይንም እኔ በነገርኳቸው መንገድ ካልሰሩት ደግሞ "እንዴት መስራት እንዳለባቸው ነግሬያቸው እያለ ለምን አላዳመጡኝም? እላለሁ፡፡ እናም አሁን ተመልከቱ ማስተካከል ያለብኝን ችግሮች!!!" በማለት ንዴቴን ምክንያት እፈጥርለት ነበር፡፡

ወይንም ደግሞ ንዴቴን በውስጤ እይዘውና ለእራሴ ማዘን እጀምራለሁ፡፡ 'እኔን ማንም አይሰማኝም። ልረዳቸው ሞክሬ ነበር ግን አይሰሙኝም።' ይህ ደግሞ ለራስ እንዳዝን የሚያደርገኝ በቅርጣን የተሞላ በርሜል ውስጥ ይከተኝ ነበር፡፡ ይህም እኔ ለራሴ ምን ያህል ቆሻሻ እንደሆንኩ እስክገነዘብ ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር በሰዎች ላይ ፈራጅና በቅሬታ የተሞላሁ ስነበርኩ ማንም አያዳምጠኝም ነበር፡፡ ከነዚያ ቀናት እስከዛሬ ድረስ ግን ብዙ ነገሮች ተቀይረዋል። ለዚህም ዋናው ምክንያቱ በሰዎች ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየት ስጀምር የራሴን ድክመቶች መረዳት ስለቻልኩ ነው። በመጀመያ ላይ የሰዎችን መልካም ነገር ማየት አልችልም ነበር፡፡ ሆኖም እያወኳቸው በሄድኩ ቁጥር እነሱ ከእኔ እጅግ፣ እጅግ የተሻሉ ሰዎች መሆናቸውን መገንዘብ ቻልኩ።

በተጨማሪም ጌታ የንዴቴ ዋናውን መንስኤ በማሳየት ከላዬ ላይ ጭምብሉን ገፈፈልኝ፡፡ የኔ ውዶች ሁሉም ሰወኛ የሆነው ንዴታችን፣ ከከፍተኛ በደል የተነሳ ካልሆነ በቀር፤ ተቃውሞዎቻችን በሙሉ እና ከባድ ማስተዋሎቻችን ሁሉ ከኩራት የመነጩ ናቸው። ይህም እኔ የተሻለ ስለማውቅ በኔ መንገድ ብቻ ሥሩት የሚል ኩራት፡፡ በቀላሉ አነጋገር ብስጭታችን የሚያተኩረው በሌሎች ችሎታ አለመኖር ላይ ሳይሆን የሌሎችን ችሎታ ማነስ የፈቀደው አምላክ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ አንዳችም ነገር ስለማይሆን ነው፡፡ ይህንን ሞኝነት ለምን ሌሎች ላይ ፈቀደ ? ይህንን የፈቀደው ምናልባት በወንድማማች ፍቅር ሊፈትነኝ ፈልጐ ይሆን? በመላዕክቶቹ ፊት ኩራትን የሚያህል መጥፎ ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ነፍስ ፀባይ ስለሚያውቅ ቀናችንን ያዘጋጅል፡፡ ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን ያውቃል። ነፍሳትን በእኛ ፊት ያመጣቸውና በሥራዎቻቸው እንፈርድባቸዋለን ወይንስ እርሱ ከነስህተቶቻችን እንደወደደን እነርሱንም እንወዳቸዋለን የሚለውን ያይበታል።

ይህንን ሳምንት አጠገቤ ባሉት ሰዎች ሁሉ ላይ ትዕግስት አጥቼ ስለነበር መጥፎ ምሳሌ ሆኜ ነበር። እነዚህ ነፍሶች ደግሞ እግዚአብሔር እየመራን መሆኑን ስላመኑ ህይወታቸውን ለጌታ አሳልፈው በመስጠት ሁሉን ነገራቸውን ትተው የፀሎት ማህበረሰብ ለመመስረት ሊረዱን የመጡ ናቸው።   ታዲያ እኔ ችግሮችን ብቻ የምፈልግ መራራ ተቺ መሆን አለብኝ? በልቤስ ውስጥ በካይ የሆኑ ፍርዶችን  በዝርዝር ማስቀመጥ አለብኝ? ለዚህ ነው እዚህ ያለሁት? ጌታ እባክህ ቀይረኝ፡፡ ምን እየሰራሁ እንዳለሁ ለመገንዘብ እንድችል እርዳኝ።

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . የኔ ውድ በእንደዚህ ሁኔታ ቀን ተቀን እየኖርሽ ያለሽው ምን ሥራ እየተሰራ እንደሆነ እንጂ በሌሎች ነፍሳት ውስጥ እየሰራሁ ያለሁት ነገር ላይ አይደለም። እኔ ከሙሽራዬ ማየት የምፈልገው ስለሌሎች ደህንነት የምትጨነቅ እናትን እንጂ ስለሚሰራው ነገር የበለጠ የምትጨነቅ መሆንዋን አይደለም፡፡ ከሰውኛ ፍላጎቶች የበለጠ እንድትመለከቺ የምፈልገው ነፍሳት ያሉበትን ሁኔታ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ፍላጎት ከሰው ነፍስ ደህንነት አይበልጥምና፡፡ በዛ ነፍስ ውስጥ ምን እየተካሄደ ነው? እንዴት ነው ልታፅናኛቸው የምትችይው? በምን መልኩ ነው በማበረታታት ወደ እኔ እንዲቀርቡ የምታደርጊው?”

“አንድን ሥራ ለማሳካት ብዙ መንገዶች ይኖራሉ።  እናም ሥራውን ብቃት ሳላቸው ሰዎች በራሳቸው መንገድ  እንዲሰሩት አሳልፈሽ ስትሰጪ በአሰራርሽ ላይ ጥበብን አያለሁ። ነገር ግን እያንዳንዱ ነፍስ ውጫዊና ውስጣዊ ማንነት አለው። ስለዚህም ከውስጥ ያለው ማንነታቸው በምን ሁኔታ ላይ እንደሆነና በውስጣቸው ምን እየተካሄደ እንደሆነ መታየት አለበት። ጥርጣሬዎቻቸው ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደምታፅናኚያቸውና እንደምትወጂያቸው፣ይህም እኔ አንቺን በወደድኩበትና ባፅናናሁበት ልክ መሆን ይገባዋል፡፡ ለነፍስ እጅግ አስፈላጊው ነገር በውስጡ ማበቡና ማደጉ ነው፡፡  ይህንን ደግሞ አንቺ ልትረጂ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በውስጥ ስትሽማቀቂና ያልሆነ ገፅታ ስትይዢ ትጠወልጊያለሽና።

"የራስ ፍላጎት፣ ለራስ ማዘን፣ ራስ ወዳድነት፣ እኔ፣ እኔ፣ እኔ የሚሉ አመለካከቶች ሰዎች ስለሚያደርጉት ነገር በእኔ ዕይታ አንፃር እንዳይመለከቱ ያደርጋቸዋል። ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ከተወሳሰቡ ከእነሱ ጋር በማይስማማ መልኩ የተደረጉ ነገሮች ሁሉ ተናገሩትም አልተናገሩትም ግሰፃ ስለሚሆን ያንን ነፍስ ያደክማል፡፡ በማህበረሰብ ውስጥ የተነገሩም ይሆኑ ያልተነገሩ የሌሎች ሰዎች ኃጥያቶችና ሽክሞች ለእናንተ ይሰማችኋል፡፡ ከጀርባችሁ የተፈረደው ፍርድ ይሰማችኋል፡፡ የሌሎችን ጥላቻና በራሳቸው ሚዛን ግፍ ተፈፅሟል የሚሉትን ስሜታቸውን ትረዳላችሁ። እናት እንደመሆንሽ መጠን እነዚህን ነገሮች በለዘበ መልኩ እንድትፈቺው እፈልጋለሁ፡፡ እነርሱ እዚህ የተገኙት በሌላው የህይወት አቅጣጫቸው ውጤታማ ስላልሆኑ ነው፡፡ አንቺ ደግሞ ከእኔ ጋር እዚህ እየሰራሽ ያለሽው እነሱን ሙሉ ለማድረግ ነው።”

"እነርሱ የራሳቸው ኩራትና ራስ ወዳድነት አይታያቸውም፡፡ የሚታያቸው የሌሎች ስህተት ብቻ ነው። ይህች ነፍስ ከየት እንደመጣች? ምን ያህል መከራን እንዳለፈች እና እኔ ወዴት እየወሰድኳት እንደሆነ አያጤኑም። እነርሱ የሚያዩት መታረም እንደሚያስፈልጋቸውና ነገሮችን መሰራት ያለባቸው እነርሱ መሰራት አለበት ብለው ባመኑት መልክ መስራት እንዳለባቸው ነው።

“እነርሱ ስኬታቸው ልባቸውን ከመገበው ከመርዛማው የኩራት ኃይቅ ላይ እየቀዱ ናቸው። ይህ ደግሞ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሁሉ በጥላቻና ፍርድ በመስጠት የሚገለፅ ነው። ራሳቸውን የሚያዩት እንደ አዳኝ እንጂ ለሰይጣን ቁጣና ፍርድ ማስፈፀሚያ መዋላቸውን አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ በመጨረሻው ለስላሳ የሆኑትን ነፍሳት ያጠፋል።

"ታዲያ ለዚህ መፍትሄው ምንድነው? አንድ ሰው አንድን ነገር በተሳሳተ መልኩ ስለሰራ አፀይፎሻል? የኔ ውድ ያለፈውን እስኪ ተመልከቺ፡፡ መቼ ነበር አንድን ነገር በተሳሳተ መልኩ በመስራትሽ ሌሎች ላይ ስራን የጨመርሽባቸው? አንድን ጊዜ አስታወስሽ ? መልካም ሌላም ፈልጊ። የማስታወስ ብቃትሽ ጥሩ ከሆነ አስታውሺ። ባለማወቅሽ የተነሳ ለሌሎች ችግር የፈጠርሽባቸውን ቢያንስ ከ3 እስከ 7 ጊዜ ታገኛለሽ ።

“ሌሎች ስላልገባቸው ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም? የድሮውን አስታውሺ ያለመድሽው አካባቢ ራስሽን አግኝተሽው ሌላ ሰው ማድረግ ያለብሽን እስኪነግርሽ ድረስ ደደብ መስለሽ የቆምሽበትን ጊዜ አስታውሺ፡፡ ሌሎች ሥራቸውን እየሰሩ እያሉ አንቺ በህይወትሽ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ስንት ጊዜያት አሳልፈሻል? ሦስት ጊዜ? በጥልቀት አስቢ።

"በእህቶችና በወንድሞች ስህተት ስታገኙ በእያንዳንዱ ወቅት እነዚህን ልምምዶች ተለማመዱት፡፡ ይህ ደግሞ ፈውሳችሁን ፈጥኖ ያመጣላችኋል። በሰው በተናደዳችሁ ቁጥር በትኩረት ወደ ውስጣችሁ በመመልከት እናንተም ይህንኑ ስህተት የፈፀማችሁበትን ጊዜ አስታውሱ፡፡

“ሌላው ነገር ደግሞ አንዳንዶች ወደ መጠለያው ሲመጡ የላቀ እውቀታቸውንና ሙያዊ ችሎታቸውን ለማሻሻል በማሰብ ይመጣሉ። እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ እጅግ ብሩህ የሆኑና ብዙ ነገሮችን በአለም ደረጃ ያሳኩ ናቸው፡፡ በአካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች ስህተት በደንብ ስለሚያውቁና በዚህ አንፃር መርዳት ቢፈልጉም ከሰው ጋር ያላቸው ግንኙነት የተንኮታኮተ ነው፡፡ ስለዚህም በማህበረሰቡ መካከል መኖር ይከብዳቸዋል። እናም ሁኔታው በመገለል ያበቃል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የሚፈልጉት መወደድን እንጂ ያለባቸውን ችግር እንዲነገራቸው አይደለምና ነው፡፡"

(ክሌር)፦ በየጠዋቱ ወደ ጌታ ስቀርብ ጌታ የሰራኋቸውን ስህተቶች ዝርዝር ይዞ አይደለም ወደ እኔ የሚመጣው፡፡ እርሱ የሚመጣው በቃ ሰላም ሊለኝ፣ ሊያቅፈኝ፣ ሳመልከውና ልመናዎቼን ሳዘንብለት ሊያደምጠኝ ነው የሚፈልገው፡፡

ሁሉም ባይሆን ብዙ ስህተቶች እንዳሉብኝ እኔ ራሴ አውቃለሁ። በእውነቱ ከሆነ የማልወደድ እንደሆንኩ እስኪሰማኝ ድረስ አፍሬ ከጌታ የምሸሽበት፣ አንገቴን እንድደፋ የሚያደርጉኝ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በእነዚህም ስህተቶቼ ሁሉ ራሴን አውግዤዋለሁ፡፡ ታዲያ አንድ እህት ወይም አንድ ወንድም ምን ያህል ተሰባሪና ደካማ መሆኔን በእርግጥ እንደገና እንዲነግሩኝ እፈልጋለሁ? ጌታስ ስለ እኔ ስህተቶች ዝርዝር እንዲነግረኝ እፈልጋለሁ? ይህንን ወይንም ያንን እንዴት በተሻለ መልኩ መስራት እንደምችልስ እንዲነግሩኝ እፈልግ ይሆን?

እራሴን ከመረመርኩበት ጨካኝ መንገድ መፈወስ እንዳለብኝ ጌታ በደንብ አድርጎ ያውቃል፡፡ አንዳንዶቹ ነገሮች እኔ ልፈፅማቸው የምችላቸው ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ለማሸነፍ ደካማ የሆንኩባቸው ናቸው። እናም በእነዚህ ነገሮች ከልቤ አፍራለሁ። ታዲያ ጌታ ስለእነዚህ ነገሮቼ እንደገና እንዲነግረኝ እፈልጋለሁ? ወይንስ የምፈልገው መወደድን፣ መፅናናትንና፣ መበረታታትንና ድጋሜ እንድነሳ የሚረዳኝን ፀጋ ማግኘትን? ምክንያቱም በራስ መተማመኔን ሲመለስልኝ ልቤ የመንፈስ ቅዱስን ሹክሹክታ ለመስማት ክፍት ይሆንና ለሚቀጥለው በተሻለ ሁኔታ ለመሥራት እበረታታለሁና ነው፡፡

ኸርት ድዌለርስ የተለዩ የአማኝ ቡድኖች ናቸው። ምክንያቱም የምንኖረው ፍቅር በሆነው በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ነው፡፡ ይህም ፍቅር በሁኔታዎች የማይለዋወጥ ፍቅርና ማበረታታት ተሞላበት ነው፡፡ ስህተቶቻችንን በደንብ እናውቃቸዋለን ነገር

ግን ደግሞ በእርሱ እግር ሥር ጥለናቸው ለመፈወስ እንፀልያለን፡፡ ስለዚህ ከማህበረሰቡ መካከል አንድ ሰው መጥቶ ስለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ነግሮኝ እንዲያስተካክልልኝ እፈልጋለሁ?

አይ አልፈልግም፡፡ በእኔ ላይ የሚሰጡት ፍርድ እንዳውም የባሰ አውዳሚ ነው። ህይወቴን እንዴት እንዳሳለፍኩ፣ አሁን ያለሁበት ለመድረስ ምን መወጣት እንደነበረብኝ፣ ምን ምን ነገሮች በራሴ የማይሸነፉ እንደሆኑ አያውቁም። እነሱ የሚያዩት ሥራዎችን እንዴት በተሻለ መልኩ ሊሰሩት እንደሚችሉና ያንንም እንዴት እንደሚሰራ ለእኔ ለማሳየት ነው። የተወደዳችሁ ይህ የእኔ ሥራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራ ነው። አዲስ ነፍስ ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀል እኔ ለእነሱ አለሁላቸው፡፡ ስላሳለፍኳቸው ፈተናዎች አንዳንድ ነገሮችን ላጋራቸው እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም እነርሱም በዚያው ጉዳይ ዙሪያ እየተቸገሩ ስለሆነ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ ይህንን እንደሚያውቁ ፈጣን የማረጋገጫ መልስ ይሰጡኛል፡፡ ግን አይገርምም እነዚህ ነፍሳት ብርጭቋቸውን በራሳቸው መፍትሄዎች ከመሙላታቸው የተነሳ እኔ ምንም ልሰጣቸው አለመቻሌ? እነርሱ የራሳቸውን ስህተቶች አሸንፈው ስለጨረሱ ለእኔ ስህተቶች መፍትሄ ሊሰጡኝ ነው፡፡ ይህ የሚያስቀኝ ጉዳይ ነው፡፡ ለምን ?? ምክንያቱም የእኔ ስህተቶች ከመብዛታቸው የተነሳ እግዚአብሔር እንኳን አስተካክሎ አልጨረሳቸውም፡፡ እናም ይኸውላችሁ አንድ ሟች ሰው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሲሞክር?? በሁሉም ነገር እኛ እንልቃለን ብለው በእውነት የሚያምኑና እኛን ለማስተካከል ሙሉ ብቃት አለን የሚሉ ነፍሳት በዚህ ነበሩ። በዚህ መሳቅ አለብኝ፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ብቃት ለውጡን ካላመጣ እናንተ የምትችሉ ይመስላችኋል?

እውነቱ እግዚአብሔር በሁላችንም ላይ ሁልጊዜ እየሰራ ነው፡፡ ሁላችንንም በድስት በሚፍለቀለቅ ውኃ ውስጥ አንድ ላይ አስቀምጦን ቆሻሻው እስኪወጣ እየጠበቀ ነው፡፡ ፈተናው ግን ቆሻሻውንና ንፁህ ያልሆነውን ነገር እንደሌለ በመቁጠር ያንን ነፍስ መዉደድ መቻል ላይ ነው። እራሳችሁን መርዳት ካቃታችሁ ማድረግ ያለባችሁ በእነሱ ስህተቶች ላይ መተከዙን በመተው መፀለይና እናንተ ይህንኑ ስህተት የሰራችሁበትን ጊዜ በቅንነት ማስታወስ ነው። እውነቱን ለመናገር ወንድማችሁ ላይ ያያችሁት ስህተት ከሶስት አንዱን ሊሆን ይችላል፡፡ ጌታ ቢገልፅላችሁ እንድትወድቁ የሚያደርጓችሁን ስህተቶች ብንተዋቸው እንኳን እናንተ ማሸነፍ ያቃታችሁ ሃያ ስህተቶች ሊኖራባችሁ ይችላል፡፡ በእርግጠኝነት ትልቁ ኃጢያት ኩራት ሲሆን ከሁሉም የገዘፈው ነው፡፡ ስለዚህም ለእነዚህ ስህተቶቻቸው ፀልዩ፡፡ በተለይም ደግሞ ለራሳችሁም በከባዱ ፀልዩ፡፡ ምክንያቱም ኩራት የሰይጣን ኃጥያት ነበር፡፡ እናም ኩራት ያ ነፍስ ሊያደርግ የሚሞክረውን ነገር ሁሉ ያበላሻል።

ኩራት ይበትናል፣ ይከፋፍላል ፣ መገለልን ያመጣል፣ ሙብትን ይጠይቃል፣ ለራስ ማዘን ውስጥ ይከታል ከሌሎች የተሻለ አውቃለሁ ያሰኛል፣ እናም ለመማር ዝግጁ አያደርግም። በአንፃሩ የብዙ ስህተቶች ባለቤት የሆነው ምስኪን ነፍስ ግን በሚገባ የሚማርና ሌሎች በዚህ ጉዳይ ሊወድቁ ይችላሉ ብሎ ዝቅ የማያደርግ ነፍስ ሊሆን ይችላል። የተወደዳችሁ እንዳውም ማድረግ ያለባችሁ ሌሎችን ከራሳችሁ የተሻሉ አድርጋችሁ ማየት ነው፡፡ በዚህ እውነታ ራሳችሁን ብታሳምኑት የቅድስና ጣራ ትደርሳላችሁ።

የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረን በአለም ስኬታማ እንድንሆን ፣ በስኬቶቻችን ራሳችንን ቀና አድርገን እንድንሄድና የሌሎችን ስህተት አጥብቀን በመመርመር በልባቸው ፍርድ እንዲያስተላልፉ ማድረግን ነው፡፡

ኢየሱስ የሚያስተምረን ግን ራሳችንን እንደምንወድ ያህል እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ነው፡፡ በሰው ፊት ምንም ያህል ከበሬታ ቢኖረንም ሌሎች ከእኛ በእውነት እንደሚሻሉ እንድንረዳ ይፈልጋል፡፡ ሌሎች ሊጨምሩበት የሚችል ባዶ ብርጭቆን ይዘን ለመማር የተዘጋጀን ሆንን እንድንቀርብ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር መሪን ወደ አዘጋጀበት ሥፍራ ልትመጡ ትችላላችሁ፡፡ ቢሆንም ግን የያዛችሁት ብርጭቆ የሞላና እየፈሰሰ ከሆነ መማር አትችሉም፡፡ ከዚህም የተነሳ ቦታው ቶሎ ይሰለቻችሁና ስትመጡ ከነበራችሁበት ሁኔታ የባሰ ሆናችሁ ከዛ ቦታ ትሄዳላችሁ፡፡ ይህንን ብዙ ጊዜ አይቻለሁ፡፡ ጌታ መድሃኒቱን ይሰጠናል ነገር ግን ነፍሳት አፋቸውን ከፍተው መድሃኒቱን አይውጡትም። እነሱ የሚያምኑት በእግዚአብሔር ምሪት ራሳቸውን አሸንፈው እንደጨረሱ ነው።

እግዚአብሔር ሊያሳያቸው የፈለገውን ነገር ምናልባት ከዚህ በፊት በተረዱት መንገድ ሳይሆን በሌላ ዕይታ እንዲያዩት ለማድረግ እንደሆነ ለማመን ተስኗቸዋል። እዚህ ከሚመጡት ነፍሳት ብዙ ተምሬያለሁ። ነገር ግን የበለጠ የተማርኩት ዝም በማለት ጥግ ከሚቆሙት ትንንሽ ነፍሳት ነው፡፡ የመጣሁት ከአለም ስኬታማ ከሚባለው የፎቶግራፍ ሙያ ስለሆነ በመንገዱ ሁሉ መሆን የማልፈልጋቸውን ብዙ ነገሮችን አስተምሮኛል። በእውነት ቅን፣ ትሁት፣ ሰላማዊ፣ መማር የሚፈልጉና የወንድማቸውን ስህተት ትኩረት የማይሰጡ ነፍሳት ሲመጡ ሚስጥራቸውን ለማወቅ እራባላሁ፣ እጠማለሁ። እናም በሁሉም ድርጊታቸው የምመለከተው ወንጌል ህይወት ዘርቶ ነው፡፡

5 የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።6 ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና። 7 የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና። 8 ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና። 9 የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። (ማቴዎስ 5፡5-9)

ደግሞም አይፈርዱም፣ ተቃውሞም አያስነሱም፣ ስህተቶችን በመፈለግ የሌሎችን ችግሮች ለማስተካከል አይሞክሩም፡፡ የራሳቸው ኃጥያት የሌሎችን ደግነት እንደሚጋርዳባቸው ስለሚያውቁ ሌሎቹን ከእነ ስህተቶቻቸው ይቀበሏቸዋል።

ልጆች እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ወደ መጠለያው ስትመጡ ሌሎችን ለማስተካከል በሚፈልግ ልምድ አትምጡ፡፡ እንዳውም ጌታ እናንተን የወደዳችሁን ያህል ሌሎችን ለመውደድ በሚል አጀንዳ ኑ። እኔም ጌታ እንድሆን ለጠራኝ እናትነት ብቁ ለመሆን እንድችል ፀልዩልኝ።

## ወደ ልቤ ለመግባት ቁልፉን እወቁ - ኤፕሪል 23 ቀን 2020 ዓ.ም

## Innocence, the Key to My Heart, April 23, 2020

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "በየቀኑ እኔን ለማግኘት ትንሽ ጥረት ብታደርጉ የማጫውታችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፡፡ ትንሿ ቤታችሁ እጅግ ቆንጆና ለሁለታችሁ ተስማሚ ነች፡፡ ሁሉ ነገር በትንሹ ሲሆን ጥሩ ነው፡፡ እናም በቤታችሁ የሚገኘውን የማያስፈልጋችሁን ነገር አስወግዱ፡፡ እኔም በዚህ አንፃር እረዳችኋለሁ፡፡"

ጌታ አመሰግንሃለሁ፡፡ እርዳታ እንደሚያስፈልገኝ አውቃለሁ፡፡

(ኢየሱስ)፡- "የኔ ውድ ክሌር አቀባበልሽንና ምስጋናሽን እንዴት ናፍቄው ነበር፡፡ በዚህ ማለዳ ስላመሰገንሽኝ ጥሩ አደረገሻል፡፡ ይህ ለሁለታችንም እጅግ መልካም ነገር ነው፡፡ ከአንቺ ጋር መሆን እጅግ ደስ ይለኛል፡፡ ምስጋናሽ ደግሞ ለግንኙነታችን እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ከአንቺ ጋር ሁልጊዜ መገኘቴን የተለመደ አድርገሽ በማሰብሽ ፀፀት ስለተሞላሽ ትክክል ነሽ፡፡ ከእኔ ጋር መለማመድ አንድ ነፍስ እግዚአብሔርን መፍራትና ማክበር እንዲተው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንን ተመራጭና ጥሩ የሆነ እግዚአብሔርን የማክበር ባህርይሽን ጠብቂው፡፡ ኸርት ድዌለርስንም እንዲሁ እንዲያደርጉ አበረታቻቸው፡፡

"ውዶች እኔ የረቀቀ አምልኮ ከእናንተ እንደማልፈልግ ታውቃላችሁ? እኔ የምወደው ከእኔ ጋር ዝም ብላችሁ ቁጭ በማለት የልባችሁን ፍቅር ስታፈሱ ነው፡፡ መዝሙር ለእኔ ያላችሁን ስሜት ሊያነሳሳ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሙዚቃ ሳይኖርም እንዲያው ዝም ብላችሁ ቁጭ ስትሉ ለእኔ ያላችሁን ፍላጎት መልስ መስጠት እችላለሁ፡፡ ይህ ማለት ግን ሙዚቃ ለአምልኮ ሚና የለውም ማለት አይደለም፡፡ ሙዚቃ ልብን በምስጋናና በውዳሴ በመሙላት ወደ አምልኮ ይመራል፡፡

"ውዳሴ እየጨመረ በሄደ መጠን ደግሞ በሁለታችን ያለውም ፍቅር እየጣፈጠ ይሄዳል፡፡ ከአንዳንዶች ጋር በህይወታቸው የምገኘው በመደበኛ መልኩ ነው፡፡ ለሌሎች ደግሞ እጅግ ህፃን በሆነ መልኩ ነው፡፡ ለእነዚህ ለየዋሆች ውድ ቦታ አስቀምጬላቸዋለሁ፡፡ ክሌር አንቺ በሰዎች መንገድ በአለም ተምረሽ ህይወትሽን ከመጣልሽ በስተቀር ልክ እንደ ህፃን ነሽ፡፡

"በልቤ ውስጥ እጅግ የጠለቀ የወዳጅነት ሥፍራ ለንፁህ ነፍሶች ተከልሎላቸዋል፡፡ የኔ ውዶች በዚህ ሥፍራ መገኘት ከፈለጋችሁ የውስጥ ፍላጎታችሁን ንፁህ አድርጉ፡፡ ሰይጣን እናንተን ለመከተት ካዘጋጀው ከሰዎች መሳሪያ ተጠንቀቁ፡፡ እርሱ ወደ እኔ የሚሞከረው በሰዎች መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ እኔ የምትመጡት ከምንም ሁኔታዎች ጋር ሳይገናኝ ለእኔ ካላችሁ ንፁህ ፍቅር ብቻ ወደ ልቤ እንደምትገቡ ካወቃችሁ በእርግጥም እባርካችኋለሁ፡፡

"ይህንን ህፃን ልጅ እንኳን ሊረዳው የሚችል ቀላል ነገር ነው፡፡ እነርሱ ወደ እኔ የሚመለከቱት በቅንና በንፁህ ዓይን ነው፡፡ እነደነዚህ ዓይነቶቹን ወደ እነርሱ አለመምጣት አልችልም፡፡ ወደ ልቤና ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ቁልፉ ንፅህና፣ ቅንነትና የዋህነት ነው፡፡ ወደ እኔ ለምምጣት ሌላ ምንም ተጨማሪ ምክንያት የሌላቸው ከምወዳቸው ልጆቼ መካከል አንዱ ያደርጋችኋል፡፡ ሌሎች ግን የሚመጡት አንድ ነገር ፈልገው ነው፡፡ እነርሱንም ቢሆን ሰምቼ እመልስላቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ታናናሾች እኔን ብቻ በመፈለግ ወደ እኔ ሲቀርቡ ልቤ በኃይል ይመታል፣ ፍቅሬንም ልቋቋመው አልችልም፡፡

"አለም ሁሉ በበሩ ላይ ተሰልፎ እንዲጠብቅ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ለእነዚህ ለታናናሾቼ በየዋሆች በር ሹልክ ብለው እንዲገቡ አደርጋለው፡፡ ይህንን ቤተ ክርስቲያኔ እንዲገባት እንዴት እመኛለሁ፡፡ ወንጌሉ ሲነገር ይህ በተጓዳኝ እንዲነገርና አመለካከታቸውን እንዲፈትሹ ሞክሬያለሁ፡፡ ነገር ግን ዘመናዊቷ ቤተ ክርስቲያን የምታተኩረው በእውቀትና በችሎታ ላይ በመሆኑ ወደ ልቤ የሚያስገባውን ቀጥተኛውን መንገድ ማየት አልቻሉም፡፡

"ኸርት ደዌለርስ እንዲሆኑ የምፈልገው የዋህ፣ እንደ ህፃን፣ ታማኝ፣ አፍቃሪና ከእኔ አንድ ጊዜ መነካትን እንዲናፍቁ ነው፡፡ በእርግጥ ነው ፍጥረታት እንዴት እንደተፈጠሩ ብዙ ጥራዝ እውቀቶችን ላካፍላችሁ እችላለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ የምመርጠው እነዚህ ነገሮች ምንም የማይመስሏቸውና ብቸኛ ፍላጎታቸው እኔን መያዝና ከእኔ ጋር መሆን የሚፈልጉትን የዋሆች፣ እኔን የሚወዱ የህፃናት አፍቃሪ ዓይኖችን ነው፡፡ በቀደመው ጊዜ የሚገቡና የሚወጡ ቢኖሩም የህፃን ዓይነት ነፍሶች የበለጠ ወደ ልቤ ሲገቡ እጅግ የተባረኩ ነኝ፡፡

"ኸርት ዱዌለርስ እንዲሆኑ የምፈልገው እንደ ህፃን ልጅ ለሁሉ ነገር እኔን አምነው ወደ እረፍቴ እንዲገቡ ነው፡፡ ህፃናቶች የማይቻለውን ለማድረግ እንቢ አይሉም፡፡ እነርሱ የሚያውቁት እኔ አድርጉ የምላቸውን ማድረግ እንደሚችሉ ነው፡፡ እኔ የምነግራቸው ገብቷቸው ያደርጉታል፡፡ እኔ ደግሞ ለማድረግ የሚያስችለውን ፀጋ ሳልሰጥ አድርጉ ብዬ ትዕዛዝ አልሰጥም፡፡

"ህዝቤ የኔ ፀጋ ልክ ወራጅ ውኃ ከተራሮች እየተደረደረ ወርዶ በታችኛው ሥፍራ እንደሚከማች ዓይነት ነው፡፡ ስለዚህም የተወደዳችሁ ንፁህና ቀላል አድርጉት፡፡ ደግሞም ነፍሶች በቀላሉ እንዲያመልኩኝ፣ እንዲያፈቅሩኝና እኔን ያስደስተኛል ብለው የሚያውቁትን እንዲያደርጉ አበረታቷቸው፡፡ ዝነኛ ለመሆን ከሚሻኮቱት ከሰዎች ውድድርና ማወሳሰብ ውጡ፡፡ ከዚህ ይልቅ እኔን ማፍቀር ሁሉ ነገራቸው በሆነ፣ እኔን ከማስደሰት በስተቀር ሌላ ምንም አጀንዳ በሌላቸውና ሌሎችን ወደ እኔ ለማቅረብ በሚፈልጉ ትንሽ መንጋ ደስ ይበላችሁ፡፡ የኔ ህዝብ እኔ የምጓጓው እንደዚህ ዓይነት ታናናሾችን ማየት ነው፡፡ እባካችሁ  እንዲቀበሉኝና እንዳይፈሩኝ ወደ እነርሱ አቅርቡኝና ፍላጎቴን አሟሉልኝ፡፡

### ሁላችሁም ልዩ ስለሆናችሁ . . . ኤፕሪል 30 ቀን 2020 ዓ.ም
### Courage, you are all unique, April 30, 2020

ውድ ቤተሰቦች ስለ ትዕግስታችሁ እና ስለ ፀሎታችሁ እናመሰግናለን ፡፡ ዘግይተን የነበረው ወደ ትንሿ ቤታችን እየገባን ስለነበር ነው፡፡ አሁን ግን በጥሩ ሁኔታ ተደራጅተናል ደግሞም ተስተካክለናል፡፡ ሰሞኑን ከእኔ ብዙ ያልሰማችት ምክንያቱ ይህ ነበር፡፡ አሁን ግን ተመልሰን እንደቀደመው ተረጋግተናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኒው ሜክሲኮ ተራሮች ላይ የሚታየው እጅግ ውብ የሆነ የፀደይ ወቅት ነው፡፡

ከጥቂት ቀናት በፊት አንድ መልዕክት ጀምሬ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ መልዕክት ለሰው ጆሮ ለመድረስ ጊዜው እንዳልሆነ ተረዳሁ።እንደዚህ በሚሆን ጊዜ ጌታ መሆኑን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥንቃቄዎችን እወስዳለሁ፡፡ ስለዚህም መልዕክቱን ለእናንተ ለማጋራት እስከ አሁን ድረስ አዘገየሁት። ጌታንም እንዲህ አልኩት 'ጌታ መንጋውን መመገብ እፈልጋለሁ... ነገር ግን እባክህ ሥጋዊ ማንነቴ ጣልቃ እንዲገባ አትፍቀድ ፡፡'

መልዕክቱን ለማሰራጨት ገና ባልተጠበቀብኝ ጊዜ ጌታ እንዲህ አለኝ . . . "ያለ በቂ ፀሎት ጥላቻ በቀላሉ ይመጣል፡፡ ከጥላቻ ጋር ፍርድ ይመጣል፡፡ ከፍርድ ጋር ደግሞ ማሳሳት ይመጣል። ይህ ለመጀመር  እንዴት ነው? "

(ክሌር):-  ጌታ ይህ እውነት ነው ፣ እውነት ነው ፡፡  እባክህ ይቅር በለኝ።  የፀሎት እጥረት እንደነበረብኝ አውቃለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት በውሸት እንድጀምር ፈቀድክ። ያንን መልዕክት ሳዘጋጅ በተሳሳተ የውስጥ ፍላጎት ነበር ያዘጋጀሁት፡፡ አሁንስ ስራው እንዲቀጥል ትፈልጋለህ?

ጌታም . . . "አዎ አንዳንድ በጣም አነስተኛ ለውጦች ተደርገውበት እንዲሰራ እፈልጋለሁ። ነገር ግን እባክሽን በትክክለኛው የውስጥ ፍላጎት፣ ይህም ፍርድ በሌለበትና ቅን በሆነ ቸርነት ስሪው፡፡ ታዲያ ይህ ሌሎችንም በትክክለኛ የውስጥ ፍላጎት ለመስራት እንዲቀጥሉ ይረዳቸዋል፡፡

"ክሌር ይቅር ብዬሻለሁ፣ የኔ ውድ አጋር ይቅር ብዬሻለሁ፡፡ እኔን ስላስጠበቅሽኝ እኔ ደግሞ በተራዬ እንዳስጠበኩሽ ማሰብሽ በትክክል ተረድተሽኛል። ደግሞም የእኔን ምህረት በመገንዘብሽ የበለጠ አድርገሻል፡፡ ምክንያቱም ምህረቴ ባይኖር ኖሮ እንደገና ተመልሰሽ ከእኔ ጋር በዚህ ሁኔታ ለመሆን ብዙ ሺህ ዓመታት መጠበቅ ይኖርብሽ ነበር፡፡ ነገር ግን የእኔን ምሕረት ስላነሳሽና ያንንም አጥብቀሽ በመያዝሽ የተነሳ እንዴት ልቋቋምሽ እችላለሁ? ይህም ሆኖ ግን ብዙ ጊዜ በጣም አስደሳች አፍታዎቹ በጣም ፈጣን የሆኑት ናቸው፡፡ እነዚህም ለጥሪዬ ያለምንም መዘግየት ፈጣን ምላሽ የምትሰጪባቸው ጊዜያቶች ማለት ነው፡፡ እኔ ከአንቺ ጋር ለመሆን እንደምመኝ አንቺም ከእኔ ጋር ለመሆን እንድትመኚ እፈልጋለሁ፡፡

“እየሽ የኔ ፍቅር እኔን ማዘግየት ድፍረት ነው፡፡ ስለዚህም እንደገመትሽው አንቺን ለማረም እገደዳለሁ፡፡ ምላሽ ለመስጠት ከምትፈጥን ነፍስ በላይ የምደሰትባቸው ነገሮች ጥቂት ናቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ለእኔ ያላችሁን ጥልቅ ፍላጎትና ፍቅር የሚገልፅ ስለሆነ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለእኔ ምላሽ ያለመስጠት ለብ የማለት የመጀመሪያው መገለጫ ነው፡፡ አሁን ግን ዛፎቹ እያበቡ ነው፡፡ ፀሐይም እያበራች ነው፣ እናም ከወዳጄ ጋር ነኝ።

"ወደተሻለ ለመለወጥ፣ በትህትና ለማደግ ፥ ራስን መስዋዕት ለማድረግ፣ ለእኔ ታማኝ ለመሆንና ህይወትሽን ለመምራት እንድትችይ ያደረግሽውን ፀሎት ሰምቻለሁ፡፡" (ክሌር፡- ይህንን ሲል የፍራንሲስካን የድህነት፣ የህይወት ሥነ-ምግባር እና መታዘዝ የሚለውን ቃል ኪዳን መጥቀሱ ነው) ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "በተቀደሰ ድህነት ውስጥ በነፃነት ለመኖር እንደምትናፍቂ አውቃለሁ እናም ፈቃደኛ የሆንሽውን ያህል እረዳሻለሁ። ነገር ግን የእኔ ውድ ይህንን ሙሉ ለሙሉ ግብሽ አታድርጊው፡፡ ምክንያቱም ስለ ወንጌል ድሃ መሆን ከንፉግነት፣ ከስግብግብነትና ከአለም ጋር ትስስር እንዳይኖራችሁ የሚጠብቃችሁ ነው። እንዲሁም ልባችሁንና አይምሮዋችሁን ከፍ ካሉ መፈለጎች ነፃ ያደርጋችኋል። በአለም ያሉ ነገሮች ሁሉ ጠቃሚ የሚሆኑት እኔን ለማገልገል ጥቅም ላይ ሲውሉ ብቻ ነው፡ከዚህ ውጪ ግን ሁሉንም ዓይነት ነገሮች ማግኘት ወጥመድ ነው፡፡ ብዙ በብልፅግና የሚያምኑ ክርስቲያኖች የወደቁት በዚህ ወጥመድ ነው። ይህ ደግሞ ከእኔ ጋር ቅርበት በሌለው ግንኙነት ምክንያት የመጣውን የባዶነት ስሜት ለማደብዘዝ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፡፡ ካሏቸው ነገሮች ጋር ማለትም ከጀልባዎቻቸው፣ ከመኪኖቻቸውና ከቤቶቻቸው ጋር በተጓዳኝ ንብረቶቻቸውን ባሉበት እንዲቆዩ ለማድረግና እንደገናም ከሌባ ለመጠበቅ ብዙ ሥራዎች ይጠብቋቸዋል፡፡ እንዲሁም ንብረቶቹ ሲሰበሩ ወይም ሲበላሹ ደግሞ በእነርሱ ተጠቅሞ ደስታ ከማግኘት ይልቅ እነሱን መጠገን ወደ ሸክምነት ይቀየራል።

“ቅዱስ ፍራንሲስ እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንዳውም ከእነዚህ ሁሉ የበለጡ ነገሮች ሊኖሩት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ በእኔ ፍቅር ስለወደቀ የዚህ አለም ነገር ሁሉ ምንም ትርጉም አልሰጠውም ነበር። ይህም የሆነው ከሁሉ እጅግ ውድ ዋጋ ያለውን ዕንቁ ስላገኘ ይህንን ለማግኘት ሲል ሁሉንም ነገሩን ሰጠ። ክሌር የዓለምን ምቾት ሁሉ እንዲተው ለሁሉም ሰው አልተሰጠም። እነዚህን ምቾቶች እንደ ማሰናከያ ድንጋይ እንዲሆኑ ብዬ አልሰጠሁም፡፡ ነገር ግን እነዚህን የሰጠሁት እኔን ደስ የሚያሰኝ ኑሮን ለመኖር እንዲረዷችሁ መሳሪያ እና ድጋፍ እንዲሆኑ ብዬ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚሆነው ከስጦታዎቹ በሚገኘው የአጭር ጊዜ ደስታ ምክንያት ሰጪው ይረሳል።”

“እውነት ነው ፣ ለቅን ክርስቲያኖች በቀላሉ የምገኝ አይደለሁም፡፡ የእኔ ከሆኑት ጋር እጅግ በጥልቀት ለመሄድ እፈልጋለሁ፡፡ በልባቸው ውስጥ መንግሥት ሰማይ እንዲኖር እጓጓለሁ፡፡ ነገር ግን በዚህች ዓለም ፍላጎቶች ተሞልተው እያሉ መንግስተ

ሰማይን ወደእነሱ ማምጣት አልቻልም። በዚህ ምክንያት ነው ፍራንሲስ ስለ ወንጌል ደሃ መሆንን የመረጠበት ትክክለኛ ምክንያት። ታስታውሻለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለምን ትተሽ በአናሎሚክ ፔንስልቬንያ በደን ውስጥ የተሰማሽን ጣፋጭ ጊዜ? ትዝ ይልሻል ምን ያህል ድሃ እንደነበርሽ ነገር ግን ደግሞ ከእኔ ጋር በመገናኘትሽ ምን ያህል ደስተኛ እንደነበርሽ?”

ክሌር:- ኢየሱስ በሕይወት ዘመኔ ወደዚያ ሥፍራ እንደገና ለመመለስ እፈልጋለሁ ፡፡

“የኔ ውድ ያለፈውን መድገም አትችይም፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙ ነገሮች የተለዩ ነበሩ፡፡ በጣም የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን ካልሆነ በቀር ባዶ ሆነሽ ነበር፡፡ ትዳርሽ እየሰመረ አልነበረም፡፡ በሥጋ ወደሙ በመውሰድ የሚገኘውን ጉልበት ገና ማግኘትሽ ነበር፡፡ ደግሞም በዙሪያሽ ካሉ ነፍሳት ጋር በተፈጠረው መልካም  ግንኙነት ገና ደስታን ያገኘሽበት ወቅት ነበር፡፡ በታላቅ ደመና ውስጥ ወደዚያ ቦታ መመለስ እችላለሁ ብለሽ ማሰብ የለብሽም ፡፡ ቢሆንም ግን ከእኔ ጋር ወደ አዳዲስ እና አስደናቂ ነገሮች ለመቀጠል መጠበቅ ትችያለሽ ፡፡

ክሌር:- ጌታ ይህ እየተሰማኝ ያለው በመመስማማቴ ነው?

“አይደለም ፣ ስለ ሕይወትሽ የወቅት ጊዜዎች፣ እኔ ምን እንደምፈልግና እንዲሁም በእያንዳንዱ ደረጃ ስለሚያስፈልጉት ነገሮች ነው ፡፡ ተቀበልሽውም አልተቀበልሺውም ሰላሣ ዓመት ታንሺ ነበር፡፡ ዕድሜ ደግሞ በሕይወትሽ ውስጥ ተፅእኖ ያለው ነገር ነው፡፡ አውቃለሁ እራስሽን እንደ ወጣት እንደምታዪ፡፡ ነገር ግን ሰውነት ደግሞ ሁልጊዜም ከዛ ጋር አይስማማም፡፡

"ቢሆንም ግን ለእኔ ባለሽ ትልቅ ታማኝነት የተነሳ እድሜ በማይሸረው መልኩ ቆንጆ ነሽ ፡፡ ክሌር ራስሽን ዝቅ ማድረግ ተይ፡፡ ህይወትን አክብደሽ ፊት ለፊት በመመልከት ነገሮችን እንደ ሁኔታው እዪ። ብዙ ነገሮች ወደታች እየጎተቱሽ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ምንም የማይደክሙ እና አንቺን እስከመጨረሻው ለመጣል የሚፈልጉት ጠላቶችሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

”ይህም ቢሆን ግን ጉዞሽን ወደ መጨረሱ ተቃርበናል፡፡ እናም በታላቅ ደስታ እና በድል እንድትወጪ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም እውቅና ለሰጠሻቸውና ላልሰጠሻቸው ውድቀቶችሽ ሁሉ፣ ውዴ ለውድቀቶችሽ በሙሉ በአንቺ እጅግ ደስ ብሎኛል። ለመድረስ ጥንካሬ የሌለሽን ነገሮች ትደርሻለሽ ብዬ አልጠብቅብሽም።  የኔ ውድ ፈቃድ እየሰጠሁሽ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከሚገባው በላይ  ከራስሽ ብዙ ትጠብቂያለሽ እያልኩኝ ነው፡፡ አንቺ መሆን የምትፈልጊውን ያህል አልሆንሽም፡፡ ነገር ግን እኔ እንድትሆኚ የምፈልገው አይነት ሰው ነሽ፡፡

“እንድትሆኚ የጠራሁሽን መሆንሽን አውቀሽ በዛ እንድትደሰቺና ሰላም እንድታገኚ እፈልጋለሁ።ፍራንሲስ የሰጠኝን ተመሳሳይ ነገር ከአንቺ አልጠብቅም ፡፡ ይልቁንስ ከልብሽ የመነጨውን ለእኔ ያለሽን ፍቅር እንደ ታላቅ ስጦታ እቆጥረዋለሁ፡፡

“ይህንን እንድትረጂ እፈልጋለሁ፣ አንቺ መሆን የምትፈልጊውን ነገር ግን ያልሆንሽው ላይ በጣም ስታተኩሪ ከውስጥሽ ካለው ሠላማዊ ቦታ መሆን እንዳትችይ ያዳክምሻል እናም ያሸንፍሻል። በዚህም ለሁለት ቦታ ትከፈያለሽ፡፡ በአንድ በኩል ባስተዋልሽው ውድቀቶች የተነሳ ትከሰሻለሽ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አብሮሽ ላለው ነፍስ ከልብ በመነጨ ርህራሄ ትሞያለሽ፡፡”
“ይህ ቤት መቀየር ትልቅ ሥራ ስለሆነብሽ እስከ መጨረሻው አድክሞሻል፡፡ ስለዚህም አሁን በሰላም ውስጥ እንድትሆኚና ወደፊት እንድትቀጥይ እፈልጋለሁ።  ያለፈውን ወደኋላ እየተመለከትሽ አታነጻጽሪ፡፡ ምክንያቱም ይህ ጊዜን ማባከንና

ማበረታቻ ነው። ይልቁንም በሚፈልጉሽ ነፍሳት ላይ ትኩረት በማድረግና የእናትነት ፍቅርሽን በእነርሱ ላይ አፍስሺ። እነርሱ በእግሮቻቸው ሊቆሙ ይገባል፡፡ አንዴ ከተነሱ በኋላ ወደ መድረሻቸው ከፍ ብለው ሲበሩ ስትመለከቺ መደሰት ትችያለሽ፡፡

“ነገር ግን በአንፃሩ ሕይወትሽን መለስ ብለሽ በማየት እነዚህ ሁሉ ውድቀቶች እና የጠበቅሽው ባለመሆኑ ከፈጠረብሽ ክብደት ጋር የምትቀጥይ ከሆነ እነሱ የሚፈልጉትን ልትሰጪቸው አትችይም፡፡ በዚህም ደግሞ ያንቺን ያለመርካት ስሜት ወደእነሱም ታስተላልፊባቸዋለሽ። እንድትሆኚ ያልተፈጠርሽውን ለመሆን መመኘት ፍፁም ኩራት ነው ፡፡ አዎ ሁልጊዜ ትንሽ ማሻሻል እዚህጋ ትንሽ ማሻሻል እዚያጋ ማድረግ ትችያለሽ፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ ልትገነዘቢ የሚገባው ነገርና ፈቃደኛ መሆን ያለብሽ እኔ እንድትሆኚ የምፈልገውን እንድትሆኚ እንጂ አንቺ ትልቅ ነፍስ ብለሽ የምታደንቂውን አምሳያ እንድትሆኚ አይደለም፡፡

“ያለሽን የመጨረሻዋን ትንሿን ነገር መስጠትሽንና እኔ ደግሞ ያንን ሺህ ጊዜ እጥፍ ማብዛቴን በማየት ተረጂ፡፡ በዚህም አንቺ ድክመቶቼ ናቸው ብለሽ ስላሰብሽው ነገሮች አትጨነቂ፡፡ እንዳውም በፊትሽ ስላመጣሁልሽ ነፍሶች ብቻ አስቢ፡፡ እነዚህንም ነፍሶች ወደ እኔ አቅርቢያቸው፣ አሠልጥኛቸው፣ እንዲሁም ፍቅር አሳድሪባቸው፡፡ እኔ ይቅር ብዬሽ የቀበርኳቸውንና ከመቃብር ተቆፍረው መውጣት የሌለባቸውን ያለፉ ኃጢአት እና የጠፉ ጊዜያቶችን እያስታወስሽ የፀፀት ስሜት ሳይሰማሽ ሁሉንም ነገርሽን ስጪቸው። እነዚህን ነገሮች የሚቆፍሩና በፊትሽ የሚያሳዩሽ የሰይጣን አገልጋዮች ናቸው፡፡ የእርሱ ሐሳብ እኔ በፊትሽ ያመጣኋቸውን ነፍሶች ምን እንደሚያስፈልጋቸው ማየት እንዳትችይ ሐሳብሽን ለመስረቅ ነው፡፡

“ኃጥያትሽን አንዴ ከተናዘዝሽ፣ ካወገዝሽውና ፊትሽን ከዛ ከመለስሽ፤ ኃጢአትሽን ከዚያ ወዲያ ደግሜ አላስበውም፡፡ በዚህ ላይ ተማመኚ ምክንያቱም ጠላት ደጋግሞ በዚህ ሊያታልልሽ እና ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ሊጎትትሽ ስለሚሞክር ነው፡፡ የእርሱ ግብ አንቺን ባለፉ ነገሮች በማስጨነቅ ሌሎችን ለመንከባከብ የተሰጠሽን ተልዕኮ እንዳትፈፅሚ ለማድረግ ነው፡፡

“ይህ የምትኖሪበት ሕግ ሊሆን ይገባል፡- ድክመትሽን ወይም ኃጢአትሽን ትገነዘቢያለሽ፣ታዝኛለሽ፣ መድገም ባለመፈለግ ለእኔ ትናዘዣለሽ፡፡ እኔም ይቅር እልሻለሁ፣ አንቺም በምህረቴ ላይ በመታመን መቀጠል ይኖርብሻል፡፡ ከድክመትሽ የተነሳ ከወደቅሽ ደግሞ ደካማ መሆንሽን ተቀበይ፡፡ ራስሽንም በማስተካከል ድጋሚ ተነስተሽ ቁሚ፣ እርዳታም ጠይቂ። ነገር ግን በወደቅሽበት ሥፍራ ራሳሽን በዛው ዝቅ አድርገሽ ከቆየሽ በእኔ ላይ እምነት ማጣትሽን ያሳያል፡፡በእውነት ነው የምልሽ ይህ እምነት ማጣት ስለሆነ እኔን ይጎዳኛል፡፡

“በራስሽ ሳትደሰቺ ስትቀሪ፣ በእውነት ከሆንሽው ሌላ ለመሆን ስትመኚ፣ ይህ የኩራት ኃጥያት ነው። እና ደግሞ እውነት ነው፡፡ ይህንንም ጆሮዎችሽ እንደገና እንዲሰሙት እደግመዋለሁ፡፡የኔ ውድ ተረዳሺኝ? እኔ ከፈጠርኩሽ ውጪ ሌላ ሰው መሆን ስትመኚ ጣኦትና ኩራት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በዙሪያሽ የሚሽከረከሩት ከተሰጠሽ ልዩ ተልዕኮ እንድትርቂ ለማድረግ ጠላት ያዘጋጀው ነው፡፡ እርሱ ራሳቸውን ከሌሎች ጋር የሚያነፃፅሩትን ያሳድዳል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ቅናትን ፣ መከፋፈልን ፣ እርካታ ማጣትን እና በመጨረሻም የራሳቸውን ልዩ ዕጣ ፈንታ እንዳይሳካላቸው ለማድረግ ነፍሳት እንዲወድቁ ለማድረግ ነው፡፡

ይህ ደግሞ ለማደግ የሚመኙ ብዙ ክርስቲያኖች የሚያደርጉት ገዳይ ስህተት ነው ፡፡ እነርሱ የሚፈልጉት ጥሩ የኑሮ ደረጃ እንዳላቸው እንደ እከሌ ወይም እንደ እከሊት ለመሆን ነው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ለሰው ደስ የሚያሰኝ የሚያምር ሕይወት ስላላቸውና እኔንም ደስ የሚያሰኙኝ ስለሚመስላቸው ነው፡፡ የለም እንደሱ አይደለም፡፡ እኔ ክርስቲያኖች ሁሉ ነገራቸው

ተመሳሳይ እንዲሆን እንደ ኩኪስ ቅርፅ ማውጫ መሳሪያ መቅረፅ አልፈልግም፡፡ እኔ የምፈልገው የተነገረላቸውን የሚያሟሉ ክርስቲያኖችን ነው፡፡ እናም ህይወታቸውን በሙሉ ከትውልዱ ጋር በማስማማት የሚኖሩ ሰዎች በመጨረሻም ይወድቃሉ ፡፡ እናም እንደነዚህ አይነቶቹ ህይወታቸውን የሚያሳልፉት ሌሎችን ለማስደሰት የውሸት ኑሮ በመኖር እኔ ለእነሱ ያዘጋጀሁላቸውን ህይወት ሳይኖሩ ስለሆነ እርካታን እንዳጡ ወደ መቃብሮቻቸው ይሄዳሉ።

“ከአንቺ የሥራ ድርሻ አንዱ ክፍል እነሱ ይኖሩባቸው የነበሩትን የተለመዱ የመቅረጫ መንገዶችን በመስበር ዕጣ ፈንታቸውን እንዲያገኙ መርዳት ነው፡፡ በዚህም እኩዮቻቸው እንዲሆኑ የነገሯቸውን ሳይሆን እኔ እንዲሆኑ ያቀድኩላቸውን እንዲሆኑ ማበረታት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ማድረግ የሚችሉት ከእኔ ጋር ሲነጋገሩና የህይወታቸው እጣ ፈንታ ከተዘራበት ከልባቸው ውስጥ እምነትና ብርታት ሲያብብ ነው፡፡ እኔ እግዚአብሔር በልባቸው የተከልኩትን እውነተኛ ዕጣ ፈንታ ሲገነዘቡ፣ ለእነርሱ ያለኝ ፈቃድ እንደሆነ በማወቅ ወደዛው ዓላማ መጓዝ ይጀምራሉ፡፡ እናም ይህንን በማወቃቸው ጠላት እነሱን ለማገድ የሚጠቀምበትን ማሰናከያዎችና ዘዴዎችን ሁሉ ችለው ይቆማሉ፡፡

ዓላማችሁን ለመከተል ቅባት እንዲኖራችሁ፣ ደፋር እንድትሆኑና በሙሉ ልባችሁ ከእኔ ጋር መጣበቅ እንድትችሉ አሁን በሚሰሙ ጆሮዎቻችሁ ባረኳችሁ።”

## ቤተ ክርስቲያኔ ተቋማዊ ሳትሆን ቤተሰባዊ ነች - ሜይ 9 ቀን 2020 ዓ.ም

## Faith family not institution- May 9-2020

(ክሌር) ውድ ቤተሰቦች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

የቀደመችውን ቤተክርስቲያን ቀላልነት ከማይረዱ ሰዎች ጋር በጥልቅ እየተፈተሸኩ ስለሆነ ጌታ እንዲረዳኝና ነገሩን ለመገንዘብ እንዲያስችለኝ ጠየኩት። እናም አሁን ጌታ ምን እንዳለኝ ላካፍላችሁ ነው፡፡ ጌታንም እንዲህ ብዬ ጠየኩት፡፡ 'ጌታ እውነተኛ እንዳልሆንን በሚያስቡ ተቋማዊ አብያተ-ክርስቲያናት ዝቅ ተደርገን እንደምንታይ አውቃለሁ።እባክህ ለዚህ ጉዳይ የአንተን አመለካከት ለመረዳት እንድችል እርዳኝ።'

ጌታም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . “በሰዎች አይን ጻድቃን የሆኑትን አይደለም ወደ ተቀደሰው ስርዓቶች ሁልጊዜ የምጠራው። እኔ የምጠራቸው ልባቸው ንፁህ የሆኑትን፣ እኔን ለመፈለግ፣ ለመውደድና ለመታዘዝ ምንም ሌላ የውስጥ ፍላጎት የሌላቸውን ነው፡፡ ይህ ግን በዓለማዊ አስተሳሰብ አይታወቅም። እነርሱ ከሰዎች ማረጋገጫዎችንና በሰው ፊት ትክክለኛ ሆኖ መገኘትን እንዲሁም ባሉበት ክብር መቆየትን ይፈልጋሉ፡፡

"በመንግሥተ ሰማይ የከፍታ ሥፍራ የሚወሰነው በልብ ንፁህነት ነው። አንድ ወንድን ወይም ሴትን ለስድስት ዓመታት የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ብታሰገቧቸው፣ ሲጀምሩ የነበረ የልብ ንፅህና በከባድ መቅረጫ ተቀርፀው ሹመትን እንዲፈልጉ ተደርገው እንዲወጡ ይደረጋሉ፡፡ እኔ በዚያ መንገድ አልሠራም። እኔ የምፈልገው ልባቸው ንፁህ የሆኑትንና በመንፈስ እና በእውነት በፅናት እኔን የሚፈልጉኝን ነው። ሰዎችን ለማስደሰት የሚሞክሩ ግን ይህንን መስፈርት ሊያሟሉ

አይችሉም። እኔ የማጸድቀው እኔን ብቻ የሚሹትን ነው፡፡ እነዚህ ነፍሳት ደግሞ ለነፃ አስተሳሰብ አጀንዳ ስጋት ስለሚፈጥሩ ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተገለዋል ፡፡ ለቃሌ ታምኝ ከመሆናቸው የተነሳ በ'ዘመናዊው' አለም ለመንቀሳቀስ አይችሉም።

"ለጥሪው ተስማሚ መሆናቸውን ለመወሰን የሰውን ቁመና አትመልከቱ። እንዲሁም ልባቸው ለእኔ ብቻ ለመኖር እንዴት እንደተሰጠና ለሰው ክብር እንዳልሆነ ተመልከቱ፡፡ ክሌር በአንዳንድ ሰዎች ትጠያለሽ፡፡ ደግሞም መናፍቅ ብለው ይጠሩሻል፡፡ ልክ እኔ እንደተባልኩት ማለት ነው። በእኔ አመለካከት ምንም አልጎደለብሽም፡፡ እንዳውም የሰዎችን አክብሮት ለማግኘት ብለሽ ለእነሱ ባለመስገድሽ ሁሉን አትርፈሻል።

ክሌር ፡ - ጌታ ተረድቻለሁ፣ ነገር ግን እባክህን አጠንክረኝ፡፡

"አጠነክርሻለሁ ደግሞም እያጠነከርኩሽ ነው፡፡ አሁን በልቤ ውስጥ ያለው ሌሎች ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል በተለያዩ ቦታዎች ጦርነቶችን እያስተናገደች በመሆኑ እየተዳከመች ስላለችው አገራችሁ ሁኔታ፡፡ ምክንያቱም ጠላት ዓለምን ሁሉ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን ጥልቅና መሰረታዊ ስራዎችን ስለዘረጋ ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ እኔ መስራት ለምፈልገው ነገር ስጋት ፈጥሯል። ምክንያቱም እነሱ ዓለም አቀፍ መንግሥትን ለመመስረት የሚያስችለውን ትምህርቶች በሙላት እያጠናቀቁ ነው ። ነገር ግን እኔ በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እነካቸዋለሁ እናም ነፃ ይወጣሉ፡፡ ውዴ ይህንን ተረጂ፡፡ ነገሮች በሁሉም ግንባር ግጭት እየፈጠሩ ነው፡፡ በዚህ ሰአት ከምድር በታች የሚደረጉ የእሳት ጦርነቶችና በምድር ላይ የበላይ ለመሆን የሚደረጉ ትግሎች አስፈሪ ናቸው። በዚህም ብዙ ጉዳተኞች አሉ፡፡ ነገር ግን የእኔ ዓላማ በህይወትና በሞት ትግል ውስጥ እንኳን እየተከናወነ ነው፡፡

አሁን ይህንን የምነግራችሁ እኔ ክሌር ነኝ፡፡ በድብቅ ስለሚደረጉ የእሳት ጦርነቶች ጉዳይ እስካሁን ያለኝን የቅርብ ጊዜ መረጃ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ። ከመሬት በታች ከሚገኙ ድርጅቶች በህገ - ወጥ መልኩ እንዲዘዋወሩ የተደረጉ 750,000 ህፃናት ተለቀዋል፡፡ ይህም የሆነው ፕሬዚዳንት ትራምፕ ወታደሮቻችን ከመሬት በታች መዋጋት የሚያስችላቸውን ስልጠና እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ በመስጠቱ ነው፡፡ እነዚህም ወታደሮች እየተጋፈጡ ያሉት በቀላሉ ጣታቸውን በማንሳት ኃይለኛ ኤሌክትሪክ ቻርጅን በማውጣት ከሚገድሏቸው ከዚህ አለም ውጪ ከሆኑ አጋንንታዊ ኤልየኖች ጋር ነው፡፡ ውዶች እባካችሁ ከምድር በታች ለሚዋጉ ለእነዚህ ሠራዊት ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይና የተጋፈጧቸውን ኃይላት ለመደምሰስ እንዲችሉ ጸልዩላቸው። እባካችሁ በመዝሙር ዘጠና አንድ (91) መሰረት ለእነሱና እነዚህን ልጆች እንዲያድኗቸው ፀልዩላቸው። እናም አንዳንዶቻችሁ የኢጋንንት ኤልየኖች የሚኖሩት በሰው ሥጋና ደም እንደሆነ ታውቃላችሁ።

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ሊንች ፒኖቹ እየተወገዱ ነው" (እዚህጋ ጌታ እየተናገረ ያለው ሃገራችን አሜሪካን ያበላሹትን አለም አቀፍ መሪዎችን ነው)

(ክሌር):- ሊንች ፒን ማለት /linchpins/ ተሽከርካሪን በቦታው እንዲቆይ በአክስሉ በኩል የሚያልፍ ሚስማር ነው፡፡ ነገር ግን ሊንችፒን የሚለው ቃል ማንኛውንም አስፈላጊ አካል ለማመልከት ሊያገለግል የሚችል ሲሆን ይህም ማንኛውንም ነገር አንድ ላይ አስተሳስሮ የሚይዝ ነው፡፡ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ ከሆነ ሊንችፒን ነው ማለት እንችላለን፡፡ ሊንችፒኑን ብታስወግዱት ሁሉም ነገር ይፈራርሳል፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . “ሊንችፒኖቹ እየተወገዱ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚያን ክፍት ቦታዎች የሚሞሉ ዝግጁ የሆኑ የሰለጠኑ ተተኪዎች አሉ፡፡ ህዝቤ የዚህን ሃገር አካሄድ የሚወስነው ጸሎታችሁ ነው፡፡ በጉልበታችሁ ወድቃችሁ በትውልዱ ውስጥ ጠልቆ ስለገባው ክፋት በህመም ወደ እግዚአብሔር ብትጮሁ፣ ያንን ብታደርጉ ፣ የአባቴ እጅ ተጨማሪ ጊዜ ፣ ተጨማሪ ጸጋ እና የበለጠ ምሕረት ሊሰጣችሁ ይንቀሳቀሳል። ስለዚህም አባት ሆይ ተጨማሪ ጊዜ ፣ ተጨማሪ ጸጋ ፣ ተጨማሪ ምሕረት ብላችሁ ወደ አባቴ ጩሁ። ይህንንም ፀሎት መጸለይ የምትቀጥሉት ከምድር በታች ስለሚካሄደው ጦርነት መንፈስ ቅዱስ ሲነግራችሁ ወይም ሲያመላክታችሁ ነው። እርሱ ያቀረባችሁትን ልመና ያዳምጣል እናም ጸጋን ይለቅላችኋል።

“በመሠዊያው ላይ የሚያገለግሉ እንደ ልቤ የሆኑትን ልጆች እያሳደኩኝ ነው፡፡ ልባቸውና ለእኔ ያላቸው ቁርጠኝነት ለዚህ ሥራ ብቁ ያደርጋቸዋል፡፡”

(ክሌር):- ጌታ ሆይ ፣ በተከታታይ የንጥቀት ንባቦችን እየሰጠኸን ነው?

"የኔን የጊዜ አደላደል ነግሬያችኋለሁ ፡፡ ነገር ግን ትክክለኛ ቀኑንና ሰአቱን እኔም እንደማላውቅ ነግሬያችኋለሁ፡፡ ይህንን መረጃ በልቡ ውስጥ የያዘው አባቴ ብቻ ነው ፡፡ የተወሰኑ መረጃዎችን ሰጥቶኛል። ቢሆንም ግን ትክክለኛው ቀንና ሰአት ከእኔም የተደበቀ ነው፡፡ ተደሰትሽ የኔ ሙሽራ?”

ክሌር:- አዎ ተደስቻለሁ ግን እንደምታውቀኝ ሥራዬን መጨረስ እፈልጋለሁ ፡፡

"ክሌር መሥራትሽንና የሚሆነውን በጥንቃቄ መመልከትሽን ቀጥዪ፡፡ ማንም ሰው ሰዓቱን አያውቅም ። ነገር ግን ብትታዘዢኝና የሚሆነውን ብትመለከቺ ዝግጁ ትሆኛለሽ ፡፡ የኔ ውድ ክሌር የእኔ ምኞት ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ እንድትሆኚ ነው፡፡ አንቺ ደግሞ የተሰጠሽን ሥራ ለመጨረስ ትመኛለሽ። ነገር ግን እንድታስታውሺ የምፈልገው ነገር አብ ነገሮችን ሁሉ የሚሰራው ፍፁም በሆነ መልኩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጊዜንም ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ጊዜ በዓለም ውስጥ ስላለው ግርግር ምንም ግንዛቤው የለሽም። ሚዛን የሚደፋው በየጊዜው መቀያየሩ ቀጥሏል፡፡ አንድ ጊዜ ጨለማው ይበረታና ፍርድን የሚያመጣ ይሆናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ምሕረት ይሆናል፡፡ እነዚህን ነገሮች እንዴት ነው የምታውቂው? ከእኔ ጋር በቅርብ ሆነሽ ከልቤ ጋር በመጣበቅ ነው፡፡ በዚህም ዝግጁ ትሆኛለሽ።

"ይህንን ቦታ ለቀሽ ከእኔ ጋር ለመሆን በማንኛውም ሰዓት ዝግጁና ፈቃደኛ ሁኚ ፡፡ ያንን በልብሽ ውስጥ ከያዝሽ ምንም ጥርጣሬ አይኖርሽም፡፡ ከተቀጠረው ጊዜ አሳልፈሽ እዚህ መሆን አትችይም፡፡ በታላቁ መከራ ጊዜ እዚህ መቆየት ለአንቺ የተሰጠ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከእኔ ጋር መሆን እንጂ፡፡ ስለዚህም አንቺ ከሄድሽ በኋላ ለሚመጡት የሥራ መሰረት እየጣልሽ ነው። እናም በየቀኑ ምህረቴን ከፍ ከፍ አድርገው የሚኖሩ ብዙ የነፍሶች ሠራዊት ይኖራሉ ፡፡ እነርሱ ቤተክርስትያኔ እንድትተርፍ የሚያስፈልጋት ልብ ይኖራቸዋል። በአደራ የሰጠሁሽ ትምህርቶች ለስኬታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ፡፡

"እኔ በተቋማት ፣ በፖለቲካ ፣ በሃብትና ከእነዚህ ነገሮች ጋር አብሮት በሚኖረው ሙስና ሁሉ በጣም ደክሜያለሁ፡፡ በእኔ ልብ ውስጥ መኖር ዓላማቸው ከአደረጉና ለእኔ ብቻ መኖር ከሚፈልጉ ነፍሳት ጋር ቀለል ባለ መልኩ፣ አባትና እናት ያለበት ቤተሰባዊ የሆነ ቤተክርስቲያኔን ለማቋቋም እኔ ዝግጁ ነኝ፡፡ ይህ እንዳይሆን ደግሞ ሰዎችና አጀንዳዎቻቸው ከፊት

ተደቅነዋል። ለዚህም ነው መንግስታቸው እየወደቀ ያለው። ቤተክርስቲያኔ ግን መቼም አትወድቅም፡፡ ቅሬታዎቹ ደግሞ እኔን በሙሉ ልባቸው የሚወዱና የተከበረውን ከተዋረደው መለየት የተማሩት ናቸው፡፡

"ሁላችንም በመንግሥተ ሰማይ እንደነበረው እንደገና አንድ ላይ በመሆን አብን ለማገልገል ባለ አንድ ንፁህ ዓላማ፣ እንዲሁም ነፍሳት እኔ ወዳሰብኩላቸው የቅድስና ሕይወት እንዲያድጉ ለማድረግ አብረን ሆነን ለማየት እደሰታለሁ፡፡ እነዚህ ንፁህ ነፍሶች እንደ አንድ ታላቅ ሠራዊት በመነሳት በምድር ያለውን መንግሥቴን ንፁህና ቅዱስ ወደነበረው ወደድሮው ሲመልሱት ለማየት በሙሉ ልቤ እመኛለሁ። ተመሳሳይ ራዕይ ያላቸው ነፍሶች ወደ አንቺ ስልክልሽ በእናትነት ፍቅርሽ እቀፊያቸውና በሰዎች ዘንድ ከግምት ውስጥ ወደማይገባው ነገር ግን ከእኔ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ወደሚያስገኘው ነፃነት ምሪያቸው፡፡ እነዚህ ነፍሶች መልሼ ለምገነባት ቤተክርስቲያኔ ከልቤ የሆኑ ሕያው መሰረቶች ይሆኑኛል።

"የእኔን መምጣት እየተጠባበቃችሁ የተሰጣችሁን ሥራ ለመፈፀም በሚያስችላችሁ ጥንካሬና ድፍረት አሁን ባረኳችሁ።"

## ከሰማያት እሳት ስለሚወድቅ ተዘጋጁ እንጂ አትፍሩ - ሜይ 12 ቀን 2020 ዓ.ም

## Fire will fall from heaven - May 12-2020

(ክሌር) ውድ ቤተሰቦች አሁን ያለነው ወደ ምድር ሊመጣ ባለ ከባድ የፍርድ ወቅት ላይ ነው፡፡ ጌታ ይህንን ከዋና አባላቶቻችን በአንዱ አማካኝነት አረጋግጦልናል፡፡ ይህም ሰው ደግሞ በአለም ላይ ሊከሰቱ ያሉ አደጋዎችን በትክክለኛው ሁኔታ በማስጠንቀቅ የታወቀ ሰው ነው፡፡ ስሙም ማይክ ይባላል የሚታወቀውም ማይክ ፍሮም አራውንድ ዘ ዎርልድ (Mike from around the world) በመባል ነው፡፡ መልዕክቱንም ካውንስልነአርክ (Council1arch)በሚል መጠሪያ በሳውንድ ክላውድ( Sound Cloud) ላይ ይተላለፋል፡፡

ይህ አባላችን ላለፉት ስምንት አመታት የአለም መጨረሻን የሚመስል የዳመና ፍርስራሽ ይከሰታል ብሎ ሲያስጠነቅቀን ነበር፡፡ ይህም ደግሞ እ.አ.አ. በሜይ 12 ቀን 2020 ዓ.ም ከመሬት ጋር ይጋጠማል ብሎን ነበር፡፡ የዚህ ዳምናም ስፋት ከ3-4 ሚሊየን ማይልስ ሲሆን ይህም ዳመና የሚያየዘው ጨለማ ከምትባለው ፕላኔት ኒብሩና ፕላኔቶቿ ወደ መሬት መቅረብ ጋር ነው፡፡ የኛ ፀሐይና ፕላኖቶቿ(our solar system) በአሁን ወቅት በዚህ ሁኔታ እያለፉ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ በምድር ላይ ምን ያህል አደጋ ሊያመጣ እንደሚችል ማንም የሚያውቅ የለም፡፡ ነገር ግን ከእኛ ዋና አባሎች ራዕይ አንፃር እሳት ከሰማያት ወደ ምድር በመውደቅ ብዙ አገራት በእሳቱ ሲቀጣጠሉ ተመልክተዋል፡፡ ከዚህ መልክት መጨረሻ ላይ ማዘር ኤሊሻ ወይም ናና ከጌታ የተሰጣትን ትንቢታዊ ቃል አካፍላችኋለሁ፡፡

ተወርዋሪ ኮከብ ምን ሊያደርስ እንደሚችል ሐሳብ እንዲኖራችሁ እንደ ምሳሌ አንድ ክስተት ላጫውታችሁ፡፡ እ.አ.አ. በሰምቴምበር 15 ቀን 2007 ዓ.ም. በፔይሩ 12,500 ጫማ በሚገኘው ካርካስ መንደር, እንዲሁም በቦሊቪያን ዳር ድንበርና በቲቲካከ ሐይቅ አጠገብ አንድ ተወርዋሪ ኮከብ በመውደቁ ምክንያት 15 ጫማ ጥልቀትና 43 ጫማ ስፋት ያለው የእሳተ ጎሞራ ጉድጓድ ፈጥሯል፡፡ ይህም በአካባቢው ጎልቶ የሚታይና ምድሪቱንና አፈሩን በእጅጉ የጎዳ ክስተት ነው፡፡ የአካባቢው ባለስልጣን እንዲህ ብሏል "የፈላ ውኃ ከእሳተ ጎሞራው መውጣት ጀምሯል፡፡ ደግሞም የድንጋይና የተቃጠሉ የከሰል

ቅንጣቶች በአጠገቡ ተገኝተዋል፡፡" ከእሳተ ጎሞራው የሚያስጠላና የሚያቅለሸልሽ ጭስ ተወርውሮ በኃይል ይወጣል፡፡ በጣም የሚሸት፣ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ነገር፣ ድኝ ከውስጡ ይወጣል፡፡

ከዚህ ነገር በኋላ ወደዚህ ሥፍራ ለመጠጋት የሞከሩ በአካባቢ ያሉ የመንደሩ ነዋሪዎች በተለያዩ ምልክቶች የታጀበ፣ ነገር ግን በውል ምን እንደሆነ ባልታወቀ በሽታ ታመዋል፡፡ የአካባቢው ባለስልጣን እንደገለፀውም ይህ የሆነው ከእሳተ ጎሞራው ከሚወጣው ነገሮች ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለፁት በጣም የሚያበራ የእሳት ኳስ፣ ጭራው የሚጨስ ከመሬት 3,300 ጫማ ከፍ በማለት ይቀሳቀስ ነበር፡፡ ይህም ኳስ መሰል ነገር የተጓዘው ወደ ሰሜን ምስራቅ ሲሆን ይህም በሚሆን ጊዜ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ አይነት ነገር በመፍጠሩ በግማሽ ማይልስ የሚገኝ ጤና ጣቢያን መስኮት ብትንትኑን አውጥቶታል፡፡ በእሳተ ጎሞራው ውስጥ የጋዝ አረፋ ሲወጣና ለብዙ ጊዜ የቆየ የቁም ዳመና ታይቷል፡፡

ክስተቱ ከተፈጠረ ወዲያ  ከ600 የሚበልጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ለጉብኝት ወደ ቦታው ሄደው ነበር፡፡ እናም እነዚህ ጎብኚዎች ሊገለጡ የማይችሉ ብዙ ምልክቶችን አስተናግደዋል፡፡ ለምሳሌ የቆዳ መጎዳት፣ ማቅለሽለሽ፣ ራስ ምታት፣ ተቅማጥና ተውከት የመሳሰሉትን፡፡ በፈረንጆች ስብቴምበር 20 ቀን 2020 ዓ.ም  የፔይሩ ሳይንቲስቶች በራራ ኮከብ መውደቁን አረጋግጠዋል፡፡ በጣም የሚገርመው ይህ ከመከሰቱ አንድ ሳምንት በፊት ከእኛ አንድ የህብረተሰብ አባል ለሳምንት ያህል በየቀኑ "እሳት ከሰማይ ይወድቃል" የሚል በሌላው ሳምንት ደግሞ "መስዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ደም" የሚል መልዕክት ትሰማ ነበር፡፡ ከዚህ ራዕይ ጋር በተያያዘ የሚሰጣት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል "በሰማይ ላይ እሳት" የሚለውን በካቶሊክ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኘው መፅሐፈ ባሮክ 6፡ 62 ላይ የሚገኝ ነበር፡፡ ይህም ክፍል እንዲህ ይላል "ከሰማይ የተላከ እሳት ተራሮችንና ጫካዎችን በማቃጠል ተልዕኮውን ይፈፅማል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የውሸት አማልዕክቶች በአቋምም ይሆን በኃይል አይወዳደሩትም፡፡"

(ከሌር)-- ጌታ ለኸርት ድዌለርስ ስለዚህ ጉዳይ ልትነግራቸው የምትፈልገው ነገር ምንድነው?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ  . . . "ከሰማያት ስለሚወድቀው እሳት እንዳይፈሩ ንገሪያቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ መፍራት ያለባቸው ለዘላለም በሚያቃጥለው ገሃነም ውስጥ መጣልን ሊሆን ይገባል፡፡ እኔ ወደገሃነም ሊጣሉ ያሉትን ከዛ ለመውጣት ወደ እኔ የሚጮኹትን ለማዳን በተጠንቀቅ ቆሜያለሁ፡፡ በምድር የምትኖሩ ሁሉ ገዢዎቻችሁ አታለዋችኋል፣ እንድትስቱ አድርገዋችኋል፡፡ ነገር ግን ክፉዎቹ እጅግ በትልቅ ሥልጣን ላይ የሚገኙት ናቸው፡፡

"እነርሱ ፍፁም ክፉ እየሰሩ መልካም እንደሰሩ እንድታምኑ በማድረግ ከትክክለኛው መንገድ አውጥተዋችኋል፡፡ እናንተ ወጣቶች የአለምን መንገድ እንድትከተሉ ተደርጋችሁ የሰለጠናችሁ፣ እናንተ ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ አድርገው ለምን በዚህ መንገድ እንዳሰለጠኗችሁ ከበስተጀርባ ያለውን አጀንዳ ምን እንደሆነ እውነቱን መግለፅ እንድትችሉ ብዙ የምትማሩት ነገር አለ፡፡

"ይህችን ቆንጆ ፕላኔት የፈጠርኳትና ያቆየኋት እኔ ነኝ፡፡ በውሸት እኔን የሚከሱኝ እነዚያ፣ እነርሱ ናቸው ለውድቀቷ ምክንያት የሆኑት፡፡  የሰይጣን አጠቃላይ አጀንዳ እናንተንና ምድሪቱን እጅግ በሚያም ሁኔታ ማጥፋት ነው፡፡ እርሱ እናንተንና በዚች ቆንጆ ፕላኔት ያለውን ሁሉ እጅግ ይጠላል፡፡ እናም የእርሱ ብቸኛ አጀንዳ ስቃይን፣ ጥፋትንና ሞትን ማምጣት ነው፡፡

"ይህንን የምነግራችሁ እናንተን ለማጥፋት ማጭበርበርና ያነጣጠረውን ጥፋት ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ ስለማታውቁ ነው፡፡ ይህ አገር አሁን ያለው መንገዱ በመጨረሻ ላይ የተዘጋ መንገድ ላይ ነው፡፡ ወደኋላ ለመመለስ የማይችልበት ነጥብ ላይ ደርሷል፡፡ አሁን እየገባችሁ ያላችሁት ወደር የሌለው ስቃይና ጥፋት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም ሁላችሁንም የምጠይቃችሁ ከአሁን ቀደም ፀልያችሁ ያማታውቁትን ያህል እንድትፀልዩ ነው፡፡ ምክንያቱም በህይወት መኖራችሁ የሚወሰነው በዚህ ስለሆነ ነው፡፡ የሚመጣውን ማመን አትችሉም፡፡ ነገር ግን የተባላችሁትን በደንብ ያከናወናችሁና የተዘጋጃችሁ ሌሎችን መርዳት እንድትችሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡"

(ክሌር) ጌታ ምን መጠበቅ እንዳለብን እባክህ ንገረን፡፡

ኢየሱስም . . . "ጥፋትና ሞትን ጠብቁ፡፡ በዚህ ወቅት ትኩረት ማድረግ ያለባችሁ ሥራ ላይ ሳይሆን የሚያስፈልገው ፀሎት፣ ፀሎትና የበለጠ ፀሎት ነው፡፡ በፀሎት ቀጥሉ፡፡ ህይወት የሚቀጥለው በታማኝነት በመፀለያችሁና ንቁ በመሆናችሁ ነው፡፡ ብዙ ነፍሶች፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሶች በሥጋ መሞታቸው ብቻ ሳይሆን ከሞቱ በኋላ መገኛቸው የት እንደሚሆን የሚወስነው በፀሎታችሁ ነው፡፡ በመጀመሪያ እንደነገርኳችሁ በመሬት ላይ ስለሚወድቀው እሳት አትጨነቁ፡፡ መጨነቅ ያለባችሁ በገሃነም መጣላችሁና የዘላለም ህይወት ማጣታችሁ ነው፡፡

"የእግዚአብሔር አገዛዝ ማንም እንደሚጠብቀው አይመጣም፡፡ እኔ የምመጣው በሙብረቅ፣ በብልጭታና በሰማይ ላይ በሚታዩ ምልክቶች ነው፡፡ እስካሁን አብዛኞች ስለመምጣቴ ዝግጁ አይደሉም፡፡ ለአባቴና ለእኔ የሚያሳስበን ይህ ጉዳይ ነው፡፡ ክሌር እኛ የምንፈልገው የበለጠ ብዙዎች እንዲድኑ ነው፡፡  ከዚህ በበለጠ ብዙዎች እንዲድኑ ነው፡፡ ሙሽራዬ እንደተዘጋጀች በማሰብ በጭንቀት የኔን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ብትሆንም፣ እኔ ግን የምመለከተው መንግስቴ እንዲመጣና ፈቃዴ በምድር ላይ እንዲፈፀም መኖር ያልያዙትን፣ ለራሳቸው ብቻ የሚኖሩትንና ራስ ወዳዶችን ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ታዲያ ይህ ስጋዊነት ይቀጥላል፡፡ ነፍሳት ምግብ፣ አልባሳት፣ መጠለያና ፍቅር ከማጣት ይሞታሉ፡፡ በዚህም እኔ ምን ያህል እንደምወዳቸው እውቀት ሳይኖራቸው ያንቀላፋሉ፡፡ ክሌር ሙሽራዬ ከዚህ ምድር ከመወሰዷ በፊት ብዙዎች እጅግ ገና ብዙዎች መዳን ያለባቸው አሉ፡፡ እያንዳንዱ ራሱን ያጠመደው በንጥቀት ላይ ሲሆን አንቺ ግን ይህንን ጥበብ ወደ እኔ ቀርበሽ በመጠየቅሽ አዋቂ ነሽ፡፡ እኔ ደግሞ የተጠመድኩት በእርሻው ላይ የሚሰራልኝን ሰራተኛ በመፈለግ ላይ ነው፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ያገኘሁት እጅግ ጥቂት ነው፡፡

"የኔ ውድ ይህ ምን ማለት ነው? እኔ ከመምጣት መዘግየት አለብኝ ማለት ነው፡፡ ሙሽራዬ እስካሁን በራሱ ጉዳይ ላይ ተይዛለች፡፡ እርሷ በስቃይ ላይ ካሉት ጋር አይደለችም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እኔ በፍቅር እንደምወዳቸው ባለማወቃቸው ከሚሰቃዩት ጋር አይደለችም፡፡ ወንጌሉ በአለም ሁሉ መሰበክ አለበት፡፡ የኔ መምጣት በማንኛውም ሰዓት ሊከናውን እንደሚችል ግልፅ ቢሆንም እኔ ግን እርሷ የደረሰውን መከር ለመሰብሰብ በታዛዥነት በእርሻው ላይ ትሰራለች ብዬ እየጠበቅኳት ነው፡፡

በዚህም ምክንያት ነው ንጥቀት አሁን የማይሆነው፡፡ ይህ በመንግስተ ሰማያት የተወሰነ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ሰዓቱ አልደረሰም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ፍንጮችን እየሰጠሁ በቅርብ የመምጣቴን እሳት ማቀጣጠል አለብኝ፡፡ ይህንንም የማደርገው ውዷ ሙሽራዬ ህይወቷን በመመርመር እኔን አለመምሰሏን የምታገኝበት ይሆናል፡፡ ይህ የማጣሪያ ነጥብ ነው፡፡

ሙሽራዬ እኔን መምሰል አለባት፡፡ ስለዚህም በአለም አይን ጥቃት ሊደርስባት፣ ተቀባይነት ልታጣና ልትናቅ ይገባታል፡፡ ይህም የሚሆነው ደግሞ በእኔ ጉዳይ ላይ፣ በእርሻው ሥራ ላይ የደረሰውን መከር በመሰብሰብ ላይ ስትጠመድ ነው፡፡"

(ክሌር) ጌታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መፆም አቅቶኛል፡፡ ይህ ደግሞ አንተ ከሰጠኸኝ ሥራ ይልቅ ራሴን ወዳድ መሆኔን የሚያሳይ ሲሆን እኔ ግን እጅግ ደካማ ሆኛለሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ እንድትረጂ የምፈልገው ለሁሉም ነፍስ በከባድ ሁኔታ እንዲፆም አልተሰጠውም፡፡ አይንሽን ከፆም ላይ አንሺና በፍቅርና በአገልግሎት ላይ አተኩሪ፡፡ ጠላት ሁኔታሽን እየተከታተለ ድካምሽ ላይ እንድታተኩሪ በማድረግ ተስፋ እያስቆረጠሽ ነው፡፡ ይህ ለእያንዳንዳችሁ ኸርት ድዌልርስም የሚሰራ እውነት ነው፡፡ ሰይጣን ክርስቲያኖችን በመክሰስ፣ የጥፋተኝነት ስሜትና ሃፍረት እንዲሰማችሁ በማድረግ ከእኔ ለመነጠል የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ አንዳንዶች ፆም ጣፆት ሆኖባቸዋል፡፡ እርግጥ ነው ፆም በህይወታችሁ ብርታት እንደሚሰጣችሁና አስፈላጊ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ነገር ግን ጣፆት አይሁንባችሁ፡፡ አልፎ አልፎ የሚፆም ጥብቅ የሆነ ፆም ካልሆነ በቀር ከእኔ ልትሰሙ ብቁ አይደላችሁም፡፡ ፆምን ጣፆት በማድረግ እኔን ለመስማት መሞከር ፍፁም ውሸት ነው፡፡ እኔን እንድትሰሙ ከመረጥኳችሁ ትሰሙኛላችሁ፡፡ ራስን መካድ አከብራለሁ፣ ነገር ግን አምላካችሁ አታድርጉት፡፡

ብዙ መብላትና ብዙ መዝናናት ስሜቶችን ስለሚያደነዝዝ በተወሰነ መልኩ መስማትን ይከለክላል፡፡ ስለዚህም ለእኔ ጥሪ ንቁ፣ ዝግጁና ትጉ እንድትሆኑ እነዚህን ነገሮች በመጠኑ አድርጓቸው፡፡ ክሌር እነዚያ የሚፆሙ ሰዎች በአይምሮአቸው ውስጥ ምን እንደሚመላለስ ብታዩ ኖሮ እጅግ ትደነግጪ ነበር፡፡ ብዙዎች  የሚፆሙት ንፁህ ባልሆነ የውስጥ ፍላጎት ነው፡፡ እነርሱ የሚፈልጉት እንደ ቅዱስ እከሌ ለመሆን ነው፡፡ ስለዚህም እንደ ቅዱስ እከሌ መፆም ስለምንችል እኛም ቅዱስ እንሆናለን በሚል እሳቤ ነው የሚፆሙት፡፡ ነገር ግን ይህ  አይሰራም፡፡ ከውጪ በሚታይ ምልከታ ሳይሆን ይህ ሊመጣ የሚችለው ልብን በሚያዘጋጅ ፍቅር፣ መታዘዝና ትህትና ነው ፡፡

"አሁን አንድን ነፍስ ከምግብ እንዲፆም ባዘው ያንን የማደርገው ለአንድ መልካም ምክንያት ሲሆን መታዘዙ ደግሞ ያስደስተኛል፡፡ መንፈሳዊ ህይወት ቅዱስ በሚመስል መልክ በተቆለለ ድፍረት የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ወጥመድ ነው፡፡ ለዚህ ነው እኔ ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጠው ፍቅር ነው ብዬ የማስተምረው፡፡ አንድ ሰው በሁሉ ነገር ብቁ፣ ስኬታማ፣ የሚፆም፣ የሚፀልይ፣ ለሌሎች የሚያነባ፣ የእውቀት ቃልን የሚናገር ሆኖ ነገር ግን የወንድማማች ፍቅር ከሌላው፣ ይህ ሰው ዋናውን ነገር አጥቷል፡፡

"ብዙ ተብሏል ነገር ግን ግልፅ ላደርግላችሁ የምፈልገው በመንግስተ ሰማያት ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ተወስኗል፡፡ ቢሆንም ሙሽራዬ ተነስታ በእርሻው ላይ እንድትሰማራና መከሩን እንድትሰበስብ በምድር ላይ ብዙ መቅሰፍቶች ይኖራሉ፡፡ ይህ የማንቂያ ደውል እንጂ የመጨረሻው መለከት መነፋቱ አይደለም፡፡ እባካችሁ በዚህ እንዳትጠራጠሩኝ፡፡ ስለዚህ የምላችሁ ይህንን ነው "እየሄደች እያለችም ትጠንቀቅ"፡፡ በተሰጣችሁ ሥልጣን መሰረት ወደ ሥራ ግቡ፡፡ ለመንግስቴ መከረን ለመሰብሰብ ወደ እርሻው ተሰማሩ፡፡ የጠወለጉትንና ለእነርሱ ያለኝን ትልቅ ፍቅር የማያውቁትን ነፍሳት ወደ እኔ በማምጣት የበኩላችሁን አስተዋፅዎ አድርጉ፡፡

"እኔ ባላሰቀመጥኩላችሁ ሚዛን እየመዘነ ሁልጊዜ የሚከሳችሁን ጠላት በመፍራት ራሳችሁን አታሸማቁ፡፡ እንዲህ አይሁን፣ እናንተ በመታዘዝ እኔን ብቻ ተከተሉ፡፡ መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈፀምም ለራሳችሁ ጣዖትን አታዘጋጁ፡፡ በያማችሁ ጊዜ የኔን መመሪያ ብቻ ተከተሉና ያንን ፍፅሙ፡፡ እኔ ብቻ ነኝ አቅማችሁን መተመን የምችለውና ለእናንተ መልካም ያልሆነውን የማውቅ፡፡ ይህንን አድርጉና በዚህ በእናንተ በደንብ ደስተኛ እሆናለሁ፡፡

"በተጨማሪ በደንብ ማየት ያለባችሁ ነገር በእናንተ አይን "የበለጠ ቅዱስ" ሥራ ነው ብላችሁ በማሰብ መሥራት የያዛችሁትን በመተው በጎን የሚመጣላችሁን ሥራ ለመስራት እንዳትሸወዱ፡፡ በቀደመው ዘመን በቀላሉ ያሸነፏችሁን ወጥመዶች፣ ትህትናና መታዘዝ በቀላሉ ያሸንፏቸዋል፡፡ የኔ ሊጋሮች አሁን ከእኔ ፅድቅ በተወለደ በጉንጉን አበባ ፀጋና ሰላም እባርካችኋለሁ፡፡ ይህም ከእኔ ጋር ያላችሁን ልዩ ግንኙነት እጅግ እንድትተማመኑበትና በትከሻችሁ እንድታርፉ የሚያስችላችሁ ነው፡፡" የጌታ መልዕክት በዚህ ላይ ያበቃል፡፡

አሁን ደግሞ ማዘር ኤሊሻ የተቀበለችውን መልዕክት በስተመጨረሻ አካፍላችኋለሁ ያልኳችሁን አካፍላችኋለሁ፡፡

ማዘር ኤሊሻ መፅሐፍ ቅደሱን ስትከፍት ጣቷ ያረፈበት መልዕክት መፅሐፈ ባሮክ ምዕራፍ 6 ቁጥር 62 በሚለው ላይ ነበር፡፡ " እና እሳት የታዘዘውን ለመፈፀም፣ ተራሮችንና ጫካዎችን ለማቃጠል እሳት ከበላይ ይላካል፡፡" ነገር ግን እነዚህ የውሸት አማልክቶች በአቋምም ይሁን በኃይል በምንም አይስተካከሉትም፡፡" እዚህጋ የሚናገረው እየተካሄደ ስላለው ጣዖትና እሳት ከበላይ ተራሮችንና ጫካዎችን ለማቃጠል ለምን እንደተላከ ነው፡፡

መፅሐፈ ሲራቅ 17፡24- 30 (የካቶሊክ መፅሐፍ ቅዱስ) <u>"ነገር ግን ንስሐ የሚገቡትን ምክንያት ሰጣቸው፣ ተስፋቸውን ያጡ ሰዎችንም ደስ ያሰኛቸዋል፡፡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ ኃጢያትህንም ተዋት፣ ከኃጢያትህ ተመልሰህ በፊቱ ተለማመጥ፡፡ ፊፅመህ ከኃጢያትህ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፣ ኃጢያትን ሁሉ ጥላ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈፅም፡፡ በህይወት ሳሉ እንደሚገዙለት ሰዎች እግዚአብሔርን በመቃብር የሚያመሰግነው ማነው? የሞተ ሰውን ግን ንስሐ እንደ ኢሚንት አለፈው፡፡ በህይወት ሳለህ ደስ እያለህ እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ብዙ ነውና የሚገዙለትን ሰዎች ይቅር ይላቸዋል፡፡ ሰው ሟች ስለሆነ ሰው ሁሉ በህይወት ፀንቶ መኖርን አይችልምና ይቅር ይላቸዋል፡፡</u>"

ይህ ሁሉ የሚያነጣጥረው ስለ አገራችን(ስለ አሜሪካ) ንስሐ መግባት ጉዳይ ነው፡፡ ኒውዮርክ ከተማ ከሁሉም ከተሞች በኮሮና ቫይረስ በከፍተኛ ደረጃ መጣቃቷ ሚስጥር አይደለም፡፡ የዚህም ምክንያት በውርጃ ስለገደሏቸውና ከእናታቸው ማህፀን ሲወጡ ስለቆራረጧቸው ልጆች ነው፡፡ ይህ እጅግ አስከፊ ነገር ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ከሆነ ኒውዮርክ ከሌሎቹ ከተሞቻችን በሚመጣው ፍርድ በከበደ መልኩ ትመታለች ብለን መጠበቅ እንችላለን፡፡

ማዘር ኤሊሺያ . . . ጌታ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ ነገር ግን ማሰብ የምችለው የበለጡ ከባድ አደጋዎች እየመጡ እንደሆነና ይህንንም በተመለከተ ብዙ ሰዎችን ማስጠንቀቅ እንዳለብኝ ነው የምትፈልገው፡፡

ኢየሱስም . . . "የተወደድሽ ሆይ የሚመጡ ነገሮች እጅግ አውዳሚና አጥፊ ናቸው፡፡ ብዙዎች ምን እየተካሄደ እንዳለና ለምን ይህ ነገር እየሆነ እንዳለ ሊገባቸው አይችልም፡፡ የተወደድሽ ይህም የሚፈፀመው ደግሞ አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረበ ነው፡፡ የተኙትን ከእንቅልፋቸው የምቀሰቅሳቸው አለምን ሁሉ ያዳረሰው ወረርሺኝ ሲያበቃ ደግሞ ሌላውን በእግሩ በመተካት ነው፡፡ እስካሁን ሆኖ የማያውቅ አሜሪካን ሁሉ የሚያካልል እሳት ደግሞ በበጋው ወቅት ይከሰታል፡፡

ይህም እሳት ሰብልን እርሻዎችንና ቤቶችን የሚያጠፋ ነው፡፡ መተዳሪያቸውንም በእነዚህ ላይ ያደረጉ ትልቅ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ እንዲሁም የእሳት አደጋ ሰራተኞችና ብዛት ያላቸው አራዊቶቼ በእሳቱ ተቃጥለው ህይወታቸው ያልፋል፡፡

"በዚህ ጊዜም ብዙዎች 'ይህ ሁሉ ሲሆን ጌታ የታለ'? ብለው ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡' እናም ህዝቤ ለእናንተ የምመልሰው ይህንን ነው፡፡እኔ እዚሁ ነኝ፡፡ ሁልጊዜ እዚሁ እንደነበርኩ እናንተ ምላሽ እስክትሰጡኝ ድረስ እዚሁ እየጠበቅሁ ነው፡፡ አሁን ምድር እያለቀላት ነው፡፡ እናም በውስጧ የቀረ መልካም ነገር የለም፡፡ ህይወታችሁ እንደ እንፋሎት የሚበን መሆኑን ስለተረዳችሁ፣ አሁን ለእኔና ለፈቃዴ ሁሉን አሳልፋችሁ ትሰጡኛላችሁ? የታመናችሁበት፣ ተስፋችሁ ፣ኃብታችሁ፣ እንዲሁም ጤናችሁ እንኳን ሊያድናችሁ እንደማይችልና እኔ ብቻ እንደምችል አሁን ተረድታችኋል፡፡

"ህዝቤ ወደ እኔ ጩኽ፡፡ ለእኔ ውድ የሆኑት በታላቅ ትህትናና ፀፀት እኔን ቢጠሩና ከኃጢያት መንገዳቸው ቢመለሱ ምድራቸውን እፈውስ ይሆናል ብዬ እየጠበቋቸው ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎቻችሁ እኔ እንዴት ነው ኃጢያት የሰራሁት እኔ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ፣ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ፣ አሥራቴን እሰጣለሁ ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ የኔ ውዶች ድነታችሁን መፈፀም ከዚያ የሚበልጥ ነው፡፡ ድነት ከኃጢያት ፍፁም ነፃ በመሆን የመኖር ፍላጎት ነው፡፡ የጠራኋችሁ እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱስ እንድትሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት ህሊናችሁን በጥልቅ በመመርመር ወይኑን የሚያጠፉትን ትንንሽ ቀበሮዎችን መቃወምና በዚህም አንፃር ህይወታችሁን መምራታችሁን የሚያመለክት ነው፡፡ በእርግጥ እኔን እየተከተላችሁኝ ነው? ጎረቤቶቻችሁን እንደ ራሳችሁ ትወዳላችሁ? የታመሙትን፣ ድሆችን የተራቡትን ትረዳላችሁ? ይህንን ስል ዝም ብሎ ገንዘብ እዚም እዛም መስጠትን ማለቴ አይደለም፡፡ በእውነት ከልባችሁ ለሌሎችና ለመንግስቴ እየኖራችሁ ነው ወይ እያልኩ ነው፡፡ ወይንስ የምትኖሩት ለራሳችሁና ለቤተሰባችሁ ብቻ ነው? የኔ ውዶች እባካችሁ ንቁ፡፡ ከእንቅልፋችሁ ንቁና ከአሁን ወዲያ አትተኙ፡፡ በአለም ላይ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት አለምን አንድ ጊዜ አናውጣታለሁ፡፡ በእርግጥም መከሩ ብዙ ነው ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡

"ደግሞ አሉ ለእኔ ታማኝ በመሆን በልባቸው በእውነት የሚፈልጉኝና ለጥያቄያቸው መልስ ከእኔ የሚጠብቁ፣ ለእናንተ መልስ አለኝ፡፡ ይህ ጊዜ የኔን ፍቅር፣ የኔን ተስፋና እምነትን በዙሪያችሁ ለሚገኙት ለማካፈል ትልቅ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን በፊታችሁ ያቀረብኩትን ተቆጥሮ የማያልቅ አጋጣሚ ከሃፍረት የተነሳ እንዳያመልጣችሁ፡፡ የኔ ውድ ሙሽሮች ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡ አብዛኛዎቻችሁ እንደደከማችሁ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡ ታላቅ መከርን የመሰብሰቢያ ወቅት ደርሷል፡፡ እንዲያውም ጀምሯል፡፡

ማዘር ኢሌሻ . . . ጌታ እባክህ እርዳን፡፡ እኔን እርዳኝ ምክንያቱም በእውነቱ ከሆነ የአንተ ሆነው እጅግ ከደከማቸው አንዷ ነኝ፡፡ በእምነትና በትልቅ ተስፋ ተነስተን ለመቆም እንድንችል አጠንክረን፡፡ ይህንንም የምንጠይቀው ለእኛ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያችንም ላሉ ጭምር ነው፡፡

ኢየሱስም . . . "አዎ የኔ ውድ በዚህ ጊዜ በትልቅ ብርታትና እምነት መነሳት ላለባቸው በእርግጥም ፀጋን እየለቀቅሁላቸው ነው፡፡ የልብሽን ጭንቀትና ስጋት እየሰማሁት ነው፡፡ የተወደድሽ ሆይ ቃል የገባሁልሽ ሁሉ በትርምሱ ጊዜ እንኳን ቢሆን ይፈፀማል፡፡ ከአመድ ውበትን እንደማወጣና ከተበላሸ ነገር ድንቅ ነገርን መፍጠር እንደምችል አስታውሺ፡፡ ስለዚህ በትርምሱ መካከል የምሰራውን ሥራ የሚመለከት ሰው ሁሉ ታማኝነቴን ይመሰክራል፡፡" ማዘር ኤሊሻ ከጌታ የተቀበለችው መልዕክት እዚህ ላይ ያበቃል፡፡

ተመሳሳይ መልዕክት የተቀበለ አንድ ወጣት አለ፡፡ ይህ ወጣት ወደ እኛ እንዲመጣ ጋብዤው ሁሉ ነገሩን እርግፍ አድርጎ ትቶ ከእኛ ጋር የተቀላቀለና እጅግ የሚደንቅ ሥራ እየሰራ ያለ ልጅ ነው፡፡ ጌታም በዚህ ወጣት በኩል እየተናገረን ነው፡፡ ጊዜ ካለ የእርሱን መልዕክት ደግሞ በሌላ ጊዜ አካፍላችኋለሁ፡፡

አሁን ግን የምላችሁ እባካችሁ ፀልዩ፡፡ በራዕይ መፅሐፍ እሳት ከሰማይ እንደሚወድቅ ልታውቁ ይገባል፡፡ ይህም ደግሞ አሁን ሊጀምር ነው፡፡ እንዳውም በአንዳንድ ቦታዎች መውደቅ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን እንደዚህ አይነት ዜና ከመገናኛ ብዙሃን አታገኙም፡፡ እስካሁን ብዙ አልወደቀም ነገር ግን ከአሁን ወዲያ እየጨመረና እየፈጠነ ሊመጣ ነው፡፡ ስለዚህ በቤታችሁ ሆናችሁ ፀልዩ፡፡ የንስሐ ህይወት ይኑራችሁ፡፡ የህይወት አቅጣጫችሁን አስተካክሉ፡፡

ዛሬ የጌታ ራት ቀን ነው፡፡ ለማንበብ ሬማ የተሰጠን ቃል ሁሉም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የሚናገሩ ናቸው፡፡ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ንስሐ ግቡ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ የሚል ነው፡፡

ኸርት ድዌለርስ ሁላችሁንም እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡ እስካሁን እኛንና መጠለያውን እየተከባከባችሁን ስላላችሁ እናመሰግናለን፡፡ በዚህ አንዳንድ መልካም ነገሮች እየተከናወኑ ናቸው፡፡ ወደፊት እነዚህን አካፍላችኋለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ለአሁን ግን ጌታ ፊቱን ያብራላችሁ፣ በክንዱ ደግፎ አቅርቦ ይያዛችሁ፣ ሰላሙን ይስጣችሁ፡፡ ደግሞም ለሚመጣው ነገር ልባችሁን አዘጋጁ፡፡ ይህም በእርሻው ላይ ተሰማርታችሁ ለተራቡት ፣ለተጠሙት፣ ለተጎዱትና አስተዋሽ ላጡት ተነስታችሁ እንድትሰሩ ነው፡፡

## በዋይት ኃውስ አደጋ እያንዣበበ ነው - ሜይ 15 ቀን 2020 ዓ.ም

## Doland Trump in a cascette- May 15- 2020

ከልብ በሆነ ፍቅር ለዚህ አለም መፀለይ እንድትችሉ የእግዚአብሔር አብ ልብ በእናንተ ውስጥ የእርሱ ቅዱስ ልብ ደግሞ በእናነተ ውስጥ ይሁን፡፡

ውድ ቤተሰቦች አንድ እውነተኛ ታሪክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ ፡፡ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አንድ ሚስትና ልጆች ያሉት መጋቢ መንጋው እንዲያድግለትና እንዲበለፅግለት በማሰብ የተለያዩ ነቢያትን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጋብዝ ነበር ። ታዲያ በወቅቱ ብዙዎች መጥተው ከፓስተሩ ጋር ከፀለዩና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የነብያቶቹ ፊት መኮሳተርና ህመም ይታይበት ነበር።

ይህ ነገር በእንዳንዳቸው ነብያቶቹ ላይ ከታየ በኋላ ለመጋቢው በተደጋጋሚ እንደዚህ ብለው ይነግሩት ነበር፡፡ “ልጅህ እንደምትጠለፍ ጌታ እየተነገረኝ ነው፡፡ ይህንን ነገር ልነግርህ ይገባል"። ወይም ደግሞ "ሴት ልጅህ በጣም አደጋ ላይ ናት ፣” እያሉ ሁሉም ነቢያት ይህንኑ የትንቢት ቃል ይነግሩት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ ታዲያ ፓስተሩ እና ሚስቱ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ምህረት ላይ በመጣል ልጃቸውን ጥበቃ እንዲደረግላት ተጨማሪ ጥንቃቄን በመውሰድ ይጸልዩላት ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ለብዙ ወራት ነብያት ወደ ቤተክርስትያኑ ሲመጡ ፣ ዓይኖቻቸው በእምባ ይሞላና ለፓስተሩ እና ለሚስቱ ይህንን ትንቢት በተመሳሳይ መልኩ “ጌታ ይህንን እየነገረኝ ነው፣ ልጃችሁ ትጠለፋለች።” ይሏቸው ነበር፡፡ ይህ

ትንቢት በተነገራቸው ቁጥር ፓስተሩ እና ሚስቱ ሳያቋርጡ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ በመጣልና በመፀለይ ደግሞም ቅድመ ጥንቃቄዎችን በማድረግን ይቀጥሉ ነበር፡፡ በመጨረሻም የአደጋው ጊዜ አለፈና ልጃቸው ቆንጆ ሴት ሆና አደገች። አያችሁ ጌታ ወደፊት ሊመጡ ስላሉ አሳዛኝ አደጋዎች በቅድሚያ ያስጠነቅቀናል፡፡ እናም እሱ ይህንን ሲያደርግ እኛ ደግሞ ምህረቱን መለመን አለብን።

ይህንን ለእናንተ ለኸርት ድዌለርስ ያካፈልኩበት ምክንያት በህልሜ በተደጋጋሚ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በኋይት ኃውስ ሞላላው ቢሮ ውስጥ በሬሳ ሣጥን ውስጥ ሆኖ በማየቴ ልቤ ስለታመመና ትልቅ ሸክም ስለሆነብኝ ነው። ይህንን ለእናንተና ለእኔም ለጥልቅ ነፍስ የማቀርበው ጥያቄ "ይህ እንዲከሰት እንፈቅዳለን ወይ?" የሚለውን ነው። ውድ አምላኬ ሆይ የመለኮታዊ ምህረት የሚለውን ፀሎት/the Divine Mercy chaplet/ በመፀለይና በየአስርቱ ፀሎት መጨረሻ ላይ ሶስት ጊዜ ደጋግመን "አባት ሆይ እባክህ የበለጠ ጊዜ ፣ የበለጠ ፀጋ ፣ የበለጠ ምህረት ስጠን" ብለን በመፀለይ ይህ አስከፊ ነገር እንዳይከሰት ማቆም እንችላለን? ይህንን በእንባዎቻችን ጅረት ማቆም እንችላለን? የእኔ ውዶች፣ እናንተ በኢየሱስ ልብ ውስጥ የምትኖሩ እና እርሱም በልባችሁ ውስጥ የሚኖረው፣ ፕሬዚዳንታችንን ለመታደግና ሀገራችን ከዚህ የጨለማ ዓለም ኃይል ማንፃት እንድንችል በማንኛውም መጠን እግዚአብሔርን መለመንና ምልጃ ማቅረብ ትችላላችሁ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ሕዝቤ ሆይ ፣ ሕዝቤ ሆይ ፣ በዋይት ኃውስ ላይ አሳዛኝ ነገር እያንዣበበ ነው። ይህ ጊዜ ጨለማ አሜሪካን እያስጨነቀ ያለበት ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ምን ልታደርጉ ነው? ይህ እንዲከናወን ትፈቅዳላችሁ? ጥግ ላይ በመቆም አገራችሁን ጨለማ እንዲወርሰው ትፈቅዳላችሁ? ምን ልታደርጉ ነው?? ይህ አዋጅ የወጣው ሕዝቦቼ ኃጢያተኛ ስለሆኑና ለከንቱ ሥራዎቻቸው ንስሐ ባለመግባታቸው የተነሳ ነው። አሁን በዚህች ሰዓት ሁላችሁም ከአለማዊ መንገዶቻችሁ ንስሐ እንድትገቡና በህይወታችሁ አዲስ ውል መግባት እንድትችሉ እየጠራኋችሁ ነው፡፡ በጽድቅ እንጂ በከንቱ ሥራዎች ህይወት ተሟልቶ ሊቀጥል አይችልም። ህዝቤ በበራችሁ ላይ መከራ ቆሟል፡፡ በኃብትና በአለማዊ ቁሳቁሶች በመማረካችሁ ምክንያት ንስሐ ትገቡ ይሆን? ፅድቁና መንግሥቴ እንዲመጣ ትፈልጋላችሁ? የእኔ ፈቃድስ እንዲፈፀም ትፈልጋላችሁ? ኃብት እና ብልጽግናን ስላመለካችሁ ንስሐ ብትገቡ፣ ለጽድቅ እና ለፍትህ የቆመች ሃገርን ለመፍጠር ከፍተኛ የንስሐ እርምጃ ብትወስዱ አባቴ ይህንን ተመልክቶ ምናልባት ከሚመጣው ፍርድ ሊያድናችሁ ይችላል።

"ከራሳችሁ ወጥታችሁ ድሆችን እንዲሁም ለመኖር እየተፍጨረጨሩ ያሉትን ትንከባከባላችሁ? የተራቡትን ትመግባላችሁ? ፣ ድሆችን ታለብሳላችሁ? እንደ መልካም እናትና አባት በመሆን የሰው ልጅን ትንከባከባላችሁ? እኔ ለዚህች አገር ብዙ ኃብት ሰጥቻለሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን የሰጠሁት ለከንቱ ሥራዎች እንዲውል ሳይሆን ድሆችን ለማጽናናትና ለመኖር እየታገሉ ያሉትን ሰዎች ኃብት በማካፈል እኩልነት እንዲመጣ በማለት ነበር ፡፡ በዚህች አገር ላይ ፕሬዚዳንታችሁ ጨለማን ለማሸነፍ የራሱንና የቤተሰቡን ሕይወት ከፍተኛ አደጋ ላይ በመጣል አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰዱ ምክንያት ትልቅ ለውጥን አይቻለሁ፡፡

"ነገር ግን ይህ ተግባር ላይ ላዩን ብቻ በማየት የሚገመገም አይደለም ፡፡ ወደ ውስጥ እየጠለቀ በሄደ ቁጥር ብልሹነቱና ሙስናው እየጨመረ የሚሄድ ነው። የትምህርት ሥርዓቱ ወጣት አሜሪካውያን በነፃነት ሰበብ እግዚአብሔራዊ ካልሆኑ አጀንዳዎች ጋር እንዲስማሙ አዘጋጅቷቸዋል። እርሱ ብዙ መልካም ነገሮችን አድርጓል፡፡ እናም የእናንተ ፀሎት በሕይወት እንዲኖርና ሥራውን እንዲቀጥል አድርጎታል።

"የዚህ ሕዝብ ልብ ከዓለም እንዲዞርና እሴቶቹ በቤተሰብና በአምላክ ላይ እንዲሆን ለማድረግ አባቴ ብዙ ብዙ ክስተቶችን ልኳል። ነገር ግን ሰዎች ትኩረታቸውን በገንዘብና በታላቅነት ላይ በማድረጋቸው በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ተላልፈዋል፡፡ በዚህም ዶላርን ለማምለክ ፈጥነው ወስነዋል ፡፡ በኮቪድ ማዕቀቦች እንኳን እውነተኛው ትኩረት ተጋርዶባቸው አሁንም አሜሪካን እንደገና ታላቅ እናደርጋታለን በሚል መፈክር ላይ ናቸው፡፡ እኔ ግን የምላችሁ አሜሪካን ቅዱስ አድርጓትና ከዚያ ብልጽግና ይከተላል። ነገር ግን ይህ የሚሆነው እንደገና በገንዘብና በንብረት ማጋበስ እንድትበላሹ መሆን የለበትም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ስልጣኔ ራሱን ያጠፋው በዚህ መንገድ ስለሆነ ነው።

"ዓለም አሁን በጥፋት አዝቅት ውስጥ ትገኛለች፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ አሁን ቢሞት አሜሪካን በብሔራዊ ብጥብጥና እርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ትሆናለች፡፡ ይህ እንዲከሰት ትፈቅዳላችሁ? ይህ እንዳይሆን አስቸጋሪ ወደሆነው ፀሎት እየጠራኋችሁ ነው። ራሳችሁን አመድ ነስንሳችሁ፣ ማቅ ልብስ ለብሳችሁ ለምህረት ጮኹ፣ ተጨማሪ ፀጋ ፣ ተጨማሪ ጊዜና ተጨማሪ ምህረት እንዲደረግ እንድትጮኽ እየጠራኋችሁ ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ የተፈጥሮ አደጋዎች በበራችሁ ላይ ናቸው፡፡ እንዲሁም የአለምን ህዝብ ቁጥር ፍፁም በሆነ መልኩ በመቀነስ አለምን ማሸነፍ እንችላለን ብሎ ባመነ ጠላት የተመረጡ ምሑራን ብቻ እስከሚቀሩ ድረስ በሚደረግ ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የተነሳ ህይወት ከንቱ ትሆናለች።

"ሕዝቤ ሆይ ፣ ከዚህ በፊት በጭራሽ ጮሃችሁ የማታውቁትን ያህል በፀሎትና በምልጃ ወደ እኔ እንድትጮሁ እየጠራኋችሁ ነው። ዶናልድ ትራምፕ በሬሳ ሣጥን ውስጥ ሆኖ የታየው ራዕይ ምህረትን ለመለመን፣ እንባችሁንና ፀሎታችሁን ለማበረታታት በቂ መሆን አለበት። ፀሎት ነገሮችን ይለውጣል ፣ ነገር ግን የፕሬዚዳንታችሁን ሞት ሊያስቀር የሚችለው በአንድነትና ከልብ በሆነ የፍቅር ስሜት የሚገለፅ ፀሎት ብቻ ነው። ለእርሱና ለራሳችሁም የወደፊት ህይወት በፅናት ብትለምኑ ምናልባትም አባቴ የፕሬዝዳንታችሁን የስልጣን እድሜ ያራዝመው ይሆናል።"

**ኮረና ቫይረስ ክትባቱ ውሎ ሲያድር ስለሚገድላችሁ አትውሰዱ - ሜይ 15 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Trust in Me alone- May 15, 2020**

**(Message from Nana)**

(ናና):- ወንድሞችና እህቶች እንዴት ናችሁ? የዩ ቲዩብ ቤተሰቦች እንደተባረካችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

አሁን የማካፍላችሁ በተከታታይ ስላየኋቸው ህልሞች ነው፡፡ ከእነዚህ ሁለቱ ደግሞ ጌታ ስለ ኮሮና ቫይረስ የተናገረኝ ነው፡፡ ልክ ከእንቅልፌ ስነቃ በመንፈሴ "ለደህንነት በእርሱ ምህረትና መልካምነት ላይ ተደገፊ እንጂ በክትባት ላይ አይሁን፡፡" የሚል መልዕክት ይዤ ተነሳሁ፡፡ ቢሆንም ግን በጣም ደክሞኝ ስለነበር እርሱ እየተናገረኝ እያለ ለተጨማሪ ሁለት ሰዓታት እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ፡፡ ከእንቅልፌም ስነቃ ወደ እርሱ ቀረብኩና ወዲያው እንዲህ አልኩት፡፡

ጌታ ወደ አንተ የቀረብኩት እጅግ በጣም አርፍጄ ነው በጣም አዝናለሁ ይቅር በለኝ፡፡ ኢየሱስ ልትነግረኝ የፈለከው ነገር አለ?

ኢየሱስም እንዲህ ሲል ጀመረ . . . "የኔ ውድ እየጠራሁሽ ያለሁት የኔን ህዝብ እንደገና እንድታስጠነቅቂልኝ ነው፡፡ እንዴት እንደደከመሽ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እያሰለጠንኩሽ ያለሁት ትጋት የሚያስፈልገው የሥራ መስክ ሥነ ምግባርን ነው፡፡ ይህም በድካምሽ ጊዜ በእኔ ፀጋ ላይ ብቻ እንድትደገፊ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚገባሽና የምታመሰግኚኝ እጅግ ቁይቶ ነው፡፡ ይህም ተልዕኮሽን ስትፈፅሚ ብዙ ረዥም ሌሊቶችን ስለምታሳልፊ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ እኔ ከአንቺ ጋር ስለምሆን ሰውነትሽ ቢዝል እንኳን ወደፊት እንድተቀጥዪና ብዙ እንድትሰሪ አስታውስሻለሁ ደግሞም ፀጋዬን እሰጥሻለሁ፡፡ ጥንካሬ የኔ ውድ፣ ፅናት፡፡

"አሁን ወደ ህዝቤ ልመለስ፡፡ ህዝቤ እባካችሁ ይህንን ማስጠንቀቂያ ተቀበሉ፡፡ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት የተዘጋው ሲከፈት ብዙ ክትባቶችና መድኃኒቶች ለሙከራ ይቀርባሉ፡፡ ቫይረሱ ይሰራጫል በሚል ፍራቻ ክትባቱን በፍጥነት ለመስጠት ይሯሯጣሉ፡፡ ሰዉም ቫይረሱ እንዳይዘው በመፍራት ክትባቱን ለመውሰድ ይጣደፋል፡፡ አንዳንዶች እንዳሉት ይህ የአውሬው ምልክት አይደለም፡፡ የአውሬውን ምልክት የማድረጊያ ጊዜ ገና አልደረሰም፡፡ ነገር ግን ይህ ክትባት የሚያደርገው በሽታ የመከላከል አቅማችሁን ከመገንባት ይልቅ ከፉኛ ይጎዳዋል፡፡ በሽታ የመከላከል አቅማችሁን ስለሚሰብረው እነሱ በሚቀጥለው አዘጋጅተው ወደ አገራችሁ ሊያሰራጩ ያሉትን ወረርሺኝ ለመቋቋም እንዳትችሉ ያደርጋል፡፡ ይህ አሁን ካለው መንግስትና  ፕሬዚዳንት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ይህ የሚመለከተው ከእርሱ በፊት የነበረውን ነው፡፡

"ህዝቤ ማስታወስ ያለባችሁ እነርሱ ይህንን ያቀዱት እጅግ ቀደም ብሎ ነው፡፡ የአለም አቀፉን ስርዓት እቅድ ለማስፈን ይጠብቁ የነበረው ትክክለኛ ጊዜ ይህ ጊዜ ነበር፡፡ የጥልቁ መንግስትና ብዙ የሰይጣን አገልጋዮች ተናደዋል፡፡ ምክንያቱም በሥልጣን የሚወጡበትን ጊዜ ለማፋጠን ብለው ይህ አገርና አለም ሁሉ እንዲቀበላቸው ለማስገደድ ሊጠቀሙበት ያሰቡትን እያንዳንዱን ጥቃት፣ እያንዳንዱን እቅድና አደጋ ስላከሸፍኩባቸው ነው፡፡ ነገር ግን እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩና ሁሉንም እንደምቆጣጠር ረስተውታል፡፡ እነርሱም እንኳን በእኔ ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶችና ወቅቶች እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ የፈቀድኩት የመንግሰተ ሰማይ ስልጣኔን በመጠቀም እኔ ባልኩት መጠን በመሥራት ህዝቤን ለማንቃትና የጠፉ ብዙ ነፍሳት ወደ አይምሮአቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ነው፡፡

"አገራት ለምን ተቆጡ? በመጨረሻ አሸናፊው በእርግጥ እኔ ብሆንም የምድር ነገስታት ጦርነት ለመግጠም ለምን ወጡ? የኔ ህዝብ ይህ ማለት ግን እኔ ቶሎ አልመጣም፣ ክስተቱም የተፈቀደው ህዝቤን ለማንቃት አይደለም የሚለውን ሐሳብ አያስተናግድም፡፡ ያንን ክስተቱ ሲፈፀም አይታችሁ ታምናላችሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን እላችኋለሁ አትፍሩ፡፡

"ይህ ጊዜ ነገሮችን እንደተለመደው የምታካሂዱበት ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ ጊዜ ነገሮችን ድሮ በምታደርጉበት መንገድ ለማድረግ የምታስቡበት ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ ጊዜ የዚህን አለም ነገር በተለመደው መልኩ የምታሽከረክሩበት ጊዜ አይደለም፡፡ የኔ ውዶች እንደዚህ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ ጊዜ እንደገና ወደ ግብፅ መመለሻ ጊዜ አይደለም፡፡ ሁላችሁንም እየጠራኋችሁ ያለሁት ከዚህ የአለም እስራት ነፃ ወጥታችሁ ወደ ልቤ እንድትገቡ ነው፡፡ እኔ እየጠራኋችሁ ያለሁት በህይወታችሁ፣ በድነታችሁና በቤተሰቦቻችሁ እጅግ አስፈላጊው ነገር ምን እንደሆነ እንድታዩ ነው፡፡ ለመሆኑ ልጆቻችሁ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ አጢናችኋል? የእናንተን መመሪያና ጥበብ ምን ያህል እንደሚፈልጉ ታውቃላችሁ? እንዴት በቶሎ እንደሚያድጉና አለም ወይም እኔ በእናንተ በኩል እንደምናስተምራቸው አትገነዘቡም? ለመሆኑ ልጆቻችሁን እንዴት እንዳጣችኋቸው ለአንድ ደቂቃ እንኳን አስባችሁ ታውቃላችሁ? ሁልጊዜ ሥራ ላይ በመሆናችሁ? ሥራን ብቻ ትኩረት

በማድረጋችሁ? የተደላቀቀ ኑሮ ለመኖር ትኩረት በማድረጋችሁ? ከዚህም የተነሳ ልጆቻችሁን ራሳችሁ ማሳደግ ሲገባችሁ ለትምህርት ቤት አሳልፋችሁ መስጠታችሁ? የተወደዳችሁ እነዚህን ነገሮች አስተውላችሁ ታውቃላችሁ?

"በኮሮናው ምክንያት አቤት እንድትውሉ የፈቀድኩበት ምክንያት ህዝቤ ከሚያየውና ከሚያመዛዝነው በላይ እጅግ ጥልቅ ነው፡፡ ይህ ጊዜ በእውነትም ራሳችሁን የምታዩበትና ለእነዚህ ትናንሽ ነፍሶች ተጠያቂ የምትሆኑበት ነው፡፡ የእኔን መንገድ ነግራችኋቸዋል? ነው ወይስ በቴሌቪዢን ፊት ተቀምጠው፣ እንዲሁም የዚህን አለም መፅሐፍ በማንበብ ከእነርሱ እንዲማሩ ነው ያደረጋችሁት? ለመሆኑ የትዳር አጋሮቻችሁ ምን ያህል ውድ እንደሆኑ ተመለከታችሁ? ደግሞስ ፍቅራችሁ፣ ማፅናናታችሁ፣ ማበረታታችሁና ምሪታችሁ  ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸው አያችሁ? ሁለታችሁ እንዴት እየተራራቃችሁ እንደነበርስ ተገነዘባችሁ?

"መሰለቻቸትና ደስተኛ ያለመሆን ሐሳብ እንዴት እያደባ ይህ ደግሞ ምኞትን አምጥቶ በመጨረሻ ከውጪ ሌላ ግንኙነት እንዴት እንደሚጀመር ተገንዝባችኋል? ባሎቻችሁ ወይም ሚስቶቻችሁ የኔ ስጦታዎች እንደሆኑ ተገንዝባችኋል? ስለዚህም ባሎች እኔ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደድኩና ነፍሴንም ለእርሷ አሳልፌ እንደሰጠሁ ሚስቶቻችሁን እንዲሁ ውደዱ፡፡ ሚስቶችም ባሎቻችሁን ውደዱ፣ ለእኔ እንደምትገዙም ተገዙላቸው፡፡ በትዳር ውስጥ ይህንን የሚፈፅሙትን አከብራለሁ፡፡ እነዚህን ተግባርና ጥበብ ከሁለት አንዳችሁ ቢፈፅም እኔ ትዳሩን እባርካለሁ፡፡ ስለዚህ የኔ ውዶች እኔ የምጠራችሁ ነፍሳችሁንና ቤተሰባችሁን በጥልቅ እንድትመረምሩ ነው፡፡ ወደኋላ ተመልሳችሁ ነገሮች እንዴት እንደነበሩ አትመልከቱ፡፡ ምክንያቱም ያ ለጥፋት የተጋለጠ መንገድ ነበር፡፡ ነገር ግን ልባችሁን ወደእኔ መልሱ፡፡ ምሳሌ በመሆንም የቤተሰባችሁን ልብ ወደእኔ መልሱ፡፡ ከአሁን ወዲያ በምታዩት፣በምትሰሙት፣ በምታነቡትና ከሰው ጋር በምትነጋገሩት ነገር ሁሉ አለምን ወደ ቤታችሁ አታስገቡ፡፡ ነገር ግን ትኩረታችሁን ሁሉ በእኔ ላይ እና አንዳችሁ ለአንዳችሁ ባለ ፍቅር ላይ አድርጉት፡፡

"የኔ ውዶች በምንም አይነት ቢሆን ክትባቱን እንዳትወስዱ፡፡ ይህ እስከዛሬ እንደተደረገው አሁንም የታቀደው ቤተሰብ የሚለውን ለማጥፋት ነው፡፡ የምትወጉት ከእናንተ እውቀት በላይ በሆነ ነገር ነው፡፡ ይህም ቀስ በቀስ ይገላችኋል፡፡ ለመዳናችሁ በእኔ ምህረትና መልካምነት ላይ ብቻ ተደገፉ፡፡ ወረርሽኙ ወደ መኖሪያችሁ ቢመጣ እንኳን እንደማድናችሁ ታመኑ፡፡ አምላኩን የሚያውቅና በአምላኩ የሚተማመን  ህዝብ ሁኑ፡፡"

## የፍርስራሾች ደመና - ሜይ 18 ቀን 2020 ዓ.ም

## Debris from the sky - May 18, 2020

ውድ ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ እንዲሁም ይጠብቃችሁ፡፡ ቻነላችንና ምሽጋችንን በደግነታችሁ ስለደገፋችሁ ለማመስገን እፈልጋለሁ። እኛ በየዕለቱ አንዳችን ከአንዳችን ብዙ ነገሮችን እየተማርን እንገኛለን፡፡ እናም ለማመን በሚከብድ መጠን እጅግ አፍቃሪና ደጋፊ በሆኑ ሰዎች ተባርከናል። ብዙዎችም በአገልግሎታቸው ወደፊት እየተጓዙ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዩኒቨርሲቲ በተጀመረ ቀን ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ ወደ እኛ የመጣው ወጣት ይገኝበታል፡፡ ይህም ወጣት በሕብረተሰቡ ውስጥ ቃል በመግባት የራሱን አገልግሎት  በመጀመር ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማበብ መጀመር ነው።  እኛ ጌታ እዚህ እያደረገ ባለው ነገር እጅግ ተደስተናል፡፡ ለዚህ ደግሞ እናንተም ተካፋዮች ስለሆናችሁ እናመሰግናለን።

አሁን ሕዝቅኤል ያየውን ህልም ለእናንተ ለማካፈል እፈልጋለሁ ፡፡ ከመጀመሬ በፊት ከሰማይ የሚወረወሩት የእሳት ኳሶች የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ከፍርስራሹ ደመና በፊት መጀመሪያ መሆኑን መናገር እፈልጋለሁ። የሥነ ከዋክብት ተመራማሪዎች (astronomers) የመጀመሪያዎቹን ደረጃዎች በመመልከት ይህ ደመና በምድር ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለማስላት አሁንም እየሞከሩ ነው። እነርሱ እንደሚሉት ከባዱ ተጽዕኖ የሚጀምረው ከ 30 እስከ 60 ቀናት በኋላ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ የሚሆነው ከሰኔና ከሐምሌ በኋላ ይመስለኛል፡፡ እስካሁን በምድር ላይ ካረፉት ጥቂት የእሳት ኳሶች በመነሳት በፊት ከተጠበቀው በላይ ትንሽ ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን ከአሁን በኋላ የሚሆነው ነገር እጅግ ሰፊ ስለሚሆን ምን እንደሚያስከትል አናውቅም።

ነገር ግን ሕዝቅኤል ስለዚህ ጉዳይ ከመንፈስ ቅዱስ መልዕክት ተቀብሏል፡፡ በህልሙም ከተራራው በታች በታኦስ ውስጥ የሚያገለግላቸውን ነፍሶች በመፈለግ ላይ ነበር፡፡ እነዚህም ነፍሶች በደቡብ በኩል በከተማይቱ መጨረሻ በሚገኝ ክሊኒክ ውጭ ተሰልፈው ነበር፡፡ እናም ደግሞ ሰዎች በየቦታው መንገዱን ሞልተውት ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች አብዛኛዎቹ ግራ የተጋቡ፣ ምን እየሆነ እንዳለና ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የማያውቁ ነበሩ፡፡ ከተለመደው በላይ በመንገዱ ላይ የሚጓዙና ወደ ክሊኒኩ ለመግባት  ተሰልፈው ተራ የሚጠብቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከመጠለያው  የመጣን እንዳንዶቻችን ደግሞ ምግብ በመስጠትና  ልዩ ልዩ መገልገያዎችን ለተለያዩ የከተማው ክፍሎች በማሰራጨት እየረዳን ነበር ።

በተጨማሪም ሕዝቅኤል የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያውን ጎብኝቶ በማንኛውም መልኩ ሊረዳቸው የሚችለው ነገር ካለ ሲጠይቃቸው በፍጥነት ተቀበሉትና የእሳት አደጋ ሰራተኞች የሚለብሱትን ጃኬትና ቦቲ ጫማ ሰጡት፡፡ ነገር ግን ልብሱ ምንም ምቾት አልሰጠውም ነበር። ሕዝቅኤልና የእሳት አደጋ ሰራተኞቹም በእሳት አደጋ መኪናው ወደ ታኦስ ሰሜናዊ ዳርቻ ሄዱ፡፡ በመንገዳቸውም ላይ ሊያቃልሉት የማይችሉት ከባድ ሁኔታ ገጠማቸው፡፡ አብረውት የነበሩትም ሰዎች እየተፈጠረ ያለው ነገር ምን እንደሆነ አልገባቸውም ነበር፡፡ የመንገዱ ጉዳት ሲታይ፣ የተቃጠሉት ቤቶች ሁኔታ እንዲሁም አጠቃላይ የጥፋቱ ሁኔታ ሁሉ የወደቁት የእሳት ኳሶች በከባድ ሁኔታ መዝነባቸውን ግልጽ አድርጎታል። ታኦስ በጭራሽ እንደድሮዋ አልነበረችም ፡፡

ህዝቄኤልም ከእሳት አደጋ መኪናው በመውጣት አገልግሎት ከሚፈልጉት ሰዎች ጋር መሆን እንዳለበት ስለተገነዘበ ከመኪናው ወረደ። ሰዎች በክሊኒኩ በር ላይ በሰልፍ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ሁለት ጊዜ  በኮቪድ የሞቱ ሰዎች አስከሬን ወደ አምቡላንስ ሲያስገቡ አዩ፡፡ በዚህም ምክንያት አካባቢው ሁሉ በተስፋ መቁረጥና ግራ በመጋባት ድባብ ተሞላ፡፡ ሕዝቅኤልም በመንገድ ላይ የነበሩ ከጠፉና ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ከማያውቁ፣ እግዚአብሔር ምን እያደረገ እንደሆነና ለምን ይህን ሁሉ እንደፈቀደ ፍንጭ ከሌላቸው ብዙ ሰዎች ጋር አብሮ በመሆን ሲያፅናናቸው ነበር። ህልሙ እዚህ ላይ ያበቃል፡፡

የተወደዳችሁ ጌታ በንጥቀት እኛን ለመውሰድ ከመምጣቱ በፊት የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ/Revival/ የሚኖረን ከሆነ፣ ሰዎች "እግዚአብሔር ለምንድን ነው ይህንን እያደረገብን ያለው?" የሚል ጥያቄ ጠይቀው መልስ ለማግኘት ይራቡ ዘንድ እኛ ከምቾቶቻችን መውጣት አለብን። በዘመኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተሰራፋው የሊብራሎች አጀንዳ ትክክል እና ስህተት የቱ እንደሆነ የማይለዩ በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሶችን አፍርቷል። በተለምዶ ተቀባይነት ያለው የሥነ ምግባር ጉድለት መለኪያ እግዚአብሔር ለምን እንደሚቀጣቸው እንኳን ለማወቅ ግራ አጋብቷቸዋል። እናም እንዲህ ይላሉ 'እኛ ጥሩ ሰዎች ነን፣ ወደ

ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፣ አሥራትም እናወጣለን፡፡ ይህ በእኛ ላይ የሆነው ለምንድን ነው?'፡፡ እግዚአብሔር ሆይ በአገልግሎታችን ኃጢያትን ኃጢያት ብለን ካልጠራን፣ ነገር ግን ሕዝቡን ለማስደሰትና ከእነርሱ የምንፈልገውን ገንዘብ ለመቀበል ብቻ አገልግለን ከሆነ እባክህ እርዳን፡፡

ክሌር ፦ ጌታ ሆይ የምትነግረን ነገር አለ?

ኢየሱስም እንዲህ አለ "የተወደዳችሁ ኸረት ድዌለርስ፣ የልቤ ሰዎች ይህ እየተፈቀደ ያለው ነገር "ሁሉም እንደተለመደው ይቀጥላል" የሚሉትን ሰዎች ወደ ውስጥ ሰብሮ ለመግባት ነው፡፡ ከሰማያት ከተለቀቁት ከእነዚህ ከእያንዳንዳቸው ምልክቶች እንኳን ነገሮች በፍፁም ልክ አይደሉም፡፡ እኛ እየሞከርን ያለነው ህሊና ያጡ ሰዎች ከክርስቲያኒያዊ ስነ ምግባር ይልቅ የተማሩትን የአሜሪካን ባህላዊ ስነ ምግባር በማስቀደማቸው የእነርሱን ትኩረት ለመሳብ ነው። ሰዎች ባህላቸውን ሃይማኖት አድርገውታል።

"በአሁን ጊዜ በዓለም ዙሪያ እየተከናወነ ያለው ነገር ምድር በቆሻሻና በኃጢያት ውስጥ እንድትዋኝ የተደረገችበት የላላ የሥነ ምግባር ውጤት ነው፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በሰማይ ያለው አባቴ እየሆነ ያለውን ነገር ካልፈቀደ፣ ትዕይንተ አለሙ ራሱ/ the cosmos/ ሁከት ያስከትላል፡፡ ይህም ሥነ ምግባር የጎደላቸው ሰዎች መንገድ እጅግ መጥፎ መሆኑን ያሳያል፡፡

"ህዝቤ ሆይ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር መቼም አትጠራጠሩ ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ለምን መከናወን እንዳለባቸው ባትረዱም እንዲሆኑ መፈቀዳቸው ግን ለላቀ ዓላማ እንደሆነ አትጠራጠሩ። ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንደሚኖር ነግሬያችኋለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁበት ምክንያት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችሁን ትታችሁ ከእርሻው ቦታ መከርን ለመሰብሰብ የተሻለ ጊዜ እንድትሰጡ ስለምፈልግ ነው።

"የተለመዱ የዕለት ተዕለት ተግባሮች ሲታገዱ ወንድምና እህቶቻችሁን ስለ እኔ ታላቅ ፍቅር ለመንገር ብዙ ጊዜ ታገኛላችሁ፡፡ ለዚህ ዝግጁ ናችሁ? በሕይወታችሁ ውስጥ የሚገኙ ነገር ግን መንግሥቴን ወደ ምድር ከማምጣትና ነፍሶችን ከማዳን ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ብዙ ነገሮችን ትተዋላችሁ? እያንዳንዳችሁ ልባችሁን እንድትመረምሩና መንፈስ ቅዱስ በፊታችሁ የሚያስቀምጣቸውን ዕድሎች ለማየት እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ጠይቁ፡፡ ነገሮች እየተጋጋሉ ሲሄዱ እነዚህም በብዛት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

"አሁን ሂዱና የኔን ጥያቄዎች በማሰላሰል በእያንዳንዱ ጊዜ ፍቅሬን ለነፍሶች ለማካፈል እድሉን እንድታገኙ በፀሎት አቅርቡ። ወደ ውጪ ስትወጡ "ጌታ ዛሬ የአንድን ሰው ህይወት ማሻሻል እንድችል እርዳኝ" በማለት ፀልያችሁ ውጡ። ይህ ደግሞ በእርግጥ የምፈፅመው ጥያቄ ነው፡፡ በመንግሥተ ሰማይ የትኛው ዘላለማዊ ሽልማት እንደሚያስገኝና የትኛው ፍፁም ሥጋዊና ዋጋ ቢስ እንደሆነ መለየት በሚያስችላችሁ በረከት አሁን ባረኳችሁ፡፡

"የምወዳችሁ ይህንን እውቀት ተግባርያዊ አድርጉት፡፡ ነገር ግን የአባታቸውን ቃል ሰምተው በመከር ወቅት ለመሰብሰብ ወደ እርሻው እንደማይወጡት አትሁኑ፡፡ እነርሱ "አዎ" ይላሉ ነገር ግን አይሄዱም፡፡ እናንተ ግን እንደዚህ መሆን የለባችሁም፡፡ ልባችሁን አዘጋጁ፣ ለነፍሶች ጊዜ ስጡ፣ ቅዱሳን መፅሐፍትን አጥኑ፡፡ ደግሞም ከእኔ ጋር ብዙ ጊዜ አሳልፉ፣ በፍቅሬ ለመሞላት ፍቀዱ፡፡ ይህንን ስታደርጉ ከእኔ የተካፈላችሁትን በሌሎች ላይ ማፍሰስ ትችላላችሁ።"

## ለጠላቶቻችሁ መፀለይ መራራነትን ይከላከላል - ሜይ 19 ቀን 2020 ዓ.ም

## Under attack-May 19, 2020

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ። ትላንት ከበጎ ፈቃደኞቻችን ውስጥ ሁለቱ ቃል በመግባት ልምዱን ለማስቀጠል ወስነዋል፡፡እግዚአብሔር የላከልንን የእነዚህን ነፍሶች ውበት ልነግራችሁ አልችልም፡፡ በእውነት እነርሱ አስገራሚ እና ደስታ የሚሰጡ ናቸው። በእውነቱ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ነፍሶች የሚያሳዩት የወንድማማች ፍቅርና እንክብካቤ ያስደንቀኛል፡፡ እነዚህ ነፍሶች ተኝተው እያለ ታዲያ አጋንንት ከባድ ጥቃት ያደርስባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ሽባ እንደማድረግ ያሉ ጥቃቶች፣ ወይም በጣም አሉታዊ እና ተስፋ የሚያስቆርጥ ሕልሞችን እንዲያዩ ያደርጋቸዋል። እነርሱ ግን ሁልጊዜ ወደ ጌታ ይሄዱና እርሱ ያጽናናቸዋል ደግሞም ያድሳቸዋል፡፡
በጣም የሚያስደንቀው ነገር ለኢየሱስ መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናቸው ነው ፡፡ ጌታ እንደነገረን ደቀመዛሙርቱ ለመሆን ከፈለግን ራሳችንን መካድ፣መስቀላችንን ማንሳትና እርሱን መከተል አለብን። ይህንን ቃል ስታስቡበት በጣም የሚያስፈራ ነው፡፡ መስቀሉ አሰቃቂ የአሟሟት መንገድ ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን እርሱ አንስተን እንድንሸከመው እየጠየቀን ነው። ይህ ማለት ደግሞ የእሾህ አክሊልም እንደፋለን ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ልክ እርሱ ጥቃት እንደደረሰበት ጥቃት ይደርስብናል ማለት ነው፡፡ ይህ ግን የሚፈፀመው በእኛ ሁኔታ ውስጥ ነው። በዚህም ለወንጌል መከራን እየተቀበልን በእርግጥ እርሱን እንድንመስል እየቀረፀን ነው፡፡

ውድ ቤተሰቦች በመጠለያው ላይ ጥቃት እየደረሰብን ስለሆነ እንድትፀልዩልን እጠይቃችኋለሁ፡፡ ይህም አንድ ህብረት ያላቸው የተወሰኑ ጠንቋዮች ተሰብስበው በህብረተሰቡ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱ ተራራውን ለቀን እንድንሄድ በእርግጥ ይፈልጋሉ። ጌታ ግን የሚፈልገው ወደ እርሱ እንዲመጡ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እንድንፀልይላቸው እየጠየቀን ነው፡፡ የዚህ ጥቃት ዜና ከደረሰኝ በኋላ እርሱ እንደሚጠብቀን ማረጋገጫ ሰጥቶናል፡፡ ይህም ቢሆን ግን የእናንተ ፀሎት ያስፈልገናል፡፡

ሰዎች በጫካ ውስጥ ሆነው ሲሰልሉንና በመኪናም እያለፉ ሕንፃዎቻችንን በካሜራ ሲቀርጹ አይተናል። አሁን በዚህ ጊዜ ሁላችንም አንድ ላይ በመሆን የምንሰባሰብበት፣ አብረን የምንበላበት፣ የምናመልክበት፣መንፈሳዊ ፊልሞችን የምናይበት፣ በጠቅላላው አብረን ሆነን የምንዝናናበት ቦታ እየሰራን እንገኛለን፡፡ ሕዝቅኤልና እኔ ካለንበት በስተቀር የመሸሸጊያው ክፍሎች እጅግ ጠባብ ናቸው፡፡ እነዚህ ክፍሎች የተሰሩት ለመፀለይና ከጌታ ጋር አብሮ ለመሆን ታስበው የተሰሩ ናቸው፡፡ ስለዚህም ክፍሎቹ ለህብረት የማይሆኑ ስለሆነ አሁን የምንሰራው ግን ለዚህ አገልግሎት እንዲውል ተደርጎ ነው፡፡ ስለዚህ ምን ያህል ሰዎች አብረውን እንዳሉ ለመናገር ከህዝቂልና ከእኔ ሌላ አራት ሰዎች ሲሆኑ በታኦስ ደግሞ ሁለት ሰዎች ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ ጌታ ያቀደው በዚህ መንገድ እጅግ ትንሽ ቤተሰብ እንድንሆን ነው፡፡ በየሁለት ሳምንቱ በሸለቆው ውስጥ ከሰዎች ጋር ለመፀለይና ምግብ ለማምጣት እንሄዳለን፡፡ እያንዳንዳችን በፀሎትና እግዚአብሔር የሰጠንን ሥራ ለመስራት መጣጣራችንን ማየት ቆንጆ ነገር ነው። እናም ደግነት የተሞላበት የእናንተ ልገሳ ይህንን እንዲሳካ ስላደረገ ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ።

የጥቃቱን ዜና ከሰማሁ በኋላ የጌታን ፊት ስፈልግ በሬማ በሰጠን ቃልና በጌታ ዕራት ወቅት በሰጠን የንባብ ክፍሎች የተናገረንን እነግራችኋለሁ፡፡

“አምላክ ሆይ ፣ ፍትሕን ስጠኝ ፤ በክፉ ላይ ያለኝን ዓላማ ጠብቅ፤ ከውሸታምና ተገቢ ካልሆኑ ሰዎች አድነኝ። አ አንተ ጌታ መጠለያዬ ነህ።

"እግዚአብሔር በባሕር ውስጥ መንገድን በኃይለኛም ውኃ ውስጥ መተላለፊያን ያደርጋል፤ እግዚአብሔር ሰረገላውንና ፈረሱን ሠራዊቱንና አርበኛውን ያወጣል፤ እነርሱ ግን በአንድነት ተኝተዋል፥ አይነሡም፤ቀርተዋል፥ እንደ ጥዋፍ ኩስታሪም ጠፍተዋል፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የፊተኛውን ነገር አታስተውሉ፥ የጥንቱንም ነገር አታስቡ። እነሆ፥ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፥ እናንተም አታውቁትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ። ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ፥ የመረጥሁትን ሕዝቤን አጠጣ ዘንድ በምድረ በዳ ውኃን በበረሀም ወንዞችን ሰጥቻለሁና የምድረ በዳ አራዊት፥ ቀበሮችና ሰጎኖች፥ ያከብሩኛል።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 43፡16-22)

ሌላው የተሰጠን ቃል ደግሞ "እግዚአብሔር *ሥራችሁንና* ሰዎችን በመርዳታችሁ የምታሳዩትን ለእሱ ያላችሁን ፍቅር አይረሳም።"
"አቤቱ፥ ሰው ረግጦኛልና ማረኝ፤ ሁልጊዜም በሰልፍ አስጨንቆኛል። የሚዋጉኝ በዝተዋልና ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ጠላቶቼ ረገጡኝ። እኔ ግን ፈራሁ በአንተም ታመንሁ። በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ፤ በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል? ሁልጊዜ ቃሎቼን ያጸይፉብኛል፤ በእኔ ላይም የሚመክሩት ሁሉ ለክፉ ነው። ይሸምቁብኛል ይሸሽጉኝማል፥ እነርሱም ተረከዜን ይመለካከታሉ፥ ሁልጊዜም ነፍሴን ይሸምቁባታል። በምንም ምን አታድናቸውም፤ አሕዛብን በቍጣ ትጥላቸዋለህ። አምላክ ሆይ፥ ሕይወቴን ነገርሁህ፤ እንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊተህ አኖርህ። በጠራሁህ ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤ አንተ አምላኬ እንደ ሆንህ እነሆ፥ አወቅሁ። በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ፤ በእግዚአብሔር ቃሉን አከብራለሁ። በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል? አቤቱ፥ የምስጋና ስእለት የምሰጥህ ከእኔ ዘንድ ነው፤ ነፍሴን ከሞት፥ እግሮቼን ከመውደቅ አድነሃልና፥ በሕያዋን ብርሃን እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ዘንድ።" (መዝሙር 56፡1-13)

ከ 20 ዓመታት በፊት ጌታ አንድ ቀን በዚህ በዚህ ሊመጣ ስላለው ህብረተሰብ ቃል ሰጥቶኝ ነበር፡፡ እናም ከተባረከችውን እናት ምሳሌ በመውሰድ "መልአኩ የነገራትን እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ብላ አመነች፡፡" በሚል የሬማ ካርድ አዘጋጅቼ ነበር፡፡ ታዲያ ዛሬ ይህ የሬማ ቃል ተሰጠን። ይህ የሬማ ቃል እግዚአብሔር የገባውን ቃል ይፈፅማል ብሎ በእምነት ለመጠበቅ በጣም ጥሩ የሆነ ቃል ነው፡፡

ትላንትና ሁላችንም በምንፀልይበት ጊዜ ኢየሱስ የገነባነው ቤት ላይ አንድ ትልቅ ሽፋን ስትሸፍን አየሁህ፡፡ በዚያን ጊዜም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሰፉ ቃሎች ያለበትን የቃልኪዳን መፅሐፍ (Bible Promise book) ውስጥ የእግዚአብሔር ጥበቃ የሚለውን ክፍል ከፈትኩ፡፡ ከዚያም ውስጥ "የእግዚአብሔር ስም የፀና ግንምብ ነው፣ ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግ ሰው ወደዚያ ይገባል እናም ደህንነቱ ይጠበቃል፡፡" የሚለውን አነበብኩ። ጌታ ጥበቃ እንደምታደርግልን በብዙ ቃል ገብተህልኛል፡፡ ኢየሱስ አንተ የምትለኝ ነገር አለ? እባክህን የኔ አዳኝ አንተን ለመስማት ጆሮዎቼን ከፈት።

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . “መላእክቶቼ በዚህ ስፍራ ሙሉ ጥበቃ እንዲያደርጉ መላእክቶቼን ስለመደብኩ በዚህ ቦታ ላይ ምንም ጉዳት አይመጣም፡፡  ከሌር የውስጥ ፍላጎትሽ ንፁህ እስከሆነ ድረስ ምንም የሚያስፈራሽ ነገር የለም። የከፉን እስራትና የተታለላችሁበትን መንገድ ለመፍታት ምርጥ የሆነውን ልኬላችኋለሁ። በዚህ ላይ እረፉ፡፡ እኔ ከዚህ ነፍስ ጋር ነኝ እናም እኔ እንዳደርግ የፈለግኩትን በትክክል ያደርጋል፡፡

“አንቺ ግን የኔ ፍቅር  ለጠላቶችሽ መፀለይ አለብሽ፡፡ ምክንያቱም እነሱ ጥቂቶች አይደሉም እናም እነርሱ እንዲድኑና ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ ተመኚላቸው። አንዳንዶቹ በእውነትም ይለወጣሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ከጨለማው ጋር የቃልኪዳን ማኅተም ስላደረጉ ከብርሃን ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም።

“እነርሱ ተራ ሰዎች ናቸው እግዚአብሔር ከጎናችሁ እያለ ምን ያደርጓችኋል? በተጨማሪም ይህ መጠለያ የእኔ እንጂ የእናንተ አይደለም፡፡ እነርሱ የሚዋጉት ተራ የሚሞቱ ሰዎችን አይደለም፡፡ የፍትህ ጉድለት ጩኸት ወደ ሰማያት ደርሷል፡፡ ስለዚህም ከእናንተ የተሰረቀ ሁሉ ይመለሳል፡፡

በአንቺ በኩል ያሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ እነዚያ ሲያሳድዱሽ የነበሩ ቅድም አያቶችና ዘመዶች ናቸው ስለዚህ ለእነርሱ ፀልይላቸው። በአልዓዛር ሕይወት ምክንያት ሐብታሙ ሰው ለወንድሞቹ ወደ እኔ እንደ ፀለየ ለእነዚህም የሚወዷቸው ሰዎች እንዲቀየሩ እየፀለዩላቸው ነው፡፡

ከዚህ በፊት አግኝቼው የማላውቀው በጣም አስደሳች ነጥብ እነሆ ፡፡ በሉቃስ 16 ከቁጥር 19 ጀምሮ የአልዓዛርና የሐብታሙ ታሪክ ይገኛል።

"19 ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። 20 አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ 21 ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር። 22 ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። 23 በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። 24 እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። 25 አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። 26 ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ። 27 እርሱም። እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ 28 እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ። 29 አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። 30 እርሱም። አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። 31 ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።" (ሉቃስ 16፡19-31)

ጌታም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . “አያችሁ፣ ሃብታሙ ምንም እንኳን በሥቃይ ውስጥ ቢሆንም፣ ድምፁ ተሰምቷል፡፡ ድምፁም ወደ እኔ ያቀረበው ልመና ነበር ፡፡ በማንኛውም ጊዜ በምድርም ቢሆን ፣ በሰማይ  ወይም መንግስተ ሰማይ

ከመግባታችሁ በፊት ባለ የማንጺያ ሥፍራ /purgatory/ ሆናችሁ ብትጮኹ እንደ ፀሎት ይቆጠራል፡፡ ምንም እንኳን መልሱ ‹አይቻልም› ቢሆንም እንኳን ሐብታሙ ሰውዬ ወደ አብርሃም ለምልጃ ጮኸ እናም ድምፁ ተሰማ፡፡ ፀሎት ማለት ይህ ነው፡፡ ሌሎችን ወክሎ ወደ እግዚአብሔር መጮህ።

ክሌር፡- ጌታ በሲኦል ውስጥ ማላጆች አሉ እያልክ ነው?

ኢየሱስም ቀጠለ ፣ "በሲኦል ወደ እኔ ይጮኻሉ እናም እሰማቸዋለሁ፡፡ በምድር ላይም ቢሆን ከምድር በታች የማልሰማው ምንም ቦታ የለም። ለራሳችሁም ሆነ ለሌላ የምትጮሁት ፀሎት ነው፡፡ ከእኔ ዘንድ ፀጋን ስትጠይቁ ይህም ፀሎት ነው፡፡

ክሌር፡- ግን በገሀነም ውስጥ ያሉትን ሰዎች ጥያቄ ትመልሳለህ?

"ክሌር እነርሱ የሰይጣን ለመሆን በመወሰናቸው ምክንያት የመፀለይ መብታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። እሰማቸዋለሁ ነገር ግን ለጥያቄዎቻቸው መልስ አልሰጥም፡፡ እነርሱ ያለምህረት ለሚያሰቃያቸውና ለሚያፌዝባቸው ሰይጣን ይጸልዩ፡፡ እሱ ከክፋትና ከስቃይ ውጪ ሌላ ይችላል ብሎ ማሰብ የሞኝነት ሃሳብ ነው። ይህ በጣም የሚያሳዝን ጉዳይ ነው፡፡ ሰይጣን እንዲዋሹ፣ እንዲሰርቁ፣ እንዲያታልሉ፣ እንዲገድሉና እንዲያጠፉ ነው ያስተማራቸው፡፡ ከዚያም ሲሞቱ ከሱ አንድ ጥሩ ነገር ለመቀበል ይጠብቃሉ? እርሱ ዋሽቷቸዋል፣ እነርሱም በተራቸው ሌሎችን ዋሽተዋል፡፡ ታዲያ ቃሉን ይፈፅማል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ? እርሱ ውሸቱን ስለተቀበሉት ያፌዝባቸዋል፣ እውነተኛ አድርገው በማሰባቸውና በድድብናቸው ቀንና ሌሊት ያሰቃያቸዋል፡፡

"እርሱ የወደቀ መልአክ ነው፡፡ ጠቅላላ ዓላማውም የሰውን ዘር በመጉዳት እኔን መጉዳት ነው፡፡ ለዚህ ነው ደግ መስሎ በመታየት የማያውቁትን ግብር አበሮቹ ለማድረግ የሚያታልላቸው። ይህንንም የሚያደርገው እኔን ትክክለኛ ያልሆንኩት እኩያ ወንድሙ አድርጎ የሚያቀርበኝ፡፡ ሃቁ ግን እርሱ ፍጡር ሲሆን እኔ ደግሞ ህይወትና ነፃ ፈቃድ የሰጠሁት ፈጣሪው ነኝ፡፡ እርሱ ለሥጋና ሥጋዊ ለሆነው ሰው የማይነገሩ ነገሮችን በማድረግ ቆንጆ መስሎ ይታያቸዋል። አጋንንቶች ደግሞ ሰዎች ወደው ስህተትን እንዲፈፅሙ ያጋግሏቸዋል፣ ያነሳሷቸዋል፡፡

"በነዚህ ነፍሳት ጥልቅ ልባቸው ውስጥ ይህንን አታድርግ፣ ፍፁም እንዳታደርገው እያለ የሚጮህ ድምጽ አለ፡፡ ነገር ግን እነሱ ለፍላጎታቸው አሳልፈው ይሰጣሉ እናም ህሊናቸው ሙሉ በሙሉ ሞቶ እኔን መስማት እንዳይችሉ ይደረጋሉ። አንቺም ያገኘሻቸው ሰዎች እንደነዚህ አይነቶቹን ነው፡፡ እነርሱ መልካሙንና ጥሩውን ትተው ክፉውን ሙሉ ለሙሉ ከተቀበሉ ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል።

"እንዲም ቢሆን ግን ብትፀልይላቸው ለአንዳንዶቹ ተስፋ አለ ፡፡ ከዚህም ባሻገር ፀሎት እነርሱ ለመስራት በሚሞክሩት ክፉ ድርጊት እንዳትናደጂና እንዳትማረሪ ይከላከልልሻል።"

**ከምድር በታች እየተደረጉ ያሉ ጦርነቶች - ሜይ 23 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Underground war In Progress, May 23, 2020**

ውድ ቤተሰቦቼ ንጥቀት በልቤ ላይ እጅግ በጣም ከብዶብኛል፡፡ አያችሁ ኢየሱስ በምድር ላይና ከምድር በታች ስለሚካሄደው ብልሹ ተግባር በጣም በትንሹ አሳይቶኝ ነበር፡፡ እናም በጣም ግራ የሚያገባ ነው፡፡

ከወታደሮች ጋር ግንኙነት ያለው አንድ የእኛ ሰው በጣም አሳዛኝ ዜና ነገረን። ዜናውም በሁሉም አገራት በምድር ውስጥ ባሉ ከተሞች ውስጥ ልጆች ለመሞከሪያና ከአይናቸው የሚገኝ አድሬኖክሮም(adrenochrome) የሚባል ፈሳሽን ለማውጣት ምን ያህል እንደሚያሰቃዩአቸው ነው፡፡ ለማለት የምችለው ይህ እንዴት አሰቃቂና ከሚታመን በላይ መሆኑን ነው፡፡

ይህ በእኛ አገር (በአሜሪካ) እጅግ የተለመደ ሲሆን ከዚህ ከማይረባ ኩረጃ ነፃ የሆነ አገር ግን ያለ አይመስለኝም፡፡ ህፃናት ታፍነው ወደ ተለያዩ ተቋማት በመላክ ብዙ ሙከራዎች ይደረግባቸዋል ወይም በማሰቃየት አድሬኖክሮም(adrenochrome) እንዲያመነጩ ይደረጋሉ። ይህ አድሬኖክሮም ለተመረጡ ምሁራን(Elites) እንዲበሉት ወይም በምድር ውስጥ ለሚገኙ የወደቁ መላዕክቶች/Demon alien/ ቴክኖሎጂ እንዲሰጡን ከመንግስታችን ጋር ለሚደራደሩ ምግብነት ይውላል። የእነዚህ የወደቁ መላክቶች ቴክኖሎጂ እኛ ከደረስንበት ስልጣኔ ውጪ በመሆኑ ለዚህ ነው ሞራላዊ በሆነ መንገድ ለመገልገል የማንችልበት ደረጃ ላይ የደረሰነው።

ይህ ታዲያ ወደ ንጥቀት ያመጣኛል፡፡ ምክንያቱም በምንም አይነት መልኩ ቢሆን አሁን አለም ያለችበት ሁኔታ እጅግ ከባድ መሆኑን ያለመግለፅ አልችልም፡፡ ፕሬዚዳንት ትራምፕ በአሜሪካ ከምድር በታች፣ በዋሻዎችና በምድር ሥር በሚገኙ ከተሞች ውስጥ የሚካሄደውን ጦርነት የሚፋለሙ ወንዶችና ሴቶች የሚገኙበት ሠራዊት አስነስቷል። ትግሉ እጅግ አስፈሪ ነው፡፡ እናም ወታደሮቻችን ከወደቁ መላዕክቶችና /demon alien/ ከአጋሮቻቸው ጋር በሚያደርጉት ጦርነት ብልጫ እንዲኖራቸው የሚደርስባችሁን ሥቃይና ፀሎቶቻችሁን ለጌታ እንድታቀርቡ ሁላችሁንም እጠይቃለሁ።

ይህ ወንጀለኛ መንግስት በዚህ ጦርነት ሊደመሰስ የሚችልበት ዕድል አለ፡፡ ነገር ግን እንቅስቃሴው በዓለም ዙሪያ የተሰራጨ፣ እጅግ ሰፊና የተለያዩ መንግስታት የተቆላለፉበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ለማጥፋት የብዙ አገራት ትብብርን ይጠይቃል ፡፡

በቅርቡ ኤርያ 51 (area 51) በሚባለው ቦታ 6.5 ሬክተር ስኬል የሚሆን የመሬት መንቀጥቀጥና ከዋናው መንቀጥቀጥም በኋላ የሚከተሉ ብዙ የመሬት መንቀጥቀጦች ተከስተዋል ፡፡ ይህም የመሬት መንቀጥቀጥ የተፈጠረው ሬዲዮ አክቲቭ ያልሆኑ ፈንጂዎች በመሬት ውስጥ የሚኖሩትን ኤሊያኖች ለማጥፋት ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች በመተከላቸው ነው፡፡

የእኛም ሠራዊት ወደ ውስጥ ዘልቀው በመግባትና ሕፃናቱን ነፃ በማውጣት ተቋሙን ከኤልያኖቹ ጋር ደምስሰውታል፡፡

የተወደዳችሁ ይህ ልብ ወለድ ታሪክ አይደለም፣ ይህ እውነታው ነው ፡፡ የኤሊያኖቹ መጓጓዣዎች በሰማይ ውስጥ በሁሉም ቦታ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም መጓጓዣዎች ብዙ ጊዜ ዳመናውን መስለው ይታያሉ፡፡ እናም እነዚህ ሁሉ ከንጥቀት በኋላ የሚታዩና በታላቅ ኃይል በመላው ምድር ላይ የሚገለጡ ይመስለኛል። ስለ ንጥቀቱም መግለጫ የሚሰጡት በምድር በጣም ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ከምድር የተወሰዱት የስልጣኔያችን እቅፋት በመሆናቸው ነው የሚሉ ይመስለኛል። ይህንን የሚያደርጉ

ይመስለኛል። ነገር ግን ለአሁኑ እነዚህን አፀያፊ የሆኑ የወደቁ መላዕክቶች/demon alien/ ከምድራችን እንዲወገዱ እግዚአብሔር ከጎናችን ሆኖ እየተዋጋ ነው።

እባካችሁ አገልግሎት እየሰጡ ስላሉ ሰዎችና ስለ ፕሬዚዳንታችን ደህንነት ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ የእናንተ ፀሎት ኃይል አለው፡፡ ደግሞም ጸጋ ሳይለቀቅ ምንም ነገር አያልፍም። በጣም ከባድ ወይም ተስፋ ቢስ ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ከእውነት የራቀ ነው ፡፡ ፀሎታችን ይህንን ጦርነት እያሸነፈ ነው፡፡ ኸርት ድዌለርስ መፀለያችሁን አታቋርጡ፣ መፀለያችሁን ቀጥሉ።

## በልቤ ላይ ዕረፉ - ጁን 3 ቀን 2020 ዓ.ም

## Rest On My Heart, June 3rd, 2020

ውድ ቤተሰቦች ጌታ ዛሬ ለእኛ የማበረታቻ ቃል አለው፡፡ ምንም እንኳን መልዕክቱ እኔን የተመለከተ ቢሆንም ለእያንዳንዳችሁ ይህ ቃል እንደሚሰራ አውቃለሁ፡፡ ምክንያቱም ሁላችሁም በፀሎትና በፆም ተግታችሁ ስለከረማችሁ ነው፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . ክሌር ሰሞኑን ስለ ፆምና ስለ ሥራ አውርተን አናውቅም፡፡ የአንቺን ትኩረት በሚፈልጉ ብዙ ነገሮች ላይ በሚቻልሽ ሁሉ ጥሩ ሰርተሻል፡፡ አሁን የምፈልገው ራስሽን በጣም እንዳታስጨንቂና ወደ ዕረፍቱ እንድትገቢ ነው፡፡ በአንቺ ደስ ብሎኛል እናም አሁን የምፈልገው ከእኔ ጋር ሆነሽ እንድትደሰቺ ነው፡፡ ከእኔ ጋር ተጣበቂ፣ ተወዛወዢ፣ ዳሰሳ አድርጊ፡፡ ከእኔ ጋር ለመዝናናት ጊዜ ውሰጂ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በእኔ መገኘት ውስጥ ዕረፍት አድርጊ፣ በሙሉ ልብሽ ከእኔ ጋር ተጣበቂ፡፡ በዚህም በፊትሽ ያዘጋጀሁትን ለመጨረስ ብዙ ኃይል ታገኛለሽ፡፡

"ራስሽን በደረቴ ላይ እንድታሳርፊ ወደ እኔ ስስብሽ እያየሽ ነበር፡፡ ለዚህ ምክንያት አለው፡፡ አዎ ይህ እውነት ነው፡፡ "እጅሽን በልቤ ላይ አሳርፊና ፍቅሬ ይመራሻል፡፡" እንዲሁም ደግሞ "ራስሽን በልቤ ላይ አስቀምጪና ፍቅሬ በአንቺ ሞልቶ ይትረፈረፍና በወንድሞችሽና በእህቶችሽ ላይ ይፈሳል፡፡ይህም ለበጎቻችን ማስማሪያ ነው፡፡

"የኔን ፈቃድ ለመፈፀም ፈቃደኛ ስለሆንሽ ለእኔ የማያቋርጥ መፅናኛ ሆኖኛል፡፡ የበጎቻችን መሰማሪያዎች እንኳን አስፈላጊ መሆኑን ሲረዱ አንቺን ለመርዳት ፈቃደኞች እየሆኑ ነው፡፡ ተረከዛቸውን የሚያነሱ ወይም ሩቅ የሚመስሉ ስለታመሙ ምግብና ምክር ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነርሱን ወደ ጎን አድርገሽ ማገልገል ለአንቺ ጥሩ ነው፡፡

"ደብዳቤዎቻቸውን እያነበብሽ በፅሑፍ ምላሽ የምትሰጪቸውን ሐሳብ ወድጄዋለሁ፡፡ በዚህ ሙከራ ብዙዎች ጥቅም አግኝተው ይታነፁበታልና ይህንን ማድረግሽን ቀጥዪ፡፡ ለአንቺ ግን የዛሬው ዋነኛው መልዕክቱ ራስሽን በመስጠት በጣም በከባድ ሁኔታ ሰርተሻልና አሁን የምፈልገው በእኔ ላይ ተደግፈሽ ሙዚቃ እንኳን በመጫወት ቢሆን እንድታገግሚ ነው፡፡ ከህዝቤ ስለ ደግነቴ ምስጋናና ክብር ስፈልግ የምስጋና መዝሙሮችሽ በልቤ ውስጥ ያለውን ህመም ያፅናናዋል፡፡ ይህ መዝሙር ለእኔ እጅግ የሚያፅናናኝ ስለሆነ ተምረሽ ለሌሎችም አስተምሪ፡፡

"በዚህ ማለዳ "ኢን ሲኑ ጀሱ" ከሚለው መፅሐፍ ያነበብሽው አባቴ እያንዳንዳችሁን እንዴት እንደሚያፈቅራችሁ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ይህ መፅሐፍ አንድ ቄስ በፀሎቱ ጊዜ የፃፈው ነው፡፡ እርሱም የቤኔዲክት መነኩሴና ቄስ ነበር፡፡ ይህ መፅሐፍ

በጣም ቆንጆ መፅሐፍ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት ለማድረግና እንዲሁም የእግዚአብሔር አብን እውነተኛ ማንነት ለማወቅ  እንደሚያስፈልገን ያሳያል፡፡ ይኸውም ኃይለኛ እግዚአብሔርን ሳይሆን ለስላሳና አፍቃሪ አባትነቱን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ትንሽ ወደኋላ ልመለስና በዚህ ማለዳ "ኢን ሲኑ ጀሱ" ከሚለው መፅሐፍ ያነበብሽው አባቴ እያንዳንዳችሁን እንዴት እንደሚያፈቅራችሁ ነው፡፡ ብዙዎች አባት እንዴት መሆን እንዳለበት አያውቁም፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን ጋብቻን ለማበላሸት፣ ፍቺንና ህመም ያለበት መለያየትን በትዳር መካከል  በመፈጠር ተሳክቶለታል፡፡ ይህ ደግሞ በአንፃሩ ብቸኛ የሆነች ሴት ለልጆቿ ምንም ኃላፊነት የማይሰማቸው ብዙ የወሲቢ ጓደኞች እንዲኖራት መንገድን ከፍቷል፡፡ በዚህ የተጎዱ ህፃናት ጉዳይ እጅግ የሚያሳዝን ሆኖ እያለ ከዚህ ባለፈ መልኩ ደግሞ አንዳንዶቹ ወንዶች እነዚህን ህፃናት ስቃይ ሲያደርሱባቸው ማየት እጅግ አሰቃቂ ነው፡፡ ይህም ከመሆኑ የተነሳ አባትነት ተጣሟል፣ በአደጋ ተጨራምቶ መሬት ላይ ተጥሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆች መፅናናት ሲፈልጉ ያለው ጠላትነት ነው፡፡

"በዚህ ምክንያት ነው አባቴ ፍቅር እንደሆነ ሰዎችን  ለማሳመን እጅግ መስራት ያለብን፡፡ እርሱ ለየዋሆች ኃይለኛ አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በአጥፊዎችም ላይ ኃይለኛ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነርሱም በወላጆቻቸው የተጠቁ ስለሆነ ነው፡፡ እርሱ የበለጠ ኃይለኛ የሚሆነው እኔን ፈልገው ሲመጡ በሃይማኖት ሰበብ ማህበራዊ ፍላጎቶችን የሚያስቀምጡትን ሃይማኖተኛ ሰዎችን ነው፡፡ እኔ እንዲያስተምሩ የምፈልገው እኔን እንዴት መውደድና ወደእኔ መቅረብ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ንፁህና የተቀደሰ ህይወት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሁሉ የበለጠ ደስታ የሚሰጣችሁ ህይወት እንዲኖራችሁ ያደርጋል፡፡

"ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ወይንም የህብረተሰብ ልማድ ከእኔ ጋር ያለውን የአንድነትን ግብ የሚፃረር ከሆነ ከእኔ ጋር እየተጣላና ህዝቡን እያሳተ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ከእኔ ጋር የቀረበ ህብረት እንደሚያስፈልግ ትምህርት እየተሰጠ፣ እየተበረታታና ትልቅ መነቃቃት እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ ከአሁን ወዲያ ያለው ጉዞ ደግሞ ለብዙ ክርስቲያኖች የማይገባ ይሆናል፡፡ ዋናው የስቃይ ሚና ደግሞ ያ ይሆናል፡፡  ምክንያቱም ይህንን እስካሁን ስላልተማሩ ብዙዎች ለምንድነው ያልተፈወስነው በማለት ግራ ይጋባሉ፡፡

"የኔ ህዝብ አባቴ ሁሉ ነገሩ ፍቅርና ቅድስና ነው፡፡ በእርግጥ ነው እንድታድጉ ለማድረግ በህይወታችሁ ብዙ ነገሮችን ይፈቅዳል፡፡ በአብዛኛው ጊዜ ግን አንድ መከራ በህይወታችሁ የሚፈጥረው ትልቅ መልካም ነገር ግልፅ ሆኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን እንድታምኑ የምፈልገው ለእያንዳንዱ ስቃይ ምክንያት እንዳለው ነው፡፡ ለመፈወስ ጊዜ አለው ላለመፈወስም ጊዜ አለው፡፡

"በብዙ የጥፋተኝነት ስሜት፣ በብዙ ክስና በድብርት ውስጥ የምታልፉት በዚህ አለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ እኔ ግን አለምን አሸንፌዋለሁና ደስ ይበላችሁ የሚለው እንዲሁም በየቀኑ በልባችሁ እያሸነፍኩት እንደሆነ ስላልገባችሁ ነው፡፡ የደረሰባችሁን ስቃይ ወይም መከራ በመቻላችሁ በህይወታቸው ተስፋ ቆርጠው ጠርዝ ላይ ለነበሩ ነፍሶች ምን ያህል እንደሰራ በመንግስተ ሰማያት ካልሆነ በስተቀር በአለም እያላችሁ ልታውቁ አትችሉም፡፡

"በመንግስተ ሰማያት ካልሆነ በቀር ፍሬውን ልታዩት አትችሉም፡፡ ቢሆንም ግን  ስለ መከራና ስለ ጥቅሙ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ብዙ ጊዜ እንደተናገርኩት በዛ ቃል ላይ አርፋችሁ እናንተ ያደረጋችሁት ነገር ከምታስቡት በላይ እንደሚጠብቃችሁ እርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ፡፡ ለጓደኞቹ ህይወትን ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር የለም፡፡ እናንተ ደግሞ በሚገጥማችሁ

በእያንዳንዱ ስቃይ የህይወታችሁን ክፍል እየሰጣችሁ ነው፡፡ እኔም ያንን በማንሳት ሶስት ቀን ውኃ ብቻ እየጠጣችሁ እንደፆማችሁ በመቁጠር ለሚያስፈልገው ነፍስ ፀጋን አካፍላለሁ፡፡

"እኔ መስቀሉን እንደተቀበልኩ የእናንተን አመድ ቀይሬ ለመቀደስ ፀጋ በማድረግ እጅግ ለሚያስፈልጋቸው እንደማጋራ በማወቅ መከራን ተቀበሉ፡፡ አሁን ይህንን የምገልፅላችሁ የሚደርስባችሁ መከራ ምድር ለሚገኘው ለእግዚአብሔር መንግስት የምትሰሩት ከባድ ሥራ እንደሆነ አውቃችሁ በጉብዝና፣ በፈቃዳችሁ፣ ባለማማረር እንድትቀበሉት እየጠየኳችሁ ነው፡፡ በዚህ መተባበራችሁ ደግሞ በምድርም ቢሆን በሰማይ የሚያስመሰግናችሁ ይሆናል፡፡ በምድር መከራን ስለተቀበላችሁና ለሌሎች በማድረጋችሁ  በመንፈስ የተገኘውን ድል በሰማያት ስታዩ ትደነግጣላችሁ፡፡

"ነገር ግን ሙሽራዬ ሁልጊዜ በስቃይ እንድትሆን አልፈልግም፡፡ ለመዝናናት፣ ለፍቅር፣ ለዕረፍት እንዲሁም እጅግ ለተጎዱ ነፍሶች ጥልቅ የሆነ የታህድሶ ጊዜ አለ፡፡ በዱዌሊንግ ፀሎት ጊዜ ከእናንተ ጋር ስለምወዛወዝ ጠብቁኝ፡፡ ወደ መንግስተ ሰማያት እንደምወስዳችሁና ለእናንተ ደስታና ፈንጠዚያ የፈጠርኩትን አስደናቂ ነገሮች እንደማስጎበኛችሁ ጠብቁኝ፡፡ እጄን ስዘረጋላችሁ እንቢ እንዳትሉኝ፡፡ ይህንን የማደርገው ደስታ ወዳለበት ወደ ዘላለማዊ ቤታችሁ ልጋብዛችሁ ነው፡፡ ይህንን ሳደርግ ደግሞ እንደሚያስፈልጋችሁ በትክክል ስለማውቅ ነው፡፡ ስለዚህም እጄን በዘረጋሁ ጊዜ አታላይ መንፈስ ነው ብላችሁ ከመጠርጠርና ከፍርሃት የተነሳ  እንቢ እንዳትሉኝ፡፡

"የኔ የልቤ ሐሳብ በእጆቼ ላቅፋችሁ፣ ወደ ደረቴ ላስጠጋችሁ፣ ወደ ተቀደሰ የፍቅር ሙዚቃ ልወስዳችሁ፣ ወደሚያስደስት ሥፍራ ልመራችሁ፣ ወደጫካ፣ ወደቤተመንግስት፣ ወደ ሃይቅና ወደ ወንዝ እንዲሁም ሙሽራዬን በእውነተኛ ፍቅር ሰላምታ ወደሚሰጡበት ሁሉም ዓይነት እንሰሶች ወደሚገኙበት ልወስዳችሁ ነው፡፡ የኔ አጋሮች ብዙ ብዙ ለእናንተ የማሳያችሁ ቆንጆ ቆንጆ ነገሮች አሉኝ፡፡ እናንተ ብቻ በዱዎለርስ ፀሎት ጊዜ ግብዣዬን ተቀበሉኝ፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች እኔ ከምሰጣችሁ ምቾት የበለጠ በምድር ላይ ምቾት የሚሰጣችሁ ምንም ነገር የለም፡፡ ልባችሁ ከእኔ ጋር ይሁን፡፡ እንዳድሳችሁና ዕረፍት እንድሰጣችሁ ፍቀዱልኝ፡፡

"ለእኔ እጅግ የሚያስደስተኝ ነገር አንዷት ነፍስ ከእኔ ጋር ለእርሷ ተብሎ ወደተዘጋጀላት ወደዛ ሚስጥራዊ ቦታ፣ ወደ ተደበቀው ንፁህ የአትክልት ሥፍራ ስትመጣ ነው፡፡ እናም እኔን በመጠርጠር እንቢ ስትለኝ ይህ በጣም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው፡፡ ለመሆኑ አባት ልጁ አሣ ሲለምነው እባብ ይሰጠዋልን? እኔም እናንተን ለማፅናናትና ለማደስ እየጓጓሁ ለሚያታልል መንፈስ አሳልፌ አልሰጣችሁም፡፡ እናንተ የተባረካችሁ የእጄን ግብዣ ተቀብላችሁ ወደ እኔ፣ ወደ ዘላለማዊው ደስታ ኑ፡፡ ወይም ዝም ብላችሁ ራሳችሁን በደረቴ ላይ አድርጋችሁ በእኔ ማንነት ውስጥ ካለውና ለእናንተ ከተዘጋጀው እጅግ ከጠለቀው የፍቅር ምንጭ ረስርሱ፡፡

"በኃጢያት ወድቃችሁ ከነበረ አትጨነቁ፣ ደግሞም እናንተ ይጠበቅብኛል ብላችሁ ራሳችሁ ካሰባችሁት የህይወት ደረጃ ባለመገኘታችሁ ግድ አይስጣችሁ፡፡ እኔን ቸል ብላችሁኝ ከነበረና ከፀሎት ራሳችሁን አግልላችሁ ከነበር ግድ የለም፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ምንም አይደሉም፡፡ እኔ ሁሉንም ይቅር ብዬአችኋለሁ፡፡ አሁን "ከእኔ ውስጥ ሞልቶ ወደሚፈሰውና የማያልቅ መፅናናት ወደሚሰጠው የህይወት ፏፏቴ ኑ" እያልኩ እጋብዛችኋለሁ፡፡ ወደእኔ ኑ፡"

## አባቶች ተነሱ - ጁን 4 ቀን 2020 ዓ.ም

## Fathers arise, June 4th, 2020

ውድ ቤተሰቦች እንዴት ናችሁ? እኔ ሲስተር ኤልሳቤጥ እባላለሁ። ማዘር ክሌር ከጌታ የተቀበልኩትን ይህንን መልዕክት እንዳካፍላችሁ ጠይቃኛለች። ከኢየሱስ ጋር በዝምታ ቁጭ ብዬ ሳለሁ ጌታ እንደዚህ ብሎ መናገር ጀመረ። . . . "ህዝቦቼ ለብቻችሁ የሆናችሁበትንና ኃሳባችሁን የሚበትን የሌለበትን ይህንን ጊዜ እየተጠቀምኩበት ያለሁት ልባችሁንና አይምሯችሁን በማዞር እኔን የማያውቁኝንና ከመንገዳቸው የወጡትን ህያው ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር እንድትመልሱ እንዲሁም የቤተሰብን ህይወት በማደስ ተግባር ላይ እንድታተኩሩ ነው፡፡

"አብዛኛዎቹ ልጆቼ በእኔ ላይ ከመተማመን ይልቅ በራሳቸውና ባላቸው ብቃት ላይ ይተማመናሉ። ይህንን እንድታውቁ እፈልጋለሁ እናንተ ከእኔ ተለይታችሁ ምንም ማድረግ አትችሉም። የኔ ሐሳብ የክርስትያን ቤተሰብ ህይወትን ማደስ፣ እምነታቸውን ማጠንከርና በሁሉም አገር ባለችው ቤተክርስቲያኔ አንድነትን መፍጠር ነው፡፡ በንስሐና ፀፀት በተሞላበት ሁኔታ በህይወታችሁ የጀመርኩት እንዲታደስ በመፈለግ ለምታለቅሱ ምላሽ መስጠት እጀምራለሁ፡፡ ድምፄን በንቃት በማድመጥ ጆሮዎቻችሁ ቃሎቼን በመስማት ወደ እኔ ዘንበል እንድትሉ እፈልጋለሁ። ወደ እኔ ማለትም ወደ መጀመሪያ ፍቅራችሁ ለመመለስ ጊዜው አልረፈደም፡፡

"የእናንተንና የቤታችሁን ልብ እፈውሳለሁ፡፡ ያለፉ ጉዳቶቻችሁን እጠግናለሁ፣ የተበላሹ ግንኙነቶታችሁን አድሳለሁ። ሌሎች ኃላፊነታቸውን አልተወጡም ብለው እንደሌላችሁ የተቆጠራችሁ አባቶች ወደላይ አነሳችኋለሁ፡፡ በቤታችሁ መንፈሳዊ መሪ አድርጌ አነሳችኋለሁ፡፡ ልጆቻችሁንና የልጅ ልጆቻችሁን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን አፍቃሪና ይቅር ባይ ስለሆነው እንዲሁም በእናንተ እጅግ ደስ ስለሚሰኘው አባቴ ታስተምሯቸዋላችሁ።"

(ኤልሳቤጥ) ፦ በዚህ ጊዜ ኢየሱስ 2ኛ ጢሞቲዎስ 3፡16 እና መፅሐፈ ምሳሌ 22፡6 አስታወሰኝ፡፡

*"ቅዱሳን መፃህፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፡፡ ለማስተማር፣ ለመገሰፅ፣ ለማቅናት በፅድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፡፡ (2ኛ ጢሞቲዎስ 3፡16)*

*ልጅን የሚሄድበትን መንገድ አስተምረው፡፡ በሚሸመግልበትም ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም(ምሳሌ 22፡6)*

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . "እኔን ስትፈልጉኝ የጠለቀ አስተሳሰብ ያለው ሰማያዊው አባታችሁ አይምሮዎችሁን በማደስና በመቀየር ሁሌም ከሚገኘውና ይቅር ባይ ከሆነው አምላካችሁ ጋር የግልና የጠለቀ ግንኙነት እንዲኖራችሁ የሚያስችለውን ብቃታችሁን ይገልጥላችኋል፡፡ ያደረጋችሁት ወይም ያላደረጋችሁት ነገር አስፈላጊ (ወሳኝ) አይደለም፡፡ ሆኖም ግን በተፀፀተ ልብ ወደ እኔ ኑ፡፡ እኔም እፈውሳችኋለሁ፣ አድሳችኋለሁ፣ የበፊቱን በመመለስ የክርስቲያን ቤት ራስ መሆን እንድትችሉ አደርጋለሁ፡፡

"አባቶች ለእናንተ ይህንን እላለሁ፣ አሁን ተነሱ! እኔ ደግሞ ፍቅረኞቻችሁ እናንተን በህይወታቸው መቀበል ይችሉ ዘንድ ልባቸውን አዘጋጃለሁ፡፡ ጠላት ከእናንተ የሰረቀውን አስመልሱ እና ደግሞ በተደጋጋሚ የሚነግሯችሁን ውሸቶች አታዳምጡ።

"እኔ በኢንተርኔት ስካይፕ (Skype) ዙም (zoom) እና ሌሎች ድረገፆችን በመጠቀም የተራራቁና የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ለማገናኘት እየሰራሁ ነው። በቤተሰቦች መካከል የሚደረጉ ንግግሮች የብዙዎችን ልብ፣ ስነ ምግባርና አይምሮን በማነቃቃት ቤተሰባዊ ግንኙነቶችን ለማደስ መንገድን ያመቻቻሉ፡፡ በተጨማሪም እርስ በርስ እና ለአምላካቸው ያላቸውን ፍቅር ይጨምራል፡፡"

(ኤልሳቤጥ) ፡- ይህ የመልዕክቱ ማብቂያ ነበር።

## የእግዚአብሔር ጥሪ ደርሷችኋልን? - June 25 ቀን 2020 ዓ.ም
## Is God calling you, June 25th, 2020

ውድ ቤተሰቦቼ ጌታ በልቤ ለእናንተ አንድ ነገር አስቀምጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዛሬ ከጌታ ራት በኋላ ስለዚሁ ጉዳይ ተናገረኝ፡፡ እናም ምን እንደተናገረ አሁን ላካፍላችሁ ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . በሥሜ የተጠሩ ብዙ ህዝቦቼ የሚኖሩት ለራሳቸው ከዚያም ባለፈ ለወላጆቻቸው ነው፡፡ የተመረጡትን ተጣራሁ፣ ተጣራሁ፣ ተጣራሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንዶች አሁን ያሉበት ህይወት ትኩረታቸውን ሁሉ ጠቅልሎ ስለያዘ ለጥሪዬ መልስ ለመስጠት እንቢ ብለዋል፡፡

ብዙዎች የሚኖሩት ለወላጆቻቸው በመሆኑ ለብዙ ዓመታት ብጠራቸውም እንኳን ከእኔ ይልቅ የሚሰሙት የወላጆቻቸውን ድምፅና ህብረተሰቡ የሚፈልግባቸውን ክብር ነው፡፡ ለመሆኑ ለስንት ጊዜ ነው የራሳችሁን መንገድ ትታችሁ ወደ እኔ እንድትመጡ መጣራት ያለብኝ?

እስከ ህይወታችሁ ፍፃሜ መቆየት አለብኝ? ከእኔ ጋር እንዲሆኑ የጠራኋቸው ጉዳዩን እየተመለከቱት ያሉት በዚህ መልኩ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ሩቅ አይደለም . . .፡፡ እነርሱ የሚሉት "በመጀመሪያ አባቴን መቅበር አለብኝ" ነው፡፡ ይህ ለምንድነው? ከአባታችሁ ፈቃድ አግኝታችሁ ውርስ ለማግኘት ነው? እኔ የጠራኋችሁ ሁሉንም እንድትተዉ ነው፡፡ ወላጆቻችሁ የመረጡላችሁን ህይወት በመኖራችሁ ራሳችሁን ይቅር ማለት አትችሉም፡፡ በኋላ በእኔ ፊት የምትቀርቡት ባዶ እጃችሁን ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉ ነገራችሁን ለአለምና አለም ለሚያባብለው ነገሮች አሳልፋችሁ ሰለሰጣችሁ ነው፡፡ አግብታችኋል፣ ልጆች ወልዳችኋል፣ አርጅታችኋል፡፡ ደግሞም ባህላችሁ ባቀረበላችሁ አስደናቂ ነገሮች ራሳችሁን አደንዝዛችኋል፡፡ እናም በዚህ ሁኔታ ቆይታችሁ ስታረጁ ነው ለእኔ ራሳችሁን መስጠት የምትፈልጉት ?

ወጣትና ጎበዝ ሆናችሁ በልባችሁ እንድትከተሉኝ ስጠራችሁ የት ነበራችሁ? ጥሪዬን በግልፅ ሰምታችሁት ነበር፡፡ ነገር ግን የመረጣችሁት መንገድ የምቾትን መንገድ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ልትቋቋሙ የማትችሉትን ውድቀትና ተስፋ መቁረጥ ዘራባችሁ፡፡ እኔ ስጠራችሁ ብትከተሉኝ ኖሮ አሁን ህይወታችሁ ንቁ፣ ጣዕም ያለውና ሰላማችሁም የማያልቅ ይሆን ነበር፡፡

ልጆቼ አሁን እየተናገርኩት ያለሁት አጥሩን አንፈራጠው የያዙትን ነው:: እናንተ ህይወታችሁ የወላጆቻችሁ እንጂ የእኔ አይደለም:: ወላጆቻችሁ እናንተን በማሳደጋቸው መልካም ሥራ ሰርተዋል:: ነገር ግን ወደእኔ እንድትመጡ ሊለቋችሁ ስላልቻሉ በዚህ ወድቀዋል:: በዚህም ምክንያት የእነሱን ፍላጎት ለማሟላት ችግር የሌለበትን የእነርሱን ፈለግ ይኸውም ኮሌጅ መጨረስ፣ ማግባትና ቤተሰብ መምራትን ተከትላችኋል:: ይህንን ለመስራት ለተመረጣችሁት ምርጫችሁን እባርካለሁ:: ምክንያቱም ይህ ተግባርያዊ የሆነው በእኔ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ ስለሆነ ነው::

ነገር ግን ይህንን አለም ትታችሁ አቧራማውንና አስቸጋሪውን መንገድ እንድትሄዱና እኔን ብቻ እንድታገለግሉ ለመረጥኳችሁ ለእናንተ ግን እንዲህ እላለሁ:: አለም ብዙም ስለማይቀጥል በህይወታችሁ ወዮቻችን እያበዛችሁ ነው:: በአለም ያላችሁን ተሳትፎ እያበዛችሁ በሄዳችሁ ቁጥር በራሳችሁ ላይ የበለጠ ስቃይ እየጨመራችሁ ትሄዳላችሁ:: ምክንያቱም ከአለም ወይም ከአምላካችሁ ለመምረጥ ትገደዳላችሁና ነው:: ልጆች በፈቃዬ አለት ላይ ካልተመሰረታችሁ ህይወታችሁ አይቀጥልም፣ ይወድቃል::

ምን አይነት ፍሬ ነው ማፍራት የምትፈልጉት? የገንዘብ ፣ የደህንነት ዋስትና፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የከፍታ ሥፍራ ወይስ ከገሃነም መንጋጋ ነፍሶችን መንጥቆ ለእግዚአብሔር መንግስት የማብቃት ፍሬ? አሁን ጊዜው ይህንን ለመመልከትና ለመወሰን ውሳኔያችሁ ወደፊት ሊያመጣ የሚችለውን ነገር በደንብ የምታጤኑበት ጊዜ ነው::

በአለም ዓይን ስኬት በሚባለው ወጥመድ መጠመድ ትፈልጋላችሁ? ወይስ እኔን ማገልገልና ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚጨመሩትን የነፍስ ፍሬዎች ትፈልጋላችሁ? እኔ ሁሉን ነገር እንዳዘጋጅላችሁ ትፈልጋላችሁ? ወይስ በራሳችሁ መንገድ፣ በራሳችሁ ጉልበት፣ አለምን ስታገለግሉ ብቃት ባገኛችሁበት መደገፍ? የኔ ወጣቶች ይህንን ስናገር እጅግ ጠንከር ብዬ ነው:: አብዛኛዎቻችሁ የተጠራችሁት ቅዱሳን ለመሆን ነው:: ነገር ግን ስህተት በመፈፀም ለወላጆቻችሁ ኃላፊነት ተሰምቷችሁ ከእኔ ይልቅ እነርሱን አስቀደማችኋል:: ይህ ዝሙት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ከእኔ ጥሪ ይልቅ እንዲሁም እኔ በዚህ ምድር ላይ ለእናንተ ካለኝ ፈቃድ ይልቅ የወላጆቻችሁን ፈቃድ መርጣችኋል:: ይህ ደግሞ ወላጆቻችሁ በእናንተ ላይ አምላክ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል::

አዎ በትክክል እየገሰፅኳችሁ ነው:: ለአለም ጀርባችሁን እንድትሰጡና ጥሪዬን እንድትቀበሉ ለብዙ ዘመን ጠብቄለሁ፣ ጠብቄያለሁ፣ጠብቄያለሁ:: ነገር ግን ብዙዎቻችሁ አሁንም በአቧራ እየተጫወታችሁና ያላችሁን አማራጮች እየመዘናችሁ ነው:: አሁን እናንተን እያልኩ ያለሁት ሐሳባችሁን ገምግሙና በውሳኔያችሁ መሰረት ህይወታችሁን መምራት ጀምሩ:: የወሰናችሁት ከእኔ ጋር ለመጓዝ ከሆነ ወደ እኔ ቅረቡና ሥራውን እንጀምር:: ምርጫችሁ አለም ከሆነ ከእኔ ጋር መጫወቱን ተዉና የመረጣችሁትን ቀጥሉ::

ለመወሰን ካቃታችሁ ደግሞ "ጌታ ሆይ ለመሥራት ፈቃደኛ ነኝና ፈቃደኛ እንድሆን አድርገኝ" በማለት ጠይቁኝ:: ከዚያም ወደእናንተ መጥቼ መስራት እጀምራለሁ:: የጌታ መልዕክት እዚህ ላይ ያበቃል::

(ክሌር) የተወደዳችሁ እኔ ደግሞ ላካፍላችሁ የምፈልገው ነገር አለኝ:: እንዲህ የሚሉ ብዙ ሰዎች አጋጥመውኛል:: "ታውቂያለሽ እኔ ሚሺነሪ ልሆን ነበር፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ ፓስተር ልሆን ነበር፣ ጌታን ላገለግል ነበር፣ ነገር ግን አገባሁ ከዚያም ህይወት በዚያ መንገድ ዝም ብሎ ቀጠለ:: ይህንንም ሲናገሩ በድምፃቸው ውስጥ የልብ ሐዘን

ይታይባቸዋል፡፡ እናም በአለም ስንሆን የሚገጥመንን ወዮ እነዚህ ሰዎች በህይወታቸው በትክክል እየተለማመዱት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልጆች ከትክክለኛው መንገድ ይወጣሉ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ልጆቻችንን እናጣለን፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሥራችንን እናጣለን፡፡ ወይም የቤታችንን ብድር መክፈል አቅቶን ቤታችንን እናጣለን፡፡ ወይም ደግሞ ኑሮ ከአቅማችን በላይ ይሆንና ታመን መሥራት እስከማንችል እንደርሳለን፡፡ አለም ተስፋ የሚያስቆርጠን እጅግ ብዙ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህ ደግሞ የአለም ባህርይ ነው፡፡ ከጌታ ጋር ከሆንን ግን የሚደርስብን ስቃይ እንኳን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚውል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ወይም ለምትፀልዩላቸው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የፆም ስጦታ ተደርጎ እንኳን ሊወሰድ ይችላል፡፡ ጌታ ሁልጊዜ በእያንዳንዷ ደቂቃ ከእናንተ ጋር ይቆማል፡፡ ስለዚህም ጌታን እንደማገልገል የሚያስደስት፣ ውጤታማና የበለጠ ድንቅ ህይወት የለም፡፡ ይህንን እንደ ሰባ አራት ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ሴት ሆኜ እመሰክራለሁ፡፡

በሃያዎቼና በሰላሳዎቼ የወጣትነት ዕድሜዬ የፎቶግራፈር ባለሞያ ነበርኩ፡፡ በዚያን ወቅት የሚያስፈልገኝን ሁሉ ማግኘት የምችል ሴት ነበርኩ፡፡ ይከፈለኝ የነበረው በቀን 500 ዶላር ነበር፡፡ በወቅቱ በአይሮፕላን፣ በጀልባ መጓዝ እንዲሁም ፈረሶችን መጋለብ፣ ብቻ ምን አለፋችሁ ማንኛውንም የምፈልገው ነገር በእጄ ነበር፡፡ ደግሞም ይህንን ሁሉ የሚያመቻቹልኝ ደንበኞቼ ነበሩ፡፡ እኔም ያንን እወደው ነበር፡፡ የኔ ሥራ ወደ ተዘጋጀልኝ ሥፍራ በመሄድ ውበትን ማድነቅና ያንንም በፊልም ቀርጬ በማምጣት ለደንበኞቼ መስጠት ነበር፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ግን ጌታን ባለማወቁ ብዙ የብቸኝነት ዘመናትን አሳልፌያለሁ፡፡ በዚያን ጊዜ ክርስቲያን አልነበርኩም፡፡ ጌታንም አላውቀውም ነበር፡፡ እንዳውም በዚያን ወቅት በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ ነበርኩ፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን በሙሉ ልቤ እውነትን እፈልግ ነበር፡፡ ጌታ በቃ ብሎ ራሱን እስኪገልጥልኝ ድረስ እውነትን ለማግኘት ያልሞከርኩት፣ ያልቆፈርኩት ጉድጓድ አልነበረም፡፡ ጌታም ራሱን ሲገልጥልኝ በእርሱ ፍቅር ተነደፍኩ፡፡

እናም አሁን እየሰራሁ ያለሁት በህይወቴ እጅግ መስራት የምፈልገውን ሥራ ነው፡፡ እናም ጌታን ካገኘሁ ወዲያ ብቸኝነት ቀርቷል፣ ደስተኛ ነኝ፣ ደግሞም ውጤታማ ነኝ፡፡ በዙሪያዬም አስደናቂ ሰዎች አሉ፡፡ ምንም እንኳን የፎቶግራፍ ሥራ ብዙ ገንዘብ ቢያስገኝም፣ የሙዚቃ ሥራዬ ግን ከዛ የበለጠ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ከዛ በበለጠ ደግሞ ከነፍሶች ጋር መስራትና የጌታን ፍቅር ማካፈል ከሁሉ የበለጠ ነገር ነው፡፡ ጌታ እንዴት ድንቅና ከሁሉ የሚለይ እንደሆነ መናገር፣ ብቻ ምን አለፋችሁ አንደበታችሁ ስለእርሱ ለመመስከር የሚገደደውን ሁሉ ለሰዎች መናገር ነው፡፡ እርሱ በጣም አፍቃሪ ነው፣ ይህ ፍቅሩ ደግሞ ለእናንተም ነው፡፡ በህይወታችሁ ለሚገጥማችሁ ማንገጫገጮች ሁሉ የሚያዝንላችሁና በህይወታችሁ ስኬታማ እንድትሆኑ እጅግ የሚጓጓ ነው፡፡ እንግዲህ የማገለግለውና እናንተንም የሚጠራችሁ አምላክ ይህ ነው፡፡ ጥሪውን ትቀበላላችሁ? ትመልሱለታላችሁ? እርሱ በእውነት እየጠበቃችሁ ነው፡፡ ለእናንተ ትልቅ ተስፋ አለው፡፡ እጅግ አስደናቂ የሆነ ዕቅድም ለእናንተ አለው፡፡ ነገር ግን ህይወታችሁን ለእርሱ አሳልፋችሁ ካልሰጣችሁ ምንም ሊያደርግ አይችልም፡፡ እናም ሳትፈሩ ሁሉንም ለጌታ አሳልፋችሁ እንድትሰጡት አበረታታችኋለሁ፡፡ ሁሉንም በእጁ ላይ አስቀምጡትና ወደ ፍፁም ፈቃዱ ይምራችሁ፡፡ ቃል የምገባላችሁና የማበረታታችሁ 30 አመት አገልግዬው በየትኛውም ነገር ላይ እንዴት ታማኝ እንደሆነ ነው፡፡ አሁን እጅግ መልካምና ፀሎትን ከሚያዘወትሩ ሰዎች ጋር እርሱ እንድሰራ የሰጠኝን ሥራ በጫካው ውስጥ እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡ እኔ በህይወቴ እንደዚህ ደስተኛ እሆናለሁ ብዬ አስቤውም አላውቅም፡፡ ህልሜ ፍፃሜ እንዲያገኝ አድርጎልኛል፡፡ እናንተም ብርቱ ሆናችሁ ያለፈ ታሪካችሁንና ወላጆቻችሁ ከእናንተ የሚጠብቁትን ትታችሁ ኢየሱስ ለእናንተ ያዘጋጀውን አጥብቃችሁ እንድትይዙ እፀልያለሁ፡፡

ወድ ጌታ ሆይ ሁለት ሐሳብ ያለንን ይቅር በለንና ወደ ቅርብ ወዳጅነትህ ምራን፡፡ አንተን ለመስማት፣ የአንተን ፈቃድ በህይወታችን ለመታዘዝና አንተ ለፈጠርከን ዓላማ ለመኖር ፈቃደኞች እንድንሆን አድርገን፡፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን፡፡

## ለፀሎቶቻችን መልስ ለማግኘት እንዴት መፀለይ አለብን? - ጁን 30 ቀን 2020 ዓ.ም

## Your parayer and answer, June 30, 2020

የተወደዳችሁ ኸርት ዱዌለርስ የጌታ ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ እንዲሁም በየዕለቱ ጌታን ምን እንደሚያስደስተው የበለጠ ማወቅ ተትረፍርፎላችሁ ደስታን ይስጣችሁ፡፡ ጌታንም እንዲህ ብዬ ጠየኩት "ለውድ ቤተሰቦችህ ዛሬ የምትላቸው ምንድነው?"፡፡

እርሱም. . . "አንቺ በልብሽ ውስጥ ያለው ምንድነው" ብሎ ጠየቀኝ፡፡

እኔም "ስለ ፀሎት ማስተማር እንዳለብን ይሰማኛል ደግሞም ለዚህም ጥያቄ ቀርቦልኛል" አልኩት፡፡

እርሱም "ስለ ፀሎት ትምህርት" አለኝ፡፡

የተወደዳችሁ ቤተሰቦቼ ይህንን ጥያቄ ሰዎች ከጠየቁኝ በኋላ በዚህ መጠለያ ውስጥ አዲስ አባላትን ስንቀበል ስለ ፀሎት ብዙ እየተማርኩና በአለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን በምን ሁኔታ ላይ እንደሆነች እየተረዳሁ መጣሁ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." የፀሎታችሁን መልስ በአውንታዊ መልኩ የምትቀበሉት በምን አይነት መንገድ ወይም ስልት መፀለያችሁ አይደለም፡፡ እንደማንኛውም መልካም አባት ፀሎታችሁን በመመለስ ደስታን መስጠት እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከእኔ የምትፈልጉትን ነገር ለመቀበል በትክክለኛው ሁኔታ ላይ አይደላችሁም፡፡ እንደ ሰማይ ከዋክብት የፀሎታችሁን መልስ የሚዘጉ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ይህንንም ስናሳጥረው መልካም ዝንባሌ ያለው ልብ፣ ንፁህ ህሊና እና ህይወታችሁ በእኔ ፈቃድ ውስጥ መሆኑ በሚለው ሊጠቃለል ይችላል፡፡ ይህም እናንተን ለኩራት የማይጋብዝና ክብርን ከንቱ የማያደርግ ሊሆን ይገባዋል፡፡

"ፀሎታችሁን ለመመለስ እጓጓለሁ፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የጠየቃችሁትን ብሰጣችሁ በህይወታችሁ ምን ሊያስከትል እንደሚችል አታውቁም፡፡ በእኔ ፈቃድ ውስጥ ናችሁ? ለሌሎች ነው የምትጠይቁት? እናንተ ለምትፈልጉላቸው ነገር ለመማር በትክክለኛው ሁኔታ ላይ ናቸው? የጠየቃችሁላቸው ነገር ይጠቅማቸዋል ወይስ ጭንቀት ይፈጥርባቸዋል? ብዙ ነገሮችን የምከለክለው የመጨረሻ ውጤቱ ለዛ ነፍስ ጥሩ እንደማይሆን ስለማውቅ ነው፡፡

"ስትጠይቁ በእኔ ፈቃድ መሰረት ከጠየቃችሁ እምነታችሁን እንዲጨምርና በእኔ እንድትታመኑ ለማድረግ መልሱ ቢዘገይም ፀሎታችሁ በእርግጥ ይመለሳል፡፡ ለእኔ የፀሎት ጥያቄ ከማቅረባችሁ በፊት እነዚህን ዝርዝር ጥያቄዎች ራሳችሁን ጠይቁ፡-

1. ጌታ ይህ ለእኔ/ ለእነርሱ/ የአንተ ፈቃድ ነው?
2. ይህ ለሌሎች ጉዳት የሚያመጣ ነው?
3. ኃጢያት ወይም ይቅር ያለማለት በህይወታችሁ/ በህይወታቸው አለ?
4. የፀሎታችሁን መልስ እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ?

5. የፀሎታችሁ መልስ ከእኔ ጋር ያላችሁን ህብረት የጠለቀ ያደርገዋል ወይስ ያበላሸዋል? ብዙ ጊዜ አንድን ነገር እጅግ ስትፈልጉ ወደ እኔ እንድትቀርቡ ያደርጋችኋል፡፡
6. ኩራትን የሚያመጣና ክብርን ከንቱ የሚያደርግ ወይም ቆይቶ ጉዳትን ሊያመጣ የሚችል ሊሆን ይችላል?
7. በምድር ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን መንግስት የሚጠቅም ነው ወይስ ለግል ጥቅም ብቻ የሚሆን ነው?
8. በመልሱ ምክንያት የሚመጣባችሁን መንፈሳዊ ውጊያ ለመመከት የሚያስችል መሰረት አላችሁ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . እነዚህ እንግዲህ ለእናንተ ፀሎት አውንታዊ መልስ ከመስጠቴ በፊት የምመለከታቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ እናም አንዳንድ ጊዜ የጠየቃችሁትን ካገኛችሁ በኋላ ያልጠበቃችሁትን ዋጋ ሲያስከፍላችሁ ታገኙታላችሁ፡፡ እዚህ ላይ ማለት የምፈልገው በእውነቱ ከሆነ ምን ጊዜም ቢሆን ያልጠበቀ ዋጋ ማስከፈሉ የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው አንድ ነፍስ አርቆ በማየት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ሁኔታዎችን ቀድሞ ሊረዳ የሚችለው፡፡

"በጥልቁ ልባችሁ ውስጥ ምንድነው ያለው? የግላችሁ አለም ነው ወይስ የኔ መንግስት? ልባችሁ ከእኔ ጋር አንድ ሆኖ ማየት እጓጓለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ የተበላሸውንና በእናንተ ላይ ግፊት የሚያመጣውን ለማንፃት ጊዜ ይወስዳል፡፡ ከእኔ ጋር አንድ እድትሆኑና አንድ ላይ በመሆን ለነፍሶች እጅግ መልካም የሆነውን ለማከናወን እጓጓለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በአንድ ሌሊት ሊፈፀም የሚችል ነገር አይደለም፡፡ በአለም ስትኖሩ ያጠራቀማችሁትን ኩራት፣ ፍርሃት፣ መዳፈርና ሌሎችንም ጤናማ ያልሆኑ ዝንባሌዎችን ከውስጣችሁ ለማስወገድ ብዙ ጊዚያትን የሚፈጅ ነው፡፡

"ልባችሁ ወደ እኔ እና ወደ አጀንዳዬ ብቻ የተመለሰ ከሆነ በአለም ምቾት እንደጠለቁት ሰዎች ብዙ ጊዜ አይፈጅም፡፡ የእኔ ውዶች እኔ የምሰጣችሁ መፅናኛ አለም ከሚሰጣችሁ መፅናኛ ጋር መቀላቀል የለበትም፡፡ ይህም የሚሆንባችሁ ደስታን ከሚሰጠው መንፈሴ ይልቅ አለም የሚሰጣችሁ ደስታ ሲያይልባችሁ ነው፡፡ ስለዚህም ከእነዚህ ነገሮች ራስን ባዶ በማድረግ ለመንፈሴ ቦታን ለመስጠትና ልቤ ህሊናችሁን እንዲገዛ ለማድረግ ጊዜ ይፈጃል፡፡

"ሌላው ደግሞ የድካም ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ ማዘር ክሌር ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ብትሞክርም እንኳን ልታሸንፋቸው ያልቻለቻቸው አንዳንድ ድካሞች አሉባት፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የልቧ ዝንባሌ ሌሎችን ለመርዳት ልጠቀምባት እንድችል የሚያስችለኝ ነው፡፡ የኔ ውዶች ከእናንተ ጋር የምሰራው በእናንተ ሁኔታ ነው፡፡ በእናንተ ኃይል ልትቀይሩ የምትችሉትን፣ እንዲሁም ባላችሁበት ወቅት ላይ ከአቅማችሁ በላይ የሆነውን ነገር እመለከታለሁ፡፡ ስለዚህም ተልዕኳችሁን በዛ መንገድ አስተካክላለሁ፡፡

"ታናሽነትን እወዳለሁ፡፡ በድካማቸው ታማኝ የሆኑትን ነፍሶች እወዳለሁ፡፡ በተደበቀ ልባቸውና ህሊናቸው ወይም በንግግራቸው በሌሎች ላይ የማይፈርዱትንና ሌሎችን የማያዋርዱትን እወዳለሁ፡፡ በሌሎች ላይ በሚፈርዱት ላይ ፊቴን አዞራለሁ፡፡ ነገር ግን የራሳቸውን ስህተት አውቀው የሌሎችን ስህተት በመሸፈን ለእነርሱ የሚፀልዩትን እቀርባለሁ፡፡ ይህ እኔን እጅግ የሚያስደስተኝና ብዙ የበለጠ ቅባቶችንና ስጦታዎችን እንድሰጥ የሚያደርገኝ ነው፡፡ ወደሚያስፈልገው ደረጃ "ደርሻለሁ" የሚሉትን ነፍሶች ነው ኩራታቸውን ተገንዝበው ንስሐ ገብተው ረዥሙን የትህትና ጉዞ እስኪጀምሩ ድረስ የማስወግዳቸው፡፡ ይህም ማለት በእኔ መስተዋት ራሳቸውን ማየት እስኪጀምሩ ድረስ ማለት ነው፡፡በዚህ መግባባት መሰረት ለእኔ መቅረብ ያለበት ጥያቄ "ጌታ ሆይ አንተ የገለጥከውን የነፍሴን ኃጢያት አይቻለሁና እባክህ ቀይረኝ፡፡" የሚለው ነው፡፡ እነዚህን ቃላቶች ስሰማ እደሰታለሁ፡፡ ለመለወጥ የሚፈልጉ ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ ፍፁም ለመለወጥ የሚጓጉትን የሚጠብቃቸው ቅባትና ክብር እነርሱ ከሚረዱት በላይ ነው፡፡

"ይህ ዑደት ሲያልቅ ነው (ይህም የማየትና የመለወጥ ዑደት) እነሱን "የኔ ሙሽራ አንቺ እንዴት አስደሳችና ቆንጆ ነሽ የኔ እርግብ" ማለት የምችለው፡፡

"አንዴ እውነተኛውን ማንነታችሁን ከተለማመዳችሁት ልዩ ሰው ትሆናላችሁ፡፡ በሌሎች ላይ ትዕግስት በማጣት ጣታችሁን በሰዎች ላይ ለመቀሰር አትሞክሩም፣ ወይም ለእነርሱ ቸርነት ለማድረግ ወደኋላ አታፈገፍጉም፡፡ የኔ እናት እንደዚህ አይነት ነፍስ ነች፡፡ ለእርሷ ለተሰጧት ነፍሶች ሁልጊዜ ጠበቃ ትቆማለች፡፡ እነዚህም ነፍሶች ሁልጊዜ እኔን በቃልና በስራ ለማስደሰት ራሳቸውን የሚሰጡ፣ ስሜቴን የሚጎዳ አንድ ነገር ደርሶብኝ ልቤ ተጎድቶ ስሰቃይ ስሜታቸው ተነክቶ በልባቸው የሚሰቃዩ ነፍሶች ናቸው፡፡ ክሌር በስቃዬ ጊዜ ቸርነት በተሞላበት ፀሎትሽ፣ ትዕግስት በተሞላ በውስጥ ፍላጎት፣ እርዳታ እንደሚጠይቁ እያየሽ በዛ ነፍስ በኩል በመቆም ራስሽን ከእኔ ጋር የበለጠ አንድ በማድረግ አፅናኝኝ፡፡ ይህንንም የምታደርጊው በፀጋዬ ነው፡፡ በዚህም የበለጠ ተሳታፊ ሆነሽ በተለይም ለጠላቶችሽ በበለጠ መልኩ ለማየትእጓጓለሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ሰይጣንን ለማገልገል ለመረጠ ሰው እንዴት ጠበቃ ሆነህ ትቆማለህ ?

እርሱም እንዲህ በማለት መለሰ . . . በህይወታቸው ምን አይነት ሁኔታዎች አጋጥሟቸው ነው ከእኔ ይልቅ ሰይጣንን ማገልገል ይሻላል ብለው እንዲያምኑ ያደረጋቸው? ብለሽ ራስሽን ጠይቂ፡፡ በህፃንነታቸው በአገልጋይ የወሲብ ጥቃት ደርሶባቸዋል? ርህራሔ በሌለው መንገድ በወላጆቻቸው ተደብድበው ከዚያም የሚያድናቸው በመፈለግ ወደ እርግማን መንገድ ገቡ? ፍቅርን እጅግ ከመፈለጋቸው የተነሳና ይህንንም ሊያገኙ የሚችሉት ብቸኛው ቦታ ሁልጊዜ አንድ ላይ የሚሰበሰቡ ጠንቋዮችጋ መስሏቸው ነው? እስከማይችሉት ድረስ ስለሚደበደቡ የት መሄድ እንዳለባቸው ስለማያውቁ በአስማተኛ ተስፋ ተስጥቷቸው የሚጠብቃቸውን ቁጥርና ኃይልን በመፈለግ ወደ አስማተኞች ሄዱ? ወይስ በጨቅላ ዕድሜያቸው ወደ ጠንቋይ እንዲሄዱ ተደርገው በግዳጅ ወንጀል እንዲፈፅሙ ተደረጉ? ለምሳሌ ህፃን ልጅ እንዲገድሉ? እነዚህ ነገሮች ሁሉ አንቺ በምትኖሪበት አካባቢ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ሰይጣን አንድ ነፍስ ለእርሱ እንዴት እስረኛ እንደሚያደርግና እዛው እንዴት እንደሚያቆይ ያውቃል፡፡

"እነዚህ ሰዎች ያልገባቸው አንድ ነገር ወደ እኔ ቢመለሱ ይቅር እንደምላቸው ነው፡፡ እንዲሁም ሰይጣን ከእኔ ጋር እኩል እንደሆነና እርሱ ደግሞ በጣም መልካም የሆነ ማንነት ያለው እንደሆነ ነው እነርሱ እንዲያምኑ የተደረጉት፡፡ በቤተክርስቲያን ደግሞ ፍርድንና አስመሳይነትን አይተዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የእኔ ባህርይ እንደዚያ መስሏቸዋል፡፡ አገልጋይን ወይም ሰውን ሳይሆን አንድ ጊዜ ብቻ ለእኔ ዕድል ቢሰጡኝና ወደ እኔ ቢመጡ እጄን ዘርግቼ እቀበላቸውና በእርጋታ ወደ ነፃነት እመራቸው ነበር፡፡

"ሰይጣን "ነፃነት" የምትለዋን ቃል አይወዳትም፡፡ ምክንያቱም እርሱ እድሜ ልኩን የኖረው በመክሰስ፣ ሽልማትን በመስጠትና በውሸት ለእርሱ ነፍሳትን እስረኛ በማድረግ ነው፡፡ እነዚህንም የሚያደርገው እንደ አንድ ነፍስ ሁኔታና የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ እርሱ የሚቀርበው ስሜትን በሚስብ መልኩ ነው፡፡ እርሱ በውሸት እጅግ የተካነ ነው፡፡ እናም ነፍሶች እርሱ መልካም እኔ ደግሞ መጥፎ እንደሆንኩ ያምናሉ፡፡ ስለዚህም ሰይጣን እንዲያምኑ ያደረጋቸውን ይህንን ውሸት ለመገልበጥና እውነቱን እንዲያውቁ ለማድረግ ብቸኛው መንገድ ፍቅርን መስጠት ነው፡፡ በምንም ነገር ላይ ያልተመረኮዘውን፣ ሰይጣንና አጋንንቶቹ ለማታለያ ከሚያቀርቡላቸው በስተቀር አይተው የማያውቁትን ንፁህ ፍቅር መስጠት ነው፡፡"

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ ለማንሳት የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ ሰይጣን አምላኪዎቹን ክብር የተሞላበት የውሸት ራዕዮችን፣ ቤተ መንግስቶችን፣ ትላልቅ ስጦታዎችንና እንደዚህ የመሳሰሉትን ነገሮች እንዲያዩ እንደተደረጉ እርግጠኛ ነኝ፡፡ እነዚህ ሁሉ የመንፈሳዊው አለም ነፀብራቅ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ክብር ያለባቸው ነገሮች የሚገኙት በመንግስተ ሰማያት በመሆናቸው ሰይጣን ሊደርስባቸው የሚችልበት ቦታዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህም እርሱ ያቀረባቸው ነገሮች ሁሉ ውሸትና ሰውን ለማማለል የሚጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ለዚህ ነው ጠላቶቻችሁን እንድትወዱና ለሚያሳድዳችሁ እንድትፀልዩ የነገርኳችሁ፡፡ ስማችሁን የሚያጠፉትንና የሚጎዷችሁን መልካም አድርጉላቸው፡፡ ውዶች እኔ የሰጣኋችሁን ፍቅር ለእነርሱም አሳዩአቸው፡፡ እኔን ለማያውቁት የኔን መልካምነት አፍሱላቸው፡፡ ምናልባትም ያላችኋቸው ተስፋ እናንተ ብቻ ልትሆኑ ትችላላችሁ ስለዚህም ፀልዩላቸው፡፡"

ከሌር ይህንን ሁሉ አሁን መናገር የያዝኩት የተከበብሽው የጨለማውን መንገድ በሚለማመዱ ሰዎች ስለሆነ ነው፡፡ በእርግጥም በአገሪቱ ከፍተኛ ስልጣን ላይ ያሉትን እንኳን አይተሻል፡፡ በውጪ ሲታዩ "ጥሩ" የሚመስሉ እነዚህ ሰዎች ለሰይጣን በጥልቅ ራሳቸውን በመስጠት በዚህ አለም ላይ የሚገኘውን መልካም ነገር ሁሉ እያበላሹ እንደሆነ የሚያምኑ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው፡፡

"ህዝቤ ሆይ መልካም የሆነውን ሁሉ እንዲያጠፉና ክፉን እንዲያበዙ አድርጎ ጠላት ላዘጋጃቸው ለእነዚህ ሰዎች ፀልዩ፡፡ እነዚህ የሚያሳዝን ዕጣ የደረሰባቸው ነገር ግን ውጤቱ የዘላለም ስቃይ እንደሆነ ያልተገነዘቡ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ዲያቢሎስ በውሸትና  ባስለመዳቸው ነገር ተገዝተው መንግስትን እንወርሳለን ብለው ያመኑ ሰዎች ናቸው፡፡ በትክክል ነው የዘላለም የእሳት ባህርን ይወርሳሉ፡፡ ይህም የሚደርስባቸው ወደ ስሜቶቻቸው ካልተመለሱ፣ ስለ እነርሱ የሚማልድ ከሌለና እውነትን ካልተቀበሉ ነው፡፡ የጌታ መልዕክት እዚህ ላይ አበቃ፡፡

አሁን ደግሞ የማቀርብላችሁ ጠንቋዮች እንዲለወጡ እንዴት መፀለይ እንዳለብን የተሰጠኝን ፀሎት ነው፡፡ ይህንንም ፀሎት የምንፀልየው ለተከታታ 30 ቀናት የሰዎቹን ሥም በመጥራት ነው፡፡ ጌታም እንዲለወጡ ፀጋን ይሰጣቸዋል፡፡ እነርሱ ካልተቀበሉ ግን ለሚቀበለው ለሌላ ነፍስ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

የተወደድህ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሰጡትን የ ________________________________ ነፍሶችን በፊትህ አቀርባለሁ፡፡ እባክህ እነዚህን ነፍሶች በቅዱሱ ዕይታህ መሰረት አድናቸው፡፡ ነፍሳቸውን ከአውሬው ባርነት ነፃ አውጣቸው፡፡ የዘላለም ድነትንም ስጣቸው፡፡ አሜን፡፡

## የጌታን ፈቃድ በትክክል መለየት ለምን ያስቸግራል? - ጁላይ 2 ቀን 2020 ዓም.

## Why Discernment Fails, July 2, 2020

የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ ዛሬ የምናወራው የጌታን ፈቃድና ሐሳብ በትክክል ስለመረዳት  /Diserenment/ ጉዳይ ነው፡፡ ፈቃዱን በትክክል ለመለየት ሳንችልና ሲዘበራረቅብን ለምን እንደነግጣለን ብለን ስናስብ ምክንያቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛ መሆን አጣዳፊ፣ የመጀመሪያ አስፈላጊና የህይወት ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ ይኸውም የጌታን ፈቃድ በትክክል መረዳት ለግል ጥበቃ፣ እንዲሁም ህይወት ቀጣይ እንዲሆን አስተማማኝ ስለሚያደርገው ነው፡፡ ይህ ላይገባን ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ውስጣዊ እውነቱና መሰረቱ ይኸው ነው፡፡ ይህ በጣም ጥልቅ የሆነ የመጀመሪያ ተፈጥሯዊ ምላሽ ነው፡፡ ለአቅርቦቶቻችን ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እንዳለብን ያህል የጌታን ፈቃድ በትክክል መረዳትም ለመኖር እጅግ አስፈላጊው ክፍል ነው፡፡ ደግሞም ሰው ስለሆንን ትክክል ያለመሆናችን የማያረጋጋና የሚያስፈራ ነገር ነው፡፡ ለመኖር የምናደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ የሰው ልጅ የሚያደርገው የመጀመሪያው ተፈጥሯዊ ምላሽ ነው፡፡ ይህም አይምሮ የሚሰጠው ምላሽ በሰውነት እንቅስቃሴ ይገለጣል፡፡ ለምሳሌ አንድ መኪና በጣም እየበረረ ሲመጣ ለማምለጥ ከመንገዱ ላይ ዘለን እንወጣለን፡፡ ስለዚህም ነው ሰዎች የተለየ ሐሳብ ለማፍለቅ ችግር የሚሆንባቸው፡፡ ጌታ እባክህ ስለዚህ ነገር እኔ ከማወራ ይልቅ አንተ የበለጠ ብትናገር ደስ ይለኛል፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . ትክክል ነሽ፡፡ አንድ ነፍስ ትንቅንቅ ሲገጥማት ራሷን ትከላከላለች፡፡ ይህ ራስን ለመከላከል የሚደረግ ዝንባሌ ደግሞ በትክክል ወደመረዳት/Discernment/ ጉዳይ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ብሎ ከዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ሁላችሁም በደንብ የምታውቁት ጉዳይ አንዲት እህት መንፈስን የመለየት ችግር ገጥሟት ነበር፡፡"

(ክሌር)፡- በትክክል ባለመለየቴ ከሚመጣብኝ ነገር የበለጠ የሚያሳፍር ነገር የለም፡፡በጣም የሚያም ነው! ይህ የሚጎዳኝ በአጠቃላይ መልኩ ነው፡፡ ማለቴ ሁሉንም የህይወቴን አቅጣጫ የሚነካ ነው፡፡ ይህም አንድ የጥርስ ሃኪም የጥርስን ህመም ለማከም እንደሚያደርገው ሳይሆን ከዛ በበለጠ መልኩ መጥፎ ስሜትን የሚፈጥር የአይምሮ ጉንፋን ዓይነት ነው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . በወሰናችሁት ውሳኔ እርግጠኞች ሳትሆኑ ስትቀሩ እንደ ጉዳዩ አሳሳቢነት መጠን መሸበር ትጀምራላችሁ፡፡ የኔ ውዶች በትክክል መለየት እንዳይቻል ስፈቅድ ዕረፍት ማድረግን እጠላለሁ፡፡ በእውነት ነው የምጠላው፡፡ ምክንያቱም የሰጠኋችሁ ቃል የማይጣስ ቃል አድርጋችሁ ስላመናችሁ በእኔ እንደተከዳችሁ እንደሚሰማችሁ አውቃለሁ፡፡

"በሁሉም የህይወት አቅጣጫዎች ከሚገባው በላይ በራስ የመተማመን ወቅት አለ፡፡ ስሜቶቻችሁን ትታችሁ ሁሉም ደህና ነው በሚል በራሳችሁ በመተማመን በግድየለሽነት በጣም ደስተኞች ትሆናላችሁ፡፡" ልክ እዚህጋ ጌታ አስቀመኝና ብሊትሊ/ blithely/ የሚለውን ቃል ከቃላት መፍቻ ላይ እንዳይ አደረገኝ፡፡ blithe የሚለው ደስተኛና ግድየለሽ በሚል ተተርጉሟል፡፡ ሲብራራም ትኩረት መስጠት የሚገባውን ያህል ትኩረት የማይሰጥ ይላል፡፡

ጌታም ቀጠለ. . . "በዚህ ጊዜ ነው በትክክል ለመለየት ችግር የሚገጥማችሁ፡፡ የሚመች፣ ሥጋት የሌለበት በሚል፣ ለደስታ የታደለ በሚል አመለካከት ውስጥ ትወድቃላችሁ፡፡ እኔ ደስተኞች መሆን የለባችሁም እያልኩ አይደለም፡፡ ነገር ግን ክርስቲያን በምንም ዓይነት ግድየለሽ ሊሆን አይገባውም፡፡ እናንተ በጠላት ዒላማ ውስጥ የገባችሁ ስለሆነ አንድ የተሳሳተ እርምጃ እንዴት ለውድቀታችሁ ሊሆን እንደሚችል ጠላት ይመለከታል፡፡ የኔ ውዶች በትክክል ለመለየት ሳይሳካላችሁ ሲቀር እንዴት እንደሚሰማችሁ እኔ በደንብ አውቀዋለሁ፡፡ እኔ ህመማችሁ እየተሰማኝ፣ ነፃ እንድትወጡ እየፀለይኩና እያፅናናኋችሁ እዛው ከእናንተ ጋር ነበርኩ፡፡ ስለ ደስታችሁና ስለ ሰላማችሁ እጅግ በጠለቀ መልኩ እጠነቀቃለሁ፡፡ ደግሞም በትክክል መለየት ያለመቻል በህይወታችሁ የሚያመጣውን ትልቅ ጥፋት አውቃለሁ፡፡ የሰራችሁት እያንዳንዱን ነገር በመጠየቅ ምን ሰርቼ ይሆን በማለት መጠየቅ ትጀምራላችሁ፡፡ ቢሆንም ግን ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ሳይሆኑ በፊት ማወቅና ስህተታችሁን እውነት ነው ብላችሁ ባመናችሁት መልኩ በጊዜው ማረሙ ጥሩ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በትክክል የመለየት ስህተት የሚመጣው አንድ ነገር በእናንተ መንገድ እንዲሆን ፅኑ ፍላጎት ሲኖራችሁ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከጉዳዩ ጋር እጅግ መያያዛችሁ እየጨመረ በሄደ መጠን በትክክል የመለየት ችሎታችሁ የሚታመን መሆኑ እየተዳከመ ይሄዳል፡፡ ይህ ቢሆንም ግን እውነቱን ለመማምጣት ከእናንተ ጋር እሰራለሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ አስታውሳለሁ ስለ ጋብቻ ለእኔ የነበረህን ፈቃድ በትክክል ለመለየት ምንም ነገር ለማመን አልቻልኩም ነበር፡፡ በእኔ ውስጥ የሚሰማኝን ለስላሳ ድምፅህን እንኳን ለማመን አልቻልኩም ነበር፡፡ ምክንያቱም ለማግባት እጅግ ፈልጌ ስለነበረ ነው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . " ለዚህ ነው ከጉዳዩ እንድትለዩ ያስተማርኩሽ፡፡ እናንተ የምትፈልጉት የኔን ፈቃድ ከሆነ በመለየት የሚገኘው ማንኛውም ውጤት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ችግር የሚከሰተው እናንተ ከነገሩ ጋር እጅግ ተጣብቃችሁ እውነቱን ለመሸፋፈን ስትሞክሩና እኔ ደግሞ ለነገሩ ትኩረት እንድትሰጡ ለማድረግ ስሞክር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ዓይነተኛ ግራ መጋባት ይመጣል፡፡ ወይም ቢያንስ አጋንንቶች የሚነግሯችሁ ይህንን ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ግራ ተጋብታችሁ ሳይሆን አንድን ነገር እንዲሆን እጅግ ከመፈለጋችሁ የተነሳ ሌላውን ውጤት ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናችሁ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ስለ ጉዳዩ በውስጣችሁ ግጭት ትፈጥራላችሁ፡፡ ይህም እውነቱን እየሸሻችሁ እንደሆነ እንኳን መገንዘብ ሳትችሉ ነው፡፡

"ይህንን ልነግራችሁ ይገባል፡፡ አጋንንት በመፅሐፍ ቅዱስ የተሰፋ ቃሎች ንባብ ላይ እንኳን ጣልቃ በመግባት በትክክል እንዳትለዩ ያውኳችኋል፡፡ ምክንያቱም በአንዳንድ ውጤቶች ላይ ጤንነት በሌለው መልኩ እንደተጣበቃችሁ ይረዳሉ፡፡ በዚህም የተሳሳተ ምሪትን በመስጠት ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እንድትሄዱ ያደርጓችኋል፡፡ እኔ ደግሞ ይህ እንዲሆን እፈቅዳለሁ፡፡ ምክንያቱም ከባድ የመፈለግ ዝንባሌ ትክክል እንዳልሆነ እንድትረዱ ነው፡፡ የተወደዳችሁ ይህ በተለያየ ዓይነት መንገድ በየቀኑ ተደጋግሞ የሚከሰት ነገር ነው፡፡

"ለዚህ ነው በሁሉም ነገር ላይ የራሳችሁን ፈቃድ ፍፁም በሆነ መልኩ መተው ለሰላማችሁና ለደስታችሁ ቁልፍ የሚሆነው፡፡ ጠላታችሁ እጅግ ብልህ ስለሆነ በልባችሁ በተደበቀው ፍላጎት መሰረት በተሳሳተ መንገድ ሊመራችሁ ይሞክራል፡፡ አንዳንዴም ይህንን የሚያደርገው እናንተ ፍላጎት እንኳን እንዳላችሁ እውቀቱ ሳይኖራችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ነው በእኔ ፈቃድ ውስጥ እንድትጓዙ የነፍስ ጓደኛ ወይም የበለጠ የህይወት ልምድ ያለውን ሰው የምልክላችሁ፡፡ በቀደሙ ጊዜያት በከፉ እረኞች የተጎዱና ለራሳቸው ጥቅም በማይገባ መልኩ በሚቆጣጠሩ እረኞች ምክንያት ትልቅ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ትክክለኛው የቱ እንደሆነ ለመለየት ማንንም አያምኑም፡፡

"በዚህ ጊዜ መለየት የምትችሉት በፍሬዎቻቸው ነው፡፡ የኔን ፈቃድ ለመለየት የምትፈልጉበት ወቅት ላይ ከሆናችሁና በፈቃዴ ውስጥ የሆናችሁ መስሏችሁ ፍሬው ግን መጥፎ ከሆነ ምናልባት ተታላችኋል፡፡ እዚህጋ አንድ የምነግራችሁ ነገር አንዳንድ ጊዜ ፍሬው መጥፎ ሊመስል ነገር ግን ሃቁ የጠላት ተቃውሞ ሊሆን ይችላል፡፡ ከጠላት ተቃውሞ ሲመጣ ደግሞ ያንን መለየት ሌላው ነጥብ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ውሳኔ ወሰናችሁ እንበል፡፡ ውሳኔው ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የወሰናችሁትን ተግባርያዊ ለማድረግ ግን ሁሉንም ዓይነት ተቃውሞ ይገጥማችኋል፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ ተጨማሪ የመለየት ነጥብ ላይ ደርሳችኋል፡፡ ስለዚህም ያደረኩት ትክክለኛ ምርጫ ነው? ጠላት እየተቃወመኝ ነው? ወይስ ጌታ ትክክል ያልሆነን ነገር እንዳልሰራ እየከለከለኝ ነው? በማለት መመርመር አለባችሁ፡፡

"አያችሁ ትክክለኛ የሆነውን ለመለየት ምንም ቀላል መልስ የለውም፡፡ የተዘበራረቀና አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህም በጣም ትዕግስተኞችና ጌታ እንደሚያስተካክለው ፍፁም እርግጠኞች መሆን አለባችሁ፡፡ የወሰዳችሁት እርምጃ ፍሬው ምንድነው? የክርስቶስን አካል የሚገነባ ነው? ወይስ መለያየትንና ቅሌትን የሚያመጣ ነው? ክሌር ይህንን የምለው ለአንቺ ነው፡፡ ምክንያቱም በቅርብ ጊዜ ከአንድ ነፍስ ጋር ያጋጠመሽ ጉዳይ ስላለ ነው፡፡ ያችም ነፍስ ሌላ አንድ ነፍስን በማሳት ቅሌትንና መከፋፈልን በመካከላችሁ ፈጥሯል፡፡ በወቅቱ ፍሬዎቹስ ምን ነበሩ? መከፋፈል፣ ጠላትንት፣ ፍርድ እንዲሁም ባለፉ ወቅቶች አብረው በደህና ሲሰሩ ከነበሩት መገለል አይደለምን?

"እነዚህ ነፍሳት ምን እየሰሩ እንደሆነ ግንዛቤው የላቸውም፡፡ ነገር ግን በፍሬው እየኖሩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ አይደለም፡፡ በእኔ ዕይታ ጥሩ አይደለም፡፡ እኔ ልጠቀምባቸው የምፈልገው በበለጠ መልኩ ነበር፡፡ ነገር ግን እነርሱ የአንቺን ትክክል የመለየት ችሎታ ሊቀበሉ አልቻሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ የእነርሱ ምርጫ ንስሐ ገብተሽ ከእነርሱ ጋር እስክትስማሚ ድረስ ከአንቺ ጋር ንግግር ማቆምን ነበር፡፡ ምክንያቱም እኔ እንዲህ አድርጉ ያልኳቸው ስለመሰላቸው ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገር ለእነርሱ ተናግሬያለሁ? በፍፁም እኔ እንዲህ አላልኩም፡፡ እኔ መከፋፈልን፣ ኩራትንና አመፅን በአካሌ ውስጥ እጠላለሁ፡፡ እነርሱ በትክክለኛው የጠላት ወጥመድ ውስጥ ነው የገቡት፡፡ ለአመፀኞቹ የምመኝላቸው ታማኝ ሆና ቃል ለገባችው በቀላል ጉዳዮች ላይ ራሳቸውን አስገዝተው እንዲሰሩ ነው፡፡

"እታዘዛለሁ በማለት ቃል የገባችሁለትን መናቅ የተሰጣችሁን ፀጋ ማጣት ነው፡፡ ይህ የእኔ መንገድ አይደለም፡፡ የኔ መንገድ አንድ ነገር አልስማማ ከሚል መሪ ጋር አብሮ መስራት ነው፡፡ የኔን መንገድ ለመረዳት የሚጎድላቸው እውነታ ካለ ደግሞ አስተምራቸዋለሁ፡፡ ባልተለመደ የኃጢያት ሁኔታ ካልሆነ በቀር ከህይወቴ አስወጥቼ ከእነርሱ ጋር ንግግርን አላቆምም፡፡ ደግሞም ይህንንም አድርጉ ብዬ አላስተምርም፡፡ በእናንተ ውስጥ የተፈጠረው ደግሞ ከዚህ ውጪና በኃሳብ ልዩነት የተከሰተ ነው፡፡ መጥፎ ፍሬ ስላችሁ ይህንን ማለቴ ነው፡፡

"የኔ ውዶች በትክክል ስለመለየት ከዚህ የበለጠ ብዙ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን በአንድ ዐረፍተ ነገር ሳጠቃልለው "ፍሬውን ተመልከቱ" የሚል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በፍሬው ለመለየት በቂ ጊዜ ላይኖር ይችል ይሆናል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ወዲያው በሚያመጣው ውጤት በምን ዓይነት የውስጥ ፍላጎት እንደተደረገ፣ መልካም ወይም ክፉ እየሰራ እንደሆነ ሊገልፀው ይችላል፡፡

"የኔ ውዶች ከጠላቶቻችሁ የበለጠ ብልህ ልትሆኑ ይገባል፡፡ ደግሞም ጠላቶቻችሁ ሁልጊዜ ጣልቃ ሲገቡ ለራሳቸው እንዲመች አድርገው ለማጣመም እንደሆነ ጠርጥሩ፡፡ ለእነርሱ የሚመቸውን ነገር እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ? ጠላት ለመስራት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥርለት መከፋፈል፣ ስሜቶችን የሚጎዱ ነገሮች፣ መለያየት፣ ጥፋት፣ ነገሮችን ተነጋግሮ ለማቃለል አለመፈለግ፣ የወንድማማች ፍቅርን የሚያጠፋና ብዙ ነፍሶችን የሚጎዳ አስቸኳይ እርምጃ በመውሰድ የሚደረግ መለየት ናቸው፡፡ የኔ መንገድ ግን ሰላም፣ በሰላም መጓዝ፣ የሰላም ሰው መሆን፣ መለያየትንና ሰውን ያለመቀበልን የሚያጋግል ድርጊት የሌለበት ነው፡፡

"ልጆቼ በትክክል መለየት ባለመቻል ምክንያት በሚመጣው ተስፋ መቁረጥ ነገሩ በትክክል ስላልገባችሁ ራሳችሁን በኃዘን ውስጥ አትጣሉ፡፡ እንዳውም በተቃራኒው ውሸትን በመመርኮዝ ተከታታይ ስህተት እንዳትፈፅሙ እኔ ጣልቃ ገብቼ ስለከለከልኳችሁ ልታመሰግኑኝ ይገባል፡፡

"ስህተትን ለመፈፀም ፈቃደኞች ሁኑ፡፡ ለመኖር ስትሉ በደመ ነፍስ የሰጣችሁትን ምላሽ በማሳታወስ ድንጋጤ ውስጥ መግባት የለባችሁም፡፡ ሰው መሆናችሁንና ስህተት መስራት ደግሞ የሰው ልጅ ተፈጥሮ እንደሆነ ልትገነዘቡ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን ለመለየት ያደረጋችሁት ጥረት ሁሉ ትክክል አይደለም ማለት አይደለም፡፡ ይህ ለእራት ከቀረበላችሁ አተር ውስጥ

አሸዋ እንዳገኛችሁ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ቅዱሱን መንፈሴን "መንፈስ ቅዱስ እርዳኝ" በማለት ተጣሩ፡፡ ትሁት ከሆናችሁ፣ ልባችሁ ትክክለኛ ዝንባሌ ያለው በመሆኑ የጠየቃችሁትን እርዳታ ታገኛላችሁ፡፡

"ነገር ግን የምትኮሩ፣በራሳችሁ የምትተማመኑ ከሆነና ከእናንተ ጋር በሐሳብ የማይስማሙትን ዝቅ አድርጋችሁ የምትመለከቱ ከሆነ እናንተ ሰይጣን ባዘጋጀው አስቀያሚ መጓጓዣ ውስጥ ገብታችሁ እየሄዳችሁ ነው፡፡ ለመሆኑ የሚኮሩ ሰዎችን መላዕክቶች ለመርዳት ፈቃደኛ እንዳልሆኑና ጥግ ይዘው እንደሚቆሙ ታውቃላችሁ? መላዕክቶቼ ለመርዳት ወደኋላ የሚሉት አስቸጋሪውን ሁኔታ እናንተን ለማስተካከል እንዴት እንደምጠቀምበት ስለሚያዩ ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ጊዜ ጣልቃ እንዲገቡ እፈቅድ እንደሆነ እኔን ይመለከታሉ፡፡ እኔም በተመሳሳይ ምክንያት ጣልቃ እንዳይገቡ አደርጋቸዋለሁ፡፡

"ለማጠቃለል በልባችሁ የዋህና ትሁት ከሆናችሁ በመለየት ወቅት ስህተት ልትሰሩ እንደምትችሉ በማወቅ ችግር ሲያጋጥማችሁ አትደናገጡ፡፡ በአንፃሩ በትልቁ ተንፍሱና እኔ ጣልቃ በመግባቴ አመስግናችሁ ከቅዱሱ መንፈሴ ጋር እውነቱን ከስህተቱ ለመለየት አብራችሁ ሥሩ፡፡ በተጨማሪም ለዚህ ስህተት ለምን እንደተዳረጋችሁ መርምሩ፡፡ ፈቃዴ እንደሆነ መለየት ከምትፈልጉት ጉዳይ ጋር ተጣብቃችሁ ነበር? ይህም የኔ ፈቃድ መሆኑን ለማወቅ የፈለጋችሁት ጉዳይ እንዲሆንላችሁ እጅግ የምትፈልጉት ነበር? በራሳችሁ ፍላጎት ተጠምዳችኋል? ይህ ልታፍሩበት የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለምን? ምክንያቱም ይህ በሁሉም የሰዎች ህይወት ውስጥ የሚገኝ የችግር ምንጭ ነው፡፡ ነገር ግን ፍፁም በሆነው መንገድ ላይ ለመጓዝ ከመረጣችሁ አሁን ቢሆን ወይም ቆይቶ የራሳችሁን ፍላጎት ትታችሁ በእኔ ፍላጎት ብቻ መኖር አለባችሁ፡፡

"እወዳችኋለሁ ደግሞም በጠለቀ ሁኔታ እከባከባችኋለሁ፡፡ መለየት አቅቷችሁ ስህተት ስትፈፅሙ እናንተ የምትጎዱትን ያህል እኔም እጎዳለሁ፡፡ ነገር ግን በቅርቡ ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማያት እንድትሆኑ ስህተት የሆነውን መንገዳችሁን ለማረም ታማኝ ነኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ጠላት በእግራችሁ ሥር በዘረጋው ወጥመድ እንዳትጠመዱ ተጠንቀቁ፡፡

"የኔ ውዶች በህይወታችሁ የኔን ፈቃድ ብቻ ለመኖር በምትፈልጉበት መንፈስ አሁን ባረኳችሁ፡፡"

## ሙሽራዬ እንድትሰማኝ እፈልጋለሁ - ጁላይ 14 ቀን 2020 ዓ.ም

## I Want My Bride To Hear Me, July 14, 2020

(ክሌር)፡- የኔ ውድ ኸርትድዌለርስ ከዚህ መልዕክት በፊት የለጠፍኩላችሁ መልዕክት የ2015 ዓ.ም ሲሆን የጌታን ድምፅ ለመስማት እንደገና ትኩረት ሰጥታችሁ ለግላችሁ የሚናገራችሁን እንድታዳምጡት ለማድረግ ነው፡፡ እርሱም እንደተናገረው በዛ ሰብቴምበር ምንም አልተፈጠረም ነበር፡፡ የመልዕክቱ አንኳር ነጥብ የጌታን ለስላሳና እንደ ሹክሹክታ የሚሰማውን ድምፁን ከልባችን ለመስማት እንድንችል ራስን ማሰልጠን አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በተለይ አሁን ብዙ ችግር እየተፈጠረ ያለበት ጊዜ በመሆኑ ከምንጊዜውም በበለጠ ድምፁን መስማት ያስፈልገናል፡፡

እስካሁንም ድረስ ታዲያ ስለ ሰብቴምበር ምንም ብሎኝ አያውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ደግሞ አሁን ለስድስት ወራት የሚበቃ ምግብና የተለያዩ አስፈላጊ ነገሮችን መጠለያ ለሚኖሩት አዘጋጁ ብሎናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር አድርጉ ለማለት ከእርሱ በፍፁም የማይጠበቅ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ትዕዛዝ እንድትቀበሉና ተግባርያዊ እንድታደርጉት እጠይቃችኋለሁ፡፡

እናም ለስድስት ወራት የሚበቃ ምግብና ሌሎች አስፈላጊ ቁሶችን አዘጋጁ፡፡ የተወደዳችሁ ይህንን እመክራችኋለሁ ምግብ ስታስቀምጡ ታዲያ ለሰውነታችሁ የማይጠቅምና ካሎሪ የሌለው የመክሰስ ምግቦችን አትምረጡ፡፡ የፋብሪካ ምግቦች ለምሳሌ በፋብሪካ የተመረቱ ጥራጥሬዎች እጅግ ውድ ናቸው፡፡ ከዚያ ይልቅ ራሳችሁ ፈጭታችሁ የምታዘጋጁት አጃ ጠቃሚነት አለው፡፡ ለቤት አገልግሎት የሚያስፈልጋችሁንም ዕቃዎች አትርሱ፡፡ ለምሳሌ ሃይድሮጂን ፐርኦክሳይድ፣ በረኪና፣ የልብስና የእጅ ሳሙናዎች እንዲሁም አንዳንድ አስፈላጊ መድኃኒቶች አስቀምጡ፡፡ እኛ ከከተማ ወጣ ያለ ሥፍራ ስለምንገኝ ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ ሻማዎችን፣ በሶላር ኃይል የሚሰሩ መብራቶችን እንዲሁም ለኤሌክትሪክ ኃይል በጋዝ የሚሰሩ ጀነሬተሮችን አዘጋጅተናል፡፡

እኔ የማበረታታችሁ ሻማዎቻችሁን አብርታችሁ እንዲህ በማለት የበረከት ቃልን ተናገሩባቸው፡፡ "እኛ መደበቅ የማንችል የአለም ብርሃን ነን፡፡ ጌታ ሆይ እባክህ በጨለማና በማያስተማምን ሁኔታ ላይ ስንሆን ብርሃኖቻችን እንዲያበሩ ባርካቸው፡፡" እባካችሁ መዝሙር 91 በየቀኑ ለእናንተና ለምትወዷቸው ፀልዩ፡፡ እግዚአብሔር ትልቅ እንደሆነ፣ እንደሚጠብቃችሁና የሚያስፈልጋችሁን እንደሚያዘጋጅ እውቁ፡፡ ጌታ ልትናገረን የምትፈልገው ነገር አለ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ. . ." ይህንን መልዕክት ስላዘጋጀሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ ህዝቤ እንዲዘጋጅና ከራሱም አልፎ ለሌሎች የሚያካፍለው በቂ ነገር እንዲኖረው እፈልጋለሁ፡፡ ሁሉም እንደተሰጠው መመሪያ ቢያዘጋጅ እጥረት በተከሰተ ጊዜ ለሁሉም የሚበቃ ይኖራል፡፡ የኔ ውዶች አስቸጋሪ ጊዜያቶች እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ ነገር ግን በፀሎትና በምስጋና ለልቤ ቅርብ እንደሆናችሁ ብትቀጥሉ፣ እንዲሁም የአለምን ነገር ሳይሆን የመንግስቱን ነገር በቅድሚያ ብትፈልጉ የተጠበቃችሁ ትሆናላችሁ፡፡

"በኢንተርኔትና በዜና የሚቀርቡ ብዙዎቹ ትክክለኛ መረጃዎች አይደሉም፡፡ ለዚህ ነው የእኔን ድምፅ ለመስማት መሰልጠን ያለባችሁ፡፡ አብዛኛዎቻችሁ ጫጫታና ማስፈራሪያ የበዛባቸውን ትንቢት ተብዬዎች እንደ ሲ-ኤን ኤን ከመሳሰሉ ዋና ከሚባሉ የሚዲያ አውታሮች እንዲሁም ከዩ-ቲዩብ ምንጮች መስማት ለምዳችኋል፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ እነዚህን ማመን የለባችሁም፡፡ ህይወታችሁን የመሰረታችሁት እዛ በሰማችሁት ላይ ከሆነ እጅግ ስህተት ላይ ናችሁ፡፡ በዚህም ምክንያት ይህቺ አገር (አሜሪካ) በምን ሁኔታ ላይ እየተጓዘች እንደሆነ እውነቱን አታውቁም፡፡ እንዲሁም ተኮለኞቹን ከአሸናፊዎቹ መለየት አትችሉም ማለት ነው፡፡ ይህንን መለየት የምትችሉት በፀሎት ብቻ ነው፡፡

"በናዚ ጀርመን ጊዜ ሂትለር ወደ ስልጣን ሲመጣ አስከፊ አድራጎቱን ህብረተሰቡ ተቀብሎ እንዲደግፈው ለማድረግ የተጠቀመው የመገናኛ ብዙሃንን ነበር፡፡ ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን የሚከፈላቸው ከመንግስት ስለነበር ለህብረተሰቡ ሲቀርብ የነበረው አይሁዶችን ለማጥፋት ሂትለር ያቀደውን አጀንዳ ተግባርያዊ ለማድረግ በሚያመች መልኩ ተቀነባብሮ ነበር፡፡

"አሁንም በዚህ አገር እየተደረገ ያለው በተመሳሳይ መልኩ ነው፡፡ ከናዚ የሚለየው ይህኛው የሚያነጣጥረው በክርስቲያኖች ላይ በመሆኑ ነው፡፡ "በስሜ ምክንያት የተጠላችሁ ትሆናላችሁ" ተብሎ እንደተፃፈ እንደዛው ይሆናል፡፡ በዚህ አገር ውስጥ የእግዚአብሔርን አጀንዳ ለማዛባት ከተሰለፉት ውስጥ ዋነኞች ተብለው ለሚጠሩ የመገናኛ ብዙሃን ተቀጥረው የሚሰሩ ይገኙበታል፡፡ የኔ ውድ ሙሽሮች ወደ ፀሎት በምተቀርቡ ጊዜ አትቸኩሉ፡፡ እኔን እየጠበቃችሁ እያለ ህሊናችሁን መርምሩ፣ እኔን የማያስደስት የሰራችሁት ትንሽ ነገር እንኳን ብታገኙ ንስሐ ግቡ፡፡ ለትልቅ ጥሪ ከተጠራችሁ ዋጋ የምትከፍሉት ነገር አለ፡፡ ሌላውን የማልጠይቀው፣ ነገር ግን እናንተ እንድትከፍሉ የምጠይቃችሁ መስዋዕቶች ሊኖሩ ይችላል፡፡

"ልቤ ሊናገራችሁ፣ ሊያሳውቃችሁ፣ ሊመክራችሁና ሊመራችሁ ይፈልጋል፡፡ ከእኔ ጋር የሚኖራችሁ እውነተኛ ግንኙነት የሚፈጥረው ደስታ ይህ ነው፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ከእናንተ ጋር መቆየትና አምልኮ በሞላበት መገናኘታችሁ ውስጥ መኖር እፈልጋለሁ፡፡ በጣፋጭ ዝማሬያችሁና ለእኔ በምትሰጡት ትኩረት አለም ለእኔ ያለውን ቀዝቃዜ አመለካከቱን ታካክሱልኛላችሁ፡፡ በእውነትና በመንፈስ ወደ እውነተኛው አምልኮ ስትገቡ ይህ ለእኔ ፍፁም ድንቅ ሲሆን በፍቅራችሁና በምስጋናችሁ ራሴን የማረሰርስበት ነው፡፡ ውዶች ይህንን ብዙ ማድረግ አትችሉም ነገር ግን በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ እኖራለሁ፡፡

"የኔን ዝቅ ያለ ድምፅ ለመስማት ችሎታ እንዲኖራቸው ለመሰልጠን የህሊናችሁንና የራሳችሁን ድምፅ ማሳነስ ያስፈልጋችኋል፡፡ ከሚያናውጥና ከሚያነሳሳ ድምፅ መራቅ አለባችሁ፡፡ እኔን ለማምለክ ሰላማዊና ፀጥተኛ አካባቢ እንዲሆን አድርጉ፡፡ መንፈሳዊ ጆሮዎቻችሁ በአለም ድምፆችና በማያስፈልጉ ወሬዎች  ተዘግተዋል፡፡ የልብ፣ የአይምሮና የሰውነት ፀጥታ ለእናንተ በግልፅ እንድናገር ለእኔ መንገዱን ያዘጋጃል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ እናቴ ማላጅ ናት፡፡ ስለዚህም የእርሷን እርዳታን ጠይቁ፡፡ እርሷ በልቧ ያለው ትልቁ ነገር እናንተ ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ነው፡፡ (ይህ የእኛ እምነት አይደለም)

"ለፀጥታ ራሳችሁን አስገዙ፡፡ ከአለም ጩኸት ርቃችሁ ፀጥ ባለ ሥፍራ ስትገኙ በቀስታ የሚነፍሰው ንፋስና የወፎች ዝማሬ እንኳን ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ልብና ነፍስ ፀጥ እንዲል ስትኮተኩቱት ከምንጊዜውም የበለጠ ለሹክሹክታዬ እንኳን ንቁ ትሆናላችሁ፡፡

ብዙዎቻችሁ በግልፅ ድምፄን ሰምታችኋል፡፡ ነገር ግን የራሳችሁ ሐሳብ እየመሰላችሁ ትታችሁታል፡፡ ይህ ትክክል ነው፡፡ በእርግጥም የኔ ቃል እንደ ራሳችሁ ሐሳብ ሆኖ ሊመጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ትንሽ የባህርይ ልዩነት አለው፡፡ በአብዛኛው ጊዜ እኔ ስናገራችሁ የራሳችሁ ሐሳብ እየመሰላችሁ ትሽፋፍኑታላችሁ፡፡

"የእኔ ድምፅ መሆኑን የምትለዩበት አንዱ መንገድ እኔ የምናገረው በጣም በጣም ለስለስ ባለ ድምፅ መሆኑ ነው፡፡ እኔ የእናንተን ነፃ ፈቃድ ስለማከብር ስናገር በጣም በለስለስ ድምፅ እንጂ ኃይለኛ በሆነ ድምፅ አልናገርም፡፡ በተጨማሪም ብዙ ጊዜ እናንተ ያላሰባችሁትን ርዕስ ወይም ዘይቤያዊ አነጋገር ልናገር እችላለሁ፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የእናንተ ሐሳብ እንዳልሆነ የምትለዩበት አንዱ መንገድ ይሆናል፡፡"

(ክሌር) ፡- ይህ ነገር እኔንም ብዙ ጊዜ ገጥሞኛል፡፡ እኔ ከማስበውና ካለሁበት ሁኔታ ውጪ በሆነ መልኩ አዲስ ሐሳብ ይመጣብኛል፡፡ በዚያን ጊዜ ታዲያ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . ሰዎችን እንደማላንኳስስና ዝቅ እንደማላደርግ ትማራላችሁ፡፡ የሰዎች ችግር ምን እንደሆነ ልነግራችሁ እችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህንን በማደርግ ጊዜ በሚያስጠላ ሁኔታ አይደለም፡፡ እንዲሁም ይህንን የማደርገው የቆሰሉና አቅጣጫን የሳቱ ነፍሶች እንደሆኑ በማስገንዘብ፣ እንድትፀልዩላቸው ለማነሳሳት ሲሆን የኔም ፍላጎት እንዲፈወሱ ነው፡፡ ለመፈወስ ደግሞ ጊዜ ስለሚፈጅ ለእነርሱ በምታደርጉት ደግነትና ትዕግስት ፈውሳቸው ይፋጠናል፡፡

"ዱዌሊንግ ፕሬየር /በጌታ ልብ ውስጥ የሚኖሩ ፀሎት/ ያስተማርኳችሁ ከእኔ ጋር በፀሎት እንድትቆዩ ለማድረግ ነው፡፡ ቸልተኝነት የሌለበትና ኃላፊነታችሁን እንዳትወጡ የሚያደርግ እስካልሆነ ድረስ ያለአስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ሁሉ ትታችሁ፣ ከእኔ ጋር ጊዜ እንድታጠፉ ለማድረግ ነው፡፡ አለምን ሁሉ ወደ ጎን ትታችሁ ከእኔ ጋር ጊዜ ስታሳልፉ እጅግ ደስተኛ ነኝ፡፡

"ለእኔ አምልኮ ሰጥታችሁ እኔ በተገኘሁበት ወደ ዕረፍቴ ስትገቡ ከዙሪያችሁ ያለው አቧራ ሁሉ ፀጥ ይላል፡፡ ይህም የአለም አቧራ ሐሳብ፣ የራሳችሁ ሐሳብ እንዲሁም የአጋንንት ሐሳብ ሁሉ ፀጥ ይላል፡፡ በአምልኮ ጊዜ የራሳችሁን ድምፅ እንኳን ፀጥ ስታደርጉ አየሩ እየነፃ ይሄዳል፡፡ ስለዚህም ድምፄንና ልቤን ለመስማት የሚመች ይሆናል፡፡ የኔ ውዶች ብዙ የምነግራችሁ ነገር አለኝ፡፡ ወደ እኔ ኑ፣ አምልኩኝ፣ ከዚያም ጥልቅ በሆነ ክብር ዕረፉ፡፡ ይህም ዕረፍት ፀጥ ያለ ልብና አዕምሮ እንዲኖራችሁ በማድረግ ለእናንተ ያለኝን ቃል ለመስማት ዝግጁ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል፡፡

"አንዳንድ ጊዜ በፀጥታ ውስጥ ሆናችሁ ምንም የሚመጣ ነገር የሌለ ሲመስላችሁ በዴቮሊንግ ፀሎት ጊዜ የሰማችኋቸውን ሙዚቃዎች አድምጡ ወይም አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ዝም ብላችሁ በማውጣት አንብቡና አሰላስሉት፡፡ እኔ ቅዱሳን መፅሐፍትን ስታነቡ ያለማቋረጥ እናገራለሁ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን መስመር በጥንቃቄ ለማንበብ መማር አለባችሁ፡፡ ስታነቡም ማወቅ ያለባችሁ የቃላቱን ትርጉም ብቻ ሳይሆን በክፍሉ ዋና ሐሳብ ላይ ምን እንዳለና ስሜቱ ምን እንደሆነ መረዳት አለባችሁ፡፡ በአብዛኛውን ጊዜ እኔ ስለ ተናገርኳችሁ አንድ ነገር ረጋ ባለ ፍንጭ ታገኛላችሁ፡፡ ደግሞ አንድን ነገር አስታውሱ እኔ በሰጠኋችሁ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል ወይም በቀደመው ዘመን እንደሚነገረው በማንኛውም መልኩ በተገለጠ ቃል (oracle) ስትቀርቡኝ፣ ርዕሱን በመቀየር ጭራሽ የማይገኛኝ፣ ነገር ግን እናንተ ማየት ያለባችሁና ለእኔ እጅግ አስፈላጊ የሆነን ነገር ላነሳ እችላለሁ፡፡

"የኔ ውድ ቤተሰቦች እጅግ አድርጌ እወዳችኋለሁ፡፡ እናም አንዳችን ከአንዳችን በቀላሉ እንደምንግባባ፣ በቅድስና እንደምታድጉ፣ ሐዘናችሁንና ደስታችሁን የበለጠ እንደምጋራ ትልቅ ተስፋ አለኝ፡፡ ተደገፉኝ፣ በእኔ ላይ ተጣበቁ፣ ፈልጉኝ፣ ጠብቁኝ፣ ተስፋ አላስቆርጣችሁም፡፡ አሁን ለስላሳውን የእኔን ድምፅ ከልባችሁ ውስጥ ለመስማት የምትችሉበት የነቃ ጆሮና እኔን ለመጠበቅ ትዕግስት እንዲኖራችሁ በሚያደርግ ፀጋ ባረኳችሁ፡፡"

## ምህረት የማያደርግ አገልጋይ - ጁላይ 23 ቀን 2020 ዓ.ም

## The unforgiving servant - July 23rd

የኔ ውድ ቤተሰቦች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለማደርገው ስህተትና ጉድለት የበለጠ መስማት አለባቸው እያልኩ ጌታን ስጠይቀው ነበር፡፡ እርሱም ህብረተሰቡን ሊያጠፉ የሚችሉትን ዋና የተባሉ ጉድለቶችን ለማጋለጥ ብዙም አልቆየም፡፡

ከእኛ ጋር አብረው ከሚኖሩት ውስጥ የህይወት ልምድ ያላቸውና የሌላቸው ሰዎች ይገኛሉ፡፡ አንድ ወጣት አለ፡፡ ይህ ወጣት የተለየና ራሱን ለጌታ የሰጠ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ሁሉን ነገሩን ትቶ ወደዚህ ለመምጣት የፈጀበት አንድ ሌሊት ብቻ ነበር፡፡ ብዙ ደብዳቤዎችን ፅፎልኝ ከእኔ መልስ ሲጠብቅ አመት ያህል የቆየ ይመስለኛል፡፡ እናም አንድ ቀን ኢሜል ሳደርግለት ወዲያው ምላሽ በመስጠት በስልክ ካወራን በኋላ ያለውን ሁሉ ትቶ በአውቶብስ በመሳፈር በሚቀጥለው ቀን እዚህ የመጣ ልጅ ነው፡፡ ከፊታችን ሊያጋጥመን የሚችለውን ችግር ግን ማናችንም አናውቅም ነበር፡፡ ከእኛ መካከል እንደ እርሱ በእድሜ ትንሽ የሆነ የለም፡፡ ምናልባት ይህም ብቸኝነት እንዲሰማው አድርጎት ሊሆን ይችላል፡፡ በልጅነቱ ደግሞ ብዙ የጉዳት ዘመኖችን ያሳለፈ ልጅ ነው፡፡ በህፃንነቱን ያደገው በሱስ በተጠመዱ ቤተሰብ ውስጥ በመሆኑ ብዙ የሁከትና የድብደባ ህይወት ያሳለፈ ልጅ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለብዙ ቀናት ምግብ ሳይበላ የሚያሳልፍባቸው ቀናት ነበሩ፡፡ ነገር ግን እንደራበው

ቢናገር እንኳን ስለሚመታ ለእናቱ ለመንገር አይደፍርም ነበር፡፡ ይህንን ሲነግረኝ ለአንዳንድ ነገሮች ለምን የሚያመነታ እንደሚመስል ገባኝ፡፡

ከዚም በኋላ ከአያቱ ጋር ለመኖር ሲሄድ ደግሞ አንድ ነገር እንዲሰራና በጣቱ እንኳን አንድ ነገር እንዲነካ አትፈቅድለትም ነበር፡፡ በፊት በጭራሽ ሰርቶ ባያውቅም እንኳን እኔን እዚህ የቤት ሥራ ያግዘኛል፡፡ ታዲያ ምንም ልምድ ስለሌለው ነገሮችን ገና ከመጀመሪያው መጀመር ነበረብን፡፡ እኔ ደግሞ ነገሮች ፍፁም በሆነ አይነት መልኩ እንዲሰራ የምፈልግ አይነት ሰው ነኝ፡፡ ስለዚህም ይህ እንዲሆን ሁልጊዜ እታገላለሁ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ምንም ቢለፋ እንኳን አንድ የምለው ነገር አይጠፋም፡፡ በዚህ ማፈር አለብኝ፡፡ ነገር ግን ደግሞ ለእርሱ ትልቅ ፍቅር ስላለኝ የኔን ስህተት እያካፈልኩት ብዙ ጊዜ አበረታታኋለሁ፡፡ ከዚህ ሁሉ በበለጠ ደግሞ ከወላጅ እናቱ ያጣውን ፍቅር ገደብ በሌለው መልኩ ከእኔ ያስፈልገዋል፡፡

ጊዜ እያለፈ በሄደ ቁጥር ታዲያ በእርሱ ላይ የበለጠ ትዕግስት እያጣሁ መጣሁ፡፡ ጭራቅ እየሆንኩ ስሄድ  እራሴን አየዋለሁ፡፡ በመጨረሻውም ጌታ ባለቤቴን ህዝቅኤልን አስረዳው፡፡ ባለቤቴም እያደረግሁት ያለሁት ነገር ጌታን እንዳላስደሰተው፣ ችግሩም ልጁ ቀሰስተኛ ሆኖ ሳይሆን እኔ ትዕግስት በማጣቴና ፍርድ የመስጠት ዝንባሌ እንዳደረብኝ በግልፅ ነገረኝ፡፡ በዛው ቀን አንድ ላይ ተሰብስበን የምናነበውን ስከፍት ምህረት  የማያደርገው አገልጋይ የሚለው ወጣልኝ፡፡ ማቴዎስ 18 ከቁጥር 21 ጀምሮ እንዲህ ይነበባል፡፡

*"21 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። 22 ኢየሱስ እንዲህ አለው፡- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።23 ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቆጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። 24  መቆጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 25  የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ። 26 ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና። ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው። 27 የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት።*

*28 ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባሮች ባልንጀሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ 28 ብሎ ያዘና አነቀው። 29 ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ። ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። 30 እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። 31 ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ። 32 ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ። አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ 33 እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። 34 ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቀዩት አሳልፎ ሰጠው። 35 ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።"*

ጌታ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . በህብረት አብሮ የመኖር ህይወት የሚመለከተው ምን ውጤት እንደተገኘ ሳይሆን እኔን ለመምሰል የምትለወጡበት ጉዞ ነው፡፡ በዚህም ጉዞ እኔ ለአንቺ በህይወቴ የገለጥኩትን ፍቅር፣ ይቅርታ ማድረግንና ከሌሎች ጋር በትዕግስት መኖርን የምትለማመጅበት ህይወት ነው፡፡ በፍቅር ካልሆነ በስተቀር ሰዎችን መረዳትና መምራት አትችይም፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ራስሽን በዛ ሰው ጫማ ውስጥ በማስገባት ሁኔታቸው በጥልቅ እየገባሽ የምትጓዢ መሆን አለበት፡፡

ከሌሎች ጋር ያለሽ ትዕግስት እኔ ከአንቺ ጋር እንዳለኝ ትዕግስት ጥልቅና የማያልቅ አይነት መሆን አለበት፡፡ በጉ መሆን ያለበት እንደ እረኛው ነው፡፡ ከባድ የትዕግስት ማጣት ስህተት በመፈፀምሽ ምክንያት ሌሎችም በወንድሞቻቸውና በእህቶቻቸው ላይ እንዴት መሆን እንዳለባቸው እያሳየሻቸው ነው፡፡ ይህ ድርጊት የትችት መንፈስ ወደ ህብረተሰቡ ለመግባት ዋና በር ከፋች ሆኖ ነበር፡፡ በክሌር ውስጥ ምንም የፍርድ ጣት እንዲገባ መፍቀድ የለብሽም ነበር፡፡

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ ሐሳብ ልሰጥ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ ነገር በእኔ ውስጥ አያደገ የመጣና ጠንካራም ነበር፡፡ ለዚህ ሰው የሚሰማኝ በጣም ጠንካራ፣ ቋሚና ጥልቅ የሆነ ስሜታዊ ምላሽ ነበር፡፡ ደግሞም የሚያስጠላ ነበር፡፡ በእውነት ለመናገር በጣም አስቀያሚና ጠንካራ ነበር፡፡ ለምንድነው እንደዚህ ጠንካራ የሆነ ስሜት የሚሰማኝ በማለት ጥያቄ ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ እናም እንደዚህ ጠንካራ የሆነበት  ምክንያት የኢጋንንት ስለሆነ ነው፡፡ ይህም እንቅስቃሴ የተጀመረው ህብረተሰባችን ለመከፋፈል ነበር፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " የተወደድሽ ሆይ ይህ አንቺን ለመገሰፅ ሳይሆን ይህ ልብሽን እንደ እናቴ ያህል እንኳን አፍቃሪና ንፁህ እንድታደርጊው ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎችን እንደምታስተምሪው አንቺም እንደዛው ማድረግ ስላለብሽ ነው፡፡ ሰይጣን ድካምሽንና የፀባይሽን ጉድለት በማግኘት በሙሉ ኃይል ከሥጋሽ ጋር ጦርነት ላይ እንድትሆኚና ይህም ቆሻሻ በውስጥሽ ከሞላ በኋላ ወደ ሌሎች እንዲፈስ በማድረግ ነው የሚሰራው፡፡ ትዕግስት ማጣት የሚመጣው አንድ ነገር በትክክልና ቶሎ እንዲደረግ ከመፈለግ ከግል ፍላጎት ወይም ጥቅም አንፃር ነው፡፡ ነገር ግን በህብረተሰብ ህይወት ውስጥ የትኩረት አቅጣጫ ነገሮች መከናወናቸው ላይ ሳይሆን የወንድማማች ፍቅር ላይ ነው፡፡ ክሌር ከአንቺም ጋር የማደርገው ይህንኑ ስለሆነ ለሌሎችም ማድረግ ያለብሽ እንደዚህ ነው፡፡

መነሻው ምን እንደሆነ ተመልከቺ፡፡ በሥራ ላይ ያለውንም ኃይል ተረጂ፡፡ ምላሹ አዝጋሚ የሆነውንና ትጋት የጎደለውን ክፍተቱን ለመሙላት ሥሪ፡፡ ደግሞም ወደ ችግሩ ምንጭ ሂጂ፡፡ ይህንን እንደምታደርጊ ደግሞ አውቃለሁ፡፡ በተለይም ነገሮችን እንዲለወጡ ለማድረግ ለችግሮቹ መፍትሄ አቅርቢ፡፡ ነገሩ ሊያመጣ የሚችለውን ሁሉ ዙሪያውን መዝኚ፡፡ በእኔ አተያየት አንፃር አንቺ መሆን ያለብሽን ያህል አለመሆንሽን ባውቅም ወደ ነበርሽበት እንድትመለሺ አላደረኩም ወይም አልተውኩሽም፡፡ አሁንም ከአንቺ ጋር እየሰራሁ ነው፡፡ የኔ ልጆች የራሳችሁን ኃጢያትና ስህተት ማወቅ  እንዴት አስፈላጊ መሰላችሁ፡፡ ከዚህ እውቀት ውጪ ትዕቢተኞችና የራሳችሁን ፅድቅ የምትቆጥሩ ትሆናላችሁ፡፡ እንደዚህ ከሆናችሁ ደግሞ እኔ ለጠራኋችሁ ጥሪ ብቁ አትሆኑም፡፡

"እስቲ በምግብ ጉዳይ ላይ ራስሽን መካድ ያቃተሽን ተመልከቺ፡፡ ለስንት ጊዜ ነው እንድትለወጪ የጠበኩሽ? አንቺስ ያንን ለማሻሻል ምን ያህል ሙከራ አደረግሽ? የኔ ምላሽ ደግሞ ያደረግሽው ሙከራ በቂ አልነበረም ነው፡፡ ይህንን የምለው ልከስሽ አይደለም፡፡ ይህንን የምናገረው በሰዎች ላይ ጉድለት ስታገኚ ወደ ትክክለኛው አመለካከት እንድትመጪ ነው፡፡ እኔ በምግብ በኩል ለአንቺ ትዕግስት እንዳደረኩት አንቺም ለሌሎች ትዕግስት እንድታደርጊ ነው፡፡

"ይህ ስለራስሽ ማን እንደሆንሽ ወይም እንዳልሆንሽ አብዮታዊ አመለካከት ይሰጥሻል፡፡ በመሬት ጉድጓድ ውስጥ ተደብቃ የነበረችውን ቆሻሻ፣ የምትሸተውንና ፍፁም ጠፍታ የነበረችውን የአራት አመቷን ልጅ አስታውሺ፡፡ ስለአንቺ ሁኔታ የሚያሳየውን የሰጠሁሽን ራዕይ ታስታውሻለሽ?

(ክሌር)፡- አዎ ያንን ራዕይ ጌታ የሰጠኝ ማን ነበር ስሙ . . . ያ በመሬት ውስጥ ተደብቆ በመጨረሻ የተገኘው የኢራቅ ጄነራል? . . . ሳዳም ሁሴን ከተገኘ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ነው ጌታ የኔን ሁኔታ በተመሳሳይ መልኩ ነገር ግን በፍፁም ምንም የማታውቅና ቆሻሻ የአራት አመት ልጅ አድርጎ ራሴን በራዕይ ያሳየኝ፡፡

"የአንቺን ሁኔታ የሚያሳየውን የሰጠሁሽን ይህንን ራዕይ አስታውሺ፡፡ ይህም ሁኔታ ትዕግስት ማጣትሽንና ከአንቺ የተለየውን አሳሳቢ የሚሆንብሽን የሚያሳይ ነው፡፡ ክሌር ይህንን አጋንንት ከህይወትሽ አስወግጂ፡፡ አንቺ ይህንን ካደረግሽ ጠላት በህብረተሰባችሁ ውስጥ መግቢያ ቀዳዳ አያገኝም፡፡ በጎች የሚጓዙት እንደ እረኛቸው ነው፡፡ የተወደድሽ ይህንን ሁልጊዜ አስታውሺ፡፡

(ክሌር)፡- ጌታ በጣም በጣም አዝናለሁ፡፡ በአንተ እርዳታ ይህንን አስቀያሚነትን አሸንፋለሁ፡፡ የኔ ፍቅር ይቅርታ አድርጌልሻለሁ፡፡ ይህንን ስህተት እንድታሸንፊ የሚያስፈልግሽን ፀጋ አሁን አካፍልሻለሁ፡፡ በተጨማሪም በማንም ላይ አንድ ዘለላ ፍርድ እንኳን በልብሽ ውስጥ ባገኝ፣ በጠላቶችሽ ላይ እንኳን ቢሆን ፣ደግሞም ብዙ ጠላቶች አሉሽ፣ መፆም የምትችይበትን ፀጋ በመስጠት እረዳሻለሁ፡፡

(ክሌር)፡- ጌታ አመሰግንሃለሁ ደግሞም አፈቅርሃለሁ፡፡

እኔም ከምትገምችው በላይ እወድሻለሁ፡፡ ይህንንም አብረን እናሸንፈዋለን፡፡

## ለድካማችሁ የኔ ስጦታ - ጁላይ 31 ቀን 2020 ዓ.ም.

## Communion-My Fullness for Your Weakness, July 31, 2020

(ክሌር)፡- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል እንደሚከባከባችሁ፣ ድምፁን እንድትሰሙ እንደሚጓጓ በምታውቁበት ጥበብና ፍቅር ይባርካችሁ፣ አሜን፡፡

የተወደዳችሁ እኔ ራሴን ያገኘሁት በአሰቃቂ የመነሳሳት ማጣትና በግልፅ ማሰብ ባለመቻል ውስጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጌታ ከዚህ ሁኔታ እንዲፈውሰኝ ሳለቅስ ነበር፡፡ ዛሬ ሥጋና ደሙን ከተቀበልኩ በኋላ ድምፁን ሰማሁ፡፡ አያችሁ በዚህ ወቅት ነው እርሱ ከሁሉም ጊዜ ይበልጥ በግልፅ የሚናገረኝ፡፡ በዚህም ምክንያት እርሱን እየጠበኩ እያለሁ ብዙ ጊዜዬን ያሳለፍኩት የሥጋና የደሙን ስጦታ በማመስገን ነበር፡፡

እርሱም ከሌላ ክፍል ሆኖ በጣም በቀስታ ወይም በሹክሹክታ በሚመስል መልኩ መናገር ጀመረ፡፡ ነገር ግን ይህንን የሹክሹክታ ንግግር የሚመስል ድምፅ ስለማውቀው የሚለኝን መፃፍ ጀመርኩ፡፡ ልብ በሉ እኔ በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነበርኩ፡፡ ነገር ግን ሥጋና ደሙን ስወስድ በዛው ጊዜ ውስጥ የእርሱን ፀጋና ጥንካሬ የመውሰድ ሐሳብም መጣብኝ፡፡

እርሱም እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ . . . " ትላንት ትቼው ከሄድኩበት እቀጥላለሁ፡፡ የምትፈልጊው ሁሉ በዚህ ውስጥ ይገኛል፡፡ ሲታይ ዳቦ ብቻ ይመስላል፡፡ እውነቱ ግን የተቀደሰው ሰውነቴ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የእኛን ህልም ልትፈፅሚ የሚያስፈልግሽን ሁሉ በእኔነቴ በሙላት እገኛለሁ፡፡ ክሌር የሚያስፈልግሽ ሁሉ የሚገኘው እዚህ በእኔ ውስጥ ነው፡፡ *ሥጋና* ደሙን ስትቀበዪ የሚያስፈልጉሽ ጥራቶች ሁሉ በእምነት ከእኔ ውስጥ ትጋርያለሽ፡፡ በዚህ መልክ የቀረበው ይህ የኔ *ሥጋ* መሆኑ፣ ይህ ደግሞ የኔ ደም፣ ነፍስና መለኮት መሆኑ እውነት ነው፡፡ ይህ በእውነት እኔ ስለሆንኩ *ሥጋና* ደሙን ስትወስጂ የኔን የመለኮት ባህርይ እንደሚያስፈልግሽ በነፃ ትካፈያለሽ፡፡

"*ሥጋና* ደሜን ስትወስጂ እኔ በዛ ውስጥ እንዳለሁ የምትቀበይው በእምነት እንደሆነ ሁሉ ለአንቺ የሚያስፈልገውን ማንነቴን በዚህ *ሥጋና* ደም ውስጥ የምትቀበይው በእምነት ነው፡፡ ይህ ሚስጥር እንዴት ታላቅ ነው!!! ይህንን ተግባርያዊ እንድታደርጊው የምፈልገው ለመልዕክቶቹ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነገር ነው፡፡ ይኸውም ለሙዚቃ፣ ነፍሶችን ለመረዳት፣ እንዲሁም ሁኔታዎችን በደንብ የምትረዳ ነፍስ እንድትሆኚ ነው፡፡ በእናት ሆድ ውስጥ በችሎታ፣ በተለያዩ ቀለማትና ህብር ተገጣጥሞ የተሰፋውን ልብስ በደንብ መረዳት እንድትችዪ ነው፡፡ የስፌቱ ጌታ ደግሞ እኔ ነኝ፡፡ የሙዚቃውም ጌታ እኔ ነኝ፡፡ ክሌር ለሚያስፈልግሽ ነገር ሁሉ ጌታው እኔ ነኝ፡፡ የሚያስፈልግሽ ነገር ቢኖር ማመን ብቻ ነው፡፡ ታምኛለሽ?"

(ክሌር)፡- አዎን ጌታዬ በእርግጠኝነት አምናለሁ!!

"እንዲህ ከሆነ ጥሩ፣ ከአሁን ወዲያ ብቻሽን አይደለሽም ማለት ነው፡፡ ስታስቢም፣ ስትዘምሪም፣ ሙዚቃ ስትጫወቺም፣ ስትፀልይም ሆነ ማንኛውንም ነገር ስታደርጊ ብቻሽን አይደለሽም ማለት ነው፡፡ እኔን በ*ሥጋ* ወደሙ ጊዜ በመጥራት፣ ወደ እኔ ሙሉነት በመጠጋት እኔ እንደምሰራው ትሰሪያለሽ ማለት ነው፡፡ ይህ እንዴት ድንቅ ነው!!!

"ይህንን አንቺም ሆንሽ ህዝቤ ተግባርያዊ ማድረግ እንድትጀምሩ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም *ሥጋና* ደሙ የኔ መሆኑን አውጃችሁ ስትወስዱ ምን እየተቀበላችሁ እንደሆነ ለረዥም ዘመናት መረዳት አልቻላችሁም ነበር፡፡ ውጤቱ ምን እንደሆነ መረዳት በማትችሉበት ሁኔታ ላይ ነበራችሁ፡፡ አሁን ግን ይህንን እያቀረብኩት እገኛለሁ፡፡ *ሥጋና* ደሜን ስትወስዱ ለሁለንተናዊ የህይወት ተግባራችሁ የጎደላችሁን ከእኔ እንደምትካፈሉ በሙሉ እምነት ከተቀበላችሁ በየቀኑ አበራላችኋለሁ፡፡

"ሰይጣን *ሥጋ* ወደሙ እውነተኛ የኔ መሆኑን አውጃችሁ ስትወስዱ ምን ማለት እንደሆነ ሰዎች እንዳይረዱ ደብቆት ነበር፡፡ እርሱ ሰራተኞቹን ልኮ ይህንን ሲሰርቅ ምን እያደረገ፣ ወደፊት ምን ሊያደርግ እንደሆነና በእኔም ላይ ምን እየሰራ እንደሆነ በትክክል ያውቅ ነበር፡፡ ይህንንም ስለሚያውቅ ሰዎች እውቀቱ እንዳይኖራቸው ብልሃት በተሞላበት ውሸት ፈፀመው፡፡ በዚህም እጅግ ውድ የሆነውን ቅዱስ ቁርባን ሰዎች እንዲያጡ አደረገ፡፡ አሁን ግን ይህንን ወደ ህዝቤ የምመልስበት ጊዜ ነው፡፡ አሁን እያያችሁ ያላችሁት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ወደ ቀደመችው ወደ መጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ስርዓት ለመመለስ እንቅስቃሴ በመጀመር በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ቅዱስ ሹመትን እየጠየቁ ነው፡፡

"ለምን? ምክንያቱም መንፈሴ "ከዚህ የሚበልጥ ነገር አለ" እያለ በተደጋጋሚ ልባቸውን እያነሳሳ ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በውስጣቸው ጥያቄ ስለፈጠረባቸው ያንን ለማግኘት ፍለጋ ላይ ናቸው፡፡ እናም ያንን የሚፈልጉትን በኦርቶዶክስና

በላቲን ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ እያገኙት ነው፡፡ ምንም እንኳን በዛም ብልሽቱ የተስፋፋ ቢሆንም ከንፁሁ ጅረት ጋር በመገናኘት ከሐዋርያት ጀምሮ የነበሩትን የተቀደሱ ልምምዶች ሚስጥራት እየተማሩ ይገኛሉ፡፡

"ለአለፉት ሁለት ሺህ አመታት ቤተ ክርስቲያኔ ብዙ ነገሯን ተነጥቃለች፡፡ ይህም ቢሆን ግን እምነታቸውን በጥልቀት መመርመር እንዳለባቸው የሚሰማቸው ሰዎች ምን ተወስዶ እንደነበረ በማግኘት የተወሰደውን እንደገና ለመመለስ ችለዋል፡፡ በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት እንኳን ብዙዎች ይህንን እየፈለጉ ይገኛሉ፡፡ አንቺንና ህዝቄልን የጠራኋችሁ በ33 ዓ.ም ወደ መሰረትኳት እውነተኛ እምነት ድልድይ እንድትሆኑ ነው፡፡ እናንተን የጠራኋችሁ በቤተ ክርስቲያኔ ዙሪያ የተከማቸውን ተረትና ውሸት አንስታችሁ በጥልቅ በመቆፈርና  የእውነትን ወርቅ በመፈለግ ቅሬታውን ወደፊት እንድታመጡ ነው፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያኔ በብዙ ውሸቶች ስለተከበበች ይህ ቀላል ሥራ አይሆንም፡፡ ከሁሉ በበለጠ ደግሞ ክፉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኔን ስለተቆጣጠሯት እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን በድብቅ ውስጥ ለውስጥ እንድትሰራ አስገድደዋታል፡፡

"እኔ የሰጠሁሽ ትምህርቶች ማለትም እንደ ደመና በዙሪያችሁ ስላሉ ምስክሮች እውነተኛ ጥቅም፣ የቁርባን ስርዓት፣ ንስሐ የመግባት ኃይል፣ ከሁሉ በበለጠው ደግሞ እኔ በእናንተ ውስጥ በመኖሬና ሥጋና ደሜን በመካፈላችሁ ስለሚገለጠው ኃይል ግልፅ ለማድረግ ነው፡፡

"ወደ ሙዚቃው ለመመለስ እንዴት እየታገልሽ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ በሥጋና ወደሙ እንዳጠነክርሽ እየጠበክሽኝ ስለሆነ ታብቢያለሽ፡፡ ክሌር ታምኚኛለሽ?"

(ክሌር)፡- ጌታ አንተን አምንሃለሁ፣ የማላምነው እራሴን ነው፡፡

"ወደ አንቺ የተላከውን ተቃውሞ ሁሉ መመለስ እንደምችል ታምኚኛለሽ?"

(ክሌር)፡- ጌታ በእርግጥ  አምናለሁ፡፡

"ጥሩ እንዲህ ከሆነ እንግዲህ ወደ ሥራ እንግባና ከነበርሽበት ጭቃ ወጥተሽ አንድ ላይ ሆነን በደስታ ወደምንፈጥርበት እንመለስ፡፡ ይህንንም የምትጨርሽው በግልሽ ሳይሆን እኔ እንደማደርገው በመቁጠር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከበድ ባለ ሁኔታ ነው የምናገረው፡፡ እንዴት እንደሚሰማሽ አውቃለሁ፣ በሰውነትሽ ምን እንደሚሰማሽ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እንዲህ እልሻለሁ "በምንም መልኩ ቢሆን በእምነት ዝም ብለሽ ስሪው፡፡ በውስጥሽ የምኖረው እኔ በፊትሽ የቆመውን ይህንን ተራራ አሸንፈዋለሁ፡፡" ምን እንደነገርኩሽ አስታውሺ፡፡ የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል እንኳን እምነት ቢኖርሽ ይህንን ተራራ ከዚህ "ተነቅል" ብትዪው ለአንቺ በመታዘዝ ይነቀላል፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ በሥጋ ወደሙ የአንተን እምነት ተቀብያለሁ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ተራራ  "በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ተነቀል" እለዋለሁ፡፡

"የኔ ፍቅር አሁን ወደ ተግባር ግቢ፡፡ ለኽርት ድዌለርስ ለሁሉም እንደ ተራራ በፊታችሁ ተገትሮ የሚቃወማችሁ የሚመስላችሁ ካለ ለእናንተ ደግሞ እንዲህ እላለሁ፡፡ *ሥጋና* ደሜን ተቀበሉና የኔን ኃይል በመቁጠር ተራራውን ከፊታችሁ አስወግዱት፡፡"

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ በቤተክርስቲያን ለማገልገል ሹመት ያልተሰጣችሁ ከሆነና *ሥጋ* ወደሙን በራሳችሁ መውሰድ ከፈለጋችሁ፣ በተቻለ መጠን የጌታ መገኘት እንዲሆን ጌታ የሰጠን ቀላል የሆነ የ*ሥጋ* ወደሙ አወሳሰድ ስላለ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ (ይህ በአማረኛ ተተርጉሞ ይገኛል)፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ትምህርቶቻችንን (በኢንጊሊዘኛ) Nebula.com ብላችሁ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ መረዳት ያለብን ነገር ዳቦው ወደ ክርስቶስ *ሥጋ* እንዲሁም ወይኑ ወደ ደሙ የሚቀየረው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡ ይህ *ሥ*ልጣን በመጀመሪያ የተሰጠው ለመጀመሪያዎቹ የጌታ ሐዋርያት ነበር፡፡ ከዚያም ሐዋርያት ለሌሎቹ ሹመቱንና ስርዓቱን በማስተላለፍ በተዋረድ ለአሁኗ ቤተ ክርስቲያን እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

(ክሌር)፡- ቢሆንም ግን በደንቡ መሰረት በቤተ ክርስቲያን ያልተሾሙ ቄሶች ወይም አገልጋዮች በማይገኙ ጊዜ ጌታ ለዚህ ለመጨረሻው ዘመን የሚሆን አማራጭ ሰጥቶናል፡፡ በደንቡ መሰረት በቤተ ክርስቲያን የተሾሙ ስንል ከሐዋርያት በተዋረድ የቀጠለውን ሹመት ለመግለፅ ሲሆን ሹመቱንም የተቀበሉት አገልጋዮች የሚሰጡት ዳቦና ወይን በእውነት የክርስቶስ *ሥጋና* ደም እንደሚሆን የሚያምኑና የሚያውጁ ናቸው፡፡ ከዚህ ጀርባ ያለው እውነት ግን መንፈስ ቅዱስ ቅን ለሆነ አማኝ እርሱ የመረጠውን ሊሰራ እንደሚችል ነው፡፡ ከጥርጣሬ ባለፈ ግን በእርግጥ የክርስቶስን *ሥጋና* ደም እንደምትወስዱ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ቁርባን እየሰጠ ወዳለ አንድ ቄስ ቀርባችሁ ሰዉ የሚያደርገውን አድርጉ፡፡ በዚህም የክርስቶስንም *ሥጋና* ደም እንደተቀበላችሁ እወቁና እንደ እምነታችሁ ትቀበላላችሁ፡፡ ከዚያም በኋላ ልባችሁን ዝም ብላችሁ አትዝጉ፡፡ ይህ ጌታን ያለማክበር ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ጌታን በልባችሁ እያሰባችሁ ከእርሱ ጋር ጊዜያችሁን አሳልፉ፡፡

በተጨማሪ *ሥጋ* ወደሙን ለመውሰድ ሐጢያታችሁን ስትናዘዙ ያንንን ኃጢያት ሁለተኛ ላለመድገም ታሳቢ ባደረገ እውነተኛ የውስጥ ፍላጎት ይሁን፡፡ እርሱ መምጣት የሚፈልገው ንፁህ በሆነ ዕቃ ውስጥ እንጂ በኃጢያት በተሞላ ዕቃ ውስጥ አይደለም፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ህዝቤ እንድታውቁት የምፈልገው እጅግ እንደምወዳችሁ ነው፡፡ በእኔ መገኘት ውስጥ እንድትኖሩ እጓጓለሁ፡፡ ከኃጢያት ነፃ ሆናችሁ እንድትኖሩ የሚያስፈልጋችሁን ብርታት ልሰጣችሁ እጓጓለሁ፡፡ የኔ ውዶች ህይወታችሁን መጋራት እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህም *ሥጋና* ደሜን በፀና የልብ እምነት ተቀበሉ፡፡ ከዚያም ግልፅ በሆነና እጅግ ዝቅ ባለ ድምፅ ልናገራችሁ ስለምችል ከእኔ ጋር የቆታ ጊዜ ይኑራችሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ሌላ እዚህጋ የምጨምረው ነገር ኃጢያታችሁን በእርግጥ ከተናዘዛችሁና ለመስተካከለም ቁራጥ የሆነ ውሳኔ ከወሰናችሁ በኋላ ስለ ኃጢያታችሁ እጅግ ድካምና ህመም የሚሰማችሁ ከሆነ ጌታ ሊያበረታችሁ ይፈልጋል፡፡ በዚህም ሁኔታ እያላችሁ ጌታ *ሥጋና* ደሙን ሊከለክላችሁ አይፈልግም፡፡ ምህረቱንና መልካምነቱን አምናችሁ ተቀበሉ፡፡ አሜን፡፡

**በየቀኑ ክርስቶስን እየመሰሉ መሄድ - ኦገስት 1 ቀን 2020ዓ.ም**

**Transformed Into Christ, Daily - August 1st, 20202**

ውድ ኸርት ድዌለርስ ከአይምሮ የሚያልፈው ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡ ውድ ቤተሰቦቼ ጌታ በፊታችሁ ለተዘጋጀው ሩጫ በደንብ እንድትታጠቁ ይፈልጋል፡፡ እናንተ በቤተ ክርስቲያን ስርዓት መሰረት የተሾማችሁ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በየቀኑ ለእግዚአብሔር የምትሰጡት ከሁሉም የሚበልጠውና ኃይል ያለው ፀሎት ወይም እርምጃ ቅዱስ መስዋዕት የሆነው የጌታ እራት ነው፡፡

አውቃለሁ አንዳንዶቻችሁ ከዚህ ልምምድ ወጥታችኋል፡፡ ስለዚህም በየቀኑ ይህንን የጌታ እራት ፀሎት አትፀልዩትም፡፡ በእኔ እጅግ የተወደዳችሁ ሆይ! እናንተ ከሁሉም በላይ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆናችሁ ለዚህ የክብር አገልግሎት የተሾማችሁ በምድር የተሰጧችሁን ነፍሶች እንድትጠብቁና እንድትማልዱላቸው ታልፈው ተሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻው መልእክቴ ጌታ በየቀኑ የእርሱን ሥጋና ደም መካፈል እንዴት ኃይል እንዳለው ጌታ አስተላልፎ ነበር፡፡ እኔ ይህንን ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ኢቫንጀሊካል በነበርኩበት ጊዜ ከዚህ አለም ውጪ ጥርት ባለ መልኩ ማየት አልችልም ነበር፡፡ በክርስቲያን ባህል እጅግ ተይዤ ነበር፡፡ ነገር ግን ወደቀደሙት ቤተ ክርስቲያናት ስሄድ ወደ አዲስ መንፈሳዊ ደረጃ ገባሁ፡፡ ይህም ክርስቶስን የበለጠ መከተልና ከዘመናዊው ባህል ይልቅ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ባህል በበለጠ ተሳብኩ፡፡

በየቀኑ ከምወስደው ከጌታ ራት የተነሳ፣ እንዲሁም ከተካፈልኩት ጥበብና ጥንካሬ ባይሆን ኖሮ አሁን እየሰራሁ ያለሁትን ነገር መስራት ባልቻልኩም ነበር፡፡ ለአንዳንዶች ይህ ዝም ብሎ የማይረባ ውይይት ይሆንብናል፡፡ እኔ ግን ሁላችንም ይህንን ነገር ትኩረት እንድንሰጠውና ለህይወታችን የሚያስፈልግ እንድናደርገው እፈልጋለሁ፡፡ የምንፀልየው ፀሎት ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እና ከቅዱሳን ጋር የምንነጋገርበት መሆን አለበት፡፡ በአንድ በኩል ብቻ የሚደረግ ንግግር ሳይሆን እውነተኛ የንግግር መለዋወጥ መሆን አለበት፡፡ እያንዳንዱ የተቀደሰ ስርዓት እርምጃ ጥልቅ የሆነ ትርጉምና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የቀረበ ግንኙነት መጋራት ነው፡፡ የተቀደሰውን የጌታን ሥጋና ደም በእጃችን ከያዝን በኋላ የሚያስፈልገን ነገር ይህ የጌታ እውነተኛ ሥጋና እውነተኛ ደም ነው ብለን በቃል ማወጅ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም የምናውጀው በእውነትም የጌታ እውነተኛ ሥጋና እውነተኛ ደም መሆኑን በሙሉ ልባችን በማመን ነው፡፡ እነዚህን ቀላል ቃላቶች ስታውጁ ነው ወደ እውነተኛ ሥጋና ደም የሚለወጠው፡፡

ሥጋውንና ደሙን በየቀኑ ስትቀበሉ ኃይልንንና የጌታን ቅርብት ብቻ አይደለም የምትቀበሉት፡፡ ይልቁንም በእንደዚህ አይነት መልኩ ስትቀበሉት እርሱን እጅግ ደስ ታሰኙታላችሁ፡፡ እርሱ በእንደዚህ በቀረበ መልኩ በእናንተ ውስጥ ለማደር ይጓጓል፡፡ እንዲህ ባይሆንማ ኖሮ በየቀኑ የጌታ እራትን እንድንፀልይ አይጠይቀንም ነበር፡፡ በተቀደሰው ሙሉ ልቡ የእናንተ የቅርብ ክፍል ለመሆን ይጓጓል፡፡ ከእናንተ ጋር ለመተሳሰር፣ አንድ ለመሆንና እናንተን ለማበርታት ይፈልጋል፡፡ ይህንን የመሰለ የሚያስገርም ልዩ ሙብት እንደ ቀላል ነገር ወደጎን ገፍተን በምትኩ ሌሎች ፀሎቶችን ወይም ሌሎች ተግባራትን መተካታችን እርሱን በእጅጉ እያቆሰልነው ነው፡፡ የጌታን እራት ከሁሉ ነገር አስቀድመን በየዕለቱ ጠዋት ወስደን ቢሆን ኖሮ ብዙ ሃዘኖችን አስወግደን ነበር፡፡ ጥበቃው፣ ጥንካሬው፣ የመንፈሳችን መጠንከር፣ ይህ ሁሉ ነገር ከእርሱ ጋር በአንድነት ለምንኖርበት ለዛ ቀን እንድንዘጋጅ ይረዳናል፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "ልጆቼ ክሌር እየተናገረች ያለችው የልቤን ነው፡፡ ይህ የእርሷ አመለካከት ወይም ሐሳብ አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የእኔን ልብ ነው ለእናንተ እየተናገረች ያለችው፡፡ እንዴት እንደምወዳችሁና እንደማከብራችሁ ! በእናንተ ውስጥ ለመኖር እንዴት እወዳለሁ ! እንዴት የእናንተ ዘረመልና የሴሎቻችሁ ክፍል መሆን እፈልጋለሁ ! እያንዳንዱን እራቴን ስታከብሩ እንዴት በኃይል እንደምለውጣችሁ! የእኔ ሥጋና ደም የማይረባውን ነፍስ እጅግ የተቀደሰ ነፍስ አድርጎ የሚለውጥ የህይወት መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ የተለወጠውን መሰረታዊ ነገር ስትቀበሉ በሰውነታችሁ የምትቀበሉት እኔ የሆንኩትን ሁሉ ነው፡፡ ከተለወጠ በኋላ የምትወስዱት ዳቦና ወይን ሳይሆን የኔን ሥጋና ደም በዳቦና በወይን መልክ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- በዚህ ላይ አንድ ተጨማሪ የምነግራችሁ ነገር የቁርባን ታምራቶች /Eucharistic Miracles/ የሚለውን ከኢንተርኔት ላይ ፈልጋችሁ እንድትመለከቱ ነው፡፡ እነዚህም ታምራቶች ወይኑ ወደ እውነተኛ ደም እንዲሁም ዳቦው ወደ እውነተኛ የልብ ጡንቻ የተቀየረበት ሁኔታ ነው፡፡ ሁሉም በታምራት የተቀየረው የደም አይነት /blood type/ ደግሞ ሁልጊዜ አንድ አይነት ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " በዚህ ቅዱስ በሆነ ድርጊት ካልሆነ በስተቀር እናንተን የምቀርብበት ሌላ ምንም መንገድ የለኝም፡፡ በሥጋዬና በደሜ ካልሆነ በቀር በሥጋ፣ በነፍስና በመንፈስ ተቀላቅለን አንድ ልንሆን የምንችልበት ሌላ ምንም መንገድ የለም፡፡ እኔን በምትቀበሉበት በእያንዳንዱ ጊዜ መለኮት ወደ እናንተ ለመኖር፣ ሊመክራችሁ፣ ሊያበረታችሁና ከሚያባብላችሁ አለምና ኃይል ሊለያችሁ ይመጣል፡፡ እኔን በታማኝነት የሚቀበሉ ነፍሶች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምንም አይጎድልባቸውም፡፡ ከእነርሱ የሚጠበቀው የተሰጣቸውን ፀጋ በመረዳትና ከፀጋው ጋር በመስማማት መንቀሳቀስ ብቻ ነው፡፡" (የመጨረሻው አረፍተ ነገር ይደገማል)፡፡

(ክሌር)፡- እዚህጋ አሁንም ተጨማሪ አለኝ፡፡ በየቀኑ የጌታን ራት መቀበልና በየቀኑ የተቀደሰውን ስብሳባ መሰብሰብ ህይወቴን በድንቅ ቀይሮታል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በህይወቴ ሊፈፀም ያለው ነገር ህልም ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር፡፡ ነገር ግን በአንፃሩ ሁሉም ወደ እውነታ እየተለወጠ መጣ፡፡ ይህንንም ያደረገው በእኔ የሚኖረው እርሱ እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . በልባችሁ የተሸከማችኋቸው እኔ በእናንተ ውስጥ እንዲወለድ ያስቀመጥኳቸው ህልሞች አሉ፡፡ እነዚህ ህልሞች እኔ ስፈጥራችሁ እናንተ እንድትፈፅሟቸው የተወሰኑ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሰይጣንና ሥጋ ከእኔ ጋር እንዳትሰሩ፣ ህልማችሁን ወደ ጎን እንድትተዉና ወደ ፍፃሜው እንዳይሄድ ለማድረግ እጅግ በጠነከረ መልኩ ሁልጊዜ መንፈሳችሁን ይዋጋሉ፡፡ ስለዚህም በውስጣችሁ ከሚገኝና ከምትመርጡት የበለጠ ኃይል ያስፈልጋችኋል፡፡ በእርግጥ ነው በውስጣችሁ በመንፈሴ እኖራለሁ፡፡ ነገር ግን በእናንተ በኩል የበለጠ ፀጋ ስለሚያስፈልጋችሁ ለዚህ ነው በሥጋና በደሜ በየቀኑ ትኩስ በሆነ መልኩ በእናንተ ውስጥ መኖር የምፈልገው፡፡

"የተወደዳችሁ ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ የራሴን ሥጋና ደም ለእናንተ እንዲሆን ከባዱን ሥቃይ ባልተቀበልኩ ነበር፡፡ በተጨማሪም የሰይጣን የሆኑት በእያንዳንዱ ቀን ከመሰዊያው ላይ ቁርባኔን በመስረቅና በሚስጥር ክብረ በአላቸው በማርከስ ትልቅ ሥቃይ ያደርሱብኛል፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ከእናንተ ጋር ለመሆን ብቻ በዚህ ስቃይ ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኛ ሆኛለሁ፡፡ እናንተ ለእኔ ይህንን ያህል ናችሁ፡፡

"ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ለተሾማችሁት ለእናንተ የምነግራችሁ ነገር ጠላት የጌታ እራት መስዋዕት ሌላ የማይረባ ስርዓት ነው ብሎ ዋሽቷችኋል፡፡ ይህ እውነት አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ወደ አብ በሥጋዬና በደሜ ወደላይ ስታነሱኝ እርሱ እንደገና ሥጋዬን ይቀበልና ፀጋን ለአለም ሁሉ ይለቃል፡፡ ይህም የሚቀድሳችሁ፣ እንዲሁም እናንተ በተለየ መልኩ ልትፈፅሙት የተሰጣችሁን ዓላማ ለመፈፀም የሚያስችላችሁ ፀጋ ነው፡፡

ስለዚህም ውዶች ቸልተኛ በሆናችሁበት ነገር ላይ አሁን ንስሐ ግቡ፡፡ ይህንን ፀሎት እንደገና ፀልዩ፡፡ በሙሉ ልባችሁ፣ በእኔ ፋንታ ሆናችሁ ለአብ ተናገሩ፡፡ ይህንንም በምታከብሩ ጊዜ በኃያሉ በእግዚአብሔር ሙሉ መገኘት ውስጥ ናችሁ፡፡ እያንዳንዱን ቃል ይሰማል፣ እያንዳንዱን የልባችሁን ዝንባሌ ያያል፡፡ በቅንነትና በእምነት ስታደርጉት ያውቃል፡፡ ለብ ስትሉና እንዲሁ እንቅስቃሴውን ብቻ ስታደርጉት ያውቃል፡፡ እኔን ወደ ምድር ለመላክ ብዙ ዋጋ አስከፍሎታልና እርሱን እንደዚህ አታድርጉት፡፡ የጌታ እራትን ስትፀልዩ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፡፡

ይህንን ፀጋ አሁን ጠይቁኝና አካፍላችኋለሁ፡፡ በዚህም በተቀደሰው ደስታ እንኖራለን፡፡ ደግሞም ለዘመናት የተነገረውን ትንቢታዊ የተስፋ ቃሎች ሲፈፀም እናያለን፡፡ በዚህም ከቆሻሻ የፀዳ፣ መጨማደድ የሌለበት፣ ነቀፌታ ያልተገኘበት በመሆን ለዘላለም ሽልማት የተገባችሁ ትሆናላችሁ፡፡ በዚህም አሁን እባርካችኋለሁ፡፡ እናም ደግሞ ቅዱሳንና መላዕክቶች በቋሚነት በእኔ እራት ላይ እንደሚገኙ እወቁ፡፡ ከእናንተም ጋር በመገኘት ይፀልያሉ ደግሞም ስርዓቱን ያከብራሉ፡፡

## ከኢየሱስ ጋር የጠለቀና አስደሳች ግንኙነት እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ? - ኦገስት 5 ቀን 2020 ዓ.ም

### Deeper and sweeter with Jesus, Agust 5, 2020

የተወደዳችሁ የኸርት ዱዌለርስ ቤተሰቦች የጌታ በረከት ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ ለመሆኑ ስንቶቻችሁ ከጌታ ጋር የጠለቀና አስደሳች ግንኙነት እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ? አሁን ያላችሁበት ሁኔታ አስጠልቷችኋል? የተወደዳችሁ እኔ ግን አስጠልቶኛል፡፡ እርሱ ደግሞ መሄድ ያለብኝን አቅጣጫ ብርሃን እያበራበት ነው፡፡ ይህንንም ለእናንተ አካፍላችኋለሁ፡፡ ምናልባትም ከእኔ ቀድማችሁ የታሰበው ቦታ ትደርሱ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ለእኔ ደስታን የሚፈጥር ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዳችሁ ከእርሱ ጋር የጠለቀ ግንኙነት ሲኖራችሁ ማየት የልቤ ምኞት ስለሆነ ነው፡፡

በዚህ ማለዳ አንድ መፅሐፍ አንስቼ ለማንበብ ተነሳሳሁ፡፡ ይህም መፅሐፍ በፈረንጆች አቆጣጠር በ1961 ዓ.ም በሪፈረንድ ፍራንሲስ ጃማርት አሲዲ የተፃፈና በአልባ ሃውስ የታተመ ነው፡፡ የመፅፉም ሥም ኮፒኢት ዶክትሪን ኦፍ ሴንት ቴሬስ ኦፍ ሊሱይክስ የሚል ነው፡፡ ይህንን የገለፅኩት ምናልባት መፅሐፉን ለማንበብ ፍላጎት ያላችሁ ከሆነ በሚል ነው፡፡ እናም ከዚህ መፅሐፍ ውስጥ ገፅ 138 ከፍቼ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ምዕራፉ የሚያወራው ስለ ቀላል ህይወት ነው፡፡

ከፍሉም እንዲህ ይላል. . . "ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስና ጠባቂዬ መላዕኩ ሚካኤል ሁልጊዜ የምወዳቸውን ነገሮች እንድተው ያበረታቱኛል፡፡ ይህንን ዓይነት ህይወት ቀደም ብዬ የምኖረው ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ ዓይነት መንገድ ስኖር በጣም በነፃ እንድኖር አድርጎኛል፡፡ ይህ አይነት አኗኗር ኢየሱስ ወደ ውስጣችን ቶሎ ዘልቆ በመግባት ፍቅሩን የሚሞላበት ባዶ ሥፍራን

ይፈጥራል፡፡ እኔ ለብዙ ዘመናት ስጦታን ለመስጠት ንፉግ ነበርኩ፡፡ ይህ ደግሞ የእኔንና የእርሱን መቀራረብ እንደጎዳው አውቅ ነበር፡፡ እናም ይህንን ጥቅስ ስከፍት ከእግዚአብሔር ጋር ወደፊት መቀጠልና ጥልቅ ፍቅር ከእርሱ ጋር በእርግጥ ከፈለግሁ፣ እንዲሁም ደስታዬ በእግዚአብሔር ብቻ እንዲሆን ከፈለግሁ እያንዳንዱን የማደርገው ነገር ከእርሱ ፍቅር የተነሳ ብቻ ማድረግ፣ ትንንሽ ደስታዎችን ሁሉ በመተው ራሴን መካድ በተግባር መግለጥ መጀመር እንዳለብኝ ማረጋገጫ አገኘሁ፡፡

ጥቅሱም እንደሚከተለው ነው፡-

"ከፍቅር የተነሳ የሚደረጉ ትንንሽ ነገሮች ናቸው የክርስቶስን ልብ የሚማርኩት፡፡"

"በጣም ትንሿን፣ የማትታየውን መስዋዕት እንኳን ለመስጠት ኢየሱስን እንቢ አትበሉ! እያንዳንዱ ሃይማኖተኛ የሚኖረው ህይወት በእውነት ትልቅ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- እዚህጋ ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ማህበረሰብ አንድ የምለው ነገር አለኝ፡፡ ሃይማኖተኛ መጥፎ ቃል ነው፡፡ ነገር ግን ሃይማኖተኛ የሚኖረው ህይወት በእውነቱ ከሆነ አለምን ሁሉ ወደኋላ በመተው ለክርስቶስ ብቻ መኖር ነው፡፡

ፀሐፊው እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " እግዚአብሔርን ስናገለግል ምንም የማይታይ ወይም የሚተው ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም አንድን ነገር ለማድረግ የሚሰጠው ዋጋ ከዕቃው አስፈላጊነት የሚመጣ ሳይሆን ያንን ነገር ለማድረግ የተነሳሳንበት የውስጥ ፍላጎትና ፍቅር መጠን የሚተመን ነው፡፡"

ትሬስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . .እግዚአብሔር ወደ እውነተኛው ክብር ለመድረስ እጅግ የሚያንፀባርቅ ሥራዎችን ማከናወን እንደሌለብኝ ነገር ግን ራሴን በመደበቅ ደግነትን መለማመድ እንዳለብኝ ይህም ቀኜ የሚያደርገውን ግራዬ እንኳን እንዳያውቅ በማድረግ እንደሆነ ለማጤን እንድችል አደረገኝ፡፡

(ክሌር)፡- ይህንን ገፅ ገና ስከፍት ጌታ ህይወቴን የበለጠ ቀላል እንዳደርግና በትንንሽ ነገሮች ራሴን እንድክድ አደራ እየጣለብኝ ወይም እያረጋገጠልኝ እንደሆነ አውቄ ነበር፡፡ ራሴን አሁን ሳየው በእርግጥም አምባገነን እንደሆንኩ ነው፡፡ የቡና ትምክህተኛ፡፡ በብዙ መንገድ ትምክህተኛ እየሆንኩና ብዙ ነገሮችን እየወደድኩ ነው፡፡ አሁን ራሴን ለመቀየር ጊዜው ነው፡፡ ለምሳሌ የተፈጨ ቆንዶ በርበሬ የሌለው ምግብ መመገብ፣ ወይም አንድ ብቻ የቀረ የምወደውን ፍራፍሬ ለሌላ ሰው መስጠት፣ ወይም በጣም የምወደውን የእርጎ ማጣፈጫ በእርጎ ውስጥ መጨመር መተውና የመሳሰሉትን ዓይነት ነገሮችን መተው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ህፃንነትና ቀላል ሊመስል ይችላል፡፡ እሺ ይህ ቢሆንስ ጌታ እንደ ህፃን ካልሆናችሁ ወደ እግዚአብሔር መንግስት አትገቡም ብሎ የለም?

ብቻ ምን ልበላችሁ እኔ የሚጣፍጡ ምግቦች እስረኛ እስከሆን ድረስ ራሴን አበላሽቻለሁ፡፡ አንድ ወቅት በጠዋት እነሳና ወዲያው ተፈልቶ የሚጠጣውን ቡናዬን እጠጣና ቀኑን ሙሉ በደህና እውል ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ቡናው በተለየ ዓይነት

መፈጨት፣ በልዩ ዓይነት መፈላት አለበት፡፡ ይህም በጣም የሚያስጠላ ነው፡፡ ድሮ ድሮ ፍራንሲስካ ሲስተርስ በነበርኩ ጊዜ ስለነዚህ ጉዳዮች ግድ አልነበረኝም፡፡ አሁን ግን የሚሰማኝ እነዚህ ምድራዊ ነገሮችና ምርጫዎች በውስጤ ጭራቆችን እየመገቡ ነው፡፡ እናም እነዚህን ሁሉ መተው አለብኝ፡፡ እነዚህንም በመተው ከውስጤ ጭራቆችን ሁሉ ማባረር አለብኝ፡፡ ኢየሱስ ስለዚህ የምትለው ነገር አለህ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "የምስራች!!! በህሊናሽ ውስጥ ሲመላለስ የነበረውን ይህንን እውቀት ተጠቅመሽ እርምጃ እንድትወስጂ እየጠበኩሽ ነበር፡፡ ክሌር በምግብ ደስታን ከማግኘት ይልቅ ለመንፈሳዊ ነገሮች ዋጋ ለመስጠት ስለመረጥሽ እጅግ ደስተኛ ታደርጊኛለሽ፡፡ እነዚህ ነገሮች በቤተክርስቲያኔ መሪ አገልጋይ ሆነሽ የተሰጠሽን ዓላማ እንዳትወጪ ያደርጋሉ፡፡ ሥጋ ወደሙ ስትቀበዩ ይህ ነገር እንዲለወጥ እርዳታ ስለጠየቅሺኝ አመሰግንሻለሁ፡፡ እነዚህ ደስታ የሚሰጡሽን ነገሮች ለመተው በጣም ልዩ ፀጋ ያስፈልግሻል፡፡

ለምሳሌ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ልታዪው ትችያለሽ፡፡ "የምትመርጪውን ምግብ በመብላት እየተዝናናሽ ነገር ግን በጣም ወፍረሽ በዩ ቲዩብ መንፈሴ የሚሰራባቸውን ቁጭ ብለሽ ማየት ትችያለሽ፡፡ ወይም ደግሞ ሸንቃጣ አገልጋይ ሆነሽ ከእኔ ጋር ጎን ለጎን የምትሰሪ ልትሆኚ ትችያለሽ፡፡ አውቃለሁ አንዳንድ ምግቦችን መብላት እንደሚያስፈልግሽ፡፡ ነገር ግን ብዙ ምግቦችን መተውና በጤንነትም መቆየት ትችያለሽ፡፡ ይህ የአንቺ ምርጫ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ይገርማችኋል ይህንን ለማረጋገጥ ጊዜ አልፈጀብኝም፡፡ ከራት በፊት ይርበኝና አንድ ነገር ሰርቼ ለመብላት ስለፈለግሁ የቅቤ ሳንድዊች ሰራሁ፡፡ በላዩ ላይ የቀይ እንጆሪ ማርሜላት ለማድረግ እጅግ ፈልጌ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ጌታ "ማር" ሲል ሰማሁት፡፡ ስለዚህም ትንሽ ማር አደረግሁበት፡፡ ሳንድዊቹን እየበላሁ እያለሁ ግን ሳስብ የነበረው 'ጌታ እኔ በእውነት የቀይ እንጆሪ ማርሜላት እወዳለሁ' እያልኩ ነበር፡፡ ነገር ግን ህም ቢሆን ሳንድዊቹን በማሩ በልቼ ጨረስኩ፡፡ እናም የእነዚህን ነገሮች አስፈላጊነት እየቀነስኩ ስሄድ ነገሮች ጥሩ እየሆኑ ይሄዳሉ ብዬ አስባለሁ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ተጨባጩ ነገር አገልጋዬ በሚደሰትበት ነገር ራሱን ከሞላ መንፈሳዊ ስጦታዎቼን በሙላት ልሰጠው አልችልም፡፡ የኔ ፍቅር ይህንን ለብቻሽ ልታደርጊው አትችይም፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ አትችይም፡፡ ነገር ግን አንቺ ከተባበርሽ በአንቺ በኩል እኔ ልሰራው እችላለሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ እባክህ ከአን ጋር ልተባበር የምችልበትንና ከስጦታዎች ጋር የምስማማበት ስጦታዎች ትሰጠኛለህ?

"አዎ የኔ ፍቅር ይህ ከዚህ ጥቅል ስጦታዎች አንዱ ክፍል ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት ቅድስና፣ ሰላምና ደስታ እንጂ ምግብና መጠጥ አይደለም፡፡ ታዲያ በህሊናሽ ራስሽን ለመካድ እየተንተተሽ እንዴት ነው ሰላምና ደስታ ሊኖርሽ የሚችለው? የሚደንቅ ነው! ይህ በእርግጥ እውነት ነው፡፡ ይህ ነገር በአይምሮዬ በጣም ነው የሚሰማኝ፡፡ ጌታ እውነት ነው ይህ በፍፁም ሰርቶ አያውቅም፡፡ የምፈልገውን እየበላሁ ምንም ያህል ራሴን ደስተኛ አድርጌ ለማስመሰል ብሞክርም በውስጤ ግን "ወደ ጌታ ለመቅረብ የምትፈልጊ ከሆነ ያለሽው በትክክለኛው መንገድ አይደለም" የሚል ትንሽ ድምፅ እሰማለሁ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ራሳቸውን ለእኔ ሲሉ ክደው ህይወታቸውን የመሩ፣ እንዲሁም ያደረጉት ነገር ሁሉ ከፍቅር የተነሳ ብቻ የሆነ ስጦታቸውና በረከታቸው እንዴት ድንቅ ነው!! እነዚህ ናቸው በመንግስቴ ውስጥ ታላላቆች፡፡ ምንም እንኳን በምድር ከሁሉም ታናሽ ሆነው ቢታዩም "እግዚአብሔር ጌታ አምላካችሁን በሙሉ ልባችሁ፣ በሙሉ ሐሳባችሁ፣ በሙሉ ኃይላችሁ ውደዱ፣ ጎረቤቶቻችሁን እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ" የሚለው ሥራቸው ለሰው ልጆች ሁሉ ይጮሃል፡፡

"በእውነትም ይህ መንፈሳዊ መለዮ ነው፡፡ እናም ይህ ደግሞ በአንድ ነፍስ ብዙ እየተገለጠና የበለጠ የራሱ እያደረገው ሲሄድ ቅድስናው እየጨመረና ሌላውንም ለመለወጥ ተፅዕኖ የሚያመጣ እየሆነ ይሄዳል፡፡ የኔ ውድ አንዳንድ የምትወጃቸውን ምግቦች ቀስ በቀስ ራስሽን በመግዛት እየተውሻቸው ስትሄጂ እኔን በቀላሉ ለመስማት እየቻልሽ እንደሆነ ተገንዝበሻል፡፡ ግሉቲን የሚባለው ውህድ ያለበትን ምግብ ለሰውነት ማስለመድ ለብ ወዳለ መንፈሳዊ ህይወት የመንሸራተት መንገድ ነው፡፡ እርግጥ ነው ራስሽን በሌላ መንገድ አሳልፈሽ መስጠት ትችያለሽ፡፡ ይህንን እንድታደርጊ ደግሞ በቀን ውስጥ የምሰጥሽ ዕድል አለ፡፡ ይህንንም ዕድል ደግሞ ልትጠቀሚበትም ሆነ ልትተዪው ትችያለሽ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን እነዚህ የኔ ስጦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የመቀራረብ ወቅቶች አንቺ እንደምትፈልጊያቸው ያህል እኔም እንደምፈልጋቸው አታውቂም?

ጌታ ለዚህ መልስ መስጠት ካለብኝ ከእኛ ይልቅ እንዳውም አንተ የበለጠ ትፈልገዋለህ፡፡

ጌታም . . . "መልሱ መቶ በመቶ ልክ ነው፡፡ ደግሞም ሳቅ አለና ለዚህ ኤ -ፕላስ እሰጥሻለሁ፡፡" አለኝ፡፡

"በዚህ ነጥብ ላይ በጥሩ ሁኔታ ጀምረሻል . . . ስለዚህ በየቀኑ ትንሽ ትንሽ እየሰራሽበት መንገድሽን እንዴት እንደማበራልሽ ታያለሽ፡፡ ክሌር ይህንን ለማየት እንዴት እጓጓለሁ፡፡ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ በሚደረገው ሥራ ላይ በነበርሽ ጊዜ "ክሌር በአንቺ ተደስቻለሁ" ያልኩሽን ታስታውሻለሽ? አንቺም በወቅቱ "ለምን" ብለሽ ስትጠይቂኝ "እኔ እንድትሆኚ የፈጠርኩሽን እየሆንሽ ስለሆነ ነው" ብዬሽ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ የተወያየነው ነገር ከአይምሮሽ ውስጥ እስካሁን ያልጠፋው በምክንያት ነው፡፡ ይህም ምክንያት ወደዛ እንድትመለሺ እየጠራሁሽ ስለሆነ ነው፡፡ እኔ ከአንቺ ይህንን ስለምጠብቅ እባክሽ ተስማሚ፡፡ በአንቺ ብዙ ለመስራት የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ አሁን የማወራው አብዛኛው ነገር በመንግስተ ሰማያት ካልሆንሽ በስተቀር ሊገባሽ የሚችል ነገር አይደለም፡፡ ስለዚህ አሁን ምንም አታስቢ፡፡ በዚያን ጊዜ ታዲያ ትደነግጫለሽ፡፡ ስለዚህ እስቲ ወደ ውስጥ እንቆፍርና ይህንን እንሥራ!!!"

አሜን ጌታዬ፣ አሜን፡፡ የአንተን ጥንካሬ እቆጥራለሁ፡፡ ነገር ግን በሙሉ ልቤ እስማማለሁ፡፡ ኢየሱስ ምን ያህል እንደምወድህ ማሳየት እፈልጋለሁ፡፡ የምወደውን ኩኪስ እየበላሁ "ኢየሱስ እወድሃለሁ" ማለትና የምወደውን ኩኪስ በመተው "ኢየሱስ እወድሃለሁ" ማለት የተለያየ ነገር እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት መለሰልኝ . . . በትክክል አግኝተሸዋል፡፡ የኔ በረከት በዚህ መንገድ ነው፡፡ የኔ ፍቅር መንገዱ ይህ ነውና ከዚህ መንገድ እንዳትወጪ፡፡

## ቅባቱ ያለው በተሿሚዎች ላይ ነው - ኦገስት 6 ቀን 2020 ዓ.ም

## The anointing is in the appointing, August 6th, 2020

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች ጌታ በሰላሙና በደስታው ይባርካችሁ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሥራዬ ላይ ያልተረጋጋና ተለዋዋጭ የሆነ ነገርን ተገነዘብኩ፡፡ ጌታንም "ይህንን ነገር የፈጠረው ምንድነው? " ብዬ ጠየኩት፡፡ እርሱም "አመፅ" በማለት መለሰልኝ፡፡ አመፅ ደግሞ በቡድን ያሉ ቅን ክርስቲያኖችን የሚከፋፍል ቀዳሚ የኢጋንንት አሰራር እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሳይቀበሉ መቅረት ለአመፅ በር ስለሚከፍት እኔ አንድ ነገር በመናገሬ ወይም በማድረጌ አመፁ እንዲጀመር አስተዋፅዎ አድርጌ ይሆን?፡፡ ነገሮችን በጥልቅ ለማወቅና ለመረዳት ስለፈለግሁ ጌታን "እነዚህ ምልክቶች ለምንድነው ሊታዩ የቻሉት?" ብዬ ጠየኩት፡፡

ጌታም ግልፅ በሆነ መንገድ "ቅናት፣ በስተጀርባው ደግሞ ኩራት አለበት" በማለት መለሰልኝ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "የኔ ፍቅር አንቺ በእውነት ትንሽና የምትናቂ ነሽ፡፡ እናም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሲያዩሽ እነርሱ በተሻለ መንገድ ነገሮችን ማከናወን እንደሚችሉ ያስባሉ፡፡ በዚህ ሐሳብ ደግሞ እስማማለሁ፡፡ በእርግጥም እነርሱ በቦታው ላይ ቢሆኑ ነገሮች የተለዩ ይሆኑ ነበር፡፡ እንዳውም የበለጠ ጥሩ ይሆኑ ነበር፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ሴት መሆንሽን ጨምሪበት፡፡ ከባህል የተነሳ ወንድ ከሴት የበለጠ ለመምራት ብቃት አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህም አንዳንዶች አንቺ የምትሰሪውን ሥራ በበለጠ መልኩ እንደሚሰሩት ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ብቻውን መሪ ከመሆን ያግዳቸዋል፡፡ እነርሱ የሚያስቡት ብዙ ወንዶች እንደሚያስቡት እንጂ እኔ እንደማስበው አይደለም፡፡

(ክሌር)፡- ጌታ ታዲያ እኔ ምን ማድረግ አለብኝ?

"አንቺ ፍቅር ስጫቸው እኔ ሌላውን እጨርሰዋለሁ፡፡ መሰበር ያለበት የሚሰበርበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ አሁን እዛ ደረጃ ላይ ነው ያለነው፡፡ የአንቺ እጅግ አስፈላጊው አቋም ፍቅር፣ የእናትነት ድጋፍና ክብካቤ ነው፡፡ ለዚህ ነው በመሪነት ቦታ ላይ የተቀመጥሽው እንጂ በብዙ ሌሎች ነገሮች ብቁ ስለሆንሽ አይደለም፡፡

የተወደድሽ በአጭሩ አንቺ የተከበብሽው ከአንቺ በእጅጉ በሚሻሉ ሰዎች ነው፡፡ ይህም የሆነው በምክንያት ሲሆን ምክንያቱን ደግሞ ወደፊት የምገልፀው ይሆናል፡፡ አንዳንዶች ከአንቺ ጋር ሲወዳደሩ ከእኔ ጋር እየተወዳደሩ እንደሆነ እስካሁን አልገባቸውም፡፡ ከመስመር ስትወጪ እኔ እርምሻለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ አቅጣጫ እንደማሳይሽ እንዲታመኑብኝ እመርጣለሁ፡፡ እናም ደግሞ በአንቺ ምን እየሰራሁ እንዳለሁ እውቀቱ እንዳለኝ እንዲታመኑ እፈልጋለሁ፡፡

ይህ ተለዋዋጭ ሆነ ብለሽ ያሰብሽው ነገር አንቺ በሐሳብሽ ያሰብሽው ብቻ ሳይሆን በእውነት የተከሰተ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ፍቅር ሁሉን ያሸንፋልና ዝቅ ብለሽ በመቆየት እንቢ የሚሉሽን ነፍሶች ደግፊያቸው፡፡ እናም እኔ መልሼ አመጣቸዋለሁ፡፡ ውድድር ባለበት ማህበረሰብ መካከል ሰላም አይኖርም፡፡ ለሌሎችም በደንብ እንዲገባቸው የምፈልገው ነገር የዲቢሎስ መሳሪያዎች በመሆን መከፋፈልን በመካከላቸው እንዳያመጡ ነው፡፡ ይህ ነፍስ ይህንን ሥራ እንዲሰራ ከጠላት የቤት ሥራ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ነገሩ ሲጀምር የጀመረው በትንሽ ነበር፡፡ ሰይጣን የሚሰራው ብልጠት በተሞላበት መንገድ ቀስ ብሎ ስለሆነ ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ ነገሩም እያደገ መጣ፡፡

ሰይጣን የሚጠቀምባቸው ነፍሶች ውስጣቸው ለአመፃ ለምን እንደሚነሳሳ እንዲሁም ከስሜቶቻቸው ጀርባ ማን እንዳለ የሚገባቸው አልፎ አልፎ ነው፡፡ ከሌር ለዚህ ነው ለአንቺ በቅንነት የምነግርሽ፡፡ ሁሉም ሰው ራሱን በእኔ መስተዋት እንዲያይና ከእንደዚህ አይነት መንፈስ ጋር መተባበር የሚያስከትለውን ውጤት እንዲገነዘብ እፈልጋለሁ፡፡ የመጨረሻ ጥሩ የምትዪውን ነገር አንቺ አድርጊ፡፡ ፍቅርን ስጫቸው ደግሞም ተንከባከቢያቸው፡፡ ሌላውን እኔ እጨርሰዋለሁ፡፡

በመመሪያ ሥር ያላችሁ ልጆች በነፍሳችሁ ላይ እየሰራ ያለውን ክፉ በጥንቃቄ መረዳት አለባችሁ፡፡ ክፉን በአስቸኳይ መቃወምና በግልፅ ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ፡፡ በውስጣችሁ ያለውንም ጥል ለማቃለል የኔን እርዳታ ጠይቁ፡፡ ይህንን አይነት አመለካከት ይዞ እየተጓዙ ምንም መልካም ነገር ሊመጣ አይችልም፡፡ በአንፃሩ ግን በአካባቢያችሁ የሚኖሩትን ሰዎች መመረዝና መከፋፈልን ያመጣል፡፡

አብዛኛዎቻችሁ እዚህ የተገኛችሁት የመሪነት ቦታ ክብር እንደሚያስፈልገው፣ ክብር የሚሰጠው ደግሞ ለተሿሚው ሲባል ሳይሆን ለቢሮው እንደሆነ በመረዳታችሁ ነው፡፡ ለምሳሌ ዳዊትን ውሰዱ፡፡ ዳዊት ሳኦል ትልቅ ጥፋት እንዳጠፋና አንድ ቀን እርሱ በሳኦል ቦታ እንደሚሾም ቢያውቅም እንኳን ለእኔ ክብር ስለነበረው እርሱን ለመጉዳት አልደፈረም ነበር፡፡ የተወደዳችሁ ከእናንተም የምጠብቀው ይህንን ነው፡፡ ቢሮውን አክብሩ ደግሞም የተሾመውን ታገሱ፡፡ መሪዎች በምን አይነት ጫና ውስጥ እንዳሉ ምንም አታውቁም፡፡

ከውጪ ሆናችሁ ስትመለከቱት እናንተ በበለጠ ልትሰሩ የምትችሉ ይመስላችኋል፡፡ ነገር ግን በእነሱ ቦታ ስትገቡ ነገሩ እንደዛ ቀላል እንዳልሆነ ወዲያው ትረዳላችሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እናንተን ወደታች ለማውረድ አዲስ ሙሉ ሌጊዮን አጋንንት ይመደብባችኋል፡፡ ምክንያቱም የእናንተ መውደቅ ማህበረሰቡን ሁሉ ስለሚያበላሽ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በደረጃዎች ላይ ሆኖ ዙፋኑን ማየትና በዙፋኑ ዕይታ ሆኖ መመልከት እጅግ ልዩነት አለው፡፡ መንፈሴ የሚሰራው አደራ ከተሰጣቸው መሪዎች ጋር ነው፡፡ በሌላው አንፃር ደግሞ ከደረጃው በታች ያሉትን ስሜታቸውን የሚያነሳሳው መንፈስ ብዙ ጊዜ የሚያተኩረው በራሳቸው ላይ ነው፡፡

ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ብናገረውም አሁንም ደግሜ መናገር አለብኝ፡፡ መልካም መሪ ማለት ታማኝና ጥሩ ተከታይ ከማለት ውጪ ምንም ማለት አይደለም፡፡ የእናንተ የተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ፣ እንዲሁም በህይወት ያገኛችሁት ልምድ ለመምራት ተመራጭ አያደርጋችሁም፡፡ ለመሪነት ጥሩ ተመራጭ የሚያደርጋችሁ ለመከተል ያላችሁ ችሎታና ለሌሎች ያላችሁ እውነተኛ ፍቅር ነው፡፡ በየትኛውም ቢሆን የትኞቹም ምንም ለውጥ አያመጡም፡፡ ቅባቱ ያለው በተሾሙት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ቅባቱ በሚሾሙት ላይ የትኛውምንም እጥረት የሚሞላና አለም የሚሰጠውን ችሎታ ሁሉ የሚያሟላ ነው፡፡

የአንድ ነፍስ ልብ በፊቴ ትክክል ሆኖ ሲታይ ለመምራት ተመራጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን ቅናት፣ የተደበቀ ቅሬታና ኩራት ካለ መርዝን ይረጫል፡፡ እነዚህ አመለካከቶች በጣም መርዘኛ ከመሆናቸውም የተነሳ አንድ ነፍስ በእነዚህ ከተያዘና በአመራር ላይ ከተቀመጠ ማህበረሰቡ በሙሉ በመርዝ ይሞላል፡፡ ምክንያቱም መሪውን የሚከተሉት ልቦች ሁሉ እንደመሪው ልብ ይሆናሉ፡፡

ለምንድነው ይህንን የምነግራችሁ? ምክንያቱም የሚከፋፍል መንፈስ ለዚህ ማህበረሰብ ስለተመደበ ነው፡፡ ለማስፈፀሚያነት ከሚመርጣቸው መሳሪያዎቹ ደግሞ ቅናትና ኩራት ይገኙበታል፡፡ ስለዚህም ይህንን የምነግራችሁ ከጠላቶቻችሁ ይልቅ ብልህ እንድትሆኑ ነው፡፡የኔ ውዶች በጥልቀት ሂዱና እናንተን እንደዚህ እንድታስቡ ያደረጋችሁን አጋንንት ለዩ፡፡ ደግሞም ለእኔ እንዲሁም ለራሳችሁ ስትሉ ይህንን በውስጣችሁ ይዛችሁ አትቀመጡ፡፡

ይህንን አመለካከት የቀሰቀሰው መንዳት ከሆነም ነገሩን በግልፅና በእውነት አንዱ ለሌላው ያቅርብና ሁላችሁም በሰላም እንድትኖሩ ይሆን፡፡ እኔ አፍቃሪ፣ በታናሽና ምንም ችሎታ በሌለው ነፍስ የምመራችሁ አምላክ ነኝ፡፡ ለዚህ ነው ለቢሮው ክብር ስጡ ብዬ የምጠይቃችሁ፡፡

እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ወደ እኔ ኑ፡፡ ንፁህ ልብ እንዲኖራችሁ እረዳችኋለሁ፡፡

## የንስሐ ጥሪ ለእግዚአብሔር ህዝብና የ፫5 ቴክኖሎጂ አደገኛነት - ኦገስት 12 ቀን 2020 ዓ.ም.

## War with China, August 12,2020

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ጠላት ሰዎች መፀለይ እንደሚገባቸው እንዲፀልዩ አይፈልግም፡፡ ከቻይና ጋር ጦርነት ለመጀመር አፋፍ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህንንም ጦርነት ሊያቆመው የሚችለው ታምራዊ የምልጃ ፀሎት ብቻ ነው፡፡ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ቻይና በአለም ላይ በሰራችው ሥራ እጅግ ተናዷል፡፡ ደግሞም በዚህ ጉዳይ ላይ አሜሪካን ለማጥፋት የሚፈልጉ ሌሎች በስተጀርባ በጉዳዩ እንዳለቡት ተረድቷል፡፡ አሜሪካ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ እንጂ እናንተን ተቃዋሚ አይደለሁም፡፡ እንደገና እንድታሰራሩ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን ከኢኮኖሚ ማንሰራራት የበለጠ እንድትታደሱ የምፈልገው በመንፈሳዊ ህይወታችሁ ነው፡፡

"እባካችሁ ልባችሁን ፈትሹና ከእኔ ጋር መሆናችሁን ወይንም እኔን እየተቃወማችሁ እንደሆነ ራሳችሁን መርምሩ፡፡ ከቁማርተኞች ጋር ናችሁ ወይንስ እነርሱን ተቃዋሚዎች ናችሁ? እባ ፈንታችሁን አገራችሁን ከሚቃወሙ ከክፉ ኃይላት ጋር አድርጋችኋል ወይንስ በእኔ በኩል ናችሁ???

"ለዚህ አገር ንስሐ መግባት አሁንም እጅግ ወሳኙ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ዋናው ቁም ነገር ብልፅግና እንደገና ማንሰራራቱ ላይ ሳይሆን የኔን ጥበቃ እንደገና ማግኘቱ ላይ በመሆኑ በዚህ አገር ላይ ስለተፈፀሙት እጅግ ክፉ ተግባራት እናንተም በመተባበራችሁ ንስሐ መግባት አለባችሁ፡፡ በሆሊውድ የሚገኘው ሁሉም የፊልም ኢንዱስትሪ ለሰይጣናዊ አምልኮ ሰዎችን በተለይም ልጆችን የወሲብ ጥቃት በማድረስ፣ በማሰቃየትና በመግደል ለብዙ አስርት አመታት የተሳተፉ ናቸው፡፡ በዚህም መንገድ በተሰራው ፊልም ሰይጣን የህብረተሰቡ ሞራል እንዲጠፋ፣ ህፃናት ልጆችን በወሲብና በሁከት ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ በመቀስቀስ የዚህ አገር ሞራል እንዲወድቅ አድርጓል፡፡

"እነዚህን ፊልሞች ለማየት ያዋላችሁት ብሮች ሁሉ የደም ገንዘብ ናቸው፡፡ እናም ይህ ከምድር ወደእኔ የሚጮኸው ደም ምንም የማያውቁ ህፃናት ደም ነው፡፡ በገንዘባችሁ ግዴለሾች በመሆን፣ ክርስቲያን ባልሆኑ ፊልሞች ላይ በማዋል፣ በጀርባው ለሚሰራው የሰይጣን አምልኮ እንዲውል አድርጋችኋል፡፡ እነዚህም አምልኮዎች፣ ወሲቦችና የብጥብጥ ተግባራት ሁሉ ፕላኔታችሁን ወደ ገሃነም እንዲቀይሩ ቀጥታ ከገሃነም የሚወጡ ናቸው፡፡

"አሁን ግን እቅዳቸው ምን እንደሆነ ስርዓት በሌለው ድርጊታቸው፣ በብጥብጥ ተግባራቸውና በአብዮተኛነታቸው ማየት ጀምራችኋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ልጆቻችሁን ለማሰልጠን በፊልሞች ላይ ተካተው ልጆቻቸው ሲያዩአቸው የነበር ነው፡፡ በዚህም ትክክለኛው ሰዓት ሲደርስ፣ ገና በለጋ እድሜያቸው ከከፉው ጋር ተቀላቅለው ይህንን አገር በመቃወም የመጀመሪያ አጥፊዎች እንዲሆኑ ነው፡፡

"ፕሬዜዳንታችሁ ሊያደርግ የሚችለው ይህንን ያህል ብቻ ነው፡፡ በንስሐና ከልብ በሆነ ፀሎት ካልሆነ በቀር በድብቁ አስተዳደር /shadow government/ የተገነባውን ይህንን መሰረት ለመናድ ያለው ተስፋ ትንሽ ነው፡፡ በፀሎት ግን ትልቅ ተስፋ አለ፡፡

ለማስተላለፍ የምፈልገውም መልዕክት ይህንኑ ነው፡፡ የእናንተ የፀሎት ጉልበት አንዱ ትልቁ መተማመኛ ኃይል ነው፡፡ ጠላት ፀሎቶቻችሁ ደካሞችና የማይረቡ ናቸው በማለት ይዋሹአችኋል፡፡ ነገር ግን እኔ ኃይል እንዳላችሁ እነግራችኋለሁ፡፡ ለዚህ ነው አገራችሁን መልሶ ለመገንባት ኸርትዴዌለርስ አንዱ የእቅዴ ክፍል የሆናችሁት፡፡

ስለ ኑክላርና ስለ ስነ-ህይወት ጦርነት/ Biological war/ መምጣት ብዙ ትንቢቶችና አመልካች ነገሮች ነበሩ፡፡ ይህም በአገራችሁ የተዋወቀውና በፀጥታ የሚገድለውን የጂ5(G5) ቴክኖሎጂ ሳይጨምር ማለት ነው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ እጅግ አደገኛ ቴክኖሎጂ ስለሆነ ተነስታችሁ መቃወም አለባችሁ፡፡ ይህም እጅግ በረቀቀ ቴክኖሎጂ በአፋጣኝ ከሚገድል በሽታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ህዝቤ እነዚህን ግንቦች በፍፁም ቸል ልትሉ አይገባም፡፡

እኔ ግን አሁን ልነግራችሁ የምፈልገው ፀሎታችሁ ህብረተሰባችሁን ለማጥፋት የታቀደውን እንዳከሸፈ ነው፡፡ በጠቅላላው በትርምሱ ፊት፣ በበሽታና በጥፋት ፊት መንገዱ ላይ በመቆም የከለከላችሁት እናንተ ናችሁ፡፡ ትንቢቱ ትክክል ነበር፡፡ ሰዎች ግን ያልገባቸው ፀሎት ያንን ሁሉ እንደከለከለው ነው፡፡ እናም የግል ፀሎታችሁ ክፉን ምንም አላቆመም የሚለውን የጠላት ውሸት ካልሰማችሁ በስተቀር ፀሎታችሁ አሁንም ክፉን ማቆሙን ይቀጥላል፡፡ ሰይጣን እንድታምኑ የሚፈልገው ይህንን ነው፡፡ ምክንያቱም የፀሎትን ኃይል መውሰድ አይችልም፡፡ ነገር ግን ለመፀለይ ያላችሁን ፈቃድ አሳምኖ መለወጥ ይችላል፡፡ በዚህም የውሸቶችን ተኩስ በመክፈት ፀሎታችሁ ያልተሰማው በሰራችሁት ስህተት ነው ብሎ ክስ በማቅረብ ተስፋ ሊያስቆርጣችሁ ይችላል፡፡

ከአንቺ ጋር በተለያየ ደረጃ እሰራለሁ፡፡ በግል ደረጃ በቅድስና ላይ ያለሽ አመለካከት ኮስታራ ስለሆነ በኃጢያትሽና በስህተትሽ ላይ እሰራለሁ፡፡ ጆሮዬን ለፀሎቶችሽ አልከለከልም፡፡ በአንፃሩ ግን በእርምት ጊዜና ወቅት ሆነሽ እንኳን ፀሎቶችሽ ከፍ ብለውና ግልፅ ሆነው ይሰሙኛል፡፡ መፆም ባለመቻልሽ ፀሎቶችሽ ዋጋ የላቸውም የሚለውን የጠላት ውሸት አትስሚ፡፡ ወይም መጥፎ ሐሳብ አስበሽ ስለነበር ፀሎቴ አይሰማም እንዳትዪ፡፡ በምድርና በሰማይ ያሉትን የቅዱሳን ፀሎት ማክበሬ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን የተሰበሩትንና የሚታገሉትንም ፀሎት እሰማለሁ፡፡

በወንጌሉ መሰረት ለመኖር ባላቸው ኃይል ሁሉ ወንድሞቻቸውን ለመውደድ፣ በደግነት የሚሰጡትንና ይቅርታ የሚያደርጉትን፣ ጊዜያቸውን ከእኔ ጋር ለማሳለፍ ስርዓት ለማበጀት የሚጥሩትን እነዚህን ነፍሶች በጉልህና በግልፅ እሰማቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም የእኔ መንግስት እንዲመጣ ብዙ ጥረዋልና ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ኃጢያታቸውን በቅንነት ለሚናዘዙ ኃጢያተኞች ጆሮዬን አልዘጋም፡፡ ስለዚህም ለማናችሁም ቢሆን ፀሎትን ማቆምና ለአገራችሁ ጥረት ላለማድረግ ምንም ሰበብ የላችሁም፡፡ ፀሎታችሁን እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም የአባቴ ክንድ የሚንቀሳቀሰው በእናንተ ፀሎት ነው፡፡

አንፃራዊ በሆነ ሰላም ይህ ህይወታችሁ እንዲቀጥል የምትፈልጉ ከሆነ መፀለይ አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም ብዙ የሰይጣን ማህበሮች ለሰይጣን እየፀለዩና ለእርሱ እየኖሩ ስለሆነ የፍትህ ሚዛኑ ወደ ጠላት እያጋደለ ነው፡፡ ፀሎታቸው ደግሞ ለአሜሪካ ሞት፣ ጥፋት፣ ሐዘንና መውደቅን የሚጨምር ነው፡፡ የኔ አካል ተነሱና ጩሁ፡፡ እናንተ እንዳይሳካላችሁ የታወጁ ትንቢቶች

ማክሸፍ አለባችሁ፡፡ አሁን ልታቆሟቸው ትችላላችሁ፡፡ የምጠይቃችሁ አንድ ነገር አባቴ ተጨማሪ ጊዜ፣ ተጨማሪ ፀጋና ተጨማሪ ምህረት እዲሰጣችሁ በሙሉ ልባችሁ እንድትፀልዩ ነው፡፡

ሥጋና ደሜን ስትቀበሉ ደግሞ ጌታ ሆይ በቅንነትና በፍቅር መፀለይ የምችልበት ልብ ስጠኝ ብላችሁ ወደ እኔ ጩሁ፡፡ ይህም ከጠየቃችሁ ብቻ የሚለቀቅላችሁ ፀጋ እየጠበቃችሁ ነው፡፡

## ወደ ልቤ እንድትቀርቡ ያዘጋጀሁትን እቅድ ማበላሸት - ኦገስት 14 ቀን 2020 ዓ.ም.
## How you frustrate my plan, August 14th, 2020

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች የጌታ የኢየሱስ ባርኮትና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡

በመንደራችን ውስጥ አዲስ አባላትን በተቀበልን ቁጥር ስለ ራሳችን ብዙ ነገር እየተማርን ነው፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ እኛ ሁላችንም ተመሳሳይ የሆነ ስህተት ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የራሳችንን ስህተት በሌሎች ላይ ካላየነው ስህተታችንን ልንረዳ አንችልም፡፡

እኔ በዚህ የተከበብኩት ቃል በቃል ማለት እችላለሁ ከእኔ እጅግ የበለጠ ችሎታ ባላቸው ነፍሶች ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ጌታ ከእኔ ጋር በመሆን ሊመራቸው ጠየቀኝ፡፡ ጌታ ራሱ ካልገለጠልኝ በስተቀር አንዳንድ ስህተቶችን አላያቸውም እንዳውም ብዙ ጊዜ አልረዳቸውም፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታ እያስተማረን ያለው ስለ ኩራት፣ ስለስንፍና እና በራሱ ሐሳብ ስለሚመራ መንፈስ ነው፡፡

በአሁን ጊዜ ከአለብን ሥራዎች እጅግ አስፈላጊው ሥራ ኩራትን ማስወገድ ወይም ኩራትን ለማስወገድ ራስን ቃል በማስገባት ላይ ነው፡፡ ከትህትና ውጪ የትኛውም ስጦታ ሊቆይ ወይም ሊቀጥል አይችልም፡፡ ከእውነተኛ ትህትና ውጪ ደግሞ ቅድስና የለም፡፡ አንድ ሰው ትሁት ለመሆን ቢያስመስልም ውሎ አድሮ ግን አንዳንድ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ከሥር የተደበቀው ኩራት ይወጣል፡፡

ጌታ ሁሉንም ስህተቶችና ድክመቶች ሲያጠራቸው የሚረብሽና እጅግ ከባድ ስለሆነ እርስ በርሳችን መዋደድ አለብን፡፡ በዚህ መንደር ያለ ነፍስ ሁሉ መልካም ልብ ያለው ነው፡፡ ደግሞም እያንዳንዱ ነፍስ ጌታን ደስ ለማሰኘት የሚፈልግ ነው፡፡ ፍሬ ነገሩ ጌታ አንዳችንን በአንዳችን በኩል ሲያስተምረን በየቀኑ የተሻልን ለመሆን ራሳችንን ማስገዛታችን ነው፡፡

ሁላችንም ወደዚህ ስንመጣ በራሳችን ሐሳብ የመመራት መንፈስን ይዘን ነው የመጣነው፡፡ ምክንያቱም በአለም እያለን ህይወታችንን ለማቆየት የለመድነው የራሳችንን ውሳኔ እየወሰንን መኖርን ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ማህበረሰብን ለመቀላቀል ስንፈልግ የራሳችንን አስተሳሰብ ውጪውን ቀይረን ነው የምንቀላቀለው፡፡ ይኸውም የሚሆነው ራሳችንን ከማህበረሰቡ ጋር ማስማማት ስለምንፈልግ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን እግዚአብሔር በሾመው በነፍስ ዳደኛ ካልተመራን በስተቀር በራሳችን መመራቱን እንቀጥልበታለን፡፡ ለሰይጣን እጅግ ከባዱ ነገር መታዘዝ ነው፡፡ ትህትናን ማስመሰል ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር እንዲሰራ ብትነግሩት የሚሰራው እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነው፡፡

ይህ በጥልቀት ሥር የሰደደ የኩራት ምልክት ነው፡፡ እኛ ሁላችንም ሰይጣን ከእግዚአብሔር መንግስት እንደወደቀ እናውቃለን፡፡ እርሱ የእግዚአብሔርን ስጦታ የሚፈልገው እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ ራሱ እንዲመለክ ስለሚፈልግ ነው፡፡ ሰይጣን እግዚአብሔርን ለመከተል እንቢ ያለና የራሱን መንገድ የመረጠ ነው፡፡ ከእኛም ውስጥ ከተሰጠን መመሪያ ይልቅ በሌላ መንገድ ለመስራት የምናስበው ከኩራት የተነሳ ነው ፡፡ የዚህም መሰረቱ የትኛው እጅግ ጥሩ እንደሆነ እኔ አውቃለሁ፣ በእኔ መንገድ የምሰራው የተሻለ ስለሆነ በእኔ መንገድ ነው የምሰራው የሚለውን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ለእኔ ጥሩ የምለው ነገር አዲስ ነፍሶች ሥሩ በተባሉት መንገድ ለመስራት ፈቃደኞች ሲሆኑ ነው፡፡ ይህ ለእነሱ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ ጌታ "በራሳቸው አይን አዋቂ ነን ለሚሉ ወዮላቸው፡፡" ይላል፡፡ ጌታ ይህንን የንባብ ክፍል ሲሰጠኝ እሸማቀቃለሁ፡፡

በእኔ ውስጥ 'እኔ የበለጠ አውቃለሁ' የሚለውን አመለካከት ሳስበው የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኛል፡፡ ለምሳሌ ይህንን መልዕክት እየፃፍኩ እያለሁ ጠማኝና የሚጠጣ ፍለጋ እየሄድኩ እያለሁ ጌታ "አሎዩ ጠጪ" ሲለኝ ሰማሁት፡፡ ነገር ግን ፊሪጁጋ ስደርስ እንዲህ ብዬ አሰብኩ 'ምናልባት ጭማቂ ወይም የቫታሚን መጠጤን ብጠጣ ይሻለኛል' በማለት አነሳሁትና መጠጣት ጀመርኩ፡፡ ልክ መጠጣት ስጀምር መንፈስ ቅዱስ "አሎዮ ጠጪ አልነበረም ያለሽ?" እያለ ሲጎነትለኝ ተሰማኝ፡፡

የሚደንቅ ነው! አዎ ጌታ እንደርሱ ነበር ያለው፡፡ ነገር ግን እርሱ ያለውን ትቼ እኔ የበለጠ ነው ያልኩትን አደረግሁ፡፡ ይህ በእኔ ውስጥ የሚገኝ መርዝ የሆነ ልማድ ነው፡፡ ይህ ጋብቻዬንም ለማስተካከል በሚደረገው ሥራ ላይ ለጌታና ለባለቤቴ የነበረኝ ክብር እንዴት ትንሽ እንደነበረ፣ እነርሱ ያሉኝን ላለማድረግ ለእኔ ምን ያህል ቀላል እንደነበረና የእነርሱን ሐሳብ በመሻር የራሴን ሐሳብ ብቻ እንዴት አደርግ እንደነበረ አሁን ነው የተገነዘብኩት፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህንን መመልከት እጅግ የሚረብሽ ነው፡፡ በአካባቢዬ የነበሩትን ሰዎች እንደ እኔ እንዲሆኑ ምክንያት እንደነበርኩ ለማየት ችያለሁ፡፡ ውድ አምላኬ ሆይ ይቅር በለኝ፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . ."ክሌር ይህ የአንቺ የህይወትሽ መንገድ ነበር፡፡ በእውነቱ ከሆነ ምን ያህል የሚበክል እንደሆነ ምንም አልተገነዘብሽም ነበር፡፡ ከሁሉም የማህበረሰብ ነፍሶች ውስጥ የሚብሰው ደግሞ የአንቺ ነው፡፡ ይህንን አሁን በማየትሽ እጅግ ደስተኛ ነኝ፡፡ በመንደሩ ውስጥ የሚገኘውን ይህንን አመለካከት ለመቀየር ብዙም ለመስራት አልቻልም ነበር፡፡ ምክንያቱም በእነርሱ ውስጥ ለመስራት በመጀመሪያ ከአንቺ መጀመር አለበት፡፡ የተወደድሽ ሆይ ሌሎች ፍሬ እንዲያፈሩ ብዙ እርምጃዎችን ተራምደሻል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስህተትም ፈፅመሻል፡፡ ነገር ግን አሁንም ይህ የአንቺ ተፈጥሮ ትልቅ ችግር ነው፡፡ ዝንባሌሽ ሳታውቂው እንኳን አንቺ ደስ የሚልሽን መስራት ነው፡፡ ለዚህ ነው በሙዚቃ በኩል ምንም መስራት ያልቻልሽው፡፡ ጊዜሽ ሙዚቃ ይምትጫወችበት ወይም የምትዘምሪበት ጊዜ ሲሆን ሁልጊዜ ቅድሚያ የምትሰጪው ሌላ ሥራ ይኖርሻል፡፡ የቱን ማስቀደም እንዳለብሽ የሰጠሁሽን የኔን መመሪያ አትከተይም፡፡ መሰረታዊ ችግሩ እዚህ ላይ ነው፡፡

"ይህንን ስህተትሽን በግልፅ ማየት እንድትችዪ የሌላን ነፍስ ስህተት በፊትሽ ማምጣት ነበረብኝ፡፡ የህይወትሽ ትግል ይህ ነው፡፡ ይህንን ካላሸነፍሽ ደግሞ በሙሉ ችሎታሽ ለመስራት የምትችይበት ቦታ ላይ አትደርሽም፡፡ ስለዚህም አንዳንድ የሰጠሁሽ ስጦታዎችም ሳይንቀሳቀሱ ይቀራሉ፡፡ ፍሬ ማፍራት የሚጠበቅባቸውን ያህል ሳያፈሩ ይቀራሉ፡፡ የሌላ ነፍስ ሁኔታ ለአንቺ መስተዋት ነው፡፡ ያንን ነፍስ በአንቺ ቦታ አድርጊና አንቺን ደግሞ በእኔ ቦታ ተክተሽ እነዚያን ሁኔታዎች

ተመልከቻቸው፡፡ አንቺ እስካሁን በጥቂቱ ያልተገራሽ ፈረስ ነሽ፡፡ እስካሁን ድረስ ተሰብረሽ የጌታን ጋሪ ለመሳብ አልበቃሽም፡፡ ሙዚቀኛ ለመሆን የተጠራሽበትን ጥሪ እንዳትሆኚ የከለከለሽ ይህ በአንቺ ውስጥ በጥልቀት የተቀመጠው ስህተት ነው፡፡ ክሌር አንቺ የመጨረሻ የራስሽ ጠላት ነሽ፡፡

"በአሁን ጊዜ አንቺ ነፃ ጊዜ እንዲኖርሽ የሚረዳሽን መዋቅር አዘጋጅቻለሁ፡፡ ነገር ግን በግል የምታደርጊው ስህተት እንደቀጠለ ነው፡፡ ውዴ አሁን መለወጥ ያለብሽ ጊዜ ነው፡፡ አሁን ጊዜው ነው፡፡ ክሌር እባክሽ ተለወጪ፣ እባክሽ ተለወጪ፡፡ በጣም ነው የምወድሽ ከዚህም የተነሳ በአንድ ክብ ውስጥ መልሰሽ መላልሰሽ ስትሽከረከሪ ማየት በጣም ነው የሚያመው፡፡ ውዴ አሁን እርዳታ ላደርግልሽ ነው፡፡ ማንነቴን ለአንቺ በመዘርጋት  በአንቺ ውስጥ ልኖርና ህልማችንን በአንቺ ልፈፅም ነው፡፡ የአንቺ ድርሻ ይህንን የሽንፈት አመለካከትሽን በመረዳት ክቡን ሰብረሽ በሚያንፀባርቅ ታዛዥነት ወደፊት መውጣት ነው፡፡ እባክሽ ይህንን አድርጊ፡፡"

(ክሌር)፡- ኢየሱስ በሙሉ ልቤ አደርገዋለሁ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ለመለወጥ እፈልጋለሁ፡፡ ጌታ እባክህ እርዳኝ፡፡ የአንተ ጥንካሬ እጅግ ያስፈልገኛል፡፡ በቀን ውስጥ ብዙ የሚያቋርጡ ጉዳዮች፣ እንዲሁም  የሚጎበኙን ሰዎች ይመጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወደ ጎን እንዴት ማድረግ  እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከመንገዴ ውጪ የተጣልኩ ይመስለኛል፡፡ እነዚህ ነገሮችን እየፈፀምኩ በአንድ ላይ ሙዚቃውን እንዴት እንደማስኬደው አላውቀም፡፡

"የኔ ውድ የእኔን እርዳታ እየላኩልሽ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ለሁሉ ነገር የሚፈልገው በግድ አንቺን ብቻ መሆን እንደሌለበት እስኪለምደው ድረስ ጊዜ ይፈጃል፡፡ ነገር ግን በዚህ ድጋፍና በእኔ እርዳታ ልትፈፅሚው ትችያለሽ፡፡ ማድረግ ትችያለሽ፡፡ ይህ ሊሰራ የሚችል ነገር ነው፡፡ አንቺ ብቻ መማር የሚያስፈልግሽ ውክልና ማብዛትንና መልዕክቶችሽን እንደጨረስሽ ወዲያው ወደ ሙዚቃሽ ለመሄድ ልዩ ትኩረት መስጠት ነው፡፡ ምክንያቱም ወደ ሙዚቃ እንድትገቢ የምፈልገው በዚያን ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ይህንን በአንተ እርዳታ አደርገዋለሁ፡፡

"የኔ ውድ ኸርትድዌለርስ ይህ ልቤን የሰበረኝ ነገር ነው፡፡ ደግሞም መሰበር ያለበት ነው፡፡ ይኸውላችሁ አሥር ጊዜ እጥፍ ከእነርሱ የባሰ ስህተት እያለብኝ የእነርሱን ስህተት ለማስተካከል እየሞከርኩ ነው፡፡ የእኔ ስህተት ደግሞ ከእነርሱ ስህተት ይልቅ በማህበረሰቡ ውስጥ የላቀ አሉታዊ ውጤትን የሚያመጣ ነው፡፡ እንዴት አፈርኩ መሰላችሁ? አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ አንድ ኃጢያት እየሰራ ያለን መነኩሴ እንዲያስተካከል እንደተጠራው ማለት ነው፡፡ ወደዚህ ሽማግሌ ወንድሞች መጥተው አንድን ሰው እንዲያስተካክል ጠየቁት፡፡ እርሱም በጀርባ የሚይዘውን ቦርሳውን በአሸዋ ሞልቶ ከታቹ ትንሽ ቀዳዳ በማድረግ ተሸከመና ከጠየቁት ወንድሞች ጋር ኃጢያት ሰራ የተባለውን መነኩሴ ለማግኘት መጓዝ ጀመረ፡፡ እነርሱም ከተሸከመው ቦርሳ ውስጥ አሸዋው ወደ መሬት እየፈሰሰ እንዳለ ተረዱ፡፡ እናም እነዚህ ወንድሞች ነገሩ ምንድነው ብለው ሲጠይቁት "እኔ አንድ ኃጢያት የሰራን ወንድም ለማስተካከል ስሄድ የእኔ ኃጢያት ደግሞ ፈስሶ መሬቱን ሁሉ እያዳረሰው ነው" አላቸው፡፡

እኔ ከአሁን ወዲያ ማድረግ ያለብኝ ጌታ አንድ ነገር እንድሰራ ሐሳብ ያቀረበልኝ መስሎ ከተሰማኝ፣ እኔ ያቀድኩትን ትቼ ምንም ሳላንገራግር፣ ጥያቄና የኔን ምክንያት ሳላቀርብ አድርጊ የተባልኩትን ወዲያው መፈፀም ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ለፀሎትም ጊዜ ነው፡፡ ህዝቄኤል ለምድሪቷ እንድንማልድ ጥያቄ ሲያቀርብ ምንም እየሰራሁ ይሁን ያንን ጥያቄ በሙሉ ልቤ መቀበልና የያዝኩትን ወዲያው በማቆም መፀለይ አለብኝ፡፡ ይህም የምሰራውን ስላቋረጥኩ በመቁነጥነጥ ሳይሆን በመልካም የውስጥ ስሜት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንንም በእኔ ውስጥ የሚፈፅመው የእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ ነው፡፡

ሰዎች በሌላው ቀን የሆነው ጌታ "ከቻይና ጋር ጦርነት ሊመጣ ነውና ፀልዩ" ባለን ጊዜ ህዝቄኤል ለፀሎት ሲጠራን የሆነው ይህ ነበር፡፡ አንድ ሰው በስልክ ደውሎ ከቻይና ጋር አንድ የሆነ ነገር እንደሆነና ፕሬዚዳንታችንም ያለው በዋይት ሃውስ ሳይሆን በሌላ ሚስጥራዊ ቦታ እንደሆነ ነገረን፡፡ ቻይና ደግሞ ህዝቡ ለጦርነት እንዲዘጋጅ በግልፅ ትዕዛዝ እየሰጠች ነው አለን፡፡ ይህ በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ማይክ ፍሮም አራውንድ ዘ ወርልድ /Mike from around the world/ አስተላልፎ የነበረውን አንድ መልዕክት እንደነገርናችሁ ታስታውሳላችሁ፡፡ መልዕክቱም "ሶስት ሚሳሎች የምስራቁን ክፍል (የአሜሪካን ይመስለኛል) ሲመታ በራዕይ አየሁ፡፡ የተወረወሩት ብዙ ሚሳይሎች ሲሆኑ ነገር ግን የምስራቁን ክፍል የመታው ሦስት ሚሳዪሎች ብቻ ናቸው" ብሎ ነበር፡፡ ይህም የሚፈፀመው "የጓደኛው እናት ከሞቱ ከአጭር ጊዜ በኋላ" እንደነበረ ተናግሮ ነበር፡፡ ይህንንም ትንቢት የተናገረው ከአሥር አመት በፊት ነበር፡፡ ያ ሰውም በቅርብ ስልክ ተደውሎለት የጓደኛው እናት እንደሞቱና የሞቱትም ልክ ማይክ በራዕይ እንዳየው እንደነበረ ተናግሯል፡፡ ህዝቄኤል ደግሞ በዚህ ወቅት እጅግ ከባድ ስቃይ ላይ ነበር፡፡ ጌታ በተደጋጋሚ ለመፅናናት እየጠራን ነበር፡፡ ጌታ አሁንም ልቡ እንደከበደ ነው፡፡ ስለዚህ ህዝቄኤል መፀለይ አለብን ሲለን እኔ ደግሞ ለማህበረሰቡ ቃሉን ማስተላለፍ ነበረበረን፡፡ ምንም እየሰራችሁ ቢሆን ማድረግ ያለብን የያዝነውን ነገር እርግፍ አድርገን በሙተው ወደ ፀሎት መግባት ነበር፡፡ ይህ በጣም ከባድ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ከባድ ነው፡፡ ከቻይና ጋር ያለው ነገር እንዴት የሚያሰጋ እንደሆነ የተረዳሁት ዛሬ ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ."ይህ በአንቺ ውስጥ እንዳለ አሁን አይተሻል፡፡ ስለዚህም ሌሎችን ለመርዳት አብረን መስራት እንችላለን፡፡ የኔ ውድ ኸርትድዌለርስ፣ ከሌላው ፈቃድ ይልቅ የራሳችሁን ፈቃድ ስትመርጡ መንፈሳዊ መሰረታችሁ ምን ያህል እንደሚናጋ ልታውቁ አትችሉም፡፡ ከሁሉም ነገር ለማቋረጥ የሚከብደው ልማድ የራስን ፈቃድ ለመተው የሚደረገው ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ደግሞ የቅድስናን መንሰላል መውጣት ከፈለገ የራሱን ፈቃድ ገና ከጅምሩ መተው አለበት፡፡

"የምትፈልጉት ነገር ላይ ስትጣበቁ ወደ ልቤ ለማቅረብ ያሰብኩትን እቅዴን ታበላሻላችሁ፡፡ ለሌሎች እጅ መስጠት ወይም መረታት ለቅድስና አንዱና የመጀመሪያው ነው፡፡ ስንፍና እና ኩራት ደግሞ የራስን ፈቃድ ለመፈፀም የሚያነሳሱ ሁለት ተለዋዋጭ ባህርያት ናቸው፡፡ አንዳንዶች አንድ ነገር እንዲያደርጉ ሲጠየቁና የተጠየቁት ነገር ብዙ ሥራ የሚያስከትልባቸው ከሆነ ይህንን ለማምለጥ ሲሉ ዳር ዳሩን በማለት፣ ለራሳቸው ምክንያትን በመስጠት፣ በመሸሽና ጥያቄውን በማደበላለቅ የሚያስከትለውን ዋጋ በማድበስበስ ለማለፍ ይሞክራሉ፡፡ በዚህም መስራት የማይፈልጉትን ነገር ትክክል እንደሆነ የማሳመኛ ነጥብ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ እኔን አያስደስተኝም፡፡ ይህ ደግሞ የዕድሜ ልክ የስንፍና ልማድ በመሆን በአካባቢያችሁ ያሉትን በመውረር አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት እጅግ አስፈላጊ ቦታ የተቀመጠ ግለሰብ ይህንን አመለካከት የሚያራምድ ከሆነ እኔ ወደፊት እንዲሄድ በጠራሁት ልክ ነገሮች ወደፊት ሊሄዱ አይችሉም፡፡ እንዲሁም ይህ ነገር ወደ ሌሎች ሰዎች ወዲያው የሚጋባ ስለሆነ እንደ ቫይረስ በሁሉ ላይ ይራባል፡፡

ሌላው ደግሞ ኩራት ሲሆን ይህ ደግሞ ምላሽ የሚያገኘው ትሁት እና ታዛዥ በመሆን ነው፡፡ ለዚህ ብዙ ሥራ ሊጠበቅባችሁ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ወደ መልካም ባህርይና ወደ ቅድስና የሚወስድ መንሰላል ስለሆነ የራስን ፈቃድ ወይም ፍላጎት በመሬት ላይ ካልጣሉ የሚገኝ አይደለም፡፡ ወደ ቅድስና ህይወት ከፍ የሚሉ ነፍሶች የራሳቸውን ፈቃድ ትተው ታዛዥ እና ትሁት በመሆን የሚኖሩና ፈቃዳቸውን ደግመውም ከጣሉበት የማያነሱ ናቸው፡፡ አንዳንዶቻችሁ በታላቅ ቅድስና ለመመላለስ በውስጣችሁ ችሎታ ያላችሁ ናችሁ፡፡ ነገር ግን በራሳችሁ ምንም እንዳልሆናችሁና ተሰባሪ ሸክላ እንደሆናችሁ በደንብ ካልገባችሁ በስተቀር እዛ ደረጃ በፍፁም ልትደርሱ አትችሉም፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ስለ ራሳችሁ እውነቱ በደንብ ሲገባችሁ፣ ጭቃ እንደሆናችሁና እኔ ደግሞ ወሰጄ የክብር ዕቃ አድርጌ እንደምሰራችሁ በማወቅ ለትንሿ ነገር እንኳን ለእኔ ክብር ስትሰጡ ነው፡፡

እንደዚህ ከሆነ የተወደዳችሁ ነፍሶች ሆይ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ይህንን መንገድ ከመረጣችሁ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ማድረግ ያለባችሁ ፀጋ እንዲለቀቅላችሁ መጠየቅ ብቻ ነው፡፡ እኔም እረዳችኋለሁ፡፡ ለዚህ ደግሞ በምድር ላይ የተሰጣችሁን ተልዕኮ ለመጨረስ እንዳትችሉ የሚያደርጋችሁን አደጋ መረዳት ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም አሁን ትሁት ለመሆን፣ ለመታዘዝ፣ እንዲሁም ነገሮችን ለመረዳት የተራበ ልብ እንዲኖራችሁ ባረኳችሁ፡፡

## ጥፋት እየመጣ ስለሆነ ጩኹ ንስሐም ግቡ!!! - ሰፕቴምበር 12 ቀን 2020 ዓ.ም
## Cry out Devastation is coming, September 12th, 2020

የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ በአሜሪካና በአለም ላይ እየመጣ ያለው ስቃይ እጅግ ከባድ ስለሆነ ጌታ ልባችሁን ያዘጋጅ፡፡ ዛሬ ጠዋቱን ሙሉ ስሰማው ያረፈድኩት የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ በሙሉ ድምፃችሁ አሰሙ፣ በመካከላችሁ የሚገኘውን ኃጢያት ሃቁን አትደብቁ፣ በሰዎች ስለሚደረገው ኃጢያት በግልፅ ተናገሩ !!! የሚለውን መዝሙር ነበር፡፡

በጌታ ፊት ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ተቀምጬ እያለሁ ትልቅ ጥቅልል ጥቁር ደመና፣ ወደ ውስጥ እየጠረገና ብዙ ቦታዎችን እየሸፈነ ከሰሜን ክፍል ሲመጣ አየሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "ከባድ ጊዜ እየመጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝቤ እስካሁን ጣኦት ከሆነበት ከተደላቀቀና ግዴለሽ ከሆነ የአኗኗር ዘይቤው ንስሐ አልገባም፡፡ ይህንን የአኗኗር ዘይቤ በቀላሉ የሜሪካኖች ጣዖተ አምልኮ ማለት ይቻላል፡፡ የሚማሩትም ጣዖት የሆነባቸውን ይህንን የአኗኗር ዘይቤ ለማግኘት ነው፡፡

"እያልኩ ያለሁት ከስግብግብነት፣ ከንፉግነት፣ ከማህበራዊ ሁኔታና ከፍትህ አልባነት የመነጨና በእውነት ላይ ያልተመረኮዘ የአኗኗር ዘይቤ በአመለካከቱ ላይ ተቀምጧል፡፡ ፕሬዜዳንታችሁ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እጅግ እየለፉ እያለ ዛፎቹን ብቻ በመመልከት ጫካውን ረስቷል፡፡ ይኸውም እድሜውን ሙሉ ስለ ህይወት የእሴት ደንብ ያለው ግንዛቤ በቢዝነስ ስኬታማ መሆን እና የተንደላቀቀ የአኗኗር ዘይቤ መከተል በሚለው ላይ ነው፡፡

"አንዳንድ የሞራል ልኮች ቢኖሩትም በማመቻመች ብዙ ነገሮችን አጥቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ ህሊናው በትክክለ አልተቀረፀም፡፡ ኃብት ስላካበቱ ብቻ መልካም ኑሮ አይኖርም፡፡ እንዳውም ብዙ ጊዜ መልካም ኑሮ የሚኖሩት ያላቸው ሳይሆኑ ድሆቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ህሊናቸው የሚከሳቸው ምንም ነገር ስለሌለ ነው፡፡ ሃብታሞቹ ግን ሌሊት በመነሳት ኃብታቸውን እንዴት አድርገው እንደሚያከማቹ ሲያቅዱ እንቅልፍ በማጣት ያድራሉ፡፡ ነገር ግን አንዳንደ ኃብታሞች ትክክለኛው የህይወት የእሴት ደንብ አላቸው፡፡

(ክሌር):- የተወደዳችሁ ኸርት ዱዌለርስ እዚህጋ እንድታውቁት የምፈልገው አንድ ነገር በምንም አይነት መልኩ ፕሬዚዳንት ዶላንድ ትራንፐ ካለን አመለካከት እንድንቀንስበት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እላይ ከተጠቀሰው፣ ነገር ግን ለእርሱ ከተሸፈነበት ከዚህ ነገር ውጪ ድንቅ ሰውና ለአገራችን ትክክለኛ ራዕይ ያለው ሰው ሲሆን ይህንን አገር ከብዙ ጥልቅ ችግሮች እያወጣ ያለ እጅግ ትልቅ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ለአገራችን ትልቅ ግርዘት ሊሆን ነው፡፡ ይህም ፕሬዚዳንታችንን የሚመለከት ሳይሆን ኃላፊነት ያለብንን እኛን በግል የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ሰው መልካም እንደሆነና ድንቅ ሥራ እየሰራ እንደሆነ፣ ነገር ግን ለእርሱ ያልታየው አንድ ነጥብ እንዳለ ይህንን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

ጌታ እየተናገረ ወዳለው እንመለስ፡፡ ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . " መልካም የሆኑት የዚህ አገር ባለፀጎች የተሰጣቸውን ለአለም የማካፈል ኃላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤው አላቸው፡፡ አዎን ያልኩት በትክክል "የተሰጣቸውን" ነው፡፡ አንዳንዶች ሰርተን ያገኘነው ነው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ለሌሎች ያልተሰጠ አጋጣሚና ተሰጥዎ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህም ለእነርሱ የማሰብ ችሎታ፣ ዕድልና የገቢ ምንጭ በማቅረብ እንዴት መልካም እንደሆንኩ ይገነዘቡ ይሆናል በማለት እየጠበኩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ለመረዳትና የገሃነም ቅጣት በራሳቸውና በዘራቸው ላይ ሳይመጣ ስጦታዎቹን ለመጠቀም ትልቅ የሞራልና የባህርይ ፅናት ይፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር አንዳንዶች ኃብታቸውን ለመንግስቱ የሚያውሉ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ለጥፋታቸው እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ዝም ብለው የሚያካብቱ አሉ፡፡

"ሃብታም መሆን ትልቅ ታማኝነትን ይጠይቃል፡፡ ኃብትን በአግባቡ መጠቀም ፀጋ ነው፡፡ ማንም ሰው ሰርቶ ገንዘብ ማግኘትና ያሰበውን እየገዛ ሊያጠፋ ይችላል፡፡ ነገር ግን የቅርብ ጎረቤቱን ወይም ራቅ ያለ ቦታ የሚኖርን ሰው ለመርዳት እጅግ ሃቀኛ መሆንን ይጠይቃል፡፡ በሌላ አባባል የማያውቃቸውንና ከእነርሱ ምንም የሚጠብቀው ነገር ሳይኖረው የሚያደርገውን ማለት ነው፡፡ የተወደዳችሁ ጌታ የሚናገረው ስለ እነዚህ ነው፡፡

"ሰውን ማዕከል ያደረገው የአለም አስተሳሰብ /Secular Humanism/ የሰይጣን ፍልስፍና ሌላው ስሙ ሲሆን የአለም የሞራል ደንብ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም እናንተ ገንዘብ ለማካበት ስትሯሯጡ የዲያቢሎስ ወኪሎች የራሳቸውን የህይወት ዘይቤ አሾልከው በማስገባት የሰውን ልጅ መርዳት በሚል የውሸት ሽፋን የክርስቲያኑን የህይወት ዘይቤ እንዲተካ አድርገዋል፡፡ የሰይጣን ቤተክርስቲያንን መሰረታዊ የእምነት መመሪያ ስትመለከቱ ሰውን ማዕከል ካደረገው የአለም አስተሳሰብ /Secular Humanism/ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይና ግንኙነት ያለው ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ አሁን በመሪነት፣ ወይንም ገና ወደ መሪነት እየመጡ ላሉ መሪዎች ዘመናዊው የእሴት ደንብ ሆኗል፡፡ ይህ አልገባችሁም? እነዚህ ሰዎች አለምን ለመግዛት ከሌሎች እጅ መውሰዳቸውን መልካም እንዳደረጉ አድርገው ነው የሚያምኑት፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን የሚመለከቱት እንደ አዳኝ አድርገው ነው፡፡ ይኸውም እነርሱ የተወለዱት የፍጥረትን ህግጋትና ጤናማውን ህሊና በመቆጣጠርና በማንቀሳቀስ እንዲሁም ግዙፍና አስቀያሚ ፍጥረታትን በላቦራቶሪ በመፍጠር አለምን ማስተካከል ነው፡፡ በተጓዳኝ ደግሞ የክርስቲያኖችን

እውነት በማንቋሸሽ፣ የእነርሱን አስበልጦ ለሁሉም በማስተማርና አሹልኮ በማስገባት በህዝቡ ውስጥ ማስረፅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በውጪ ሲመለከቱት ምንም ችግር የሌለበት ይመስላል፡፡ እውነቱ ግን በውጪ ታጥቦ ነጭ የሚመስል ነገር ግን አለምንና በውስጧ ያለውን ለማጥፋት የተዘጋጀውን የሰይጣንን ሥራ ለመሸፈን የተደረገ ድርጊት ነው፡፡ በዚህ ላይ እኔ የምለው ነገር እነዚህ ሰዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ አያውቁትም ነው፡፡ በእውነት ለአለም መልካም እየሰሩ ይመስላቸዋል? በስህተት እየተመሩና እየተታለሉ እንደሆነ በፍፁም ማየት አልቻሉም፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . . እነርሱ የሚያምኑት ከሁሉ ዘር የበላይ እንደሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ውጪ አለምን ለማስተካከልና ለመቆጣጠር ልዩ መብት እንዳላቸው ነው፡፡ በእርግጥ ከሆነ እነርሱ ራሳቸውን የሚያዩት በምድር ላይ ለሚገኝ የሰው ዘር ሐሳብን ለማስፋፋት ኃላፊነት ያለባቸው አማልክት አድርገው ነው፡፡

"በአሜሪካ ያላችሁ ህዝቦቼ! አንዳንዶቻችሁ ባገኛችሁት ገንዘብ የሚያበረታታ ነገር አድርጋችኋል፡፡ ሌሎቻችሁ ግን ለሚያሳፈር፣ ለስስትና ሃብት ለማጋበስ ንግስናን በመስጠት የገሃነምን ህመም  ለራሳቸው አከማችተዋል፡፡ ክሌር እያልኩ ያለሁት ፕሬዚዳንታችሁ ህሊናው በትክክሉ መንገድ ያልተቀረፀ እጅግ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ በእርግጥ ነው የፕሬዚዳንትነቱን ቢሮ ከያዘ ጀምሮ እየተሻሻለ ይገኛል፡፡ ቢሆንም ግን አሁንም ፍትህን የሚያዛቡ ሁኔታዎች ምሽግ እንደያዙ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እርሱ የድሆች አባት ስላልሆነ ነው፡፡ አገራችሁ በሞራል ጉዳዮች ላይ ትልቅ ስጦታ ያለውን ሰው መርጣለች፡፡ ነገር ግን እውነተኛ የህይወት እሴቶችን በጠለቀ መልኩ እና እስካሁን በማያውቀው ሁኔታ መማር አለበት፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ከእርሱ ጋር ስለሆንኩ ይማራል፡፡ እርሱ ለስኬታማ አሜሪካዊ ሞዴል ለመሆን ተመራጭ ሰው ነው፡፡ ለዚህ ነው ለእርሱና ለአሜሪካ እውነተኛ ትህትና የሚያስፈልገው፡፡ እርሱ የአሜሪካን ህልም እየኖርን ነው ብለው ለሚሰማቸው ለብዙዎች የስኬት መስታወት ነው፡፡ ነገር ግን በቅርብ ሲነቁ ይህ የሚያስቡት የአሜሪካ ቅዠት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡

"በአለም ላይ ላላችሁት ህዝቤ ሁሉ በተለይም ደግሞ በአሜሪካ ላለችሁት የምመኘው ነገር እጅግ በተትረፈረፈ ኃብት ውስጥ ኖራችሁ ያላከፈላችሁ ንስሐ እንድትገቡና የማካፈል ህይወት ምን እንደሆነ እንድትማሩ ነው፡፡ ወላጆቻችሁ ራሳቸውን ብቻ እያገለገሉ በመኖራቸውና ይህንንም የህይወት ዘይቤ ለእናንተ እንደ ምሳሌ ስለተዉላችሁ መልካምና ክፉ የቱ እንደሆነ ተገለባብጦባችኋል፡፡ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የህይወት ጥሪያቸውን ይኸውም እኔን ማስቀደምና ለድሆች ማካፈልን ረስተዋል፡፡

"ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች እጅግ ብዙ ኃብትን ሲያግበሰብሱ በአንፃሩ ደግሞ በአለም ላይ ያሉ ድሆች ፍትህ በማጣት ወደ ሰማያት የጮኹትን ጩኸት እኔ የእናንተ አምላክ ሰምቼዋለሁ፡፡ በሰማያት ያለው የፍትህ ምክር ቤት የተጠራቀመውን አቤቱታና የተሰራውን መልካም ሥራ መዝኖ አይቷል፡፡ በዚህም አንፃር በአሜሪካ መሰረታዊ የሆነ ችግር ተገኝቷል፡፡ ይህም ከኢኮኖሚው ማንሰራራቱ ጋር ምንም የሚያያይዘው ነገር የለም፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ በአንድ በኩል በቢሮ ለመቆየት በማሰብ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ የሚያስችል መመሪያ አውጥቷል፡፡

"ነገር ግን እኔ አሁንም የማየው በዚህ አገር ያለውን ስግብግብነት፣ አሰቃቂ የሆነውን የአኗኗር ዘይቤ ለመኖር ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት፣ በአንፃሩ ደግሞ ድሆች በመበዝበዛቸው ወደ ሰማያት የጨኹትን ጩኸት ነው፡፡ ይህ ፕሬዜዳንት ብዙ መልካም ነገሮችን አከናውኗል፡፡ ነገር ግን ስለ ገንዘብ ያለው መሰረታዊ አመለካከት የተጣመመ ስለሆነ እኔ ስለ ገንዘብ ያለኝ ደረጃ

ከሚታየው የገንዘብ ደረጃ ጋር ተቃራኒ እንደሆነ መገንዘብ አይችልም፡፡ ይህንን ኃጢያት በአጠቃላይ ህዝቡም ሊገነዘበው አይችልም፡፡ ይህም ኃጢያት በዚህ አገር ላይ በተለይ መልኩ ለሚመጣው ቅጣት በር ከፋች ሆኗል፡፡

"አሜሪካ ተነሱ! ተነሱ! ፍርድ በእናንተ ላይ ሊሆን ደርሷል፡፡ ከአሁን ወዲያ በመካከላችሁና በአለም ያለውን የድሆችን ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት አትችሉም፡፡ ከአሁን ወዲያ በምድር ላይ ለራሳችሁ ብዙ ኃብት ልታጠራቅሙ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ከልባችሁ ምት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተቃጥሎ ያልቃልና ነው፡፡ የኔን ጥበቃ ከፈለጋችሁ በእኔ ደንብ መኖር ብቻ ሳይሆን ለአገራት አባት መሆን አለባችሁ፡፡ ይህም ፍትህንና እኩልነትን በማምጣት የድሆችን ብዝበዛ እንዲቆም ማድረግ አለባችሁ፡፡

"በተጨማሪም እነዚህ ነገሮች በአገራችሁ ህጋዊ መሆን የለባቸውም፡-

1. የዘር እህሎች በተፈጥሮ ተመልሰው መራባት የሚችሉበትን ከውስጣቸው በማጥፋት ከድሆች ላይ መስረቅን፡፡ እኔ ዘሮች ሁሉ በራሳቸው እንዲባዙና እንዲያድጉ አላደረኩምን? ታዲያ ለምንድነው ይህንን አስፈላጊ ስጦታ ከደሃው ላይ የሰረቃችሁት? በድሆች ላይ ካቅማቸው በላይ ህይወት እንዲከብድባቸው ለፈፀማችሁት ለዚህና ለሌሎች ወንጀሎች ሁሉ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡

2. ወንዶችና ሴቶችን አዋርዶ እንደ እንስሳት የሚያደርገውን የወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችንና ፊልሞችን /pornography/ በህግ መፈቀድ የለበትም ፡፡ ይህም ለአጋንንቶች ሥፍራን በመስጠት በሰው ልጆች ላይ ሊነገር የማይችል ጥፋትን የሚያመጣና በውስጣቸው በመኖር ትልቅ ወንጀልን እንዲፈፅሙ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ አሜሪካ! የወሲብ ድርጊቶችን በግላጭ ማየት/pornography/ የሚፈቅደው ይህ ህግ በአገራችሁ መፈቀድ የለበትም፡፡ ተነሱ! የኃጢያታችሁ ጩኸት ወደ ሰማያት ደርሶ የጥፋት መዶሻው ሊመታ ነው፡፡

3. ምንም የማያውቁ ህፃናትን በውርጃ/abortion/ እየጨረሳችሁ እንደሆነ በደንብ ታውቁታላችሁ፡፡ የዚህን ኃጢያት ውጤት ምን እንደሆነ ለማየት የኒውዮርክ ከተማን ማየት ብቻ ይበቃችኋል፡፡ ለዚህ ከተማ እኔ እስካሁን ምህረትን አድርጌያለሁ፡፡ ነገር ግን ፍትህ እየጮኸ ስለሆነ የፍትህ ሚዛኑ ወደ አንድ በኩል እያመዘነ ነው፡፡ ሚዛኑም ያጋደለው ከተማዋን በመደገፍ አይደለም፡፡

4. ለወሲብ ሰዎችን ማጓጓዝ/ Sex trafficking/ ይህንን ወንጀል ለመከላከልና በመካከላችሁ ያሉትን የወደቁ መላዕክት/alien demons/ ጦርነት በመክፈት መልካም ሥራ ሰርታችኋል፡፡ ነገር ግን ለምንድነው አንድ ላይ የተደራጁ ላቦራቶሪዎች/corporate laboratories/ ሰዎችንና እንሰሳትን እያዳቀሉ እንዲፈጥሩ፣ እንዲሁም ምንም ከፉ ትዕዛዝ ቢታዘዙ እንዲፈፅሙ የተደረጉ ነፍስ የሌላቸው ሰዎችን እንዲፈጥሩና ሊነገር የማይችል ጥፋት እንዲያመጡ ነፃነት የሰጣችኋቸው? እነዚህ ኮርፖሬሽኖች ሳይንቲስቶች ሳይሆኑ ስግብግብ ወንጀለኞች ናቸው፡፡ እኔ በዚህ ምድር ላይ ለህይወት የሚያስፈልጋቸውን፣ ደስታን እንዲያገኙና እንዲያብቡ የፈጠርኳቸውን ነፍሶች ሊጠገን በማይችል ጥፋት ያጠፉ ናቸው፡፡

5. የጥንቆላ ሥራ በአገራችሁ በፍፁም ህጋዊ መሆን የለበትም፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡ የሰይጣን አምልኮና ጥንቆላ ህጋዊ መሆን የለበትም፡፡ እነዚህ ሁለቱ፣ ሰዎች በሚስጥራዊ ጥበብ የበለጠ እንዲደሰቱ በማድረግ የሰውን ልጆችንና ምድርን የሚያጠፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ትዕዛዙን የሚቀበሉት ብቸኛው አጀንዳ ሊነገር የማይቻለውን ህመምና ሞት ከሚያመጣው፣ ለማብዛት የተፈጠረችውን ምድርን ከሚያጠፋው፣ እንዲሁም እስትንፋስ የተሰጣቸውን ወንዶችና ሴቶችን ከሚያጠፋው ከሰይጣን ዘንድ ነው፡፡ እነዚህ ገዳዮችና ሌቦች ሆነው ሳለ እናንተ ግን በሃይማኖት እኩልነት ሰበብ በመካከላችሁ እንዲሆኑ ፈቀዳችሁላቸው??? ምንም የማያውቁትን ለመስረቅ፣ ለመግደልና ለማጥፋት፣ እንዲሁም የማያልቅ ኃይል ታገኛላችሁ በሚል ውሸትና የተስፋ ቃል የሰውን ልጅ ለማበላሸት ፈቀዳችሁላቸው? አሜሪካ ይህንን በመካከላችሁ ለምን ፈቀዳችሁ? እኔ የምህረት አምላክ ስለሆንኩና የሰራሁትን ሁሉ የምወድ ስለሆነ በእናንተ ላይ ያለውን ኃጢያት ለመንብኘት አልመጣሁም፡፡ ነገር ግን እናንተ የሰይጣንን እና የጥንቆላን አምልኮ እንዲቀጥል ስለፈቀዳችሁ ይህ ጥፋት እንዲመጣ ችላ ብላችኋል፡፡ ለመሆኑ በአደገኛ ሱስ የተያዘ ወጣት እንዲሁም ህፃናት የሚደርስባቸው ወሲባዊ የሞራል ውድቀት ከጥንቆላ ጋር ያለውን ግንኙነት አታስተውሉምን? ለዚህ ከፉ ጉዳይ መፍትሔ ስላልፈለጋችሁ በራሳችሁ ላይ ይህንን እንዳመጣ አይታያችሁምን?

6. ወሲብና ብጥብጥ በፊልሙ ኢንዱስትሪ፡- አሜሪካ! ለመሆኑ ህሊናችሁ የት ነው የተቀበረው? በታረዱት ሰውነት በታች? እነዚህ የተገደሉት እኮ ምንም የማያውቁ፣ መልካም ነገር እንዳለ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው የተደረጉና ለክፉ ምሳሌ ለመሆን አይምሯቸው በፕሮግራም እንዲቀረፅ የተደረጉ ናቸው፡፡ ለእንደዚህ አይነቱ አፀያፊ መዝናኛ አይኖቻችሁን ስትጨፍኑ ልጆቻችሁ ዘማዊ ገዳዮች ለመሆን እየተቀረፁ እንደሆነ አታውቁም? ታዳጊዎች በቪዲዮ ጨዋታና በፊልም ደም ለማፍሰስ እንዲጠሙ፣ መልካምና ምንም የማያውቁትን ለመግደል እየሰለጠኑ እንደሆነ አታውቁምን??? እንዴት ነው ይህንን ብልሹ ሁኔታን በመፍቀድ እውቀት ያጣችሁትና የሚቀጥለውን ትውልድ ገዳይና ደፋሪ አድርጋችሁ የምታሳድጉት?? ለዚህም መልሱ ስስትና ለገንዘብ መስገብገብ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ይሸጡና ለሰው ልጆች ጠላት ለሆኑት ለጭራቆች ገንዘብ ያስገኛሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ከእናንተ እውቀት ውጪ በራሳችሁ ጣራ ሥር እነዚህ ነገሮች እየተካሄዱ ናቸው፡፡

7. የፆታ ግራ መጋባት፡- ይህ ትምህርት እየተካሄደ ያለው የሞራል ባሕርይን ለመፋቅና የሰውን ዘር ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ነው፡፡ እንዲሁም ምንም የተሻለ እውቀት የሌላቸውን የልጆችን ህሊና ለማበላሸት ነው፡፡ እናንተ ይህንን ፈቀዳችሁ??? አሜሪካ የት ናችሁ??? የት ናችሁ??? ለህይወት ዘይቤያችሁ/Life style/ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ተጨማሪ ሥራ ስትሰሩ ልጆቻችሁ ግን እንዴት ሰውን እንደሚያሰቃዩ፣ እንደሚደፍሩና እንደሚገድሉ እናንተ በከፈላችሁት የቪዲዮ ጨዋታዎች እየተማሩ ነው፡፡ በዚያም የቤተሰብን እሴቶች በማጥፋት ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን እየተማሩ ነው፡፡ የት ናችሁ?

8. ሌሎች ብዙ ፍትህ ያጡ ጉዳዮች ቢኖሩም ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ጎልተው ከወጡት ጥቂቶቹ ናቸው፡- ሌሎች አገራትን በወታደር፣ ሽብርና ረብሻን በማስነሳት መቆጣጠር፣ በትክክለኛው መንገድ የተመረጠውን መንግስት እንዲወርድ በማድረግ፣ አካባቢ የሚበክሉና የሚያጠፉ፤ እንዲሁም የሰው ልጆችን ህይወት የሚጎዱ ሙከራዎች በመሞከር ሊቆጠር የማይችል ኃዘን በሰው ልጆች መካከል እንዲሁም በራሳቸው ህዝብ ላይ አምጥታችኋል፡፡

እንዲሁም የአሜሪካን ህይወት በመካድ በዙሪያችሁ ስለ ተፈፀመው ኃጢያትና በዚህም ምክንያት በህዝቡ ላይ ስለተፈጠረው ኃዘን ግድ የለሾች መሆናችሁ ነው፡፡

አሜሪካ ኃጢያታችሁ! ኃጢያታችሁ! ኃጢያታችሁ! ለፍትህ ወደ ሰማያት ጩኹ፡፡ ከተኛችሁበት ንቁ፣ ህይወታችሁን መርምሩና ንስሐ ግቡ፡፡ በእናንተ ላይ የፍርዱ ሰዓት ተቃርቧልና!!!

ከአሁን ወዲያ አምላካችሁ በእናንተ ወንጀል ምክንያት በሰው ዘር ላይ የሚፈፀመውን የፍትህ መጓደል ዝም ሊል አይችልም፡፡ ከአሁን ወዲያ የሚገባችሁን ለማድረግ ዝም አንልም፡፡ ትሁት በመሆን መንገዳችሁን ፈትሹና ስለ እናንተ የቀረበው ክስ እውነት እንደሆነ መርምሩ፡፡ በመካከላችሁ ያሉትን የድሆች ጩኸት ንቃችሁ ስለ ምህረት ወደ እኔ የምትጮኹትን ጩኸት ልስማን? ፍርድ የሚመጣው ከሰሜን ሲሆን ፍርዱም በደጃችሁ ነው፡፡ በመካከላችሁ ስላለው ፍትህ ማጣትና ግፍ ንስሐ ስትገቡ፣ እንዲሁም ልዩነት በሌለው ህይወት ስትኖሩ የነበረውን ህይወት ለመለወጥ ጥረት ስታደርጉና ራሳቸውን ለመከላከል ለማችሉት ስትቆሙላቸው ፀሎታችሁን እንደምሰማ እወቁ፡፡ ቅዱሱ መንፈሴ በልባችሁ ውስጥ ብርሃንን በማብራት፣ የነፍሳችሁን ሁኔታ በእውነት እንድታውቁና በፊቴ ሙሉ ንስሐ እንድትገቡ ይረዳችኋል፡፡ በዚህም ክፉ ድርጊታችሁንና ፍትህ አልባ መሆናችሁን በማሳየት እንደገና በእውነት ላይ እንድትመሰረቱ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሁሉ ግን በፍቅር እወዳችኋለሁ፡፡ ስለምወዳችሁ እንድትነቁ እየጠበቅኋችሁ ነው፡፡ አሜሪካ ተነሱ !!!

## ለንጥቀት የደወል ማስጠንቀቂያ - ክፍል 1 - ኖቬምበር 29 ቀን 2020 ዓ.ም

## Rapture Alert 1, November 29, 2020

(ክሌር)፤- ውድ ኸርት ድዌለርስ ይህ መልዕክት ለመነጠቅ እንድንዘጋጅ ከጌታ የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ነው!!! እኔም በፀሎት ወደ ጌታ ፊት ቀርቤ የበለጠ ጊዜ፣ የበለጠ ፀጋ የበለጠ ምህረት እንዲሰጠን እየጠየኩት ነበር፡፡

ጌታም አቋረጠኝና "በእርግጥ የምትፈልጊው ይህንን ነው አለኝ?"

እኔም አሰብኩና በእውነት ከሆነ አይደለም፣ እኔ ደክሞኛል፡፡ ጌታዬ በልቤ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፡፡ በብዙ ነገሮች ወድቄያለሁ፡፡ እድምዬን እንዲሁ አባክኛለሁ፡፡ እስካሁንም ራስ ወዳድና መሻሻል ያልቻልኩ ሆኛለሁ፡፡ ሙዚቃውንም ቀጥዬ መስራት አልቻልኩም፡፡ ልቤ ትክክለኛ ፍትህን ባለማድረግ፣ በስፍናና እምነት በማጣት ደቋል፡፡

ኢየሱስም . . . "ይቅርታ ተደርጎልሻል፡፡ አሁን ለማዘን ጊዜ የለም፡፡ ያለብሽን ዕዳ ሁሉ አጥቤ ንፁህ አድርጌዋለሁ፡፡ እንደዚህ ንፁህ እንደሆነ ለጥቂት ጊዜያት ለማቆየት ሞክሪ፡፡ በነገራችን ላይ ሙዚቃውን ወደ ጎን አድርገሽ እርዳታ በእውነት የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች በመርዳትሽ እንዴት እንደኮራሁብሽ አልነገርኩሽም? ነግሬሽ ቢሆንማ አሁን እንደዚህ አዝነሽ አታለቅሽም ነበር፡፡"

(ክሌር) ይህ ትክክል ነው፡፡ ይህንን ሁሉ ጊዜ እያለቀስኩ ነበር፡፡

ኢየሱስም . . ."ክሌር ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገሽ እንድትተዪ ምን ያህል ኃይላት ተባብረው ከአንቺ በተቃራኒ እንደቆሙ ምንም አታውቂም፡፡ እንዲህ ልበል ሁሉንም ያለመተውሽ በራሱ ሁሉንም እንዳጠናቀቅሽ ይቆጠራል፡፡

(ክሴር) ሁሉንም ያደረገው የአንተ ፀጋ ነው፡፡

ኢየሱስም . . ." ይህም ሆኖ ግን እያየሁሽ ያለሁት እንደ ደከማት፣ እንደ አረጀች፣ ግማሽ ሰውነቷ እንደሞተ ሴት ጎብጠሽ ሳይሆን በኮርቻው ላይ ከፍ ብለሽ ተቀምጠሽ ነው፡፡ ራስሽን እንደዛ መመልከትሽን አቁሚ፡፡ አንቺ በእኔ አይን ወጣትና የተነቃቃሽ ነሽ፡፡"

(ክሴር)፡- ጌታ ይህንን የግጥም ድርሰት አድርጌ ነው የምወስደው

*(ኢየሱስ)፡- "አሁን በዚህ ፊት ላይ ፈገግታን ለማየት ስለምፈልግ ምንም ነገር እሰጣለሁ፡፡ እንዴት እንደሚሰማሽ አውቃለሁ፡፡ የኔ ፍቅር በአንቺ ውስጥ ስለምኖር በደንብ አውቀዋለሁ፡፡ አንቺ ስታለቅሺ እኔም አብሬ አለቅሳለሁ፡፡ ነገር ግን የማለቅሰው በሚደንቅ ሁኔታ እንዴት ታማኝ እንደነበርሽ ባለማወቅሽ ነው፡፡"*

*(ክሴር)፡- ጌታ እኔ በህይወት ዘመኔ ሙሉ ኤ አምጥቼ በፍፁም የማላውቅ ተማሪ ነኝ፡፡*

ሁሉንም በኤ ነጥብ አልጀመርሽም ነበር፡፡ በወጣትነትሽ ግን በከባድ ቡጢ ስላሸነፍሽ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን አይን ውስጥ ገባሽ፡፡ በዚያን ጊዜ መሆን የነበረበት አሁን ምንም አይጠቅምም፡፡ እውነቱ ግን አሁን ያለሽበት ሁኔታ ነው፡፡ እናም በነበረሽ ትንሽ ነገር ጥሩ ሰርተሻል፡፡ የአንቺ ችግር የተፈጥሮ ፍላጎትሽ ሁልጊዜ የሚያየው ምን መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ነገር ግን ያ እንዲሆን የሚያስችል መሳሪያው ሁሉ የለሽም፡፡ ነገር ግን በእድሜ እየገፋሽ ስትሄጂ ብልህ እየሆንሽ መጣሽ፡፡ ስለዚህም አሁን የምትችውን ያህል እየሰራሽ ነው፡፡ ስትወድቂና ንስሐ መግባት እንዳለብሽ ስነግርሽ ንስሐ ትገቢያለሽ፡፡ አየሽ ብዙ የምኮራብሽ ነገር አለ፡፡

*(ኢየሱስ)፡- "አሁን ለኽርት ድዌለርስ በተመሳሳይ መልኩ እንድትነግሪያቸው እፈልጋለሁ፡፡ የኔ ውዶች ከእናንተ ውስጥ ፀጋዬ እንደረዳችሁ መጠን ሁለመናችሁን በእውነት የሰጣችሁ አላችሁ፡፡ ሌሎቻችሁ ደግሞ ለመስጠት ፈልጋችሁ ግን ያልቻላችሁ አላችሁ፡፡ ለእናንተ የምለው አሁን ትልቁ የምህረት ጊዜ በእናንተ ላይ ነው፡፡ በሥጋችሁና ከጀርባው በሚሰሩ ኢጋንንቶች እንዴት በተፅዕኖ ውስጥ እንደነበራችሁ ድካማችሁን አይቻለሁ፡፡ በጣም እጅግ ብዙዎቻችሁ በሚገርም ተቃውሞ ተሰቃይታችኋል፡፡ ነገር ግን እኔንና የገባሁላችሁን ቃል በማመን ሁሉን አልፋችኋል፡፡ ይህ ብቻውን የመንግስተ ሰማያትን ደስታ ሁሉ ለእኔ ለማምጣት በቂ ነው፡፡*

*"ነገር ግን ሥጋቸው በፈጠረባቸው ጫና የተነሳ አንዳንድ ጊዜ እጅግ ድካም ከታየባቸው ወገን ብትሆኑ እንኳን ጠላት ምን ያህል ጫና ሲፈጥርባችሁ እንደነበረ አላያችሁም፡፡ እናም አሁን ራሳችሁን መኮነን እንድታቆሙ እፈልጋለሁ፡፡ ለእነዚያ ሁኔታዎች ሁሉ የሚያስፈልገው ንስሐ መግባት ነው፡፡ ስለዚህም ልባችሁን መርምሩ፣ ንስሐ ያልገባችሁትን ኃጢያት አስታውሱ፣ ትክክል ያልሰራችሁትን አስታውሱ፣ ሥጋችሁና ጠላት አድርጉ ሲላችሁ ያደረጋችሁትን አስቡና ከሰውነታችሁ አስወግዱ፡፡ ወደ እኔ ኑና በግልፅ በመናገር ይቅርታ ጠይቁኝ፡፡ ከዚያም ይቅርታ ይደረግላችኋል፡፡ ነገር ግን ወደ እኔ ስትቀርቡ መሆን ያለበት ፍፁም እውነትን ይዛችሁና ከአይምሯችሁ ጀርባ ምንም የተደበቀ ነገር ሳይኖር ነው፡፡ በዚህ መልኩ በመምጣት በራሴው ደም እንደ በረዶ አነፃችኋለሁ፡፡ ከዚያ በኋላም እነዚህን ነገሮች በአይምሯችሁ እንዳታሰቧቸው፡፡ ደግሞም እኔ እየመጣሁ ስለሆነ እነዚህን ኃጢያቶች ደግማችሁ ላለመስራት ጠንካራ የማስተካከያ እርምጃ ወስዳችሁ ራሳችሁን እጅግ ንፁህ አድርጋችሁ ጠብቁኝ፡፡*

*"በአካባቢያችሁ ያሉትን ለመውደድና ለማገልገል የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ፡፡ ሙብራታችሁ እንዳይጠፋ እኔን፣ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን የምትወዱበት የፍቅር ዘይት እንደ ነደደ ይቆይ፡፡ ወደ ቤታችሁ ለመምጣት እየተዘረጋችሁ ስለሆነ የትኛውንም ኢጋጣሚ ለሰዎች ቅድሚያ በመስጠት ራሳችሁን ለመካድ ተጠቀሙበት፡፡ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ በማንኛውም ደቂቃ ለእናንተ እመጣላችኋለሁ፡፡*

*ተዘጋጁ! ተዘጋጁ! ተዘጋጁ፡፡ እባካችሁ ተዘጋጁ፡፡ ቸርነት ለማድረግ ፣ እንዲሁም ራሳችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ልታቀርቡ የምትችሉበት የትኛውም አጋጣሚ እያምልጣችሁ፡፡ በሁሉም አድራጎታችሁ ለእኔ እንዳደረጋችሁ በመቁጠር እንጂ ስለ ራሳችሁ አታስቡ፡፡*

*"አሁን በዋናነት እንድታውቁ የምፈልገው ያሳለፋችሁትን ብዙ ድካም እንደምቆጥረው ነው፡፡ አሁንም በድካማችሁ ጊዜ በጥንካሬዬ ላግዛችሁ እዚሁ ነኝ፡፡ ስለዚህም እጆቼን አጥብቃችሁ ያዙ ደግሞም ለአንድ ደቂቃ እንኳን አትልቀቁኝ፡፡ እጁንና መንገዴን አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ በደከማችሁና በወደቃችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ተናዘዙና ንስሐ ግቡ፡፡ እኔም ይቅር በማለት እንደገና በአዲስ አድሳችኋለሁ፡፡ ጊዜው ስለደረሰ በፍፁም መቆየት የለባችሁም፡፡ የሚሆነው በፍጥነት ስለሆነ አትዘግዩ፡፡*

*"ከሁሉ በበለጠ ግን ሁላችሁም እንድታውቁት የምፈልገው እንዴት ትግል ላይ እንደነበራችሁና* ስለእናንተም በሰማይ የሚኖረውን አባቴን እጅግ እንዳመሰገንኩት ነው፡፡ ምክንያቱም በጨለማ ተውጣችሁ፣ ግራ ተጋብታችሁ፣ ተከዳችሁና በሐዘን በነበራችሁ ወቅት እንኳን የነበረባችሁን ትግል ሁሉ አይቸዋለሁ፡፡ ትክክለኛ ባለሆነው መንገድ ለመሄድ እየፈለጋችሁ ነገር ግን በትክክለኛውን መንገድ ስለሄዳችሁ ለዚህ ሁሉ አካሄዳችሁ አባቴን አመስግኜዋለሁ፡፡ ወደኋላ አልተንሸራተታችሁም ይህ ደግሞ በመንግስተ ሰማያት ከጥሩ ባህርያት ሁሉ አንዱና ትልቁ ነው፡፡

"ይህ እስካሁን ሲሰደረግ እንደነበረው የንጥቀት የልምምድ ወቅት አይደለም፡፡ የአሁኑ እውነተኛ የንጥቀት ማንቂያ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህም እዚህ ባላችሁ ወቅት ማድረግ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ፡፡በማንኛውም ነገር ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ በመጨረሻውም በእኔ ፀጋ ምን እንዳከናወናችሁ ስታዩ ትደነግጣላችሁ፡፡ በመንግስተ ሰማያት ሆናችሁ በወሳኝ የህይወት ምዕራፎቻችሁ እናንተን ለመቃወም የተሰለፉትን ተቃዋሚዎች በግልፅ ማየት ትችላላችሁ፡፡ ያፈራችሁትንም ፍሬዎች ትመለከታላችሁ፡፡ እናም ስትቆፍሩ፣ ስትዘሩና ስታጠጡ የነበረውን ውጤት ትመለከታላችሁ፡፡ ለእኔ ለመስራት እንድትቀጥሉ በማለት ሆን ብዬ ነው እስካሁን እንዳታዩት ያደረግሁት፡፡ በመንግስተ ሰማያት ግን ሁሉንም ታዩታላችሁ፡፡

(ክሌር)፡- ኢየሱስ መጥፎ የሰራናቸውን ነገሮች ሁሉ እናያቸዋለን?

"መጥፎ መሆኑን አይታችሁ ንስሐ የገባችሁበት በሙሉ ከህይወታችሁ ተጠርጓል ፡፡ ትክክል አለመሆኑን ያላስተዋላችሁትና ንስሐ ያልገባችሁት ግን ሙሉ በሆነው ይቅርታና ምህረት ተሸፍኖ ታዩታላችሁ፡፡ እንደገናም ታጥባችሁ ትነፃላችሁ፡፡ አሁን ግን አጥብቄ ልነግራችሁ የምፈልገው ጥሩ እንደሰራችሁና እናንተም በህይወት ዘመናችሁ የተሰጣችሁን በምን ያህል ደረጃ እንዳሳደጋችሁት ስታዩ በብዙ ደስታ እንደምትሞሉ ነው፡፡ ለሁላችሁም ማለት የምፈልገው እናንተ ሰርቻለሁ ብላችሁ ከሚሰማችሁ በበለጠ መልኩ እንደሰራችሁ ነው፡፡ ስለዚህም ትልቅ የደስታና የሽልማት ቀን ይኖራል፡፡ ለምትነጠቁት ለእናንተ በእሳት ውስጥ ማለፍ አይኖርም፡፡ ይህ ትልቅ ይቅርታ የሚደረግበት የኢዮቤልዩ ቀን ነው፡፡

"በመንግስተ ሰማያት እስካሁን ስትመኙ የነበረውን ፀጋ ትታጠቃላችሁ፡፡ ደግሞም የሚቃወማችሁ ጠላት የለም፡፡ በዛን ጊዜ በየዕለቱ የለመዳችሁትና እናንተን የሚያደቀው ተቋውሞ እንደሌለ ስትረዱ በምድር ላይ እንዴት እንዳሳለፋችሁ ጨረፍታው ይታያችኋል፡፡ ይህ ደግሞ ገደብ የሌለው ደስታ ይሰጣችኋል፡፡ የእኔ ሙሽሮች አሁን ኑ፡፡ ወደ እኔ ልወስዳችሁ በመጠበቂያ ክፍል እየጠበኳችሁ ነው፡፡ ህሊናችሁን ከመረመራችሁ በኋላ ለቅሷችሁን ወደዚያ ተዉ፡፡ ወደኋላ እያሰባችሁ መፀፀታችሁንና ሐዘናችሁን አቁማችሁ የተትረፈረፈውን ደስታ መያዝ እስኪችል ድረስ ልባችሁን በማስፋት አዘጋጁት፡፡ ነፃ የምትወጡበት ጊዜ መጥቷልና ደስ ይበላችሁ፡፡" የጌታ መልዕክት እዚህ ላይ ያበቃል፡፡

(ክሌር)፡- ውድ ቤተሰቦቼ እንግዲህ ምን እላለሁ? አሁን ለጌታ ዶናልድ ትራምፕ እንደገና ሲመረጥ ንጥቀት ይሆናል ብዬ አልጠበኩም ነበር በማለት ነግረዋለሁ፡፡ እርሱ ዳግም ተመርጧል፡፡ ነገር ግን ችግሩ በጨለማ ያሉት ቢሮውን እንዳይዝ ለማድረግ የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ በመካከለኛው ምስራቅና በቻይና እንቅስቃሴዎች እየጨመሩ እንደሆነ ለእናንተ መናገር አለብኝ፡፡ ነገር ግን ትራምፕ ቢሮውን ከመያዙ በፊት ጦርነት የሚያስነሱ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በጦርነት ጊዜ ፕሬዜዳንት ቢሮውን መልቀቅ የለበትም የሚል ነገር የሰማሁ ይመስለኛል ነገር ግን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

እንደማስታውሰው ከሆነ ከስድስት አመት በፊት ለመነጠቅ እጅግ የምንጠባበቅበት ወቅት ነበር፡፡ ጌታ ግን "እኔ የምመጣው ይመጣል ብላችሁ ምንም በማትጠብቁት ጊዜ ነው" ብሎን ነበር፡፡ ለእኔ እንደሚመስለኝ ትራምፕ ለሁለተኛ ጊዜ ቢሮውን ሲረከብና ይህ ጊዜ ብዙ መልካም ነገሮች ልንሰራ የምንችልበት ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን ለትንሽ ደቂቃ በደንብ አስቡ፡፡ በዚህ ማሸነፍ መካከል እኛ ብንወሰድስ? ጥግ ላይ የነበሩ ሁሉ ከእንቅልፋቸው በመንቃት ትልቅ መነቃቃት ቢሆንስ? ይህንን አስቡት ስሜት የሚሰጥ አይመስላችሁም? በአንድ ቅፅበት ውስጥ እንደ ድንጋይ የጠነከረ እምነት ያለውና በታላቁ መከራ ውስጥ ሊያልፍ የሚችል፣ራሱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥ ወይም በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ የሚሆን አዲስ የክርስቶስ አካል በምድር ላይ ይፈጠራል!!!

ምን አይነት እጅግ የበለጠ መነቃቃት እንደሚሆን ይታያችኋል? በሌላኛው አንፃር ደግሞ ምን አይነት ትልቅ ወድቀት ይከሰት ይሆን? ለጌታ ራሳቸውን በእውነት የሰጡ ወደፊት መጓዝ ሲሆንላቸው በአንፃሩ ደግሞ ለጌታ ራሳቸውን በእውነት ሰጥተው የማያውቁ ወድቀው ይህንን አለም ሊገዛ ለሚመጣው ለክፉው እጅ ታልፈው ይሰጣሉ፡፡ ውዶች ምንም ይሁን ምንም ይህ የማንቂያ ደውል ለሁላችንም እጅግ ጠንካራ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

በተጨማሪም ሁሉንም የንጥቀት ራዕይ ብታስታውሱ እኛ ወደ ላይ ስንወሰድ የእግዚአብሔር ሠራዊት ደግሞ በምድር ላይ ፍርድን ለማምጣት ወደታች እንደሚወርዱ የሚያሳይ ነበር፡፡ አዎን እኛ ወደላይ ስንወሰድ የጥፋት ተዋጊዎች ሙሉ የጥፋት ጦርነት ለማድረግ ወደታች ወደ ምድር ይወርዳሉ፡፡ በራዕዩ ላይ እንደታየው በአየር ላይ ከእነርሱ ጋር እንገናኛለን፡፡ እንዲሁም በራዕዩ ላይ እኛ ምድርን እየለቀቅን እያለ በምድር ላይ ሰላም ተወስዶ ነበር፡፡ እዚህ ላይ በመካከለኛው ምስራቅ በግብፅና በእስራኤል መካከል የተደረገውን ትኩረት የሚስብ የሰላም ስምምነት ማስታወስ እጅግ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ይህ ስምምነት ሲፈፀም ትኩረቴን የሳበ ድርጊት በመሆኑ ቶሎ በአይምሮዬ የመጣው "ሰላም ሰላም ይላሉ ነገር ግን ሰላም የለም " የሚለውን የቃሉን ክፍል ነበር፡፡ ይህ በተሰማኝ ጊዜ ለዚህ ነገር ትኩረት መስጠት እንዳለብኝ ከመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሰጠኝ አድርጌ ወስጄዋለሁ፡፡ ስለዚህም በማንኛውም ሰአት ሰላም ከእኛ ሊወሰድ እንደሚችል መረዳት አለብን፡፡ ለዚህ ነው በቃሉ "በመጨረሻም ሰላም ይላሉ ነገር ግን አይፀናም" ተብሎ የተፃፈው፡፡

በሌላ አንፃር ደግሞ ይህ ማስጠንቀቂያ ሊሆን የሚችለውና ሁላችንም አትኩረን ልናየው የሚገባን ጉዳይ ጌታ ለመጨረሻው ጉዞአችን እንደገና ሊያስታጥቀን እንደሆነ ነው፡፡ ይህ የተሰጠን ዕድል ራሳችንን ለማስተካከል የመጨረሻው እንደሆነና እንዲሁም የተሰጠንንም ሥራ እንድንጨርስ ሊያስገነዝበን ይሆናል፡፡ ይህ ማስጠንቀቂያ ለዚህ ከሆነ እኔ እጅግ ደስ ይለኛል ምክንያቱም የተሰጠኝን የሙዚቃ ሥራ ለመጨረስ ዕድል ስለማገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ማለት እፈልጋለሁ ቀድሞ ኪቦርዴን ለመጫወት፣ እንዲሁም የሙዚቃ ድርሰት ለመፃፍ የነበረኝን ፍላጎትና ደስታ እንዳጣሁ ነው፡፡ ይህ ለእኔ እጅግ ከባዱ ሥራ ሆኖብኛል፡፡ ስለዚህ ጌታ ፀጋ ካልሰጠኝ በስተቀር የጊዜ መጨመር ለእኔ ምንም ለውጥ ሊያመጣልኝ አይችልም፡፡ ለሌሎች እንዳውም የባሰ ሊሆንባቸው ይችል ይሆናል፡፡ እንዴት እናውቃለን? ይህንን በእርሱ እጅ ላይ እተወዋለሁ፡፡ የትኛው እንደሚሆን የሚያውቀው እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ

ሥፍራችሁን አትልቀቁ፣ የተሰጣችሁን ሥራ መስራታችሁን አትተዉ፣ እግዚአብሔር በየቀኑ በሚሰጣችሁ ብርታት ሥሩ፡፡ የምድር ፍርድ እየመጣ ስለሆነ ደስ ይበላችሁ፡፡ ደግሞም በአለም ላይ እየሆነ ያለውን ነገር በጥሞና ተከታተሉ፡፡ ሙሽራው በእውነት እየመጣ ስለሆነ ተዘጋጁ፡፡ ማህበረሰቦች ተዘጋጁ፡፡ ለመስጠት የምትችሉትን ሁሉ የሥርግ ስጦታ አድርጋችሁ ለኢየሱስ አቅርቡ፡፡ በእውነት ሙሽራው ይመጣል!!!

## ለንጥቀት የደወል ማስጠንቀቂያ - ክፍል 2 - ኖቬምበር 30 ቀን 2020 ዓ.ም

## Rapture Alert 1, Novembere 30, 2020

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." ክሌር እንደነገርኩሽ በዚህ ጊዜ ንጥቀትን የምትለማመጂበት ጊዜ ሳይሆን እውነተኛው ንጥቀት የሚሆንበት ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ጠርዝ ላይ ደርሰናል፡፡ ሙዚቃውን ለመስራት አትችይም ብዬ ተስፋሽን ዝቅ ማድረግ አልፈልግም፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ቀናቶች ውስጥ በአለም ያለው ሁኔታ ከአምስት አመት በፊት ከነበረው ሁኔታ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ይህ ነው ጠርዙ፡፡ ስለዚህም በማንኛውም ሰአት ወደ አንዱ ጎን ሊያዘነብል ይችላል፡፡ እባካችሁ መፀለያችሁን ቀጥሉ፣ ቸላ አትበሉ፡፡ እባካችሁ ልባችሁንና ስሜታችሁን በፀሎት ላይ አድርጉት፡፡ በሩ እየተዘጋ ቢሆንም አጋጣሚው ግን አለ፡፡ ስለዚህም ነገሮችን ተመልከቱ፣ ፀልዩ፣ መስዋዕትን አቅርቡ፣ እንዲሁም በየቀኑ ዝግጁ ሁኑ፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር መሆኔን እንደነገርኳችሁ ይህንን አስታውሱ፡፡ ስለዚህም እጄን አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ በየደቂቃው እኔ ከእናንተ ጋር መሆኔን ተገንዘቡ፡፡ የተወደዳችሁ ሥራችሁን ደግሞ መስራት አትርሱ፡፡ ልወስዳችሁ ስመጣ በሥራ ተግታችሁ እንዳገኛችሁ የጀመራችሁን መስራት ቀጥሉ፡፡" የጌታ መልዕክት እዚህጋ ያበቃል፡፡

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ ለማለት የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ ይህንን መልዕክት በህብረተሰብ ውስጥ ከሚገኙ ከሌሎች ተጂሚዎች ጋር በመሆን ደግሜ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ፡፡ ይህንን ማለት አለብኝ፡ ባለፉት ጊዜያቶች ስለ ንጥቀት የማስጠንቀቂያ መልዕክት ሲሰጠኝ ተጨማሪ ጊዜ፣ የበለጠ ፀጋና የበለጠ ምህረት ብንጠይቅ ፀሎታችን እንደሚመልስ በጥልቅ ይሰማኝ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህ ነገር ሊሰማኝ አልቻለም፡፡ በእውነቱ ከሆነ በመልዕክቱ መጨረሻ ላይ የተሰማኝ ነገር ቃል በቃል ማለት እችላለሁ በሰማይ ላይ ተንጠልጥዬ ነበር፡፡ ስለዚህም በዚህ ጊዜ ንጥቀቱ ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ የኔ ውዶች ላካፍላችሁ የምፈልገው ይህንን ነው፡፡ ምናልባት እናንተ የበለጠ አተያየት ሊኖራችሁ ይችላል፡፡ ምንም ይሁን ምንም እየጠየቀን ያለው ግን እንድንፀልይ ነው፡፡ ስለዚህም በጉልበታችን እንበርከክ፡፡ ሁላችሁንም በፍቅር እወዳችኋለሁ፡፡ ጠላቶቼ የሆናችሁትን እንኳን ቢሆን እወዳችኋለሁ፡፡ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት እንገናኝ ይሆናል፡፡

**ጊዜው እየቀረበ ስለሆነ የመጨረሻውን ዝግጅት አድረጉ - ዲሴምበር 17 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Keep your oil, December 17th, 2020**

ጌታ እንዲህ ይላል . . . "አሁን በዚህ ሰዓት እጅግ አስፈላጊው ነገር ንስሐ መግባት ነው፡፡ ንስሐ ያልገባችሁ አንዳንዶች ሳትወሰዱ ትቀራላችሁ፡፡ የኔ ልጆች ህይወታችሁን በሙሉ ከወጣትነት ጀምሮ እስካሁኗ ደቂቃ ያለውን በደንብ እንድትፈትሹና ኃጢያታችሁን እንድትናዘዙ አበረታታችኋለሁ፡፡  በፊት ያደረጋችሁት አንድ ነገር በአይምሯችሁ ከመጣ ንስሐ ግቡ፡፡ በሐሳባችሁ እንኳን የሰራችሁት ኃጢያት ንስሐ ልትገቡበት ይገባል፡፡ ስመጣ ሙሽራዬ ንፁህ እንድትሆን እፈልጋለሁ፡፡ ይህ ማለት ለብዙዎቻችሁ ህይወታችሁን ጠንከር ባለ መልኩ መፈተሽን፣ ኃጢያት መስራታችሁን ማመንና ጥልቅ የሆነ ንስሐ መግባትን ይጠይቃል፡፡

*"ይህም በሐሳባችሁ ያሰባችሁት ነገር እናንተን ወደ ሲኦል ሊከታችሁ እንደሚችል በማወቅ ነው፡፡ ድርጊቱን አልፈፀማችሁት ሊሆን ይችላል ነገር ግን በጎረቤቶቻችሁ ላይ ቂም በመያዝ መጥፎ ነገር እንዲደርስባቸው ከፈለጋችሁ ከባድ ኃጢያት ሰርታችኋል፡፡ ይቅርታ ያለማድረግ ውርሻ አካሂዳችሁ ንስሐ ካልገባችሁ በዚህ ምድር ላይ አስሮ እንደሚያስቀራችሁ ልክ እንደዛው በዚህ ያስቀራችኋል፡፡ አሁን የምትቀልዱበት ጊዜ አይደለም፡፡ እኔ የምላችሁን ነገር አክብዳችሁ እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ፡፡*

*"በእናንተ ቅር ከተሰኙት ጋር ሁሉ ሰላም ፍጠሩ፡፡ ሁሉንም ሰው ይቅር በሉ፣ ከሰዎችም ዘንድ ይቅርታቸውን ተቀበሉ፡፡ በህይወት ዘመናችሁ ያስከፋችኋቸውን ቁስላቸውን እንዳከምላቸው በፀሎት እኔን ጠይቁኝ፡፡ ሳይነጠቁ ለሚቀሩት ፀልዩ፡፡ በድንገት መለየየት በሚሆነው በዚህ ክስተት በምድር ላይ በብዙዎች ላይ ስቃይ የሚያመጣውን ህመም ለመቀነስ ለዘመዶቻችሁ የፍቅር ደብዳቤ በመፃፍ የተቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፡፡ ተስፋ እንዳለ፣ ነገር ግን የአውሬውን ምልክት ከተቀበሉ የዘላለም ህይወት እንደሚያጡና በገሃነም እሳት ውስጥ ለዘላለም እንደሚወረወሩ አስጠንቅቋቸው፡፡ ንጥቀት ሲሆን በአይናቸው ማየታቸው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን ማረጋገጫ ይሆናቸዋል፡፡ በመሆኑም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተፅፎ ያልተፈፀመና የሚቀጥለው ተፈፃሚው ትንቢት የአውሬውን ቁጥር የሚቀበል ለዘላለም ወደ እሳት ባህር መጣሉ ነው፡፡ ይህም እንደ ንጥቀቱ እውነት መሆኑን አውቀው የአውሬውን ቁጥር እንዳይቀበሉ አስጠንቅቋቸው፡፡*

*በዛ ወቅት የአውሬውን ቁጥር እንድትወስዱ  ብልፅግናና ደህንነት ይሆናል በሚል የአውሬውን ቁጥር ከተቀበላችሁ በኋላ ተከትሎ እንዲጀመር የሚያደርጉት ነገር የሚያመጣው ጥልቅ የሆነ የአካል ስቃይ ከምትገምቱት፣ ይሆናል ብላችሁ ከምታስቡትና መቋቋም ከምትችሉት በላይ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ ስቃዩ እጅግ በዝቶባችሁ ለመሞት ብትፈልጉ እንኳን መሞት አለመቻላችሁ ነው፡፡ ይህ የሰይጣን መሳሪያ እኔን እንድትረግሙና ንስሐ ሳትገቡ እንድትሞቱ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህም እንደገና የማስጠነቅቃችሁ ለምህረት ወደ እኔ እንድትጮኹ ነው፡፡ ደግሞ ማስታወስ ያለባችሁ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉ ለዘላለም እንደሚሰቃዩ ነው፡፡ የአውሬውን ምልክት ተቀብላችሁ፣ ለጥቂት ወራት በልፅጋችሁ፣ ከዚያም በመሰቃየት ሞታችሁ ለዘላለም ወደ ገሃነም ከምትጣሉ ይልቅ ለእናንተ መልካም የሚሆነው የአውሬውን ምልክት ሳትቀበሉ በቅፅበታዊ ሞት ወደ መንግስተ ሰማያት ገብታችሁ ከእኔ ጋር ለዘላለም ብትኖሩ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡*

*"ኢጅግ ኢደርጌ እወዳችኋለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ ትልቁ ምኞቴ ፍፁም የሆነ ንስሐ ገብታችሁ እኔ ስመጣ እወስዳችሁ ዘንድ ነው፡፡ እባካችሁ ንስሐ መግባት ያለባችሁን ነገር መንፈስ ቅዱስን በመጠየቅ ተረድታችሁ ለእያንዳንዱ ኃጢያታችሁ ንስሐ ግቡ፡፡ እኔም ይቅር እላችኋለሁ፡፡ በዚህም የሠርግ ልብሳችሁ ምንም የቆሻሻ ጠብታ፣ መጨማደድና ምንም እንከን የሌለበት ይሆናል፡፡"*

**ስለ ንጥቀት የወቅቱ መልዕክት - እ.አ.አ. ዲሴምበር 24 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Rapture Update, December 24th, 2020**

ውድ ቤተሰቦቼ ከማነባቸው ኢሜሎችና ከምትሰጡኝ ሐሳቦች የተነሳ ንጥቀት በጣም በቅርብ እንደሚሆን የሚያመለክተውን መልዕክቶች ያልተረዳችሁ አድርጌ ወስጄ ነበር፡፡ እኔም እንደዛ መስሎኝ እንደነበር መናዘዝ እፈልጋለሁ፡፡ በቅርብ መሆኑን ስረዳ ግን ለዚህ ዝግጁ መሆኔን ለማወቅ እራሴን በጥልቅ እንድመለከት ረድቶኛል፡፡ ስለደከመኝ ንጥቀቱን እንደምፈልገው አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ጥያቄው እኔ ለዛ ዝግጁ ነኝ ወይ የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ አካሉን ለማነሳሳት የራሱ መንገድ እንዳለው በትዕግስት ተረዱ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መንገዱ ትንሽ የሚያም ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ንጥቀቱ በማንኛውም ሰአት እንደሚሆን አውቀን ውስጣችንን በእውነተኛው መንገድ ስንፈትሸውና እንዳልተዘጋጀን ሲገባን የሚፈጥርብን ህመም ዓይነት ማለት ነው፡፡ የዚህ መሰረታዊ ቁም ነገሩ ለንጥቀቱ ዝግጁ መሆን አለብን የሚል ነው፡፡

በቅርቡ በኢንተርኔት የሚያገለግል አንድ አገልጋይ ጌታ ንጥቀቱ በአስር አመት ይሆናል ብሎኛል በማለት ተናግሯል፡፡ እርሱ የተናገረውን ይህንን መልዕክት በማስረጃ ለማረጋገጥ አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን ይህ አገልጋይ በእርግጠኝነት ጌታን ያውቃል ደግሞም የተወሰኑ ጊዜያቶችን በመንግስተ ሰማያት አሳልፏል፡፡ ስለዚህም ይህ ደግሞ እኔን ለሐሳብ አሳልፎ ሰጠኝ፡፡ በዚህም ምክንያት የጌታን ፊት በመፍለግ "ጌታ ምን እየተካሄደ ነው ያለው? ትክክል ያለሆነ ቃል ነው እኔ የሰማሁት ወይስ ምንድነው?" አልኩት

ብዙዎቻችሁ ዝግጁ እንዳልሆናችሁ ስሜቶቻችሁ ይገልፃላችኋል፡፡ ደግሞም ዝግጁ አለመሆናችሁ እውነት ነው፡፡ በግድግዳው ላይ 'ንጥቀቱ በማንኛውም ሰዓት ሊሆን ይችላል' ተብሎ የተፃፈውን አየሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ ትኩረታችን ሊሆን ባለው ነገር ላይ መሆን እንደሌለበት አውቃለሁ፡፡ ምክንያቱም ትኩረታችንን በዛ ላይ ካደረግን ከፋኖሳችን ውስጥ ዘይቱ ለማለቅ ብዙ ዕድል አለው፡፡ በእያንዳንዷ ደቂቃ ትኩረታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈፀም ላይ፣ በታማኝነት ለእርሱ በመኖርና በሙሉ ልባችን እርሱን በማፍቀር ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለዚህም ጌታን "ይህ አገልጋይ ከአንተ ንጥቀቱ በአሥር አመት ይሆናል የሚለውን እንዴት ሊቀበል ቻለ?" ብዬ ጠየኩት፡፡

እናም መንፈስ ቅዱስ እንዲህ በማለት መለሰልኝ . . . "እርሱን የምመራበት መንገድ ሌላ ነው፡፡ የአንቺ ኃላፊነት ምን እንደሆነ አሁን በግልፅ ሊገባሽ አይችልም በኋላ ግን ይገባሻል፡፡ ይህንን መንጋ የሰጠሁሽ ጠንካራ ምክንያት አለው፡፡ አንቺን የምመራበት መንገድ በተለየ በተዘጋጀ ህጎች ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ጠንካራ የሆኑ በቂ ምክንያቶች አሉት፡፡ አንቺን

የምመራበት መንገድ የተለየ ነው፡፡ እርሱንና መንጋውን በመልካም የምመራበት መንገድ ለአንቺ መልካም ሆኖ ላይገኝ ይችላል፡፡"

ነገር ግን ጌታ አንተ እኮ ሰዎችን አታታልልም፡፡ ስለዚህም ይህንን ስንል በሁሉም በኩል አንድ መሆን አለበት፡፡

መንፈስ ቅዱስም " ይህ እውነት ነው፡፡ ቢሆንም ግን ሊሆኑ በሚችሉ ሁኔታዎች ምክንያት ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገርን ማለት እችላለሁ፡፡ አንቺ መምራት የያዝሽው እድሜያቸው የገፋና የበሰሉ ብዙ ህዝቦችን ነው፡፡ እርሱ ደግሞ ብዙ ወጣቶች አሉት፡፡ እርሱን የምመራበት መንገድ ከአንቺ ፍፁም የተለየ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ቀኑንም ሆነ ሰአቱን ማንም አያውቀውም፡፡ ማንም አያውቀውም ይህ ደግሞ እኔንም ይጨምራል፡፡ እኔ መናገር የምችለው አባቴ የሚነግረኝን በመስማትና በዚህ ምድር የሚደረገውን ከምከታተለው ነው፡፡ ይህ የስላሴ ሚስጥር ነው፡፡ ይህም ሁኔታው ሲፈፀም በተነጣል የሚደረግ እውነትን መከፋፈል ነው፡፡"

ጌታ ይቅርታ አድርግልኝ ፡፡ ይህ ግን የሚመስለው አስመሳይ መንፈስ ውሸትን ትክክልና የግብረ ገብ ሁኔታ እንደሆነ ለማስረዳት የሚያደርገው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ የተወሰኑ ነገሮች ትክክል እንደሆኑ ለማሳመን የሚደረግ ማለት ነው፡፡ አንተ ግን በፍፁም አትዋሸንም፡፡

እርሱም "በእኔ ላይ ያለሽ እምነት የታል? አለኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ይህንን ጥያቄ ይገፔ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፅሐፍን ይቅርታ የሚለውን ገፅ 106 ከፍቼ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ትንሽ የተሻለ ነገር ሆነ፡፡

ከዚያም መንፈስ ቅዱስ "ማንን ነው የምታምኚው? እኔ በተቀደሰው ቃሌ ንጥቀት መቼ እንደሆነ ማንም ሰው አያውቅም እያልኩ ንጥቀቱ በአሥር ዓመት ይሆናል ማለት መዳፈር አይሆንም?"

(ክሌር)፦ ነገር ግን የንጥቀት ወቅት ነው ብለሃል፡፡ ስለዚህም ያለነው በአዲስ ወቅት ላይ እንዳውም በአዲስ ዘመን ላይ ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ ከፓስተሩ ቃል ጋር ይስማማል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እባክህ እርዳኝ፡፡ ምራኝ ደግሞም አስተካክለኝ፡፡

"እየረዳሁሽ ነው፡፡ አሁን ይህንን የምናደርገው አብረን ነው፡፡ የተወደድሽ ክሌር ይህንን ወዲያው የሚሆነውን ጊዜ መጠየቅሽ ትክክል አድርገሻል፡፡ አየሽ ይህ እስካሁን ውሳኔ አልተሰጠበትም፡፡ ነገር ግን ማስጠንቀቂያ እየተሰጠ በሄደ ቁጥር ሰዎች እየተንበረከኩና ምህረትን እየጠየቁ ነው፡፡ ምህረት እየጠየቁ ያሉት አንቺ ጊዜሽን እንዳባከንሽው እነሱም የተሰጣቸውን ጊዜ ስላባከኑ ነው፡፡ ሌላው ምህረት እየጠየቁ ያሉት የሚወዷቸው ባለመዳናቸው ነው፡፡ አየሽ እስካሁን ገና ውሳኔ አልተሰጠም፡፡ ስለዚህ ማስጠንቀቂያ በተሰጠ ቁጥር ሰዎች እየተንበረከኩ ምህረት እየፈለጉ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ አንቺ ጊዜያቸውን ስላባከኑ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ አሁን ተረድተውታል፡፡ ደግሞም ምህረት እየጠየቁ ያሉት ስላልዳኑት ውዶቻቸው ነው፡፡ ምህረት እየጠየቁ ያሉት ስላልተደረሱ ሰዎች ነው፡፡

"ስለዚህም ስለጊዜው መጠየቅሽና ምናልባትም ተጨማሪ ጊዜ ይኖር እንደሆነ ተስፋ ማድረግሽ ልክ ነሽ፡፡ ነገር ግን እንዲገባሽ የሚያስፈልገው ሉአላዊው አብ ስለሆነ የሚመርጠው እርሱ ብቻ ነው፡፡ ለመሆኑ ስንት ማስጠንቀቂያዎች ተደርገዋል? ከእነዚያ ማስጠንቀቂያዎች ምን ውጤት ተገኘ? አንዳንዱ መልካም ውጤት ሲኖረው አንዳንዱ ደግሞ እስከዚህም መልካም ነገር አልነበረውም፡፡ የተሻለ ነገር ለማድረግ ስትወስኚ ተሸንፈሽ ከውሳኔሽ እንድትወርጂ ለማድረግ እንዲሁም መስራት

ካለብሽ እጅግ አስፈላጊ ከሆነ ነገር በማባበል ሊነጥሉሽ ኢጋንንቶች ወደ አንቺ ተልከው እንደነበር እውነት ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህ ማለት እፈልጋለሁ የወንድማማች ፍቅርን ባለመሰልቸት ዋና አጀንዳ በማድረግ ጠብቀሻል፡፡ እጅግ የሚያስፈልገው ዋናው ነገር ደግሞ ያ ነው፡፡ ሙሽሪትን ወደ ቤቷ እንድትመጣ የሚደረገው ጥሪ የእኛ ጥሪ አይደለም (የመንፈስ ቅዱስና የኢየሱስ)፡፡ ይህ የአብ ጥሪ ስለሆነ እርሱ ደግሞ ይህንን የሚወስነው በልብ ውስጥ ባለ ፍፁም ለውጥ ነው፡፡ ይህም ምን ያህል ጥልቅ ንስሐ እንደተገባ እና በዚህም ንስሐ ምክንያት ለሦስት አመት ሳያፈራ የቀረው ዛፍ ምን ያህል ፍሬ እንዳፈራ በማየት ነው፡፡ እርሻው አሁን ዙሪያውን እየተኮተኮተ፣ መሬቱ እንዲለመልም ፍግ እየተደረገበት ነው፡፡ ይህም ምናልባት ዛፉ እውነተኛ ፍሬ ያፈራ ይሆናል በማለት ነው፡፡

"አየሽ የተጠራሽው እስካሁን ከሄድሽበት በተሻለ መልኩ ለትልቅ ከፍታ ነው፡፡ ወደዚህ ከፍታ እንዳትደርሺ የሚያደርግሽ ደግሞ ስንፍና፣ ድካም፣ የጠላት ውሸት፣ በእምነት መሰልቸት፣ እናም በመጨረሻም ሰይፍሽን አንስተሽ መዋጋት ሲገባሽ ለሥጋ ዕድል ፈንታ በመስጠትሽ ነው፡፡ ክሌር በስህተቶች ተበሳስተሽል፡፡ ነገር ግን ፍቅርሽ ትልቅ ነው፡፡ ፍቅርሽን አከብራለሁ፡፡ የኔ ልጅ እውነተኛ የሆነውን ለሌሎች የምትሰጪውን ክብካቤ አከብራለሁ፡፡ በውሸት አባት ደግሞ እንዴት እንደተሸነፍሽ አይቻለሁ፡፡ ቢሆንም ግን አሁን አገግመሽ መሥራት ያለብሽን ነገር በትጋት መሥራት አለብሽ፡፡ ይህንንም በማድረግሽ ንጥቀቱ በወር ውስጥ ቢሆን ወይም ከዚያ በኋላ ራስሽን ለዛ ዝግጁ ታደርጊያለሽ፡፡ የአንቺ ኃጢያትና ድክመት የሰው ልጆች ሁሉ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን የአንቺ ባህርይ ደግሞ ትልቅ ነው፡፡ ይህም አንድ ነገር እንድታስተካክይ ስትጠየቂ የቀረውን የቆሸሸውን፣ የተጨማደደውንና የጎደፈውን ሁሉ ታስወግጂዋለሽ፡፡ ስለዚህም የንጥቀቱ ጊዜ ቅርብ እንደሆነ ለማወቅ እንዲያስችል መልካም ሽብር መፍጠርና የማነቂያ ደውል ማሰማት ለሁላችሁም እጅግ ጥሩው መንገድ ሲሆን ይህም እውነተኛ ማንነታችሁን ለመፈተሽ፣ ምን እንደሰራችሁ፣ ምን ለመስራት እንዳቃታችሁ የሚያሳይ ነው፡፡

"ኢየሱስ የሚፈልገው ንፁህ የሆነችውን ሙሽሪት ነው፡፡ እናም አብ ከሁሉም ክብሯ ጋር ሆና ሲያየት ወደ ቤት እንድትመጣ ይጠራታል፡፡ ሙሽሪት ራስዋን ስላላዘጋጀች የንጥቀቱ ጊዜ ሊዘገይ ይችላል ብለሽ መጠርጠርሽ ልክ ነሽ፡፡ እናም የራስሽን ፈቃድና የሥጋን ፈቃድ ለማሸነፍ ስትፀኚ፣ እንዲሁም በመንገድሽ ማብቂያ ላይ ሆነሽ እነዚህን ትግሎችና ማሸነፎችን ስታጋሪ ሌሎችም "እርሷ ከቻለችው እኔም እችላለሁ" በማለት በፅናት ይቆማሉ፡፡ ከዚህ ግብ በከፋ ሁኔታ ሩቅ ሆነው ያሉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ኢየሱስ ደግሞ ሁሉንም ይፈልጋቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ለንጥቀት መጥራት የሚቻል ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የአብ ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልገው፡፡ እርሱ ነው የሁሉንም አማኞች እንዲሁም ለማመን የተጠሩትን አጠቃላይ ሁኔታ በመቆጣጠር መቼ እንደሚጠራት ውሳኔ የሚሰጠው፡፡ ስለዚህም ለመሥራት ጥቂት ጊዜ አለ፡፡ ነገር ግን እንዲህም ቢሆን ቶሎ ወደ ቤት ትጠሩ ወይም አሥር ተጨማሪ አመታት ይሰጣችሁ ምንም የሚያስተማምን ነገር የለም፡፡ በፍፁም የሚያስተማምን ምንም ነገር የለም፡፡ የክርስቶስ ተቃዋሚው ከመካከላችን ነው ብለሽ መናገርሽ ትክክል ነው፡፡ በህልምሽ በመርከቡ ወለል ላይ ከሄለሪ ክሊንተን ጋር ሆነሽ ያየሽው ያ ደግሞ እውነቱ ነው፡፡"

ጌታ መንፈስ ቅዱስ እያወራ ያለው ህልም እንዲህ ነበር፡፡ እኔ ወደ ሜክሲኮ በሚሄድ መርከብ ላይ ነበርኩ፡፡ የመዳረሻ ሥፍራችን ሜክሲኮ ከተማ ይመስለኛል፡፡ በዛም መርከብ ወለል ላይ ከሄለሪ ክሊንተን አጠገብ ነበርኩኝ፡፡ እናም ሄለሪ ክሊንተን ወደ እኔ ዞር ብላ አይታኝ "እርሱ ከእኛ ጋር ነው" አለችኝ፡፡ እኔም በዛን ጊዜ ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚው እንደምታወራና እርሱም ከመርከቡ በታች፣ ከዕይታ ውጪ ባለው ሥፍራ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ በዚያን ጊዜ የኮዞቮ ጦርነት እየተካሄደ ያለበት ጊዜ ነበር፡፡ እኛ ደግሞ አሁን ባለንበት ተራራው ላይ ከበጎቻችን ጋር እየኖርን ነበር፡፡ ከዚያም ከህልሙ

ስነቃ ህልሙ የመንፈስ ቅዱስ ፊርማ እንዳለበት አወቅሁ፡፡ ይህ ሰው ዲሞክራቲክ ፓርቲን ወክሎ ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር እስኪመረጥ ድረስ ማን እንደሆነ አላወቅሁም ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ሰውዬ ሳየው ጌታ በራዕይ በካፒቶል ህንፃ ውስጥ ያሳየኝ ሰው እንደሆነ ልለየው ቻልኩ፡፡ በራዕዩ ውስጥ አንድ በሚከበር በአል ላይ አንዲት ሴት ወደፊት በመምጣት አዳኛችን በማለት አስተዋወቀችው፡፡ ከዚያም ረዥም፣ ቀጠን ያለ ጥቁር ሰው ከበሩ ኋላ መጣ፡፡ እኔ ግን በዛ ራዕይ ውስጥ የተሰማኝ ሰውዬው ሙስሊም እንደሆነ ስለነበር ለብሶ ይመጣል ብዬ የጠበኩት የሙስሊሞችን ልብስ ሲሆን እርሱ ግን ኮትና ሱሪ ነበር ለብሶ የመጣው፡፡

መንፈስ ቅዱስም . . . " ስለዚህ አየሽ ብዙ የሚገጣጠሙ ቁርጥራጭ ስዕሎች አሉሽ፡፡ ይህ ወቅቱ ነው ማለትሽ ትክክል ነሽ፡፡ ምክንያቱም እንደ እውነቱ ከሆነ እርሱ ከጀርባ በማይታይ ሁኔታ ሆኖ አገራትና ህዝቦች በህብረት በአንድ ስምምነት ላይ በእርሱ አንድ አለም አቀፍ አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ እየሰራ ነው ያለው፡፡"

ጌታ ግን ይህ ፓስተር ማየት የቻለው እኔ ግን ማየት ያልቻልኩት ምንድነው? ማለቴ ይህ አሥር አመት ያለው ፓስተር ፡፡

መንፈስ ቅዱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." እርሱ እየተከባከበ ያለው ስጦታቸውን ለመጠቀም የተወሰነ ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ብዙ ወጣቶችን ነው፡፡ ስለዚህም ጊዜው አልቋል በማለት በስንፍና ወደኋላ እንዳይመለሱ ነው፡፡ አሁን ለአንቺ እያልኩ ያለሁት አንቺም ሆንሽ መንጋዎችሽ ያላችሁት እዚሁ ነው፡፡ ጊዜያችሁ ገና አላለቀም፡፡ ጨለማው በቅርብ በእናንተ ላይ ይመጣልና ቀን ሳለ አሁን ሥራችሁን ሥሩ፡፡

ቀን ሳለ በምልበት ጊዜ እያልኩ ያለሁት ጥቃቱ እያየለ ከመሄዱ በፊት፣ በህይወት ለመቆየት እንኳን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ መሰደድ ከመጀመሩ በፊት ማለቴ ነው፡፡ አሁን ኢንተርኔት አላችሁ፣ ስጦታና የሚያስፈልጓችሁ ቁሳቁሶች አሏችሁ፡፡ እንዲሁም ቀዩን ዘንዶ ወደኋላ የሚገትት ፕሬዚዳንት አላችሁ፡፡ በተጨማሪም በአለም ላይ በግራና በቀኝ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ለመለዋወጥ የምትችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ አሁን በዚህ ሁሉ አንፃራዊ ነፃነት አላችሁ፡፡ በአጭሩ አሁን ከመንጋው ጋር መቀላቀል ያለባቸውን በጎች ለመጥራት ዕድል ስላለ ይህንን ሥራ ለመተው እጅግ ከባድ ጊዜ ነው፡፡ አውቃለሁ በልብሽ ውስጠኛው ክፍል የምትፈልጊው በእውነት የምትፈልጊው የተሰጠሽን ስጦታ ሳታባክኚ ሩጫውን ለመጨረስ ነው፡፡ ይህንን በደንብ አውቀዋለሁ ምክንያቱም የምኖረው በውስጥሽ ስለሆነና አንቺ በሃዘን ተውጠሽ ስታለቅሺ እኔም አብሬሽ ስለማዝን ነው፡፡ ነገር ግን ደግሞ እንዴት እንደደከመሽና ሰውነትሽ ከዚህ ተጨማሪ እድሜ መሸከም የማይችል እስኪመስል ድረስ እንደደረሰ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ክሌር ይህንን ሩጫ ለመጨረስ የሚያስፈልገውን ሁሉ እኛ ለመስጠት ሙሉ ችሎታ እንዳለን አታውቂምን? እዚህጋ ነው እምነት የጎደለሽና የቡድን ጠንቋዩች ቀለበት ውስጥ የገባሽው፡፡ በነገራችን ላይ እነርሱ ከእኔ ቅባት ጋር ምንም ሊወዳደሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ምናልባት ድንገት ጥርጣሬ ካለሽ ብዬ ነው፡፡ ይህ እንዲሰራ ለማድረግ እኔ የምፈልገው አንድ ነገር አስተሳሰብሽን ከእኛ ጋር እንድታስማሚ ብቻ ነው፡፡ እኔ የምናገረው እውነት ነው፡፡ ከአንቺ የሚፈለገው ይህ ብቻ ነው፡፡

"በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን እግዚአብሔር አብ ከበላይ ሆኖ ሁሉንም ነገር ስለሚመለከት እርሱ ብቻ ነው ሙሽሪት መቼ መምጣት እንዳለባት የሚወስነው፡፡ ነገር ግን እየጠበቅን እያለ ሁላችሁም ከድካማችሁ ወጥታችሁ በተጠንቀቅ እንድትቆሙ የሚያነሳሳችሁን እጅግ ምርጡን መንገድ እንከተላለን፡፡ እናንተ በእድሜ የገፋችሁ ከወጣቱ ትውልድ ብዙ ብልጫ አላችሁ፡፡ በዚህም የምታጠፉት ምንም ጊዜ የላችሁም፡፡ በቀደመው ዘመናችሁ በጠላት እጅ ወድቃችሁ ደርቃችኋል፡፡ የሰውነታችሁም

ሆርሞን የጦፈ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ የሚረዳ ነው፡፡ በሌላ አንፃር ግን ይህ ደግሞ ለመነሳሳት ያላችሁን ስሜት ይቀንሳል፡፡ ስለዚህም በእነዚህ አመታት በላያችሁ ላይ የተጠራቀመውን አቧራ አራግፋችሁ በመውጣት ወደ ቤት ለመሮጥ የምታደርጉትን ሩጫ ለኢየሱስ እንድትሮጡ እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን አሁን ባላችሁ የተወሰነ የአመለካከት ደረጃ ከተቆፈረው ወጥታችሁ ወደ ቤቱ መሰረት ለመጓዝ አትችሉም፡፡ ችግር አለ? አዎ ችግር አለ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ድል ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ በአምልኮ ጊዜ ፈውስን መቀበል፣ እንዲሁም ቀድሞ ለማየት ኃይልን መቀበልና ከማካፍላችሁ ግፊትና ቅባት የተነሳ ወደፊት ቀድማችሁ ለመሄድ ትችላላችሁ፡፡ በአጭሩ ውስን የሆነው አስተሳሰባችሁ መታደስ ያስፈልገዋል፡፡

(ክሌር) ይህ እንቅስቃሴ ላና ቫውሰር (Lana Vawser) በቅርቡ አንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ስለሚመጣው እንቅስቃሴ የተናገረችው ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." እየመጣ ነው ያለው፡፡ ሲመጣም የሚሆነው በውኃ ላይ እንደመንሳፈፍ ነው፡፡ በሁኔታ ውስጥ በመሆን ልትይዙት የምትችሉት በመታዘዝና በአምልኮ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ጌታ ኢየሱስ በትክክለኛው መንገድ ሲመራችሁ ነበር፡፡ አሁን የሚያስፈልገው የበለጠ ጥረትን፣ የበለጠ መታዘዝን፣ በራስ መደገፍ መተውን፣ እርሱን የበለጠ ማመንንና እምነታችሁን በእርሱ ላይ መጣልን ነው፡፡ በሥጋ ራሳችሁን ስላሰመጣችሁ ከዛ ለመውጣት አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ መስሎ ቢታይም እንኳን ብቸኛው አማራጭ ግን መታዘዝ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የምትመለከቱት እናንተ ያላችሁን እንጂ ሊኖራችሁ የሚችለውን አይደለም፡፡ ለራሳችሁ ረክታችሁ ካልተቀመጣችሁ በስተቀር ልትሆኑ የምትችሉት ነገር ብዙ ነው፡፡ በቃን ብላችሁ ረክታችሁ አትቀመጡ፡፡ ለመንፈሴ የመገለጫ ምልክቶችና ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሙላት ጩኹ፡፡ በሩ ለእናንተ እስኪከፈትላችሁ ድረስ አንኳኩ ደግሞ ጩኹ፡፡ ስለዚህ አያችሁ ከውስን አመለካከታችሁ የተነሳ ነው እንጂ ገና ትችላላችሁ፡፡ ወደ ቤት እስክንጠራችሁ እስከመጨረሻው ጠብታ ድረስ በጥንካሬ እንድትሰሩ እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን እናንተ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ከመበርታት፣ መልካምን ለመስራት ቀሪውን ዕድል ከመጠቀም ፣ የተሰጣችሁን ስጦታ ሥራ ላይ ከማዋል፣ ለእግዚአብሔር ብቻ ከመኖር ይልቅ ወደ ኋላ በመመለስና ዕረፍት በማድረግ፣ መጨረሻው እንዲመጣ በመጠበቅ በማይረባ ነገር ጊዜያችሁን አሳልፋችኋል፡፡ ይህ እንዲነግድበት ታላንት ተሰጥቶት ታላንቱን የቀበረውን አገልጋይ አይነት ነው፡፡ ስለዚህም ችላ ብላችሁ የተዋችሁት የትኛው ነገር እንደሆነ በመመርመርና ፈቃዳችሁን አጥብቃችሁ በመያዝ መንፈሳችሁን እንዲታዘዝ ማድረግ ያስፈልጋችኋል፡፡

"ቅዱሳንም ያደረጉት ይህንን ነው፡፡ ሥጋቸውን በኃይል በመጎሰምና የድካም መንፈስ ምን መስራት እንደሚችሉ ወይም እንደማይችሉ ለመወሰን ዕድል ባለመስጠትና በመቃወም መንግስተ ሰማያትን ተናጥቀው ወሰዷት፡፡ 'መንግስተ ሰማያት በብዙ ትገፋለች፣ የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው' ተብሎ አልተፃፈምን(ማቴዎስ 11:12)፡፡ ስለዚህ አያችሁ የሚቀጥለው ሳምንት ወይም የሚቀጥለው ወር ወይም የሚቀጥለው አመት በማንኛውም ጊዜ ወደ ቤት ብትጠሩ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ ራሳችሁን በጌታችሁ ሥራ ላይ ማጥመድ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ይዘገያል በማለት ወደኋላ እንደተመለሱት እንደነዛ ሰነፍ አገልጋዮች አንዳትሆኑ፡፡ ብዙ የሚያሳዝኑ ነፍሶች አሉ የጌታቸውን ሥራ ከመሥራት ይልቅ ዝም ብለው የሚጠብቁ፡፡ የንጥቀቱ ማስጠንቀቂያ መምጣት ሲጀምር እነሱ ሥራቸውን አቆመው በጀርባቸው ተንጋለው ሰማዩን እያዩ "ሩጫውን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ብጨርሰው እመኝ ነበር" ይላሉ፡፡ በፍፁም እኛ የምንጠብቀው ምላሽ እንዲህ አይነቱን አይደለም !!! እኛ የምንፈልገው ካላችሁበት ዘላችሁ በመነሳት እስከምንወስዳችሁ የመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ የበለጠ እንድትሰሩ ነው፡፡ ስለዚህ

የሚነገራችሁ እያንዳንዱ ከባድ የንጥቀት ማስጠንቀቂያ መልዕክት ሲገጥማችሁ ነቅታችሁ ተነሱና ራሳችሁን ወደ ሥራ አሰማሩ የሚል እንጂ ወደኋላ ተመልሳችሁ ከዚህ በበለጠ ለመስራት ነበር የምፈልገው እንድትሉ አይደለም፡፡

"በዚህ ቻናል ብዙዎች አሉ የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ምድር ለማምጣት የሚቻላቸውን ያህል የማይሰሩ፡፡ የሚኖሩት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለራሳቸው ነው፡፡ ይህ ቸልተኝነታቸው ደግሞ የሚያስከትለው ውጤት አለ፡፡ ክሌር ጊዜ ውድ ስለሆነ ከአሁን ወዲያ በፍፁም እንዳታባክኚው፡፡ ወዳጄ እያንዳንዱን ጊዜሽን ተቆጣጠሪ፡፡ እኔ ከአንቺና ከኽርት ድዌለርስ ፍቅር ይዞኛል፡፡ እናም ከጠላት በተሰነዘረባቸው ጥቃትና እንዲሁም ከሥጋ ድካም የተነሳ ዝርክርክ ለሆነ ዝንባሌ ራሳቸውን ሲሰጡ በጣም አዝናለሁ፡፡

ራሳችሁን አሳልፋችሁ ለሥጋ በፍፁም አትስጡ፡፡ በእናንተ ውስጥ የበለጠ ህይወት አለ፡፡ የሚያነቃቃችሁ ንፋስ ደግሞ ለሁላችሁም እየመጣ ነው፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ ከየት እንደወደቃችሁና ቦታችሁን እንደተዋችሁ መርምሩና ንስሐ ግቡ፡፡ ይህም የማይነቃነቅ ዓላማን በመሻሻልና በፍፁም ለውጥ ላይ በማድረግ የአውሬውን ቀንድ ይዞ በመታገል አቧራው ላይ በመጣል ነው፡፡ እናንተ ሁላችሁም ከዚህ የበለጠ ለማድረግ ችሎታ አላችሁ፡፡ ነገር ግን ልትፈልጉትና ልትደርሱበት ያስፈልጋል፡፡ ዋናው ቁም ነገር ንጥቀቱ በማንኛውም ደቂቃ ሊሆን ወይም ሊዘገይ ይችላል፡፡ አሁን ሁላችሁም የሚያስደነግጥና ንቁ የሚያደርግ ጥሪ ደርሷችኋል፡፡ ይህም ጥሪ ጊዜያችሁን በአግባቡ ባለመጠቀማችሁ ለመስራት የተሰጣችሁን ሳትሰሩ ቀርታችሁ በፍርድ ወንበር ፊት ባዶ እጃችሁን ራሳችሁን እንዳታገኙትና እንዳታዝኑ የሚል ነው፡፡

"ይህ ማስጠንቀቂያ የተሰጣችሁ በእርግጥ ተዘጋጅታችሁ እንደሆነ ራሳችሁን በደንብ እንድትፈትሹ ነው፡፡ የተጠራችሁበትን ጥሪ ሁሉንም ስለፈፀማችሁ በውስጣችሁ ሰላም አለ? ወይስ ብዙ ያልሰራችሁት ነገር ስላለ ሐዘን ይሰማችኋል? ይህንን ስላችሁ ግን ንጥቀት ይዘገያል እያልኩ አይደለም፡፡ እያልኩ ያለሁት ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት እንድታዩና ያልሰራችሁት የቀረ ሥራ በትንሹ እንኳን ቢኖር እንድትጨርሱት የሚያስደነግጥ ጥሪ ደርሷችኋል ነው፡፡ እኔ ደግሞ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡

"ከልባቸው ተሰምቷቸው ለሚፀልዩና ልመና ለሚያቀርቡ እኔ ምላሽ አሰጣለሁ፡፡ ሥራችሁን እንዴት አድርጋችሁ በመስራት እጅግ አትራፊ የምትሆኑበትን እኔ እመራችኋለሁ፡፡ በቋሚነት በእያንዳንዱ ደቂቃ እናንተ ትክክለኛውን ምርጫ እንድትመርጡ ለማድረግ ስሜታችሁን ለመሳብ እየሞከርኩ ነው፡፡ ይህንን በሙሉ ልባችሁ እንድታምኑ እፈልጋለሁ፡፡ እናም ከዚህ ደቂቃ ጀምሮ ወደ ቤታችሁ ተወስዳችሁ ለዘላለም ከእኔ ጋር ለመኖር እስክትወሰዱ ድረስ የመጨረሻ አካሄዳችሁን በፊታችሁ አድርጉ፡፡

"ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ዋናው ቁም ነገር ንጥቀት መቼ እንደሚከናወን አይደለም፡፡ ነገር ግን ወሳኙ ነገር እግዚአብሔር በሚመጣበት በዛች ሰዓት ለእርሱ ምን እየሰራችሁ እንዳለ ነው፡፡ መንግስታችን እንዲመጣና ፈቃዳችን እንዲፈፀም ይህንን አስፈላጊ ሁኔታ ማሟላት የምትችሉት ከአሁን ሰአት ጀምራችሁ ችሎታችሁን በከፍተኛ ደረጃ ተግባርያዊ ስታደርጉት ነው፡፡ ኸርት ድዌለርስ በእናንተ እምነት ስለጣልን ይህንን ከእናንተ እንፈልጋለን፡፡ ብርሃናችሁ እያንፀባረቀ ይብራ፣ ዘይታችሁ ሙሉ ይሁን፣ ሁልጊዜም የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መልዕክት በዚህ ላይ ያበቃል፡፡

(ክሌር)፡- የኔ ውዶች ልነግራችሁ የምችለው መልዕክቱን ከመቀበሌ በፊት የጠረጠርኩት ይህ መልዕክት መምጣቱ ነው ፡፡ ይህም በሥራ ተጠመዱ፣ ጊዜውን በብልሃት ተጠቀሙበት፣ ይህ ካልሆነ ግን እጅግ በጣም ታዝናላችሁ የሚል ነው፡፡

ቤተሰቦች የምትኖሩት ለራሳችሁ ከሆነ ይህ የሚያሳየው በንጥቀት እንደማትወሰዱ ነው፡፡ ነገር ግን እየኖራችሁ ያላችሁት የምትችሉትን ያህል ለእግዚአብሔር ከሆነ እንደምትወሰዱ አምናለሁ፡፡

ለእግዚአብሔር ለመኖር በህዝብ የሚታወቅ አገልግሎት ሊኖራችሁ አያስፈልግም፡፡ ማላጆች ተደብቀው እየፀለዩ ለእግዚአብሔር እጅግ ድንቅ ሥራ እየሰሩ ነው፡፡ እናም ፍሬያቸው በአለም ሁሉ እየታየ ነው፡፡ ነገር ግን ማን እንደሆኑ ማንም አያውቃቸውም፡፡ የሚቆሙበት መድረክ ወይም ስልጣን ማንም ሰጥቷቸው አያውቅም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ማን እንደሆኑ ያውቃል፡፡ እናም እነዚህ ሰዎች ወደ ቤት እስከንጠራ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እየሰሩ ናቸው፡፡ ዝግጁ አለመሆናችሁ ለሚሰማችሁ ለእናንተ እንዲህ እላለሁ እኔም ዝግጁ አይደለሁም፡፡ ስለዚህም ሁላችንም ከሰአቱና ከጊዜው አቆጣጠር ላይ አይናችንን እናንሳና በእኛ ውስጥ ባለው ኃይል መጠን ጌታን ለመታዘዝ በተሰጠን ስጦታ እንስራ፡፡ ያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በንጥቀቱ በድንገት ያስደስተናል፡፡ ነገር ግን ተቀምጣችሁ "ንጥቀት የተባለው ታዲያ የት አለ" የምትሉ ከሆነ እናንተ ምናልባት ሳትነጠቁ በምድር ላይ ትቀራላችሁ፡፡

ስለዚህ ስህተቶቻችንና ጉድለቶቻችንን ለማረም እንነሳ ፡፡ የሠርግ ልብሳችንን እንጠብ፣ ከሠርግ ልብሳችን ላይ የቆሻሻ ነጠብጣቦችን ሁሉ እናፅዳ፣ የተጨራመተውን እናስተካክል፣ የጎደፈውን ሁሉ እንጠብ፡፡ በተሰጠንን ሥራ እንጠመድ፡፡ ቤተሰብን በመከባከብ ሙዚቃ በመድረስ ወይም በጓዳ ጠላትን በመዋጋት ቢሆን በተሰጠን በዛው እንጠመድ፡፡ እኛ ወደ ሥራ እንግባ፣ ለእርሱ በእውነት ለእርሱ ብቻ እንኑር በትክክለኛውና ፍፁም በሆነው ሰዓት ደግሞ እንወሰዳለን፡፡ ሁሉ ነገር ይታያል፣ የእግዚአብሔር ጊዜ እንከን የለበትም፡፡

ክርት ዱዌለርስ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡

## ወደ ሰማያዊው ቤታችሁ መዘርጋት - ዲሴምበር 28 ቀን 2020 ዓ.ም.

## The Home Streach, December 28th, 2020

(ክሌር)፡ - ጌታ በደስታው ያጠንክራችሁ፡፡ እንዲሁም በዚህ ምድር ላይ እንድትሰሩ የሰጣችሁን ሥራ ለመጨረስ የሚያስችላችሁን ፅናት ይስጣችሁ፡፡ የኔ ውዶች በ2017 ዓ.ም የተቀበልኩትን መልዕክት እንደገና በድጋሚ ላስተላልፈው እየተዘጋጀሁ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ መልዕክት አሁን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ ምን ያህል እንደምንቆይ ምንም የሚያስተማምን የጊዜ ገደብ የለም፡፡ በተሰጠን የፀጋ ስጦታ የተጣለብንን አደራ በተቻለ ትኩረት መጠን መስራት አለብን፡፡ አሁን ስለ ንጥቀት የሚነገረው ማስጠንቀቂያ እንድንነቃቃ ለማድረግ ሳይሆን ይህ እውነተኛው የመጨረሻው ለመነጠቅ እየተሰጠ ያለ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡

በ2017 ዓ.ም ለመነጠቅ ተጨማሪ አመታት ይመስለኛል አምስት አመት ሊጨመር ይችላል የሚል ሐሳብ ነበር፡፡ ነገር ግን ጌታን እየሰማሁ የነበርኩት ነገር "የተላከሽበትን ተልዕኮ ለመፈፀም ራስሽን በሥራ ጥመጂ እንጂ ቁጭ ብለሽ ንጥቀትን አትጠብቂ አለበለዚያ አትነጠቂም" የሚል ነበር፡፡ ይህ የተረጋገጠ ነው፡፡ ጌታ በዚህ ነገር አሁንም እያነሳሳን ያለው በዚህ በቀረው ህይወታችን የምንችለውን

ያህል በሥራ እየተጋን በሰማያት ያለችውን የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ምድር እንድናመጣ ነው፡፡ ነገር ግን ተመልሳችሁ ቁጭ ካላችሁ እንደገና አንዴ ማሰብ አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም ሳትወሰዱ ልትቀሩ ትችላላችሁና ነው፡፡

ጌታ እየተጫወተ አይደለም፡፡ ነገር ግን እርሱ ለብ ያሉ ክርስቲያኖች እንዲነሱ ዕድል እየሰጣቸው ነው፡፡ ይህም ቸልተኝነታቸውንና ግድየለሽነታቸውን በመተው በሥራ እንዲጠመዱ እየነገራቸው ነው፡፡ እኔም እንደነሱ በነበርኩበት ወቅት የተናዘዝኩበት ጊዜ ነበር፡፡ በምንም አይነት መልኩ ራሳችሁን በሥራ ካላጠመዳችሁና ለራሳችሁ ብቻ የምትኖሩ ከሆነ የታላቁን መከራ ዘመን እዚህ ልታሳልፉ ወይም ልትሞቱ ትችላላችሁ፡፡ ቤተሰቦች ከዚህ በኋላ ጨዋታ የለም፡፡ ይህ እርግጡ ነገር ነው፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ጌታ ኢየሱስ በኦክቶበር 2017 ዓ.ም የተናገረውን ያንኑ አሁን እየደገመው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እየተነገረ ያለው መልዕክት ከዛን ጊዜ የሚለየው በዛን ወቅት ተጨማሪ ጊዜ ሊኖር ይችላል የሚል የተስፋ ቃል ነበር፡፡ ነገር ግን በአሁኑ መልዕክት "ምንም የሚያስተማምን የተሰጠ ጊዜ የለም" የሚል ነው፡፡ስለዚህም በሚቀጥለው ወር በድንገት ሁሉም ነገር ሊያበቃ ይችላል ወይም ደግሞ ሊቆይ ይችላል ማለት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ ወደ ቤታችን ለመሄድ በመዘርጋት ላይ መሆናችንና በማንኛውም ደቂቃ መለከቱ ሊነፋ እንደሚችል የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው ማለት ነው፡፡ ኩራዛቸውን አብርተው ተጨማሪ ዘይት ይዘው ጌታቸውን የሚጠባበቁ ደስተኞች ናቸው፡፡

በ2017 ዓ.ም የተሰጠው መልዕክት ውስጥ የጠየቀንን አንዳንድ ነገሮች አሁንም በዚህ ጊዜ እየጠየቀን ነው፡፡ በዛ መልዕክት ውስጥ አምስት፣ ሶስት ወይም ሁለት አመት ተጨማሪ አመት ይኖራል ብሎ የተወሰነ የአመታት ጭማሪ እንዳለ ምንም ማረጋገጫ አልሰጠንም ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁንም እንደዛው የጊዜ ገደብ የለም፡፡ ነገር ግን አሁን በእርግጠኝነት ወደቤታችን ለመሄድ በመዘርጋት ላይ እንገኛለን፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ ጌታ ይባርካችሁ፡፡ ይህ መልዕክት እጅግ ጥሩና ወደፊት ለመጓዝ ጥንካሬና ብርታት የሚሰጣችሁ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እንዲህ በማለት መልዕክቱን ላስተዋውቃችሁ እፈልጋለሁ፡፡ የዚህች ምድር ቅጣት እንዲቆይ ለማድረግ የመጨረሻ ዕንባቸውን እነማን እንዳፈሰሱ አናውቅም፡፡ ነገር ግን የተሰበሩ ልቦች ሁሉ ፣ የዕንባ ወንዞች፣ ፆምና ህመሞች ሁሉ ተጨማሪ ጊዜ፣ ተጨማሪ ቅባትና ተጨማሪ ምህረት እንዲሰጥ ለአብ እንደ ስጦታ ቀርበዋል፡፡ ይህም ደግሞ ተሰምቷል፡፡ ስለዚህም ከጦርነቶች ሁሉ የከፋው ጦርነት እንዳይከሰትና ንጥቀት እንዳይሆን ትዕዛዝ ከመስጠት የእግዚአብሔርን እጆች ከልክሏል፡፡ ከዚህም የተነሳ ጊዜው ተራዝሟል፡፡

አንዳንዶቻችሁ ይህንን የተናገረው ጌታ እንደሆነ ለማመን ትጠራጠሩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንድ መናገር የምችለው ነገር ዛሬ ምሽት ይህንን መልዕክት ሲሰጠኝ ለብዙ ጊዜ ያላየሁት ጥንካሬና ግልፅነት ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት መልዕክቱ ከእርሱ መሆኑን ማረጋገጫ ሆኖኛል፡፡

ኢየሱስ ዛሬ ምሽት ፈቃድህን ገልጠህልናል፡፡ እናመሰግንሃለን፡፡ እባክህ የሰጠኸንን ጊዜ በታማኝነት እንድንጠቀምበት ኃይል ስጠን፡፡ አሜን፡፡

ዛሬ ምሽት ከጌታ ዕራት በኋላ ጌታ ኢየሱስ ስለ ንጥቀቱ ጊዜ መናገር ጀመረ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ . . . " ስለ ክስተቶች ቅደም ተከተል ለማወቅ እንደምትጓጉ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው አሁንም ትንሽ ጊዜ እንዳለ የምነግራችሁ፡፡"

(ክሴር)፡- ይህ ምን ማለት እንደሆነ ይገባኛል፡፡ ነገር ግን አምስት አመት? ብዬ ጠየኩት፡፡

እርሱም "ምናልባት፣ በምድራዊ አቆጣጠር ከቆጠራችሁትና ጊዜውን በደንብ ከተጠቀማችሁበት ብዙ ሊሰራበት ይችላል፡፡ በዛውም መጠን ደግሞ መሰናከልም ሊኖር ይችላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ብዙ ክፉ ድርጊት ተፈፅሞ በግልፅ ሊታይ ይችላል፡፡ ለዚህ ነው እንደ ግብፅ ወረርሽኝ የተራባውን የክፉን ስራ በጩኸት እንዲጥሉና ክፉና ጠማማውን በፀሎት እንዲያወርዱ ግንባር ቀደም የቡድን ማላጀችን  የምፈልገው፡፡

"ክሴር በልብሽ ተጨማሪ ጊዜ እንዳለ ታውቂያለሽ፡፡ ይህንን ታውቂያለሽ አይደለም?"

ጌታ አዎን አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ጊዜው እያለቀ ነው ብለሃል፡፡

ጌታም "አምስት አመት ደግሞ እንደ አምስት ደቂቃ ነው" አለ፡፡

"ተወዳዳሪ የሌለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ሊሆን ነው፡፡ የኔ ታማኞች ደግሞ ወደዛ እየገቡ ነው፡፡ ብዙዎች ለብዙ አመታት ስለተዘጋጁና ከእኔ ጋር ስለተጣበቁ ፍሬ አፍርተዋል፡፡ ነገር ግን አሁን አዲስ ትውልድ አለኝ፡፡ አዲስ ራዕይ ያላቸው አዲስ ወታደሮችና ሙሽሮች አሉኝ፡፡ እነዚህም የኔን ፍቅር በጨለማው ጥግ ሁሉ እንዲያሰራጩ ነው፡፡ ደግሞም እያሰራጩ ነው፡፡

"በአለም ላይ ሁሉ የእምነት ፍንዳታ ሊፈነዳ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአንዳንድ አገልጋዮችና አገሮች ጀምሯል፡፡ ይህ በኃይል እንዲጨምር አደርጋለሁ፡፡ ይህንን ፍንዳታ በቅዱሱ መንፈሴ እያቀጣጠልኩት ነው፡፡

"ብዙ ሲነገር የነበረው ትንቢት አሁን መፈፀሚያው ነው፡፡ አሜሪካ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንዲሆን ፊት መሪ ትሆናለች፡፡ አባቴና እኔ ተጨማሪ ጊዜ ተጨማሪ ቅባትና ተጨማሪ ምህረት እንዲሆን መርጠናል፡፡

"ይህም ቢሆን ግን ሙሽሮቼ መሳሪያችሁን እንድታስቀምጡ ሳይሆን የምጠራችሁ ወደ ምድር እያመጣሁ ያለሁትን እንድትጠብቁ ነው፡፡ ለዚህም አንቺ ወይም ኽርትድዌለርስ መፆማችሁን እንዲሁም መተው ያለባችሁን እንድትቀጥሉ የምፈልገው ሁላችሁም በትልቅ ስጦታ ምህረቴን ወደ ምድር ለመጥራት እንድትታጠቁ ነው፡፡

"ይህንን ሁኔታችሁን በማየት በብዙዎች አትወደዱም፡፡ ብዙዎች ያሽሟጥጧችኋል፣ የሐሰት ወሬዎች ይነዙባችኋል፡፡ አንዳንዶች ቻናሉን ትተው ይሄዳሉ፡፡ ነገር ግን ልቤ ለእናንተ ለሁላችሁም ራሳችሁን የመካድ ህይወት እንድትኖሩ፣ ቀላል ህይወት እየኖራችሁ ሥጋችሁ አርጅቶ እስኪሞት ወይም በራሃብ እስኪሞት ድረስ ተሸፍኖ እንዲኖር ነው፡፡ ነገር ግን እስከዚያው ድረስ በቅባቴ እየጠነከራችሁ፣ እየጠነከራችሁ ትሄዳላችሁ፡፡

"ለመፆምና ለማዘን ጊዜ አለ፣ ደግሞም የሐዘን ልብስን አውልቆ የምስጋናን ልብስ የማንሳት ጊዜ አለ፡፡ ነገር ግን አሁንም የምጠራችሁ ሥጋችሁን ፀጥ እንድታሰኙ ነው፡፡ ይህ ምን ይመስላል? ሆዳችሁ የሚፈልገውን ጣፋጭ ምግብ ለመስራት ብላችሁ ብዙ ሰአትን በማዕድ ቤት አታጥፉ፡፡ ገንዘባችሁን ውድ የሆነ ምግብ ለመግዛት አታውሉ፡፡ ቀኖቻችሁን የሦስተኛው አለም ሰዎች እንደሚኖሩት ኑሩ፡፡ ይህም ቀላል ምግብ ሆኖ ለሰውነት የሚጠቅም ምግብ ብሉ እንጂ በጣም ጣፋጭ ሆኖ ለሰውነት የማይጠቅመውን ምግብ አትብሉ፡፡"

(ክሴር)፡-  ጌታ እንደ ቴራሚሱ ኬክ አይነት ማለት ነው?

"በትክክል፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ ኃብት ከሥጋ ፍላጎት በልጦ ብታገኙትም እንደ እነዚህ አይነት ጣፋጭ ምግቦች በመንግስተ ሰማያት ይጠብቋችኋል፡፡ በመንግስተ ሰማያት ዘላለማዊ ደስታ ቢኖራችሁም የተትረፈረፈ የበለፀጉ ምግቦችም ይኖራችኋል፡፡ በተለይም በግብግባ ቀናት፡፡"

(ክሌር)፡- የግብግባ ቀናት?

"አዎን ታላላቅ የድል መታሰቢያዎችና ታሪካዊ ምልክቶች አሉ፡፡ እነዚህም ህዝቤን ነፃ አውጥቼ በመንፈሴ ያጠብኩባቸው፣ በአንድነት ከክፉ ነፃ ያወጣኋቸው መታሰቢያዎች ናቸው፡፡ በእርግጥም በምድር አይታችሁ የማታውቁት ክብረ በአላት ይኖራሉ፡፡

"ነገር ግን ለአሁን የምፈልገው የእኔ ለመሆን የሚያውቁትን ነው፡፡ የተገረዝና ከአለም የተለየ ህይወት እንዲኖሩ፤ በልባቸው ለአለም የማይቃጠሉ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ፡፡ ደግሞም እኔ እንደመረጥኳቸው በማወቅ ከጥፋተኝነት በፀዳ ህሊና በነፃነት እንዲያመልኩኝ እፈልጋለሁ፡፡ ዛሬ ማታ ወደ አንቺ መጥቼ ከአንቺ ጋር መሆን እንዴት ደስ እንደሚለኝ እንደነገርኩሽ ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በምድር ላይ እየለቀኩት ላለው ፀጋ ይህ ፍፁም አስፈላጊ ነው፡፡ ምንም ነገር ቢሆን ከእኔ ወዳጅነት ጋር የሚደራደር ነገር አታድርጉ፡፡ ምህረቴንና ትዕግስቴን እንዳትሞክሩ ፡፡ ይልቅስ በትንሽ ነገር እንኳን ታማኝ ሁኑ፡፡"

(ክሌር)፡- እኔ እዚህጋ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ እኔ ከዚህ ቀደም አንድ ነገር ለማግኘት ሁለት የሚያህሉ የማይረቡ ፈታኝ ሐሳቦች ነበሩብኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ታዲያ ወደራሴ ፍላጎት ስሳብ ወይም እርሱ ጭራሽ የማይደሰትበትን ነገር እያወቅሁ ላደርግ ስል ጌታ ራሱን ከእኔ እንዴት ያርቅ እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡ ያ ደግሞ ጉዳት የሚያስከትል ስለሆነ ላደርገው አልችልም ነበር፡፡ ይህም እኔ ለማድረግ የምፈልገው ነገር አስፈላጊነቱ ከእርሱ ጋር ካለኝ ህብረት ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም እጅግ አናሳ ነገር ነው፡፡ ስለዚህም ባለፉት አመታት የማደርጋቸው የግልግል ሐሳቦች ጥፋተኛ አድርገውኛል፡፡ ነገር ግን ብዙ ዋጋ አስከፍለውኛል፡፡ ስታበላሹ ደግሞ በእርግጥ ታውቁታላችሁ፡፡እናም የእርሱ ዝምታ ደግሞ እጅግ ያማል፡፡

ኢየሱስም . . ."እኔ የምመኝላቸው ትልቁን ስጦታ ለማግኘት እንዲገፉበት ነው፡፡ እነዚህም የትንቢት፣ የፈውስና የደንቅ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች ስለ እኔ ኃይልና ስለ ፍቅሬ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ስጦታዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ከአለም ደስታ መራቅ አለባቸው፡፡ ኃጢያት መስራት እንደሌለባቸው ደግሞ የታወቀ ነው፡፡ ፍላጎታቸውን የተሻሉ ነገሮችን ከመምረጥና ብዙ ከመፈለግ መቆጠብ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ጥሩ ምግብ፣ ጥሩ ልብስ፣ በድሆች የማይታወቁ ቅንጦና ምቾት ያላቸውን ነገሮች መተው አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ በውስጣችሁ ለሚኖረው መንፈስ መርዞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም በሥጋ ላይ ጥገኛ ሆናችሁ ወደታች እንድትወርዱና ራስ ወዳድነትን እንድትጨምሩ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

"ይህ አይሆንም፡፡ እኔ የምፈልገው እስረኞችን  የሚፈታ የተሻለ ስጦታ ለማግኘት እንዲጥሩ ነው፡፡ ይህ ሥራ ነው፡፡ ይህ ከተጣበቃችሁበት የበለጠ በመላቀቅ በዙሪያችሁ ያሉትን ሌሎችን ሰዎች እንድትንከባከቡ የሚያደርግ ትልቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ ሁላችሁንም ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ፍቅር ወደምትሰጡበት ህይወት እየጠራኋችሁ ነው፡፡ ከአለም ራሳችሁን እየለያችሁ በሄዳችሁ ቁጥር በደረሳችሁበት ሁሉ ቸርነት ለማድረግ የተቃጠላችሁ እንድትሆኑ ፍቅርን እጨምርላችኋለሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ቶሎ ወደ ገበያ ቦታዎች በሄደ ጊዜ ሥራው ሰዎችን ማገልገል በመሆኑ እርሱን ባየሁ ጊዜ ሁሉ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኛል፡፡ እኔ ወደ ገበያ ቦታዎች ስሄድ የምፈልገውን ገዝቼ ቶሎ መውጣት እንጂ በዙሪያዬ የሚገኙትን ለማገልገል አስቤም አላውቅም፡፡ እኔ የምፈልገው ከዛ ቶሎ መውጣት ብቻ ነው፡፡ ይህ መጥፎ ነገር ነው?

ኢየሱስም . . . "አንድን ነፍስ ስታገለግዪ ምን ይሰማሻል?"

(ክሌር)፡- በጣም ድንቅ ነገር ይሰማኛል፡፡

ኢየሱስም . . . "እንደዚያ ነው መሆን ያለበትም፡፡ ራስሽን ስትክጂ በገበያ ሥፍራ የቀረበው ነገር ምንም ስሜት አይሰጥሽም፡፡ በምትኩ የተጎዱ ነፍሶችን በእኔ ፍቅርና በሚያፅናና ቃል ለመንካት እድል ትሰጫለሽ፡፡ ራስሽን ስትክጂ፣ ራስሽን መውደድ ትተሽ ፍላጎትሽን ባዶ በማድረግ በውስጥሽ ያለው ፍቅሬ እንዲቆጣጠርሽ ሥፍራን ትሰጫለሽ፡፡

"ይህ ደግሞ አንቺንም ገጥሞሽ ያውቃል፡፡ ታዲያ ያ እጅግ የሚያስደስትና ያንን ለማድረግ የሚጠይቀውን ሁሉ ቢወስድ የተገባ አልነበረም?"

(ክሌር)፡- ጌታ አዎ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሚሰጠኝ ደስታና እርካታ ነው፡፡

(ኢየሱስ)፡- "የመጣሁት ህይወትን ላበዛላችሁ ነው" ማለቴ እኮ ይህንን ነው፡፡ ይህ ነው የተትረፈረፈ ህይወት ማለት፡፡ ምክንያቱም ህይወት አላችሁ፡፡ ስለዚህም ነው ህያውነትን ለሌሎች የምታገለግሉት፡፡ እናንተ በእውነትም አምባሳደሮቼ ናችሁ፡፡ ስለዚህም ሞኝ ለሆነ ነገር መስጠት ያለባችሁ ሥፍራ ትንሽ ስለሆነ ራሳችሁን ለትንሽ ነገር አታነሳሱ፡፡

"አንቺንና ህዝቄልን በተመለከተ ሌሎችን በከፍተኛ ደረጃ ማገልገል እንዲትችሉ በአገልጋዮቼ ላይ ከባድ የሆነ ፈውስ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን ማስታወስ ያለባችሁ ምንግዜም ቢሆን የስምዖን አይነት መስቀል የመሸከም ስጦታ እንደሚኖር ነው፡፡ ይህ ሁልጊዜም የሚኖር ነው፡፡ ነገር ግን ሥጋቸውን ከሥጋ ደስታ ለለዩ ህመሙ እየቀነሰ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

"አውቃለሁ ይህ ለብዙዎቻችሁ ቀላል አይሆንም፡፡ ነገር ግን ለዚህ መስቀል ብዙዎችን አልጠራሁም፡፡ ለዚህ ሥራ የጠራሁት በጣም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን ሙሽሮቼን ነው፡፡ ወደ ከፍታ መውጣቱ ግን ገና አላለቀም፡፡ ፈቃደኞች ከሆናችሁ ከዚህ በበለጠ ወደ ተራራው ከፍታ እንወጣለን፡፡

"ራስን የመካድ ህይወት መኖር ለሁሉም አይደለም፡፡ ፍሬው ግን ሁሉም የሚያየው ይሆናል፡፡ ስለዚህም አንዳንዶቻችሁ በእርሻው ላይ ለመሳተፍ እንቢ ያላችሁ በሌሎች ላይ የታየውን ፍሬ ስትመለከቱ እናንተ ብትወጡ ኖሮ ምን ልትሰሩ ትችሉ እንደነበር በማሰብ ሐሳባችሁን ትቀይሩና የኔን ፈቃድ መፈፀም ትጀምራላችሁ፡፡

(ክሌር)፡- ኦ! ይህ እኔንም የሚመለከት ነው፡፡ ጌታ እዚህ ላይ ግልፅ እንዲሆን ስለዚህ ገና አምስት አመት አለን ማለት ነው?

ኢየሱስም . . . " አይደለም፡፡ እያልኩ ያለሁት ከዚህ በፊት ሦስት አመት ብለሽ ካሰብሽው የበለጠ ጊዜ አለ ነው፡፡ እያልኩ ያለሁት አባቴ ከመጨረሻዋ ሰዓት በፊት ምህረቱ እንዲያብብ ቁርጥ ውሳኔ ወስኗል፡፡ ይህም ከዚያ በኋላ ማንም አጥሩን መዝለል እንዳይችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሥጋ ፍላጎታችሁን ቅድሚያ ስጥታችሁ ለብ ያለ ህይወት እየኖራችሁ እንዳላችሁ ለምታውቁ ለእናንተም ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሙሉ ክብር ያላቸው ወንድና ሴት ልጆች ሆኖ ለማደግ ዕድል አላችሁ፡፡

ጥሪ እያቀረብኩ ያለሁት ህይወታችሁን በኃጢያት እየመራችሁ ያላችሁ፣ ነገር ግን ደግሞ በመጨረሻዋ ደቂቃ የእኔ ምህረት እንደሚሸፍናችሁ ተስፋ እያደረገችሁ ላላችሁት ነው፡፡ ይህ አይሆንም በዛች ሰአት ምህረቴ አይሸፍናችሁም፡፡ ከአሁን ጀምራችሁ እኔ ለጠራኋችሁ ህይወት መኖር ጀምሩ ወይም ደግሞ እዚህ ቀርታችሁ የስቃይ ህይወት ኑሩ፡፡ ምርጫው የእናንተ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ለመነሳት የሚያስችል ሰባሪ አላችሁ፡፡

መዳናችሁን ለሌላ ጊዜ አታስተላልፉት፡፡ ወደ ጎንም አታድርጉት፡፡ በኃጢያታችሁ አፈርና አመድ ላይ ትጣላላችሁ፡፡ አንድ ላይ መኖር ከያዛችሁ ተጋብታችሁ ኑሩ ወይም ተለያዩ፡፡ የምትሰርቁ ከሆነ አቁሙና የሰረቃችሁትን መልሱ፡፡ ለራሳችሁ ብቻ የምትኖሩ ከሆነ ድሆችን ማገልገል ጀምሩ፡፡ ምንም ለሌላቸው ስጡ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ስለዚህ እያልክ ያለኸው ተጨማሪ ሦስት ወይም አራት አመት አለን ነው?

ጌታም . . ." ደርሰሽበታል ነገር ግን ትክክለኛውን የጊዜ ሰሌዳ አልነግርሽም፡፡ ነገር ግን የአባቴ ፍርድ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ በኩል በምድር ላይ መገለጡ እየጨመረ እንደሚሄድ መንገር አለብኝ፡፡ ብቸኛው ማምለጫ ሊሆን የሚችለው በማንኛውም ጊዜ ወደቤታችሁ ለመጠራት የሚያስችላችሁን ህይወት መኖር ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም መተማመኛ አልሰጣችሁም፡፡

"ትክክለኛ የሆነውም ትክክለኛ ያልሆነውም አንድ ላይ ይሞታሉ፡፡ በመጨረሻው ግን የሁለቱ መገኛ ሥፍራ ፍፁም የተለየ ነው፡፡

"እየነገርኳችሁ ያለሁት የተሰጣችሁን ስጦታዎች ፍሬ እንዲያፈራ አድርጉ ነው፡፡ በቅባቴ ጠንክራችሁ ሥሩ፡፡ ለራሳችሁ መኖርን አቁሙ፡፡ የሥጋ ፍላጎታችሁን መመገብ ትታችሁ ደካማውንና የቆሰለውን በመፈለግ ባላችሁ አቅም ማድረግ የምትችሉትን አድርጉ፡፡

"በገበያ ሥፍራ እንድታገለግሉ ከተጠራችሁ በዛ ሥፍራ ማገልገል የያዙትንና በወንጌሉ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ደግፉ፡፡ እኔ በምመጣ ጊዜ መልካም ይሆንላችኋል፡፡ በእውነት እላችኋለሁ ሽልማታችሁን ታገኛላችሁ፡፡

"እያንዳንዱ ቀን የመጨረሻው ቀን እንደሆነ በማሰብ በፊቴ ኑሩ፡፡ ምክንያቱም የምጥ ጊዜው እየተቃረበ ሲሄድ ጣሩ እየበዛ እንደሚሄድ ሁሉ ወረርሽኙ፣ ጦርነቱና በምድር የሚከሰተው አሰቃቂ አደጋ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ መቼ እንደምጠራችሁ ቀኑን አታውቁም፡፡ ስትጠሩ ደግሞ ምን እንደሰራችሁ ትጠየቃላችሁ፡፡

"ስለዚህም ለእኔና ለአጀንዳዬ አሁን መኖር ጀምሩ፡፡ ይህንን ስታደርጉ በመንግስተ ሰማያት ኃብትን ታከማቻላችሁ፡፡

" በሞኝነት ታላንታችሁን ቀብራችሁ የኔን መምጣት ብቻ በመጠባበቅ ራሳችሁን ላጠመዳችሁት ለእናንተ ደግሞ እንዲህ እላለሁ አሁን ነገሮችን ለማስተካከል እድል አላችሁ፡፡ ተነሱና በሥራ ተጠመዱ፡፡ በእኔ ጉዳይ ላይ ከተጠመዳችሁ ቀኑን ወይም ሰአቱን ማወቅ አያስፈልጋችሁም፡፡ ደግሞም ከንጥቀት ወደኋላ አትቀሩም፡፡

"በዚህ ጉዳይ ላይ ስህተት መፈፀም የለባችሁም፡፡ ራሳችሁን በቤት ጣርያ ላይ የሰቀላችሁ፣ በራስ ወዳድነት ጊዜያችሁን እያሳለፋችሁና በነፃ ጉዞ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመሄድ በመጠባበቅ ላይ ያላችሁ ሳትወሰዱ ትቀራላችሁ፡፡ በንጥቀት የሚወሰዱት በእኔ ስራ ላይ ራሳቸውን ያጠመዱ ወይም ህይወታቸውን በታማኝነት የመሩ፣ እንዲሁም ልጆቻቸውን መስጠትና ማገልገል እንዴት እንዳለባቸው የሚያስተምሩት ብቻ ናቸው፡፡

"እኔን መስማትና ማየት አልመቻላቸውን በመናገር የቀጠላችሁ እናንተን እንዲህ በማለት እገስፃችኋለሁ፡፡ በበቂ መጠን አልፈለጋችሁኝም፡፡ እንዲሁም ከአለም ጋር ተደባልቃችሁ እየኖራችሁ ስለሆነ በአንድ ልብ ከእኔ ጋር እየኖራችሁ አይደለም፡፡ ለእናንተ ሁሉ ነገራችሁና ሁለንተናችሁ አልሆንኩም፡፡ ወይም እኔ እንዲህ በማለት መተማመኛ እሰጣችኋለሁ፡፡ ከእኔ ጠንካራ ምሪት፣ ጠንካራ እጅና አፍቃሪ ክንድ ውጪ አትሆኑም፡፡

"በመልካም ልብ ሆናችሁ አንድን ሰው ለማግኘት ከመንገዳችሁ ወጥታችሁ ስትሄዱ ሳቅፋችሁ  አልተሰማችሁም? ጥልቅ የሆነው ምስጋናዬ አልተሰማችሁም? ለዚህ ሚስጥሩ በየቀኑ የበለጠ ማድረግ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የኔን መገኘትና ለእናንተ ያለኝን ማረጋገጫ ለመሰማት የለመዳችሁ ትሆናላችሁ፡፡

"ይህንን ማረጋገጫ ይዛችሁ ተስፋ አድርጋችሁ ወደ ፀሎት ሥፍራችሁ በመሄድ የልብሴን ጫፍ እስክትነኩ ድረስ በራችሁን ዘግታችሁ ፀልዩ፡፡

"አብዛኛዎቻችሁ ከስንፍና የተነሳ እኔን ለመስማትና ለማየት አለመቻላችሁን በልባችሁ ታውቁታላችሁ፡፡ ለዚህ የተገባችሁ እንዳልሆናችሁ በልባችሁ ራሳችሁን አሳምናችኋል፡፡ ምክንያቱም ራሳችሁን ከእኔ ቆጥባችኋልና ነው፡፡

"ይህ ሥራ እኮ ለፅድቅ የሚሰራ ሳይሆን ከማፍቀር የተነሳ የሚሰራ ሥራ ነው፡፡ አንድን ሰው ስታፈቅሩት የእናንተን ቅድሚያ በሙተው ያፈቀራችሁትን ሰው አጀንዳ መፈፀም ትጀምራላችሁ፡፡ ይህንን ስታደርጉ ግን ከዛ ሰው ጋር መገናኘትና ማውራት ትጠብቃላችሁ፡፡ ምክንያቱም እየኖራችሁ ያላችሁት ላፈቀራችሁት ለዛ ሰው ስለሆነ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- በጣም የሚገርም ነው፡፡ ይህ ሐሳብ ይህንን መልዕክት ጨርሼ የተቀበልኩት የሬማ ቃል ነው፡፡ የሬማ ቃሉም እንዲህ ይነበባል፡፡ "አገልጋዩ በዛ ቀን መፆም ፈልጎ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የሚጠበቅበት ሥራ ደግሞ ቀኑን ሙሉ በመቆፈርና በማረስ እንዲያሳልፍ ነው፡፡ ወይም የፈለገውን ሌላ ሥራ ነው፡፡" ይህ አገልጋይ በአግባቡ ምሪት የተቀበለ ከሆነ እንዲህ ብሎ ያስባል፡፡ "ፆሜ ይህንን ሥራ ብሰራ ምናልባት ጌታዬን እንደሚፈልገው መጠን ላለስደስተው እችላለሁ" ፡፡ ታዲያ ይህ ሰው ምን ያደርጋል? ስለዚህም ይህ ሰው ቁርሱን ይበላና ራሱን ወይም ሥጋውን በሌላ አይነት መንገድ ይክዳል፡፡ በዚህም አንፃር አንድን ነገር ለማከናወን ስንፈልግ ሁልጊዜ መምረጥ ያለብን ለእግዚአብሔር ትልቅ ክብር የሚሰጠውን ነገር ሊሆን ይገባል፡፡" ይህንን ማን እንደተናገረ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ነገር ግን ቅዱስ ጆን ቫኒ ይመስለኛል፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." የኔ ሙሽሮች በአጠቃላይ በትክክለኛው ባቡር ላይ ነው ያላችሁት፡፡ የኔ ሙሽሮች በሥጋ አትፁሙ፡፡ በሌላ አነጋገር እኔ እንድመራችሁ ፍቀዱ፡፡ የተለያዩ የፆም አይነቶችን አዘጋጅታችሁ በሬማ ካርድ ሳጥናችሁ ውስጥ አስቀምጡ፡፡ በየቀኑ የሬማ ካርዱን ስትጠቀሙ(ስትስቡ) የፆም የሬማ ካርድ ከወጣላችሁ በወጣላችሁ የፆም አይነት ትፆማላችሁ፡፡ የፆሙ ዓላማ እናንተን ለማስራብ ሳይሆን የምግብ ምርጫ እንዳይኖራችሁ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም ምግብን የምትበሉት ለሰውነታችሁ ስለሚያስፈልግ እንጂ ምግብን ከመውደድና ከምግብ ደስታን ለማግኘት እንዳይሆን ለማድረግ ነው፡፡"

*"ሁላችሁም የቀን የሬማ መልዕክት ማስቀመጫ ሳጥን እንዲኖራችሁ አበረታታለሁ፡፡ ይህም ልክ እለታዊ የዳቦ ሳጥን ወይም ኢንዴክስ ካርድ ሳጥን ሆኖ በውስጡ ኢንዴክስ ካርዶች ያሉበት ማለት ነው፡፡ ይህም ሊዳብር የሚችለው ጌታ የሚሰጣችውን የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል፣ የትንቢት ቃል፣ በራሳችሁ በኩል ይሁን ወይም በነቢያቶች በኩል የሰጣችሁን የተስፋ ቃሎች በተለያዩ ካርዶች በመፃፍ እዚህ ሳጥን ውስጥ አስቀምጡት፡፡ ከዚያም በጣም ከፍ ስትሉ፣ ስትደርቁ ፣ከጌታ ጋር መገናኘት ሲሳናችሁ እና ድምፁን መስማት ሲከብዳችሁ፣ «ጌታ ሆይ ወዴት ነህ?» ማለት ሲሰማችሁ ይህንን አድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ለመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ፡፡ ከዚያም የውሸት መናፍስቶችን በሬማ ሳጥኑ ላይ እንዳይሰራ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም በማሰር ከመልዕክት ሳጥኑ ውስጥ ሶስት ካርድ ውሰዱ፡፡ ካርዶቹንም በምታነቡ ጊዜ አሁን በምን ደረጃ ላይ ወይም ሁኔታ ላይ እንደምትገኙ እንድትገነዘቡ፣ እንዲሁም ካላችሁበት የዝቅታ ሥፍራ እንደሚያወጣችሁና ለዚህም ጌታን እንድታምኑት ይረዳችኋል፡፡"* (ይህ ስለ ሬማ ካርድ አዘገጃጀት ክሌር የተናገረችው መልዕክት የተወሰደው መንፈስን ስለመለየት ጌታ ያስተማረው ትምህርት ከሚለው ሲሆን ስለ ሬማ ካርድ ትንሽ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ለማድረግ የዝግጅት ክፍሉ ቀንጭቦ ያቀረበው ነው፡፡)

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ ለማለት የምፈልገው ነገር አለ፡፡ እኔ የምግቡ ጣዕም እንዲቀንስ ለማድረግ የተፈጨ ተልባን እጠቀም ነበር፡፡ እንዲሁም ውኃ እጅግ ጣፋጭ የሆነ ምግብን ጣዕሙን ለመቀነስ እጅግ ጥሩ ነገር ነው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "እነዚህ የምታደርጓቸው ነገሮች ሁሉ የምታደርጉት ከእኔ ፍቅር የተነሳ ስለሆነ ተቀባይነት ያላቸው ስጦታዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ማሰብ ያለባችሁ አብዛኛዎቻችሁ ቤተሰባችሁን የሚያሳምም ወይም የቤተሰባችሁን ሁኔታ የሚጨፈልቅ በቂ የሆነ መስቀል ተሸክማችኋል፡፡ አሁን የምፈልገው ጠንካራ ሆናችሁ በሥራ ላይ እንድትሆኑ፣ ግን ደግሞ ለምግብ ምንም ምርጫ እንዳይኖራችሁ ነው፡፡ ይህ የሥጋችሁን ፍላጎት ለማሟላት በቋሚነት እንዳትተጉ በሮችን ሁሉ ይዘጋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ጊዜያችሁን ሁሉ ወደ መንፈሳዊ ህይወት እንድታዘነብሉ ያደርጋል፡፡

"ህዝቦቼ በምትጓዙት ጉዞ ታምራዊ ለውጥን ጠብቁ፡፡

## እንጉዳይ ቅርፅ ዳመና በኒዮርክ ከተማ ላይ - ዲሰምበር 29 ቀን 2020 ዓ.ም.

## Musheroom cloud, December 29th, 2020

ለአለም ማላጆች በሙሉ ጌታ ጉብዝናን፣ ጥበብንና ብርታትን ያካፍላችሁ፡፡ አሜን፡፡

ባለፈው እሁድ የጌታን ዕራትስንወስድ እንጉዳይ ቅርፅ ያለው ኒኩላር በክፍሉ ውስጥ አየሁ፡፡ አብረውኝ ለነበሩትም ይህንን ሳሳያቸው ሁሉም በግልፅ አዩት፡፡ አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ ሲሆን ጌታ ሁላችንም እንድናይ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ፡፡ ስለዚህም ይህ ለእኛ ያልተለመደ ነገር አልነበረም፡፡

ለፀሎት በጌታ ፊት ስቀርብ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጀመረ . . . " በኒዮርክ ከተማ ይፈፀማል የተባለውና ለመፈፀም ብዙ ጊዜ የፈጀው አሁን ሊሆን ተቃርቧል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ምንም ለማያቁትና በሚሆነው ነገር ለሚጎዱት ታናናሾች ልቤ እስከ ሞት ድረስ ታሟል፡፡ ሁላችሁም ለታናናሾች እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም ወዲያው ወደ እኔ እንዲወሰዱ ነው፡፡

ጌታ በዛ ከተማ እኮ ብዙ መልካም ሰዎች አሉ ፡፡ ኢፖች ታይም እንኳን በዛ ናቸው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " መልካሞቹ ወደ ቤት ወደ እኔ ይወሰዳሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እስከ መጨረሻው ፍርድ ድረስ በምድር አፈር ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ለሁሉም ፀልዩ፡፡ ስቃይ ሊደርስባቸው እንዳለው አይነት ማንም እንዲይሰቃይ አልፈልግም፡፡ ሞት በፍጥነት እንዲወስዳቸው ፀልዩ፡፡ በራሳችሁ የባህር ኃይል ክህደት ይፈፀማል፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ እንደሰማሁት ከሆነ ይህ ሊሆን ያለው ነገር በእኛ ባህር ኃይል ላይ በፐርል ሃርቦር እንደተደረገው ጥቃት ዓይነት ነው፡፡ እናም የማምነው በፐርል ሃርቦር አየሩን ሲቆጣጠሩ የነበሩ ሰዎች ጥቃቱን እንዳይመክቱ ተነግሯቸው ነበር፡፡ ምናልባትም አሁን ሊሆን ያለውም ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . . "ክፉ ሰዎች ከክፉ አሰራራቸው ጋር፣ እንዲሁም የባህር ኃይላችሁ ክህደት ያለበት ነው፡፡"

ጌታ ማያሚስ?

"ያም በጊዜው ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚህ የጊዜ ሰሌዳ አይደለም፡፡ አሁን እንደታቀደው ዋናው ኢላማ የኒዮርክ ከተማ ነው፡፡ በቀደሙት ጊዜያት ያልኩትን አስታውሳለሁ፡፡ ነገር ግን የጊዜ ሰሌዳ ማስተካከያዎች ከሁኔታዎች ጋር ይለዋወጣሉ፡፡ አባቴ የሚሰራው ነገር ሁሉ

አግባብ ያለውና ትክክል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የቆየ ነገር አሁን ግን እየመጣ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን ጊዜው እየተቃረበ ሲመጣ ልቤ ተለያይቶ ሊቀደድ ነው፡፡

"የጊዜ ሰሌዳውን ያለመጠየቅሽ ብልህነት ነው፡፡ የተሰጠው ማስጠንቀቂያው ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ጊዜው የሚወሰነው ከተለያዩ ሁነቶች ጋር ተያይዞ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ጠላቶቻችሁ የሆኑ ከእናንተ ጋር የሚኖሩ አሉ፡፡ እነርሱ በኢጋንንት እምነት ይህም በኮሚኒስት ፖለቲካ ዘይቤ አይናቸው ታውሯል፡፡ እነርሱ እምነት አልባ የሆነውን አስተዳደር በማምጣታቸው ለሰው ልጆች ውለታ እንደሰሩ ነው የሚቆጥሩት፡፡ ለእነዚህ አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ ፀልዩ፣ መንግስትን ደግሞ አስጠንቅቁ፡፡ ፓርቲውን በሚቃወሙ ከሃዲዎች ብዙ ነገር ይጠፋል፡፡ ለእነዚህም ፀልዩ፡፡ ክሴር እንደዚህ ዓይነት መጥፎ ዜና ለማምጣት የልቤ ሃሳብ አልነበረም፡፡ ነገር ግን የእንጉዳዩን ዳመና አይተሻል፡፡ ያ ደግሞ መሆኑ የማይቀር እንደሆነ የሰጠሁሽ ምልክት ነው፡፡"

ጌታ ዋሽንግተን ዲሲስ?

"እስካሁን ገና ነው፡፡ አሁን በዚህ ጊዜ እንድትፀልዩ የምፈልገው ስለ ሁለት ነገሮች ነው፡፡ በዚህ አገር የሚኖሩ ሬድ ቻይናዎች እንዲነቁና ኮምኒዝም በእውነቱ ከሆነ እንደማይሰራ ነው፡፡ ያ በቲዎሪ ብቻ የሚሆን ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የሚሰራው ፍፁም ሰው ባለበት፣ አድልዎ የሚደረግለት ቡድን ወይም ግለሰብ በሌለበት ነው፡፡ ሰው ግን የተበላሸ በመሆኑ ከእኔ ውጪ የማይሆንና እኔ ልገዛ ካልመጣሁ ሊሆን የማይችል ነው፡፡

"በቻይና ያላችሁ ህዝቦቼ ደግሞ ለአገራችሁና እንዲሁም በዚህ ነፃነት ባለበት አገር እንዲኖሩ ለተተከሉት እንድትፀልዩ እለምናችኋለሁ፡፡ ይህም እንዲለወጡና በዚህ ምድር እየኖሩ እስካሁን መልካም ሲያደርጉላቸው የነበሩትን ሰዎች ከውስጥ ሆነው በመነሳት እንዳያጠፏቸው ፀልዩ፡፡ ከእኔ ጋር እንዲገናኙ ፀልዩ፡፡ ይህ ነው ሁሉን ነገር ሊለውጥ የሚችለው፡፡"